# ጠጠሮች

## እና ሌሎችም

6ኛ ዕትም

አዘጋጅ

ዲ/ን ዳንኤል ክብረት

አሳታሚ እና አከፋፋይ፡- አግዮስ ኅትመት እና ጠቅላላ ንግድ
ኃ.የተ.የግል ማኅበር

መጋቢት 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ጠጠሮቹ

# እና

# ሌሎች

በዳንኤል ክብረት

መጋቢት 2003 ዓም



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

© ዳንኤል ክብረት፣ 2003 ዓ.ም.

የመጀመሪያ ዕትም መጋቢት 2003 ዓ.ም.
ሁለተኛ ዕትም ሰኔ 2003 ዓ.ም.
ሦስተኛ ዕትም መጋቢት 2004 ዓ.ም.
አራተኛ ዕትም ጥር 2005 ዓ.ም.
አምስተኛ ዕትም ሰኔ 2007 ዓ.ም.
ስድስተኛ ዕትም ነሐሴ 2008 ዓ.ም.

**አሳታሚ**

አግዮስ ንትመትና ጠቅላላ ንግድ ሥራ ሐላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር

**አድራሻ**

መገናኛ ለም ሆቴል ባቡር ጣቢያ ፊት ለፊት፣ ማትያስ ሕንፃ ቢሮ ቁጥር 404 / G – 06

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ 251 0930 098254/ 0116 639902

ኢሜይል danielk@agyos.com

ገጸ ድር www. agyos.com

www.danielkibret.com

Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ማውጫ


1. ግንዶ ....................................7
2. ለምጣዱ ሲባል ....................................16
3. ቫቲካን.................................... 25
4. ባሕር ዛፍ ....................................37
5. የአማልክት ምድር ....................................44
6. ማማሽ ነው ሙሉ? ....................................55
7. ባለ ራእይዋ ደሴት ....................................63
8. ተባቢ .................................... 75
9. ከሞ ሳሻ ....................................83
10. «የታሪክ እና ቅርስ ፓርቲ» ....................................92
11. ይምርሃን – ያልተጠናው ሥልጣኔያችን ......101
12. ፎጭ እና አፎፎጭ ....................................112
13. የጃፓን እንቁራሪቶች ....................................120
14. ባሉችም ያረግዛሉ ....................................128
15. ተራራው .................................... 137
16. ዘገዬ .................................... 146




Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

17. የዶክተር ውሳኔ ........................................155
18. ወንደኛ አጻሬዎች ........................................164
19. ጠጠሮቹ ........................................173
20. ኳሱን አትንኩብን ........................................181
21. ምን አደረግናችሁ? ........................................ 190
22. እውነት ይሆን እንዴ ........................................ 198
23. ቁንጮን ሲያታልሏት፣ ጋንክ ብለው ጠሯት . 204
24. ዝምታ ወርቅ አይደለም ........................................ 211
25. 171ኛው ሆስፒታል ........................................ 219
26. ቅኝ አልተገዛንም? ........................................ 227
27. «ቦሴ» ለትዳር» ........................................236
28. ኑ እንፍጠር ........................................244
29. ድንጋይ ስድብ ነው ወይ? ........................................252
30. ፈረንጆቹ ........................................260
31. ካልሞትክ አይገሉህም ........................................269



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# መግቢያ

*«የሁለት ሐውልቶች ወግ»* የተባለውን የዚህን መጽሐፍ ቀዳሚ ሳሳትም ሌላም እንደሚከተለው ገልጬ ነበር:: ይኼው አብሮ አደጉ ተከትሎታል::

በዚህኛው መጽሐፍ ላይ በቀድሞዋ አዲስ ነገር ጋዜጣ እና በኋለኛዋ ሮዝ መጽሔት ላይ የወጡ ወጎች በአየር ላይ ጦማሬ ላይ ከወጡት ጋር ኅብረት ፈጥረው መጥተዋል::

እነዚህ ጽሑፎች እዚህ ላይ ሲወጡ ሳነበቧቸው ማስታወሻ፣ ላላገኟቸው መዳረሻ እንዲሆኑ ታስቦ ነው:: በሁለት ሐውልቶች ወግ ላይ የወጡ ጽሑፎችን በጋዜጣ ላይ ሲወጡ ያላነበቧቸው አያሌ አንባብያን የማንበብ ዕድል እንዳገኙ በስልክ፣ በአካል እና በኢሜይል ገልጠውልኛል::

ይህ ሁኔታም ሕዝባችንን በንባብ ለማዳረስ እንዲቻል የተለያዩ ዓይነት መንገዶችን መጠቀሙ የተሻለ አማራጭ መሆኑን ተገንዝቤበታለሁ::

የዚህ መጽሐፍ መታተም በመጋቢት 15 ቀን አንደኛ ዓመቱን ላከበረው www.danielkibret.com ለተሰኘው ጦማር /blog/ መታሰቢያ እንዲሆን ታስቦ ነው:: በዚህም የተነሣ በጦማሩ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ ቀርበው በብዙ አንባብያን የተወደዱ ወጎች እንዲታተሙበት ተደርገዋል።

በግሪክ፣ በጣልያን እና በሌሎችም የአውሮፓ ሀገሮች ያደረግኳቸውን ጉዞዎች የመቻቼትን እንቶች እና ወንድሞች በዚሁ አጋጣሚ ላመሰግናቸው እወድዳለሁ። እነዚህ የጉዞ ማስታወሻዎች በዳያስጶራ የሚገኘው ወገናችንን የዚህ ዘመን ገጽታዎች የሚያሳዩ መስተዋቶች ናቸው ብዬ አምናለሁ።

እንደ ከዚህ በፊቱ ሁሉ አስተያየቶቻችሁ እና ሃሳቦቻችሁን እናፍቃለሁ።

ይህ መጽሐፍ ለመጀመርያ ጊዜ ከታተመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሦስተኛው የወግ መጽሐፍ ታትሞ ወጥቷል። እድሜ ጤና ሰጥቶን በአራተኛው መጽሐፍ ላይ ደግመን እንገናኝ።

መልካም ንባብ ይሁን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ገንዳ

**ለጃሮ** መምህሬ ነበሩ:: ስለ አንድ ጉዳይ ጠይቀናቸው ያብራሩልንና ዘወትር የማትለወጥ ምክር አለቻቸው:: «ገንዳ እንዳትሆኑ» ይሉናል:: ብዙ ጊዜ እሰማታለሁ እንጂ ለምን ብዬ ጠይቄ አላውቅም ነበር:: አንድ ቀን ግን ምን ማለታቸው እንደ ሆነ ለማወቅ ፈለግኩና ጠየቅኳቸው: «እያችሁ፣ ገንዳ ለከብቱ ሁሉ ያጠጣል እንጂ ለራሱ አይጠጣም:: እንዲያውም ባጠጣ ቁጥር እየጎደለ ሄዶ ጭራሹኑ ይደርቃል:: እናንተም እንደዚያ እንዳትሆኑ» አሉን::

ለብዙዎች ምክር የሚሰጡ ለራሳቸው መካሪ ካጡ፤ ለብዙዎች የደስታ ምንጭ የሆኑ እነርሱ በኀዘን ከሰመጡ፤ ብዙዎችን የሚያገናኙ እነርሱ ግን ከተደበቁ፤ ለብዙዎች የሀብት ምንጭ የሆኑ እነርሱ ግን በድኅነት ከተቆራመዱ ገንዳነት ማለት ይሄ አይደል እንዴ::

በካባ ውስጥ ያለን ድንቁርናና እና በቡቱቶ ውስጥ ያለን ዕውቀት ፈጣሪ ብቻ ነው የሚያውቀው ይባላል:: መድረክ ላይ ወጥተው፣ ዓይን የሚስበውን እና ልብ የሚማርከውን ልብስ ለብሰው፣ ሕይወትን በቀልድ ቀምመው እኛን በሳቅ የሚያፈነዱን ሰዎች በእውነት የእነርሱ ሕይወት ትስቃለች? በኪናዊ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሥራዎቻቸው እኛ የገዛ ሕይወታችንን መለስ ብለን እንድናይ ያደረጉን እነዚህ ሰዎች ሕይወታቸውን መለስ ብለው የሚያዩበት መነጽር አላቸው?

የትዳርን መልካምነት፣ የፍቅርን ጣፋጭነት፣የቤተሰብን ደስታ፣ የማኅበራዊ ኑሮን ርካታ በዜማዎቻቸው ከሸነው ያቀነቀኑልን ወገኖች ትዳራቸውን እና የፍቅር ሕይወታቸውን፣ ቤተሰባቸውን እና ማኅበራዊ ኑሯቸውን ሲገመግሙት ያቀነቀኑላትን ያህል ሆኖ ያገኙታል? ወይስ ለዜማው ስኬት፣ ለገበያው ሥምረት፣ ለአድማጩ ሐሴት ሲሉ ብቻ ነው ያቀነቀኑት?

በፊልሞቻቸውም ይሁን በመድረክ ትወናቸው ኅብረተሰባችን ምቀኝነትን እና ክፋትን፣ ቅናትን እና ስግብግብነትን፣ ቂምን እና በቀልን፣ መሠሪነትን እና ተንኮለኛነትን እንዲያርቅ የሚያስተምሩን እና የሚያሳዩን ወገኖቻችን መልእክቱ ለተመልካቹ ብቻ ነው ወይንስ እነርሱንም ይመለከታል? መልእክቱ ለመድረክ ብቻ ነው ወይስ ወደ ቤታቸውም ይሄዳል? ጉዳዩ የኅብረተሰቡ ብቻ ነው ወይንስ እነርሱንም ይዳስሳል? ለመሆኑ እርስ በርሳቸው ደኅና ናቸው?

«ተማር ልጄ» ብለው እያዜሙ እነርሱ ግን «ትምህርት እስከ ስድስት፣ ዘመድ እስከ አክስት» የሚሉ ከሆነ፣ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ስለ አንድነት እየሰበኩ እነርሱ ግን ግላዊነት የሚያጠቃቸው ከሆነ፣ ስለ ፍቅር እያቀነቀኑ እነርሱ ግን የትዳ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ራቸውን ነገር ውኃ ውኃ የሚያደርጉት ከሆነ፡ አንድ ሰው ለአንድ ነው ካሉን በኋላ አንድ ለአሥር የሚመሩ ከሆነ፡ ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ እያስተማሩ፣ በዚህ እና በዚያ መንገድ ትያዛላችሁ ብለው እየሰበኩ፣ እነርሱ ግን «እንቺው ታመጭው ፣እንቺው ትሮጭው» እንደ ሚባለው ምክሩን ለራሳቸው የማይ ጠቀሙበት ከሆነ ከዚህ በላይ ገንዳነት ምን አለ?

ሌሎች ሰዎች ሀብታቸውን ለሀገር ልማት እንዲያውሉት መን ገር ብቻ ነው እንዴ፣ እኛስ ሀብታችንን የትም ከምንረጨው ለምን መሥመር አናስይዘውም፡ ሌሎች አንጻች ነገር ሲያስ መርቁ ተገኝተን ምረቃውን እንደምናሞቀው ሁሉ የራሳ ችንን ነገርስ ለምን አናስመርቅም፡ ነው ወይስ ከምሽት ክበብ እና ከኩትሮ ቤት በላይ ማቋቋም አንችልም? የሕግ አማካሪ፣ የቢዝ ነስ አማካሪ፣ የሂሳብ ባለሞያ፣ የሞያ አማካሪ እንዳይኖረን ያገደው የትኛው ሕግ ነው?

«አይሆንም እንጂ ቢሆንማ፣ ሽርሽር ወደ ጅማ» የሚል አንድ ዘፈን ሠርግ ላይ ሰምቻለሁ:: አይሆንም እንጂ ቢሆንማ እኛም ሞያችንን በዕወቀት ብንደግፈው፣ ለሞያችን እና ለዕድገታችን የሚሆኑ ትምህርቶችን ከፍለን ተምረን ራሳችንም መሥመራ ችንን ብናውቀው ጥሩ ነበር:: ዲፕሎማ እና ዲግሪክ ለመቀ ጠር ብቻ አይደለም:: ይህ ካልሆነ ደግሞ የተማሩትን ቀጥረን በዘመናዊ መንገድ ሕይወታችንን ብንመራ መልካም ነበር::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«አይሆንም እንጂ ቢሆንማ» አሉ:: ከልጆቻችን ጋር ስለ ትምህርታቸው ለመወያየት፣ ትምህርት ቤትም ሄዶ የልጆችን ነገር ለመጠየቅ፣ ወደ ውጭ ወጣ ሲሉ በጣት ከማውራት ለመዳን፣ እኛም በውቀናል ጉድኅድ ምሰናልም ለማለት፣ መማርን የመሰለ ነገር የለም::

ብዙ ሰዎች ሊያደንቁን ይችላሉ፣ ሊወደን የሚችል ግን አንድ ሰው ወይንም አንዲት ሴት ብቻ ናት፤ በብዙ ቦታዎች ልንጋበዝ እንችላለን፣ ሊኖረን የሚችለው ትዳር ግን አንድ ብቻ ነው፤ ፎርማችንን ብዙዎች ይፈልጉት ይሆናል፤ እውነተኛ ፍቅራችንን እና እኛነታችንን የሚፈልጉት ግን ጥቂቶች ናቸው፤ ከኛ አንዳች ነገር መስማት የሚፈልጉ አያሌዎች ናቸው፤ ለኛ ጥቂት ነገር ሊነግሩን የሚችሉ ግን በጣት ይቆጠራሉ፤

ከኛ የሚፈልጉ አሉ፤ እኛን የሚፈልጉ መኖራቸው ግን ያጠራጥራል፤ በኛ የሚጠቀሙሞልተዋል፣ እነዚያ ሁሉ ግን እኛን ይጠቅማሉ ማለት አይደለም፤ ዝና ለተወሰነ ጊዜ ነው፣ ሕይወት ግን እስከ ሞት ድረስ ናት፤ መድረክ ላይ የሚያጨበጭቡልን እልፍ አእላፋት ናቸው፣ ከመድረክ ስንጠፋ የሚፈልጉን ግን እጅግ በጣም ጥቂት፤ ስንስቅ የሚስቁ እናገኛለን፤ ስናለቅስ ዕንባችንን የሚያብሱ ማግኘት ግን ይቸግራል? ሞያችንን የምናካፍለው ቁጥሩ ብዙ ነው፣ ችግራችንን የምናካፍለው ግን የት ይገኛል?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አውሮፕላን አገልግሎቱን በሚገባ ለመስጠት ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ያስፈልጉታል:: ሊነሣበት እና ሊያርፍበት የሚችል አውሮፕላን ማረፊያ እና ሊበርበት የሚችል አየር:: በቴክኖሎጂው ምጥቀት የተነሣ በሰዓት የፈለገውን ያህል ኪሎሜትር ቢበርም፣ ምቾቱ የተጠበቀ፣ ደረጃው የላቀ ቢሆንም፣ የቱንም ያህል ወደ ላይ እንደ ንሥር ቢነጠቅም፣ መነሻ እና ማረፊያ ከሌለው ግን ሂደ፣ ሂዶ ነዳጁ ሲያልቅ መከስከሱ አይቀርም::

በዜማቸው፣ በኪን ጥበብ ውጤቶቻቸው፣ በትወናቸው፣ በሀብታቸው፣ በፖለቲካ ተሳትፏቸው፣ በሊቅነታቸው ወዘተ ታዋቂ የሆኑ እና አያሌዎችን ከኋላቸው ወይንም በሥሪያቸው ለማሰለፍ የበቁ ሰዎች፣ የቱንም ያህል ወደ ላይ እና ወደ ጎን በክብር እና በዝና፣ በአድናቆት እና በምስጋና፣ በሀብት እና በንብረት ቢመጥቁም፣ የቱንም ያህል በሕዝቡ ተወዳጅ እና ተፈቃጅ ቢሆኑም፣ እንደ አውሮፕላኑ ማረፊያ እና መነሻ ከሌላቸው ግን አንድ ቀን እነርሱም መከስከሳቸው የማይቀር ነው::

ብዙ ሺዎች ሲያደንቁህ ከነበረበት መድረክ ወርደህ ቤትህ ስትገባ ምን ይጠብቅሃል፣ ቤትህ እንደ መድረኩ ይሞቃልለ? ብዙዎችን ካዝናናህበት የሳቅ ባሕር ወጥተህ ብቻህን ስትሆን ነፍስህ ምን ትልሃለች፣ አያሌዎች የተጠቀሙበትን ጉዳይ አቅ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ርበህ ራስክን ስታየው ምንድን ነህ ይልሃል? ይህ ነው ከባዱ ጥያቄ።

አንዳንድ ጊዜ ለዚህች ሀገር ባለውለታ የሆኑ የሥነ ጥበብ እና የኪነ ጥበብ ሰዎች ታመው መታከሚያ፣ ተቸግረው መኖርያ፣ ዐርፈው መቀበርያ አያጡ ሲለመንላቸው ሳይ እኒያ መምህር የተናገሩት ነገር ትዝ ይለኛል። እነሰም በዛም በወቅቱ ጥቂት ነገር አግኝተው ይሆናል፤ በወቅቱ መሬት ለማግኘት፣ ቤት ለመሥራት፣ ጥሪት ለመቋጠር ምቹ የነበሩ ሁኔታዎች እነር ሱንም የሚመለከቱ ነበሩ፤ በወቅቱ አያሌ አድናቂዎች እና እነርሱ ካልመጡ ሞተን እንገኛለን የሚሉ ተመልካቾች ነበሯ ቸው። ታድያ ለምን እዚህ ደረጃ ላይ ወደቁ?

እኔ እንደሚመስለኝ የእኛ እንጂ የራሳቸው እንዲሆኑ ስላል ረዳናቸው ነው። አጨብጨብንላቸው፣ አፏጨንላቸው፣ አቆላመ ጥናቸው፣ ጋበዝናቸው፣ እፍ እፍ አልንላቸው፣ አበድንላቸው ራሳቸውን ሆነው ማረፊያ ኖሯቸው እንዲኖሩ ግን አላደረግ ናቸውም።

በየመንደራችን ጉልት ቸርችረው፣ ጠላ ጠምቀው፣ እንጨት ሰብረው፣ የዕለት ሥራ ተቀጥረው ሕይወትን ይገፉ የነበሩ ሰ ዎች፣ ቢያንስ የቀበሌ ቤት ለመከራየት፣ ዕድር እና ዕቁብ ለመግባት፣ ልጆቻቸውን አስተምረው የተሻለ ቦታ ለማድረስ የሚያከራዩት ሰርቢስ ቤት ለመሥራት ሞክረዋል፤ «የልዝብ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ልጆች፥ እየተባሉ የኖሩ የኪነ ጥበብ እና የሥነ ጥበብ ሰዎች ግን፣ የሕዝብ ብቻ ሆነው የራሳቸው ሳይሆኑ ቀሩ። «የሁሉም የሆነ የማንም አይሆንም» ይባል የለ።

እንደ አውሮፕላኑ መነሻ እና ማረፊያ እንዲኖራቸው ማድረግ ነበረብን። መምከር ነበረብን። ማስጨነቅ ነበረብን። እነርሱም ማሰብ ነበረባቸው።

አርቲስት ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ፤ ታዋቂ ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ፤ ደራሲ ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ፤ ጋዜጠኛ ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ፤ ፖለቲከኛ ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ፤ ነጋዴ ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ። ሰው ባትሆኑ ኖሮ እነዚህን ነገሮች ሁሉ መሆን አትችሉም ነበር። ሰው መሆናችሁ ሲያቆም ደግሞ እነዚህ ሁሉ ነገሮች አብረው ያቆማሉ። ስለዚህም ዝናን እና ታዋቂነትን፣ ክብርን እና ሽልማትን፣ ገንዘብን እና ሀብትን፣ አድናቆትን እና ተወዳጅነትን ስላገኛችሁበት ነገር ብቻ ሳይሆን ሰው ስለሆናችሁበትም ነገር ማሰብ አለባችሁ።

አገር መውደድ ቤተሰብን እና ትዳርን ከመውደድ፣ ሕዝብን ማስተማር ራስን ከማስተማር፣ ሌላውን ማዝናናት የትዳር ጓደኛን ከማዝናናት፣ ተወዳጅነት በገዛ ልጆቻችን ከመወደድ፣ መደነቅ በትዳር አጋር ከመደነቅ፣ መከበር በመንደራችን ከመከበር፣ ደስተኛነት በግል ሕይወት ከሚገኝ ርካታ መጀመር



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አለበት:: አውሮፕላን ማረፊያውን ለትቶን አየር ላይ ብቻ
የምንንሳፈፍ ከሆን መክስከሳችን አይቀሬ ነው::

ጊዜ ስለሌለን፣ ኪን ጥበብ የሕዝብ ስለሆነች፣ ሕዝቡን በየአጋ
ጣሚው ማገልገል ስላለብን፣ ሥራችን ሊሊትም ቀንም ስለሆነ፣
ሞያችን አንዳንድ ጊዜ ለብቻ መሆንን ስለሚፈልግ፣ ወደ
ውጭ ሀገር በብዛት ስለምንወጣ፣ እዚህም እዚያም ስለምንፈ
ለግ፣ እያልን የምንተወው ቤተሰብ፣ የምናሳዝናቸው የትዳር
አጋሮቻችን እና ልጆቻችን በኋላ ዋጋ ያስከፍሉናል:: ጊዜ ላይ
ኖረን ይችላል:: ነገር ግን ሰው ነንና ለቤተሰብ ጊዜ መስጠት
የግድ ያስፈልገናል:: ቤተሰብ የመነሻ እና የማረፊያ ሜዳችን
ነው:: አውሮፕላኑ ቢበላሽ ወርዶ የሚሠራው ማረፊያው ላይ
ነው:: ማረፊያው ከተበላሸ ምን መሆን ይችላል? «ምላጭ ቢያ
ብጥ በምን ይበጡታል፣ ውኃ ቢያንቅ በምን ይውጡታል»
ይባል የለ?

ሕዝብ አይጨበጥም:: ሕዝብ የሚባል መቀቅርም የለም::
ሕዝብ ተቆጥሮ በትክክል አይታወቅም:: ስለ ሕዝብም አፍን
ሞልቶ ትክክለኛውን ስሜት መናገር አይቻልም:: ሕዝብ የሚ
ባል ተቋምም በሕግ ዘንድ የለም:: ቤተሰብ ግን ይጨበጣል፣
ይቆጠራል:: አፍን ሞልቶ ሊናገሩለትም ይቻላል:: በሕግም
የታወቀ ትርጉም እና ጥበቃ አለው:: እናም የማይጨበጠ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የሕዝብ ከመሆናችን በፊት፣ የሚፈልበጠው የቤተሰባችን እንሁን።

የጂኦግራፊ መምህራችን ምድር ሁለት ዓይነት ዙረት አላት ብለውናል። በፀሐይ ዙርያ እና በራስዋ ዛቢያ። እነዚህ ሁለቱ ተጠባብቀው ይኖራሉ። እኛም በፀሐይ ዙርያ ብቻ ሳይሆን እንደ ምድር በራሳችንም ዙርያ እንዙር። እነዚህ ሁለቱ ተጠ ባብቀው ይኑሩ።

ለምንድነው ቢሉ፣ ግንዳ እንዳንሆን።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ለምጣዱ ሲባል

በትግራይ የሚነገር አንድ ብሂል አለ:: አንድ ባል እና ሚስት አንዲት ትንሽ አይጥ አስቸገረቻቸው:: አንድ ቀን ባል እና ሚስቱ ዱላ ዱላቸውን አንስተው የቤቱን ዕቃ ሁሉ ገልብጠው አይጧን ማሳደድ ጀመሩ:: በዚህ ሲሏት በዚያ፣ በዚያ ሲሏት በዚህ ብዙ እያለች በጣም አደከመቻቸው:: በመካከሉ ሚስቲቱ አይጧን ስታባርር አይጧ ዘልላ ምጣዱ ላይ ወጥታ ቁጭ አለች:: ሚስቲቱም የሠነዘረችውን ዱላ ወደ ኋላ መልሳ፣ አይጧን በአግራሞት ማየት ጀመረች:: ባልዋም የሚስቱን ሁኔታ ተመልክቶ «ምነው ትቆሚያለሽ አትያትም ወይ?» አላት:: ብልኋ ሚስትም «መምታቱ አቅቶኝ አልነበረም ነገር ግን «ምእንቲ ዛ ምጎጎ እታ አንጭዋ ትሕልፍ» አለችው ይባላል:: «ስለ ምጣዱ ሲባል አይጧ ትለፍ ብዬ ነው» ማለቷ ነው::

ለዚያች እናት ምጣዱ የትዳሯ ትልቁ አስፈላጊ ነገር ነው:: እንዲህ እንደ ዛሬ እንጀራ ተገዝቶ መበላት ሳይጀምር በፊት ያልጋገረ ሰው እንጀራን አያገኘውም:: ከዚያውም በላይ ደኅኛ ምጣድ ከገበያ እንደ ልብ አይገኝም:: ቢገኝም ማሟሸቱ ብዙ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሞያ እና ድካምን ይጠይቃል። እናቶቻችን ወዝ የለመደ ምጣድ የሚሉት አላቸው። የጋጋሪዋን ወዝ የለመደ፣ ጋጋሪዋም ጠባዩን የለመደችው ምጣድ ማለት ነው። እንዲያውም እንዲህ ያለው ምጣድ የትም ስለማይገኝ ለድግስ ሥራ ሲጠሩ የራሳቸውን ምጣድ ይዘው ሄደው የእንርሱን ድርሻ በለመዱት ምጣድ የሚጋግሩ እናቶች ነበሩ። አሉም። ለዚህ ነው ያቺ እናት «ምእንቲ ዛ ምጎጎ እታ እንጭዋ ትሕልፍ» ያለችው።

ገበሬ እንኳን እርሻውን ሲያርም ሁሉንም ነገር አያርመውም። አንዳንዱን አረም ተስማሚውን ጊዜ በመፈለግ ያልፈዋል። አንዳንዱ እንደ እንክርዳድ ያለው አረም ከእህሉ ጋር ሥር ለሥር ይያያዝና ለእርማት ያስቸግራል። አንዳንዱም በጣም ጥቃቅን አረም ከመሆኑ የተነሣ ያንን አረም በማረም የሚፈጀው ጊዜ አረሙ ቢታረም ከሚያስገኘው ጥቅም ስለሚበልጥበት ይተወዋል። በዚህ ጊዜ ዋና ዋናውን አረም ያርምና ያንን ያልፈዋል። የማሳ እና የሰው ንጹሕ የለውም ነውና የገበሬው ብሂል። እንክርዳዱን እንነቅላለን ስትሉ ስንዴውንም አብራችሁ እንዳትነቅሉት እንደተባለው። እንዲህ ያለውን አረም ከእህሉ የሚያስወግደው በመከር ጊዜ እያበራየ ነው።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በትዳር ውስጥ ያሉ ባል እና ሚስት ትዳራቸውን አጽንተው ለመኖር ከፈለጉ ከሌሎች ብዙ ነገሮች ጋር ሊከተሉት የሚገባው ነገር አንዱ «ምእንቲ ዛ ምጎጎ እታ እንጭዋ ትሕልፍ» የሚለው ነው፡፡ የተጋቡት ሰዎች ፍጹማን እና እንከን የለሾች አይደሉም፡፡ በእያንዳንዷ ስሕተት እና ጉድለት ላይ በመነታረክ፣ እያንዳንዷን ጥፋት እየቆጠሩ ነጥብ በማስቆጠር፣ ትዳርን አጽንቶ ማኖር ከባድ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰምጣዱ ሲባል አይቧን ማሳለፍ የሚገባበት ጊዜ አለ፡፡ ሰው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሚሠራው ይሳሳታል፡፡ ዐውቆ የሠራውን በተግሳጽ፣ ሳያውቅ የሠራው አሳልፎ በመነጋገር መፍታቱ የተሻለ ነው፡፡

በተለይም ሰው በተሳሳተበት ጊዜ ቢነግሩት የማይሰማቸውን ጉዳዮች አውሰው አሳድረው፣ ነገር አብርደው እና ዘና አድርገው ቢነግሩት ነጠብጣብ እንደ ወረደበት መሬት በሚገባ ይቀበለዋል፡፡ እሳትን በእሳት ማጥፋት፣ ውኃንም በውኃ ማቆም አይቻልምና፡፡ ትዳርን ያህል ትልቁን ምጣድ ላለመስበር ሲባል ሊያልፉ የሚችሉትን ትናንሽ አይጦች ማሳለፍ ይገባል፡፡ ምክር የሚፈታው ችግር አለ፡፡ ተግሣጽ የሚፈታው ችግር አለ፣ ማሳለፍ የሚፈታውም ችግር አለ፡፡ አይቧን የሚያመጣውን ጉዳይ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳንፈታ ወደ ቤት የሚመጡትም አይጦች በመግደል ብቻ አይጦችን ማጥፋት አይቻልም።

እንኳንስ ዐዋቂዎቹ ባል እና ሚስት ቀርተው ሕፃናትን እንኳን በየአንዳንዱ በሚያጠፉት ጥፋት የምንናገራቸው ከሆነ ይደን ዛሉ እንጂ አይሰሉም። በየደቂቃው የምትጠጣ ነጠብጣብ ውኃ ጥም እንደማትቆርጠው ሁሉ በየደቂቃው ተው፣ አረፍ፣ እን ዲህ አድርግ፣ እንዲያ አታድርግ፣ እያሉ መናገር ልጅን አያር መውም። አባቴ ለማዱ ነው፣ እናቴም ለማዷ ነው እያለ ሰምቶ እንዳልሰማ ያልፈዋል እንጂ።

ዐፄ ቴዎድሮስ ደብረ ታቦር ላይ ቆመው እያሉ አንድ ገበሬ ሰክሮ በአጠገባቸው ያልፋል። ያም ገበሬ ወደ ንጉሡ ጠጋ ይልና «በቅሎው ይሸጣል» ይላቸዋል። የዐፄ ቴዎድሮስ ጋሻ ጃግሬዎች እነ ገብርዬ ሰይፍ መዝዘው «እንዴት ንጉሡን በድ ፍረት ይናገራል፤ እንበለው» አሏቸው። ንጉሡም ትእግሥት አድርገው «ተውት፣ ይሂድ። ነገር ግን የሚገባበትን ቤት ተከ ታትላችሁ ተመልከቱት አሏቸውና ተከታትለው ተመለከቱት።

በማግሥቱ ያንን ሰው ንጉሡ አስጠሩት። እየፈራ እየተንቀ ጠቀጠ መጣ። «ትናንትና እነዚህ ሁሉ ሰዎች ባሉበት በቅሎ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ዱን ለመግዛት ጠይቀህ ነበርና እንድንስማማ ነው ያስጠራሁህ» አሉት። ሰውዬው ግን ማመን አልቻለም። የንጉሥ በቅሉ፣ ያውም ታጠቅ የተባለውን የዐፄ ቴዎድሮስን በቅሉ ለመግዛት የምጠይቅ እኔ ማነኝ ብሎ ደነገጠ። «የለም ንጉሥ ሆይ እኔ ብቻዬን ሆኜ እንዲህ ያለውን ሃሳብ አላስበውም። ይህንን ጥያቄ ያቀረብነው ከጓደኞቼ ጋር አብረን ሆነን ነውና ከእነርሱ ጋር ተማክሬ መልስ ልስጥ» ብሎ ጠየቀ።

ንጉሡም «ትናንትና ስናይህ ብቻህን ነበርክ። ሌላ ጓደኛ አልነበረህም። ከየት አምጥተህ ነው የምትማከረው?» ሲሉ ገርሟቸው ጠየቁት። ያም ገበሬ «ንጉሥ ሆይ አላዩዋቸውም እንጂ አብረውኝ እነ ብቅል፣ ጌሾ፣ እነ ደረቆት፣ እነ ጠጅ፣ እነ ጠላ፣ እነ አረቂ ነበሩ። እነርሱ በሌሉበት ይህንን ነገር ብቻዬን አልናገረውም» ብሎ አሳቃቸው። ንጉሡም በአነጋገሩ ተገርመው ምሕረት አደረጉለት ይባላል። ለዚህ ነው ለምጣዱ ሲባል አይጧን ማሳለፍ የሚጠቅመው። ያንን ድፍረት የደፈረው ገበሬው ብቻውን አይደለም። እነ አረቂ፣ ጠላ፣እና እነ ጠጅ ናቸው። ስለዚህም አይጧን ከምጣዱ ለይቶ መምታቱ መልካም ነው።

ሰዎች በማኅበርም ሆነ በድርጅት፣ በኮሚኒቲም ሆነ በፓርቲ ለአንድ ዓላማ፣ በተወሰኑ መሠረታውያን ነገሮች ላይ ትስማ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ምተው አብረው ይሠራሉ፡፡ ሰዎች አብረው ለመሥራት በሁሉም ነገር ላይ የግድ መስማማት የለባቸውም፡፡ ሌላው ቀርቶ በአንድ ቤት፣ አንድ አካል ሆነው የሚኖሩት ባል እና ሚስት እንኳን በመሠረታውያን ነገሮች ላይ እንጂ በሁሉም ነገሮች ላይ መስማማት አይችሉም፡፡ ሁለት ከመሆን የተነሣ የሚመጡ ልዩነቶች አሉና፡፡ ቢያንስ በምግብ ምርጫ ሊለያዩ ይችላሉ፡፡

እነዚህ ማኅበራት፣ ተቋማት፣ ድርጅቶች እና ፓርቲዎች አንዳንድ ጊዜ ለምጣዱ ሲባል አይጧን ማሳለፍ አለባቸው፡፡ በትንሽ በትልቁ በመጨቃጨቅ እና ባለመስማማት፣ በሆነው ባልሆነው በመለያየት እና እንደ አሜባ በመከፋፈል ምጣዱን የሚሰብሩት ከሆነ በውኑ ይህች ሀገር ተስፋዋ ምንድን ነው? ሰዎች ሲሠሩ ይሳሳታሉ፡፡ ከዕውቀት ማነስ ይሳሳታሉ፣ ከመቸኮል ይሳሳታሉ፣ ትክክለኛ ነገር የሠሩ መስሏቸውም ይሳሳታሉ፡፡ ማናቸውንም ዓይነት የሰዎችን ስሕተት ለመታገሥ የማንችል ከሆነ ሰዎችን የሚያሰባስቡ ተቋማትን መመሥረት የለብንም ማለት ነው፡፡ እናም መጀመርያ እኔ በእነርሱ ቦታ ብሆን ኖሮ ምን አደርግ ነበር? ብሎ ራስን መጠየቅ ቀጥሎም፣ ልናልፈው የሚ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ገባንን ነገር ልንናገርበት እና ልንከራከርበት ከሚገባን ነገር ለመየት አለብን።

አካሄዳችን እና እርማታችን ዋናው ዓላማው ያቋቋምነውን ድር ጅት፣ ማኅበር፣ ፓርቲ፣ ተቋም ማነጽ፣ ማጠናከር፣ እና የተ ሻለ ማድረግ ከሆነ ማናችውም ነገራችን ምጣዱን የማይ ሰብር መሆኑን ማረጋገጥ አለብን። ያለበለዚያ ግን አንዳንድ ጥቃቅን የስሕተት አይጦችን እናጠፋለን ብለን የደከምንበትን፣ ስንት ወዝ እና ልፋት የፈሰሰበትን፣ ስንቶች እንደ እሳት ነድደው ያሟሹትን፣ የስንቶች ድካም እና ሞያ የፈሰሰበትን፣ ምጣድ መስበር ይመጣል።

ዛሬ በታላላቅ ቤተ እምነቶች የምናየው ጠባይ ለአይጧ ሲባል ምጣዱ ይሠበር የሚል የሞኝ አሠራር እየሆነ ነው። አይጧን ከምጣዱ ለይተው መምታት አቅቷቸው ለብዙ ሺ ዓመታት የተደከመባቸው ትልልቆቹ ምጣዶች እየተሠበሩ ነው። ያቺ ገብሬ እናት ትእግሥትን ገንዘብ አድርጋ፣ ለትልቁ ምጣድ ሲባል እስኪ ለጊዜው አይጧን ባባልፋት ያለችው አይጧ ታስ ፈልጋለች፣ ችግር አትፈጥርም፣ እያደረገችው ያለው ነገር ትክ ክል ነው፣ ቤቱን ማውደሟ፣ ያልለፋችበትን ነገር መብላቷ፣ ቀበኛ መሆንዋ ተገቢ ነው፤ በዚህ ሁኔታም መኖር አለባት ብላ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አይደለም። ምሢዷን አትርፋ አይሟን ብቻ የምትመታበትን ተስማሚ ጊዜ ለማግኘት እንጂ። በአንድ ጊዜ ሁለት ጥፋት ላለማጥፋት።

የሃይማኖት አባቶች የዚህችን እናት ጥበብ እና ብልሃት ዛሬ ከወዴት ባገኙት?

የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት አንግበው የተነሡ ኃይላትም ኢትዮጵያን ያህል ብዙ ትውልድ ደክሞ ያሟሻትን ምጣድ፣ ስንቶች እንደ እሳት የተማገዱባትን ምጣድ፣ ስንት የማንነት፣ የታሪክ፣ የባህል፣ የቅርስ፣ የእምነት እና የወግ እንጀራ ሲጋገርባት የኖረችውን ምጣድ፤ እናጠፋቸዋለን ብለው ለሚያስቧቸው አይጦች ሲባል እንዳይሰብሯት መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ሀገር ከፖለቲካ አመለካከት፣ ከርእዮተ ዓለም፣ ከፍላጎት፣ ከአስተሳሰብ እና ከምኞት ሁሉ ትበልጣለች።

የችግር፣ የኋላ ቀርነት፣ የግፍ፣ የጭቆና፣ የመብት ረገጣ፣ የፍትሕ ማጣት፣ የእኩልነት ማጣት፣ የሰብአዊ መብት ማጣት የምንላቸው አይጦች መጥፋት አለባቸው። እነዚህ ነገሮች ለዕድገታችን ዕንቅፋቶች፣ለኋላ ቀርነታችን ምንጮች መሆናቸውን የሚክድ የለም። መጥፋት የለባቸውም ብሎ የሚከራ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ክርን፦ የለም። ነገር ግን ምጣዱ ሳይሰበር መሆን አለበት። እነ ዚህን አይጦች እናጠፋለን ብለን ዛሬ ከአንዳንድ ኃይሎች ጋር የምንመሠርተው ግንኙነት፣ የምንፈጥረው ኅብረት እና የምን ዋዋለው ቃል ኪዳን አብሮ ምጣዱን የሚሰብር እንዳይሆን ደግሞ ደጋግሞ ማሰብ ያስፈልጋል።

በታሪካችን ውስጥ ያለፍንባቸው ብዙ አሳዛኝ እና ክፉ ነገሮች አሉን። እነዚህን ዛሬ ሁላችንም የምንጸየፋቸውን እና እንዳይ ደገሙ የምንታገላቸውን የትናንት ጠባሳዎች ለማረም የምናደ ርገው ሂደታችን አይጧን በማጥፋት ሰበብ ምጣዱን የሚሰብር እንዳይሆን ጥንቃቄ ያስፈልገናል። ሰው ጠባሳውን አጠፋለሁ ብሎ ቆዳውን አይልጥም። የሀገራቱን አንድነት፣ የሕዝቦችን በተዋሕዶ እና በተገናዝቦ መኖር፣ የነገን አዲስ ራእይ እና የት ውልዱን የወደፊት ጉዞ የምንጋግርባትን ኢትዮጵያ የምት ባለ ውን የተሟሸች ምጣድ፣ እዚህም እዚያም የሚያስቸግሩንን እና አንዳንድ ጊዜም ልናልፋቸው የሚገቡንን አይጦች በማጥፋት ሰበብ መስበሩ ለጫማ ሲባል እግርን እንደመቁረጥ ያለ ነው።

እናም እስኪ አንዳንድ ጊዜ «ምእንቲ ዛ ምንጎ እታ አንጭዋ ትሕልፍ ለምጣዱ ሲባል አይጧ ትለፍ» እንበል።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ቫቲካን



***መሪጌታ*** አብርሃም «ሮም ድረስ መጥተህ ቫቲካንን ሳታ ያት እንዴት ትቀራለህ» ብሎ ቀጠሮ ያዝን:: ኤፍሬም የተባለ ወዳጄ ደግሞ መኪናውን አስነሥቶ ወደ ቫቲካን ይዞኝ ተጓዘ:: ከተማውን አቋርጠን ወጥተን፣ ወንዝ ተሻግረን እና መስኩን አቋርጠን ቢያንስ አንድ ዐርባ ኪሎ ሜትር እንጓዛለን የሚል ግምት ነበረኝ::

የኤፍሬም መኪና በሮም ከተማ መካከል በአንድ የመኪና ማቆ ሚያ ላይ ስትቆም ግን ግራ ገባኝ:: አሁንም እንደ ሀገሩ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ልማድ የሚጠጣ ለመግዛት የቆምን ነበር የመሰለኝ:: ነገር ግን ኤፍሬም ወዳጄ «ቅርብ ስለሆነ በእግራችን እንሂድ» ሲለን መገረሜን ይበልጥ ጨመረው:: «የት?» አልኩት እኔ:: «ቫቲካን::» አለ:: የሚሆነውን ለማየት ዝም ብዬ ተከተልኩት:: አንድ እድሜ ጠገብ የሆነ ግንብ እየታከክን በስተ ግራ ታጥ ፈን ግራ ቀኝ በተዘረጉት የግንብ ሱቆች መካከል እያለፍን ወደፊት ገሠገስን::

«እነሆ ቫቲካን» አለን ኤፍሬም:: እጅግ ሰፊ ከሆነ፣ ወንበሮች ከዳር እስከ ዳር ከሞሉት፣ በአራት ወገን የቴሌቭዥን ስክሪን ከተገጠመለት አደባባይ ፊት ለፊት ያለውን ታላቅ ካቴድራል እያመለከተ::

በሚዲያ ስንሰማት እና ስናያት፣ በታሪክ ስናነባት ሥዕሏን አግ ዝፈን የምንስለው ቫቲካን፣ ለካስ በሮም ከተማ መካከል የምት ገኝ መንደር ናት? አልኩ በልቤ:: እንዴት ያለ አስተዳደር፣ እንዴትስ ያለ አሠራር፣ እንዴት ያለ ኃይል፣ እንዴትስ ያለ ጥበብ ቢኖራት ነው ይህች መንደር እንዲህ ስሟ ሊገንን የቻ ለውለ? የሚለው ነበር በኀሊ ናዬ ሲመላለስ የነበረው ጥያቄ::

የካቶሊኩ ፖፕ በታላላቅ በዓላት ጊዜ በሚያስተምሩበት የቅ ዱስ ጴጥሮስ አደባባይ ከመላው ዓለም የመጣው ቱሪስት እንደ ጉንዳን ይርመሰመሳል:: ያች ትንሽ መንደር የተሸከመችው የቱሪስት ብዛት ምናልባትም መላዋ ኢትዮጵያ ከምትሸ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

መው በብዙ እጥፍ ሳይበልጥ አይቀርም:: ከፊት ለፊት በኩል ቀጥ ብሎ የገባው ጎዳና ግንቦቹ ወደ ጎን እየተለጠጡ ይሄዱና ከቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል ፊት ለፊት ሲደርስ የሰንቁላል ቅርጽ ይሠራል:: ከዚያም ቀጥ ብሎ ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ ካቴ ድራል ያመራል:: በመካከሉ የሂሮግላፊክስ ጽሑፍ የሲለበት የግብጻውያን ጥንታዊ ሐውልት ቆሟል:: ይሕ ሐውልት በራ ምሲ 2ኛ ዘመን የተሠራ ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ37 ዓመት በንጉሥ ካሊጎላ አማካኝነት ከግብጽ የተወሰደ ነው:: ከአደባባዩ ስፋት የተነሣ ከአንዱ ጫፍ ሆኖ የተደረደረውን ወንበር ሌላኛውን ጫፍ በውል ለማየት ያስቸግራል:: በሰፊው ቦታ ላይ የከበቡ ዲያሜትር ወደ 240 ሜትር ይጠጋልና::

ከ300000 ሕዝብ በላይ በሚይዘው አደባባይ ዙርያ በሁለት ረድፍ የቆሙ፣ 88 ዓምዶች እና 284 ቋሚዎች አሉ:: በረድ ፎቹ መካከል ለሰዎች መተላለፊያ የሚሆን ኮሪዶር አለው:: የየአንዳንዱ ዓምድ ከፍታ 60 ጫማ ይደርሳል:: በግንቦቹ ላይ እና ለብቻቸው የቆሙ 140 ቅርጾች ይገኛሉ::

ወደ ላይ ቀና ስትሉ በስተ ግራ በኩል በትንሹ 800 ዓመት የሞላቸው ጥንታውያን ሕንፃዎች የጥንቱን ውበት እና ቅርጽ እንደያዙ አሁንም አሉ:: በማዶ፣ ሟቹ ዮሐንስ ጳውሎስ በመስ ኮታቸው በኩል ብቅ ብለው በቴሌቭዥን መስኮት ቡራኬ የሚ ሰጡባት የመኖርያ ቤታቸው ትታያለች:: ከውጭ ሲያዩዋት



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እጅግ ጥንታዊ ከመሆኗ ባሻገር የተለየ ቅንጦት አይታይባትም፡ የውስጡን ፈጣሪ ይጠቀሙ:: እዚህ ቦታ ታሪካዊ ነገር ከዘመ ናዊ ነገር ይልቅ ልዩ ዋጋ አለው::

የመጀመሪያው ጉብኝታችን የቅዱስ ጴጥሮስ መቃብር ወይ ሆነው ካቴድራል ነበር:: ምናልባትም እኛ ከያዝነው ሰልፍ ፊት ለፊት ሁለት ሺ የሚሆኑ ሰዎች ባይሰለፉ አይቀሬም:: በቦታው ያገኘሁት መረጃ እንደሚያሳየው ይህች ትንሽ ከተማ በዓመት ከ3 ሚሊዮን ቱሪስቶች በላይ ታስተናግዳለች:: ዘር ያዋን በግንብ የታጠረች በከተማ ውስጥ የምትገኝ ይህች «ቅዱስ ከተማ» ጠቅላላ ስፋቷ 44 ሄክታር፣ ወይንም 110 ኤከር፣ ወይንም ደግሞ 0.44 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ያህል ብቻ ነው:: በውስጧ የያዘችው ሕዝብ 890 ሲሆን በዓለም ላይ በስፋትም ሆነ በሕዝብ ብዛት ትንሿ ሀገር ናት ይሏታል::

ቫቲካን ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ጳውሎስ ኔሮን በተባለው የሮም ንጉሥ ትእዛዝ በሰማዕትነት ካረፉበት ዘመን ጀምሮ ነበር የክርስቲያኖችን ትኩረት ያገኘችው:: በተለይም ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በ326 ዓም በቅዱስ ጴጥሮስ መቃብር ላይ የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን ካነፀ በኋላ የመላውን ዓለም ክርስቲያኖች ክብር እና ትኩረት አገኘች::

በርግጥ የቫቲካን ታሪክ ከክርስትናም የሚቀድም ነው:: ቫቲካን የሚለው ስም «ሞንስ ቫቲካነስ– የቫቲካን ኮረብታ» ከሚለው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የመጣ ሲሆን አሁን የቫቲካን ከተማ የያዘችው ቦታ የዚህን ግብታ ክፈል እና በአጠገቡ የሚገኘውን መስክ የጨመረ ነው:: የካቶሊክ ፖፖች በቦታው «ቤተ ፖፕ» ሠርተው መደበኛ መቀመጫ ቦታ ማድረግ የጀመሩት ከ5ኛው መቶዘ ጀምሮ ሲሆን ከዚያም በየጊዜው ተጨማሪ ግንባታዎችን እያስተናገደ ከዛሬው ዘመን ደርሷል::

አሁን ሰልፉ እየተጋመሰ ነው:: ወደ ካቴድራሉ እስክንገባ ድረስ እስኪ ታሪኳን እየቃኘን እንቆይ::

አሁን ያለችው የቫቲካን የከተማ ሃይማኖታዊ መንግሥት ሆና የተቋቋመችው ፌብሩዋሪ 11 ቀን 1929 ዓም በፖፑ እና በጣልያን መንግሥት መካከል በተፈረመው ስምምነት መሠረት ነው:: በዚህ ስምምነት የቫቲካን ነጻ መንግሥትነት ዕውቅና ያገኘ ሲሆን፣ የከተማዋ ክልሎች፣ መብቶች እና ሥልጣኖች፣ ጥቅሞች እና ገቢዎች በዝርዝር ታትተዋል::

አሁን ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል እንግባ:: ልክ በሩ ላይ ስንደርስ በጥንቱ የሮማውያን ወታደሮች አለባበስ ያሸበረቁ ወታደሮችን እናገኛለን:: የስዊዝ ወታደሮች /ስዊዝ ጉዋርድስ/ ይባላሉ ከ1503 ዓም ጀምሮ የቫቲካን ጠባቂዎች እና ፖሊሳዊ ሥራውን የሚሠሩት ከስዊዘርላንድ የመጡ ጠባቂዎች ናቸው::

መቼም እዚህ ቦታ ታሪክ እና ቅርስ የሚጠበቀው በንብረት ብቻ ሳይሆን በአለባበስም ጭምር ነው:: የስዊዝ ጠባቂዎች



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ዝብርቅርቅ ያለ እና ከታሪካችን እና ከትውፊታችን ጋር አን ዳችም ግንኙነት የሌለውን አለባበስ ለብሰው የሚቆሙትን የ ገሬን የቤተ መንግሥት እና የቤተ ክህነት ጥበቃዎች አስታ ወሱኝ::

ወደ ላይ ያለው ከፍታ ረዥምም ባይሆን ኖሮ ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ የግድ እንደ ዘኬዎስ ዛፍ ላይ መውጣት ይገባኝ ነበር:: የካቴድራሉ ስፋት የጃንሜዳን አንድ ሦስተኛ ሳያክል አይቀ ርም:: የተደረደሩት ዓምዶች በሰልፍ የቆሙ ጥንቁቅ ወታደ ሮችን ይመስላሉ:: ጣራው ላይ በልዩ ልዩ ቅርጽ የተለበጠው ወርቅማ ቅርጽ በመካከሉ ካቀፋቸው ሥዕሎቹ ጋር ሲታይ ዓይን እንደ ተተከለ ይቀርበታል:: በዓለም ላይ ረዥሙ ዶም የሚባለው የቤተ መቅደሱ ዶም 136.57 ሜትር ከጣራው በላይ ርዝመት ሲኖረው፣ የስፋቱ ዲያሜትር 41.47 ሜትር ይደርሳል::

በቀጥታ ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ መቃብር ከሕዝቡ ጋር እየተ ከታተልን ወረድን:: መቃብሩ የሚገኘው ከታች ነው:: ዙር ያውን በብረት አጥር ተከብቦ እና በመስተዋት ተጋርዶ ጎብኝ ሊመለከተው በሚችል መንገድ መቃብሩ ተከፍቷል:: ይህ ቦታ የቅዱስ ጴጥሮስ መቃብር መሆኑ እንዴት ሊታወቅ እንደ ቻለም አርኪዎሎጂካዊ እና ትውፊታዊ መረጃዎቹ ከአጠገቡ ተጽፈዋል:: «ጴጥሮስ ያረፈው እዚህ ነው» ተብሎ በመቃብሩ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ በላቲን ተጽፎ የተገኘው የመጀመሪያው መነዘ መረጃ ከማስረጃዎቹ አንዱ ሆኖ ተቀምጧል።

በካቴድራሉ ግራ እና ቀኝ የጎብኙውን እግር እየተከተላችሁ ስትጓዙ በዚያች መንበር ያገለገሉ ፓፖች መቃብር በብረት ፍርግርግ ታጥሮ ወይንም ከግድግዳው ጋር አብሮ ተሠርቶ ይገበኛል። በያንዳንዱ መቃብር ላይ ያረፈውን ሰው የሚያመለክት ጥበብ የተሞላበት ሐውልት ይታያል። እያንዳንዱን በሚገባ ለማየት ወደ አንድ ሰዓት ይወስዳል።

ቫቲካን የራስዋ የሆነ ልዩ አስተዳደር አላት። 1 ቢሊዮን የሚደርሱትን መላውን ካቶሊካውያንን እና የቫቲካን ከተ ማን በበላይነት የሚያስተዳድርዋት ፖፑ ናቸው። ፖፑ ይህንን ኃላፊነት የሚወጡት ከካርዲናሎች ጉባኤ በሚያገኙት ርዳታ ነው። ነገር ግን ከፖፑ ሥር ለልዩ ልዩ የመንግሥት አስተዳደሮች አሉ። በፓፓው የሚሾሙ ካርዲናሎችን የሚያቅፍ የሕግ አውጭ ኮሚሽን ሲኖር በእርሱ ሥር ደግሞ የከተማዋ ገኘ ሥራ አስፈጻሚውን ይመራል። ቫቲካን የራስዋ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም አላት።

የፍርድ አስተዳደር ሥርዓቱ በፓፓው የበላይነት በአራት ደረጃዎች የተዋቀረ ነው። የአጥቢያ ዳኛ /ማጅስትሬት/፣ የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ናቸው።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እስከ ከካቴድራሉ እንውጣና በዓለም ላይ እጅግ ታዋቂ ወደ ሆነው የቫቲካን ሙዝየም እና ቤተ መጻሕፍት እናምራ:: በቫቲካን ከለላ አብዛኛውን ቦታ ከያዙት ሕንፃዎች መካከል የቫቲካን ሙዝየም ሕንፃ አንዱ ነው:: ሕንፃው ጥንታዊ የውስጥ አሠራሩ ግን ዘመናዊ እና እጅግ ጥብቅ ነው:: እነዚህን በዓመት ከ2.5 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የሚጎበኛቸው ሙዝየሞች ለመጎብኘት በየሰዓቱ የሚሰለፈው ሕዝብ ብዛት ያልተፈቀደ ሰላማዊ ሰልፍ ነው የሚመስለው::

ሌላው በቫቲካን ያለው ውድ ሥፍራ የቫቲካን ቤተ መጻሕፍት ነው:: ከ15ኛው መክዘ ጀምረው ሲሰባሰቡ የቆዩ ጥንታውያን መጻሕፍትን እና መረጃዎችን የያዘው ይህ ቤተ መጻሕፍት 2 ሚሊዮን የታተሙ መጻሕፍትን፣ በላቲን፣ ግሪክ፣ ዕብራይስጥ፣ ፋርስ፣ ግእዝ፣ አራማይክ የተጻፉ 80000 የብራና መጻሕፍትን፣ 10000 በራሪ ወረ ቀቶች /INCUNA BULA/፣ እና 100000 የድንጋይ ላይ ጽሑፎችን፣ እንዲሁም 33000 የግሪክ፣ የሮም እና የቫቲካን ፖፖች ሳንቲሞችን የያዘ ነው:: የቤተ መጻሕፍቱ ካታሎግ 2 ሚሊዮን ካርዶችን የያዘ ሲሆን፣ በየዓመቱ 6000 አዳዲስ መጻሕፍት ይጨመሩበታል:: ከእነዚህ መካከል በማኅ የሚገቡት 25 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው:: ይህ ቤተ መጻሕፍት ከ2005 ጀምሮ ለጥገና የተዘጋ ሲሆን የሚከፈተው በ2010 ነው::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አንዳንድ ጊዜ የሚፈለጉትን መረጃዎች ለማግኘት አስቀድሞ ፕሮግራም መያዝና የሚጠየቁትን መመዘኛዎች ማሟላትን ይጠይቃል:: ችግሩ እነዚህ መመዘኛዎች እንደ ጎብኝው ሰው ሀገር ይለያያሉ:: በአውሮፓ በተዘዋወርኩበት ቦታ ሁሉ እንዳ የሁት የኢትዮጵያ መዛግብት ባሉባቸው ቦታዎች ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለጉብኝት ፈቃድ ማግኘትም ሆነ፣ ፈቃዱ ከተገኘም በኋላ በቂ መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ነው:: ኢትዮጵያን በተመለከተ የተሰባሰቡ የብራና መጻሕፍትንም ሆነ መዛግብትን ማግኘቱ ከኛ ይልቅ ለሌሎች ይቀልላል::

ከቫቲካን ቤተ መጻሕፍት ቀጥሎ ሌላው የቫቲካን ከተማ ጌጥ የቫቲካን ጥንታውያን መዛግብት ማዕከል /ቫቲካን አርካይቭስ/ ነው:: ከመላው ዓለም በቫቲካን መልእክተኞች አማካኝነት ሲሰ ባሰቡ ለዘመናት የኖሩት 150000 አርካይቮች ማረፊያቸው እዚያ ነው::

የቫቲካን ነዋሪዎች የቫቲካን መታወቂያ እና ፓስፖርት አላ ቸው:: ከተማዋ የራስዋ የባቡር ጣቢያ፣ ባንክ፣ ሱፐር ማር ኬት፣ የሄሊኮፕተር ማረፊያ፣ የእሳት አደጋ መከላከያ እና የአምቡላንስ አገልግሎት፣ የጤና ተቋማት እና ፋርማሲ አሏት:: የቫቲካን ብሔራዊ ባንክ የአውሮፓን ዩሮ የሚጠቀም ሲሆን በሳንቲሞቹ ላይ እንደ ማንኛውም ሀገር የራሱን ምስ ሎች ያሳትማል:: በዓለም ላይ ትልቁን አንቴና /directional



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

antenna/ የያዘ፣ በ32 ቋንቋዎች አገልግሎት የሚሰጡ ሁለት የአጭር ሞገድ፣ ሦስት የመካከለኛ ሞገድ እና አራት የኤፍ ኤም የሬዲዮ ጣቢያዎች፣ ከ1861 ዓም ጀምሮ በታሳትሚዎቹ የነበሩ ጋዜጦች፣ በ1983 ዓም አገልግሎት የጀመረ የራሱ የቴሌቭዥን ጣቢያ፣ ሁለት የዜና አገልግሎት ኤጀንሲዎች እንዲሁም ለመረጃ ማስተላለፊያ የምትጠቀምባቸው 93 ኢንተርኔት አገልግሎት መስጫዎች /service providers/ አሏት::

120 አባላት ያሉት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካርዲናሎች ጉባኤ ስለሚሰበሰብበት ቦታ ታሪካዊ ትውፊት ሳልናገር ማለፍ የለብኝም:: በተለይም አዲስ ፖፕ ለመምረጥ መብቱ ያላቸው እድሜያቸው ከሰማንያ ዓመት በታች የሆኑ ካርዲናሎች በሲስቲን መቅደስ የየራሳቸውን ምርጫ ይዘው ይሰባሰባሉ:: ጉባኤው ሃሳቦቹን እያጠበበ፣ ከብዙ ወደ ጥቂት ሃሳቦች እየተሰባሰበ ለመሄድ ቀናት ይፈጃሉ:: ሕዝቡ በቅዱስ ጴጥሮስ አደባባይ ቆሞ ይጠብቃል::

አንድን ፖፕ ለመምረጥ ከመራጮች መካከል የሁለት ሦስተኛ ሲደመር አንድ ድምፅ ማግኘት ያስፈልጋል:: በየጊዜው ድምፅ ይሰጣል:: ፖፑን ለመምረጥ የሚያስችል በቂ ድምፅ ካልተገኘ በጭስ መውጫው በኩል ጥቁር ጢስ ይወጣል:: አንዳንዶች እንደሚነገሩኝ የተመረጠባቸው የምርጫ ካርዶች ጥቁር ጢስ ከሚያወጣ ኬሚካል ጋር ሲቃጠል የሚወጣ ነው:: የልዩነቱ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሃሳብ ወደ ሕዝቡ አይወጣም፡ የተለየ ሃሳብ ለምን ሰጠህ ተብሎ የሚወነጀልና አደጋ የሚደርስበትም የለም። እያንዳንዱ ካርዲናልም ምርጫ ከመጀመሩ በፊት ምሥጢር ለመጠበቅ መሐላ ይፈጥማል። መሐላውን ያፈረሰ ከተገኘ ወዲያውኑ ይለያል።

በየቀኑ ሕዝቡ በአደባባዩ ይሰባሰባል፣ ጥቁሩን ጢስ ካየ፣ አዲስ ፖፕ ገና አልተመረጠምና ጸሎቱን ይቀጥላል። ካርዲናሎቹ ወደ አንድ ሃሳብ ከመጡና ፖፑን ለመምረጥ የሚያስችለው ድምፅ ከተገኘ ነጭ ጢስ በሲስተይን መቅደስ በኩል ይታያል። ያን ጊዜ ሕዝቡ በደስታ ይፈነጥዛል።

ኢትዮጵያውያን የቅዱስ ጴጥሮስን እና የቅዱስ ጳውሎስን መቃብሮች ለመሳለም ወደ ቫቲካን መንገዝ የጀመሩት ከመካከለኛው ዘመን ቀደም ብሎ መሆኑ ይነገራል። መጀመርያ ወደ ግብጽ፣ ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም፣ በመጨረሻም ወደ ሮም በመምጣት ነበር ይሳለሙ የነበሩት። ለእነዚህ ኢትዮጵያውያን ማረፊያ የተሠሩ ቤቶች ነበሩ። በኋላ ደግሞ በ14ኛው መከዘ የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያውያን መገልገያነት ታነጸ። እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ሥዕሎች እንደ ተሞላ ታሪክ እየመሰከረ ይታያል። ከኢትዮጵያ የሚሄዱ ካቶሊካውያንም በአሁኑ ጊዜ ይገለገሉበታል።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በውስጧ ሰው የማይወለድባት ትንሿ ሀገር ቫቲካን በመሬት ይዞታዋ ትንሽ ትሁን እንጂ የያዘችው ታሪክ እና ትርክ ግን ከታላላቆቹ ሀገሮች እጅግ የሚበልጥ ነው። ለዚህ ነው "ሮምን ከመጎብኘት ቫቲካንን ፎቶ ማንሣት ይቀላል" ብሎ ሾቶ ጸሐፊ የመሰከረው። እውነትም ከተማዋን ከአንድ ትልቅ ሕንፃ ላይ ቆሞ ፎቶ ማንሳት እጅግ ቀላል ነው፤ በውስጧ ያሉትን ለማየት ግን ዓመታትን ይጠይቃል። ያውም ከተፈቀደ። ቫቲካን፣ ጣሊያን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ባሕር ዛፍ

**አሜሪካ፣ ሜሪ ላንድ** ግዛት፣ ሲልቨር ስፕሪንግ ከተማ ውስጥ፣ ስታር ባክስ የተሰኘ አንድ ቡና መሸጫ ቤት ተቀምጠን ሰው እንጠብቃለን:: ዕድሜያቸው ከዓርባዎቹ በላይ የሆኑ ሁለት ኢትዮጵያውያን ከኛ አጠገብ ከሚገኘው ጠረጴዛ ዙርያ ተቀምጠው የሞቀ ክርክር ይዘዋል:: ክርክሩ ሲጀመር አልደረስንም:: ከንግግራቸው ግን የክርክሩ መነሻ ጉዳይ ይታወቃል::

በተለይም አንደኛው ሰውዬ በአካባቢው ሰው መኖሩን እስኪረሳው ድረስ እጁን እያወና ጨፈና እየጮኸ «የለም የለም በዛ፣ ዲቪ፣ አሳይለም፣ ስኮላርሺፕ ምናምን እያሉ ማንንም እየሰበሰቡ ኑሮውን አበላሹት፣ ስንት ነገር ነው የቀረው:: ድሮኮ አበሻ ብርቅ ነበረ፤ ዛሬማ እንደ ጠጠር ረከሰ:: ያለነውን በሚገባ ሳይይዙ መጨመር ምን ዋጋ አለው» ይላል::

ጓደኛው ደግሞ «አሜሪካ የእኩል ዕድል ሀገር ናት:: እድሉ ይሰጥሃል፤ አጠቃቀሙ የራስህ ነው:: በመብዛት በማነስ አይደለም::» እያለ ቻይና ዎችን እና ላቲኖችን እየጠቀሰ ይከራከረዋል:: ያኛው ግን እየደጋገመ «በጭራሽ በጭራሽ ሲደተኛ አበሻ በዝቷል» እያለ እጁን ያወናጭፋል::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ በኋላ መገረም ጀመርኩ «ዶ/ኪ. ሰው እንኳንም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ኃላፊ አልሆነ፡፡ እርሱ ራሱ በሰው ሀገር መጥቶ አየሩ ሊላውን መጥመጥት የለበትም፤ መብዛት የለበትም እያለ እንዴት ነው የሚከራከረው?» ብዬ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ «የሰው ኃይሏን ለምታጣው ኢትዮጵያ ተቆርቋሪ ነው እንዳልል የሚያንገበግበው ሰው ከሀገሩ መውጣቱ ሳይሆን እርሱ በሚኖርበት ሀገር መብዛቱ ነው፡፡ ለስደተኛው አዝኖ ነው እንዳልል ተንቀባርረን እንዳንኖር አበሻ እንደ ጠጠር በዝቶ እድሉ ሁሉ ተበላሸ ነው የሚለው፡፡ ታድያ የዚህ ሰው ችግሩ ምንድንነው?»

መልሱን የሰጠኝ አንድ ወዳጄ ነው፡፡ ባሕር ዛፍነት ነው ችግሩ አለኝ፡፡

መነሻው አውስትራልያ ሆኖ እስያን፤ አፍሪካን፤ አውሮፓን፤ ሰሜን አሜሪካን እና ደቡብ አሜሪካን ያጥለቀለቀው ባሕር ዛፍ የድኾችን ጉሮሮ በማዘጋት እና የማገዶን ፍጆታ በመቻል ረገድ ትልቅ አስተዋጽዖ ቢኖረውም ጠባዩ ግን አስቸጋሪ ነው፡፡

ባሕር ዛፍ ብዙ ውኃ ይፈልጋል፡፡ ከተተከለበት አካባቢ ይነሣና በዙርያው ያለውን ውኃ ሥሩ እስከደረሰበት ድረስ መጥጥ አድርጎ ነው የሚሰበስበው፡፡ ሌሎቹ ዛፎች በአካባቢው ቢኖሩም ባይኖሩም እርሱ ግን ለራሱ ብቻ የሚሆን ውኃ ወደ ታች እና ወደ ጎን ሥሮቹን እየላከ መሰብሰብ ብቻ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ ሌሎቹ ዛፎች ያላቸው አማራጭ ሁለት ነው፡፡ ነቅሎ ሌላ ቦታ የሚተክላቸው ካገኙ አካባቢውን መልቀቅ ያለ በለዚያም መድረቅ፡፡



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳንዱ ሰው ጠባዩ እንደ ባሕር ዛፍ ነው፡፡ ሥልጣንንም፣ ገንዘብንም ፣ ትምህርትንም፣ ዕድልንም፣ ሁብትንም የሚችልበት ቦታ ድረስ ሥሩን እየሰደደ ብቻውን መሰብሰብና ብቻውን ማደግ ይወዳል፡፡ ስለ ሀገር፣ ስለ ትውልድ፣ ስለ ወገን፣ ስለ ሌላ የሰው ዘር ግድ የለውም፡፡ ብቻ የሚገኘውን ነገር ሁሉ እርሱ ራሱ ብቻ አግኝቶ ማደግ ነው ሃሳቡ፡፡

እነርሱ ውጭ ሀገር ሄደው በርዳታ በተገኘ ገንዘብ ተምረው፣የቤት ዕቃ እና መኪና ገዝተው፣ በመጠኑም ቢሆን ገንዘብ ሰብስበው የሚመጡ ሰዎች አሉ፡፡ የሄዱበትን መንገድ፣ ያገኙትን ጥቅም ያውቁታል፡፡ ያ መንገድ ሌሎች ብዙ ወገኖቻቸውን ሊጠቅም እነርሱ የበሉትን ዓይነት እንጀራ እንዲያገኙ ሊያደርግ እንደሚችል ያውቃሉ፡፡

ወደ ሀገራቸው ተመልሰው የሥልጣኑን ቦታ ሲይዙት ግን የባሕር ዛፍን ጠባይ ይዘው ቁጭ ይላሉ፡፡ የሚረዱት የውጭ መንግሥታት መረረን ሳይሉ፡፡ የሚልከው የኢትዮጵያ መንግሥት አትላኩ ሳይል፡፡ የሚቀበሉት የውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ሞላን ሳይሉ የሀገራችን ባሕር ዛፎች ግን ዕድሉን ብቻቸውን ተጠቅመው ለሌላው በሩን ዘግተው ቁጭ ይላሉ፡፡ ሥራቸው እንደ ባሕር ዛፍ ብዙ ነውና በቢሮክራሲ እና በቀጠሮ ብዛት፣ አልፎ አልፎም ደግሞ ለሰው ከባድ የሆኑ መመርያዎችን በማውጣት ዕድሉን ሁሉ ይዘጉታል፡፡



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«ብዙ ጊዜ ማስተርስና ፒኤች ዲ በስንት መከራ ነበር የሚገኘው:: ሰው ተመርጦ ነበር የሚሄደው:: ዛሬማ ማንንም እየላኩ አበላሹት፤ ክብሩን አሳጡት» ይላሉ:: እንዲህ የሚሉት ግን ለማዕረጉ ክብር ተጨንቀውላት ሳይሆን የባሕር ዛፍ ጠባያቸው ሁሉን እኔ ብቻ ስለሚያሰኛቸው ነው::

በምዕራቡ ዓለም ያሉ ድርጅቶች ሰውን በማስታወቂያ ከመቅጠር ይልቅ እዚያው ድርጅት የሚሠራ ሰው በሚያቀርበው በጎ አስተያየት /ሪኮመን ዴሽን/ መቅጠር ይወዳሉ:: ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣ ብለው ነው መሰል:: ታድያ በዚህ መንገድ ሕንዶች፤ ቻይናዎችን እና ላቲኖችን ያህል የተጠቀመበት የለም::

በአሜሪካ ምድር ስዘዋወር የምሰማው የኛ ታሪክ ግን ለየት ያለ ነው:: በአንድ ድርጅት አንድ አበሻ ከተቀጠረ ማንንም ሪኮመንድ ማድረግ አይፈልግም:: ከአፍሪካ ተወስዶ የእንስሳት ማቆያ ውስጥ እንደ ተቀመጠ ቺፓንዚ ብቻውን እየተጎበኘ ቢኖር ደስ ይለዋል:: ቀጣሪዎቹ እና የሥራ ባልደረቦቹ ሌላ የርሱን ወገን ባለማየታቸው «ይህ አበሻ የሚባል ዘር እየጠፋ ያለ ዘር ነው እንዴ» እስኪሉ ድረስ ቢገረሙም፤ ቢሞት ሌላ ወገኑ እዚያ እንዲመጣ አይፈልግም::

መሬት ለሁሉ ትበቃለች:: የአማዞንን እና የኮንጎን ጫካዎች በአንድ አካባቢ አስተናግዳ የምትኖር ናት:: መሬት:: ባሕር ዛፍ ግን ሁሉንም ውኃ እሚጥጥ ካልጠጣ አይደሰትም:: ይህም ሰው እንዲህ ነው:: የድርጅት



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሀብት ከርሱ ሌላ ሺዎችን ሊያስተናግድ በቻለም ሥፍን ሰድዶ ብቻውን ካላሟጠጠ የኖረ አይመስለውም።

በአንዳንድ መሥሪያ ቤቶችኮ በየስብሰባው፤ በየዐውደ ጥናቱ፤ ገንዘብ ሊያስገኝ በሚችል ጉዞ፤ በውጭ ሀገር ተልዕኮ ተመሳሳይ ዓይነት ሰዎች ነው የምናየው። ሌላ ባለሞያ፤ ሌላ የተማረ፤ ሌላ ዐቅም ያለው ሰው የሌለ ይመስል ለሂሳብም ጉዳይ፤ ለኤች አይ ቪ/ ኤድስም ጉዳይ፤ ለአካባቢ ጥበቃም ጉዳይ፤ ለሴቶችም ጉዳይ፤ ለሕፃናትም ጉዳይ፤ ለመዝገብ አያያዝም ጉዳይ፤ ለድርጅቱ ጥበቃም ጉዳይ እነዚያው ተመሳሳይ ሰዎች ናቸው የሚሄዱት።

እነዚህ ሰዎች ሁለገብ የሆነ ዕውቀት እንዲኖራቸው ተፈልጎ፤ ወይንም በመሥሪያ ቤቱ የሚላክ ሰው ጠፍቶ፤ ያለበለዚያም ሞያው የሚመለከተው ሰው አልሄድም ብሎ አይደለም። እንደ ባሕር ዛፍ ሥርን ዘርግቶ ሁሉን የመሰብሰብ አባዜ ነው እንጂ። ባሕር ዛፍ የአካባውን ውኃ ሁሉ መልጭ አድርጎ እንደሚጠቀማት ሁሉ እነዚህም በመሥሪያ ቤቱ የተገኘን ዕድል ሁሉ ብቻቸውን ሙልጭ አድርገው ነው የሚጠቀሙት።

በሀገራችንኮ ሌሎች ነጋዴዎች ሊደርሱባቸው የማይችሉ ጥቂት ሰዎች ብቻ የሚጠቀሙባቸው ስንት የንግድ መንገዶች አሉ። እነዚህ ዕድለኛ ነጋዴዎች ሥራቸውን በሚገባ ይሰድዱና በአካባቢያቸው ላለው ለሌላው ነጋዴ ሳያዝኑ ውኃውን ሁሉ ሙልጭ አድርገው ወደ ራሳቸው ይሰበስቡታል።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እነርሱ ያድጋሉ ሌላው ይቀጨጫል:: ያንጊዜ ሌላው ኪሣራ ያለው እማሪጭ ሁለት ነው:: ዐቅም ካለው ወደ ሌላ ሥራ ወይንም ቦታ ይሄዳል:: ዐቅም ከሌለው ግን ሥራውን በኪሳራ ይዘጋል::

ባሕር ዛፍ የአካባቢውን ውኃ ሙልጭ አድርጎ ለራሱ ብቻ በመውሰድ ሌላ ዓይነት ዛፍ እንዳይበቅል ማድረጉ ብቻ አይደለም:: በአካባቢው ሌላ ዛፍ የሚበቅልም ከሆነ ያው እንደ እርሱ ዓይነት ባሕር ዛፍ መሆን አለበት:: እንደ እርሱ የሚሻማ:: ለሌላ ግድ የሌለው:: ሥሩን የቻለውን ያህል ሰድዶ ውኃውን የሚሰበስብ ሌላ ተመሳሳይ ባሕር ዛፍ:: ባሕር ዛፎች ለአካ ቢያቸው አያዝኑለትም:: የአካባቢው ሥነ ምዕዳር ቢበላሽም:: መሬቱን በማድረቅ ወንዞች እንዲነጥፉ ቢደረግም:: ሌሎች ዛፎች በመድረቃቸው ምክንያት የአካባቢው የአየር ሁኔታ ቢዛባም ለባሕር ዛፎች ምንም አይሰ ማቸውም:: ብቻ እነርሱ ያግኙ፤ እነርሱ ይደጉ::

የባሕር ዛፍ ጠባይ ያላቸውም ሰዎች እንደዚሁ ናቸው:: እነርሱ በሚገኙበት ቦታ ሊገኝ የሚችለው እንደ እነርሱ ባሕር ዛፍ የሆነ ብቻ ነው:: ሲበሉ የሚበላ፤ ሲሰርቁ የሚሰርቅ፤ ሕግ ሲጥሱ የሚጥስ፤ ሲጨክኑ የሚጨክን፤ ሀገር ሲጎዱ አብሮ አገር የሚጎዳ የነርሱው ቢጤ:: ስለ ሀገር ጥቅም:: ስለ ትውልድ አያስቡም:: ብቻ እነርሱ ይጠቀሙ::

አሜሪካ ውስጥ ፓርኪንግን በመሳሰሉ በአንዳንድ ሥራዎች የሚቀጠሩ ሰዎች የስርቆት ሥርዓት ይዘረጋሉ:: እዚያ ቦታ ላይ የማይሰርቅ ሰው መቀመጥ አይችልም:: ሌሎችን ያጋልጣላ:: እነዚያ ሥራቸውን ሰድደው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የሰው ገንዘብ መሰብሰብ የለመዱ ባሕር ዛፎች ከእነርሱ ውጭ ሌላ ዓይነት ዛፍ እንዲመጣ ስለማይፈልጉ ነገር ዓለሙን ሁሉ ዘጋግተው ሰውዬው አካባቢውን ጥሎ እንዲሄድ ያለበለዚያም እንደ እነርሱ ባሕር ዛፍ እንዲሆን ያደርጉታል፡፡

ባሕር ዛፍ ከተስማማም ከሌላ ባሕር ዛፍ ጋር ነው፡፡ ባሕር ዛፍ የሆኑ ሰዎችም ከተስማሙም በዘር እና በትውልድ ቦታ ከሚመስላቸው ጋር ብቻ ነው፡፡ «የወንዛቸውን» ሰው ካልሰበሰቡ በቀር ሌላ ዐይነት ዛፍ አይታ ያቸውም፡፡ ሌላው ቀርቶ «ከትናንት ወዲያ»/አዲስ አበባ/ እና «ሠለስትና» /ጎጃም/፣ ከትናንት በስቲያ/ጎንደር/ የሚሉ ሦስት ዓይነት ዛፎችን እንኳን ለማስተናገድ ፈቃደኞች ያልሆኑ ባሕር ዛፎች አሉ፡፡

ለዚህም ነው አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን፣ አንዳንድ መሥሪያ ቤት፣ አንዳንድ ድርጅት፣ አንዳንድ አካባቢ፣ አንዳንድ የሥራ መስክ ውስጥ ተመሳሳይ የዘር ሐረግ ወይንም የትውልድ ቦታ ወይንም ቀየ ያላቸውን ሰዎች ብቻ የምናየው፡፡ በባሕር ዛፍነት ጠባይ ምክንያት፡፡



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# የአማልክት ምድር



**እነሆ** በዚህ ሰዓት አሪስቶትል እና ሶቅራጥስ፣ አፍላጦን እና አርስጣጣሊስ በፍልስፍናቸው ይራቀቁባት በነበረው፣ የሕዝብ አስተዳደር የሚባለው ዴሞክራሲ በተወጠነባት፣ ለዛሬዎቹ ሕንፃዎች እና መንገዶች መሠረት በተጣለባት፣ እነ እስቂለስ ሶፎቅለስ እና ኢውሪፒደስ በቅኔያቸው እና በድራማቸው ተመልካችን ጉድ ያሰኙ በነበረባት፣ አሪስቶፋለስ የተውኔትን ጥበብ ወደ ከፍተኛ ፖለቲካዊ ሳታየር ባራቀቀባት፣ ሄሮዶቱስ የዓለ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ምን ታሪክ ባዘጋጀባት፣ እና ሎሚር ግቀምን ከአፈ ታሪክ ጋር አዛምዶው ቅኑ በተመሩባት የአቴና ከተማ እምብርት ላይ እገኛለሁ፡፡

ፀሐይ አቴናን በከበቧት ተራሮች ጀርባ መውረድ ስትጀምር፣ ወይን ጠጅ የመሰለ ጨረሯን ከሳሮኒክ የባሕር ሰላጤ እንሥታ በሩቅ እስከሚገኘው የፔሎፖኒዝ ሦስት መንዝናዊ ከፍታ ድረስ ስትለቅቀው፣ ለከተማዋ ሐምራዊ ዘውድ ትደፋላታለች፡፡ ያን ጊዜ ታድያ ከተማዋን ከአይዮስ ጊዮርጊስ ተራራ ላይ ሆኖ ለተመለከታት፣ እነዚያ ሁሉ አማልክት አቴናን ዙፋናቸው አድርገው ለምን እንደመረጧት የሚተርከውን የግሪክ አፈ ታሪክ ለመቀበል ይዳዳዋል፡፡

ከተማዋን ጎብኝቶ ለመጨረስ አንድ ወር እንኳን መብቃቱን እጠራጠራለሁ፡፡ ታሪክ፣ ቅርስ፣ አፈ ታሪክ፣ እና መልክዐ ምድር ተግባብተው በሠሯት በዚህች ከተማ የማይታይ ነገር የለም፡፡ የታላላቆቹ ፈላስፎች የማስተማርያ ቦታ የነበረው «አካ ዳሚያ» ይሄው ከፊት ለፊቴ ተዘርግቷል፡፡ እዚያ ማዶ ደግሞ አቴናውያን በማራቶን ጦርነት በፋርሶች ላይ የተቀዳጁትን ድል ለማብሠር የመጣው መልእክተኛ ድሉን ካበሠረ በኋላ ያረፈበት ቦታ ይታያል፡፡

እኔ ግን ከተማዋን በአራቱም መዓዝን ከየሁባት ከ*አይዮስ ጊዮርጊስ* ተራራ ልውረድና አስደናቂ ወደ ሆነውና በአቴና እም



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

***አክሮፖሊስ*** ልውሰዳችሁ:: እርሱን ስት
ብርት ወደሚገኘው
በኝ የሦስት ሺ ዘመን ታሪክ እንዳያችሁ ቁጠሩት::

በአቴና እምብርት የተገነባው አክሮፖሊስ የአቴናውያን የሥ
ጥበብ፣ የኪነ ጥበብ እና የእምነት ማዕከል ነው:: 156 ሜትር
ከባሕር ጠለል በላይ ከፍ ብሎ 300 ሜትር በ150 ሜትር
ስፋት ባለው ተራራ ላይ የተቆረቆረው አክሮፖሊስ መላውን
ከተማዋን እና የባሕሩን ጠረፍ ወለል አድርጎ የሚያሳይ ስትራ
ቴጂያዊ ቦታ ነው::

ተራራው መስቀለኛ ካለመሆኑ በቀር የግሼንን ተራራ ይመ
ሳል:: መግቢያውም እንደ ግሼን ተራራ አንድ እና ያውቃ
ከላይ እስከ ታች በተደረደሩ ደረጃዎች የተነጠፈ ነው:: ተራ
ራው ላይ ብቅ ሲሉ ፊት ለፊት «***የቤሌ በር***» የተሰኘውን
ቅስት ያገኛሉ:: ስሙን ያገኘው በአካባቢው በ1852 ዓም ጥና
ታዊ ቁፋሮ ካደረገው ፈረንሳዊ ተመራማሪ ከኧርነስት ቤሌ
ነው:: በስተ ቀኝ በኩል ያለው ሠገነት በኋላ ዘመን እንደገና
የተገነባ ሲሆን ለትኬት መቆጣጠሪያነት ያገለግላል:: የቤሌ
በር ወደ አክሮፖሊስ ያስገቡ ከነበሩት ሁለት ጥንታውያን
በሮች አንዱ ነበረ::

ወደ ውስጥ አለፍ ስትሉ የፍቅር አምላክ የሆነችው የአፍሮ
ዳይት ቤተ መቅደስን ፍራሽ ታገኙታላችሁ:: አፍሮዳይትን
አይታችሁ ወደ ቀኝ ስትሻገሩ አስደናቂውንና «ፕሮፒሊያ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የተሰኘውን ጥንታዊ ቤተ መቅደስ ታያላችሁ። ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ437 እስከ 432 ባለው ጊዜ የተገነባው ፕሮፒ ሊያ ሚኒስኪልስ የተባለው የአቴና አርክቴክት የእጅግሮ ጥበብ ከፔንተሊክ እብነ በረድ እና ከኤሊውዚኒያን ድንጋዮች ጋር ተዋሕደው የገነቡት ነው።

አራት ማዕዘናዊ የሆነውን እና ስድስት ስድስት ዶሪክ ዓምዶች በውስጥ እና በውጭ ደግፈው የያዙትን ይህንን ቤተ መቅደስ ለመገንባት 2012 የዚያን ዘመን ገንዘብ ፈጅቷል። ዓምዶቹ 29 ጫማ ከፍታ እና 5 ጫማ ዲያሜትር ስፋት አላቸው። ጣራው ከእብነ በረድ ድንጋይ የተገነባ ነው።

እስቲ ወደፊት እንሂድና በአቴና ከቀሩት የታሪክ ቅርሶች ውስጥ አስደናቂ የተባለውን ፓርቴኖን እንጎብኘው። የውስጥ ቅርሳ ቅርሶቹ በሎርድ ኤርጊን አማካኝነት ተዘርፎ ወደ እንግሊዝ ቢወሰድበትም የሕንፃ ጥበቡ ግን ዛሬም በተገነባበት ቦታ ይታያል። የጥበብ አምላክ ለሆነችው *ለፎንግዚ ለቆና* መቅደስ ሆኖ የተሠራው ይህ ሕንፃ በታወቁት የአቴና አርክቴክቶች በኢክቲዮስ፣ በካሊክራተስ እና በካርፒዮን ታስቦ በመሐንዲሱ በእሉምፒያን ፐርኪለስ ሞያ የታነፀ ነው።

በ438 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ሥራው የተጠናቀቀው ፓርቴኖን 1000 ታለንት ወይንም 6 ሚሊዮን ድራክማ /የዚያ ዘመን ገንዘቦች/ ፈጅቷል። 228 ጫማ ርዝመት፣ 101 ጫማ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ስፋት እና 66 ጫማ ከፍታ ያለው ይህ አራት መዓዘናዊ ቤተ መቅደስ የተገነባው ከእብነ በረድ ነው:: ጠጋ ብላችሁ እብነ በረዱን ስታዩት እስፖንጅ ይመስላል:: ብዙ ሰው በእብነ በረዱ ዓይነት እየተደነቀ በእጁ ስለሚነካው አሁን አሁን መንካት ተከልክሏል:: ከመሠረት 6 ጫማ ከአንድ ተኩል ኢንች፣ ጣራ ላይ ሲደርሱ ደግሞ እስከ 34 ጫማ የሚደርስ ዲያሜትር ስፋት ባላቸው በ46 ዓምዶች ተከብቧል::

ቤተ መቅደሱ በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን አነስተኛው ክፍል የጥበብ አምላኳ የአቴና ምስል የሚቀመጥበትና ካህናቱ መሥዋዕቱን የሚያቀርቡበት ቦታ ነው:: ሰፊው ቦታ ደግሞ ሕዝቡ ይሰበሰብበታል::

ከፓርቴኖን በስተ ግራ ራቅ ብሎ በአቴናውያን ዘንድ እጅግ የተቀደሰ ሥፍራ ይባል የነበረው ***ኤሬክቲየም*** ቆሟል:: ይህ የሦስት አብያተ መቅደስ ቅምር የሆነ ሥፍራ የመጀመርያው መቅደስ የአቴና ፖሊያ፣ ሁለተኛው የኤሬክቲየስ፣ ሦስተኛው ደግሞ የፓንድሮስስ ነው:: በፊት ለፊት በኩል ያለውን የጣራውን ክፍል ስድስት የሴት ሐውልቶች ተሸክመውታል::

እርሱን እንለፍና ወደ ውስጥ እንዝለቅ:: የሮም እና የአውግስጦስን መቅደስ፣ የአቴናን መሠዊያ፣ የዜውስ ፖሊየስን መቅደስ እዚህም እዚያም ፈራርሶ እናገኘዋለን:: የዓምዶቹ ግዝፈት፣ መሬት ላይ ወድቀው የምታዩዋቸው የጥንት ጣራዎች አቀራ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ራጾ፣ ከድንጋይ እና ከእብነ በረድ የተገነቡት መሠረቶች አክሮ ፖሊስን የጥበብ መናገሻ አድርገውታል:: ይህንን ጥበብ ለማድ ነቅ ከመላው ዓለም የጎረፈው ቱሪስት ለፎቶ ሲሻማ ማየት በራሱ ደግሞ ሌላ የቱሪስት መስሕብ ነው::

ጊዜ የለንምና አክሮፖሊስን እንልቀቀው:: ለቅቀንም በገባንበት በኩል በስተ ግራ ወርደን ከአክሮፖሊስ ተራራ ወደ ሰሜን እና ቅና:: እዚያ አንድ ዐለታማ ጉብታ እናገኛለን:: *አርዮስፋጎስ* ይባላል:: ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት የግሪክ ምሁራን እዚያ ቦታ እየተሰበሰቡ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ይመክሩ ነበር:: ሐዋ ርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ54 ዓም አቴና ገብቶ የመጀመርያ ውን ስብከት ያካሄደው በዚህ ኮረብታ ላይ ነበር::

እሁንም እንውረድ:: ከአክሮፖሊስ ፊት ለፊት መጥተን ወደ ደቡብ አቅጣጫ እናምራ:: በዚያ የግሪክ የኪን ጥበብ ባለሞያ ዎች ለዛሬው ፊልም እና ድራማ መሠረት የጣሉበትን አምፊ ቴያትር እናገኛለን:: የዲዮናስዮስ መቅደስ እና ቴአትር:: ከክር ስቶስ ልደት በፊት በ5ኛው መክዘ የተገነባው ይህ አምፊ ቴአ ትር አንድን ጉብታ ተንተርሶ የተገነባና ጉብታው እየተገረደ መቀመጫዎች የተሠሩለት ነው:: 13000 ተመልካች የሚይዙ 67 መሥመሮች ያሉት መቀመጫ በጉብታው ላይ በድንጋይ ተነጥፏል:: የተውኔት ማሳያው መድረክ መሬት ላይ ተነጥፎ ከላይ ወደ ታች የሚታይ ነው::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ከተመልካቹ መቀመጫ ፊት ለፊት እና ከመድረኩ ጀርባ ለ ዮናስዮስ መቅደስ ሊቀ ካህናት እና ለተውኔት ገምጋሚ ዎ ሩን የተዘጋጀ ልዩ መቀመጫ አለ:: አሁንም ድረስ የልዩ መ መጫው አብዛኛው ክፍል ሳይፈራርስ ይታያል:: የማማሽ ክ ቅርጽ ያለው መድረክ በእብነ በረድ የተነጠፈ ሲሆን በግ ቀለማት አጊጧል::

የዲዮናስዮስ ዓመታዊ በዓል ሲከበር የአቴና ሕዝብ እዚህ በ ተሰብስቦ ነበር የአስቺለስን፣ የሶፎቅለስን እና የኢውሪፒደስን ትራጀዲያዊ ተውኔቶች፣ የአሪስቶፓለስን እና የሜናንድሮስን ኮሚዲያዊ ድራማዎች ይኮመኩም የነበረው::

አሁንም ከአክሮፖሊስ በስተ ጀርባ በእግር ጉዟችን እንቀጥል፡ የአቴና ፀሐይ እናት እናታችንን ማለት ጀምራለች:: ሙቀቱ እንደኛ ላለ ልብስ ለሚለብስ ሰው የሚቀመስ አይደለም:: ፈረ ንጆቹ እንደሆን መለመላቸውን ሊቀሩ ጥቂት ነው የቀራቸው፡ እንዲህ ሆነው ሲሄዱ የሀገሬ ሰው ቢያያቸው ሁለት ሰባት ያ ፈልጋቸዋል ብሎ ጻድቃኔ እንደሚወስዳቸው አልጠራጠርም፡ እነሆ እንዘር:: ወደ ***ሄሮድስ አንቲቀስ ቲአትር፡***

በ161 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ታዋቂው የአቴና የገንዘ አዋቂ እና ፈላስፋ ሄሮድስ አንቲቀስ ለሚስቱ ለሬጊለስ መታ ሰቢያ የገነባው ይህ ቲአትር ግማሽ ክብ ቅርጽ ኖሮት መድ ረኩ በግማሽ ክቡ መጨረሻ ላይ ይገኛል:: ከመድረኩ ጀር



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ለዝምጋሚ ምሁራን እና ለክቡራን ተመልካቾች ሠገነት ተገንብቷል:: መድረኩ 35.4 ሜትር ርዝመት፣ 1.1 ሜትር ስፋት እና 6 ሜትር ከፍታ አለው:: 5000 ተመልካች ይይዝ ዘንድ የተሠራው መቀመጫ በድንጋይ ተነጥፏል:: በዚህ ቦታ በጥንቷ ግሪክ ድራማዎች እና ኮንሰርቶች ይቀርቡ ነበር:: ዛሬም አቴናውያን ቦታውን መልሰው ጠግነው ለዘመናዊው ሥነ ጥበብ ይጠቀሙበታል::

ወደፊት ቀጠልን:: በአክሮፖሊስ ጀርባ ዞርንና ወደ ምሥራቅ መጣን:: አሁን የአቴናውያንን የጥንት የገበያ ሥፍራ እናገኘዋለን:: እነርሱ «አጎራ» ይሉታል:: በግሪክ ቋንቋ «መሰባሰቢያ» ማለት ነው:: ሱቆች፣ አብያተ መቅደስ፣ ምክር ቤት፣ መቃብር፣ ምግብ ቤቶች፣ አዳራሾች፣ ምን የሌሉት ነገር ነበር:: 500 የአቴና ሴናተሮች እዚያ ነበር የሚመክሩት:: የጦፈው ገበያ እዚያ ነበር:: አዋጅ እና መመሪያ እዚያ ተነብቦ እዚያ ነበር የሚለጠፈው:: የሚትሩን ቤተ መቅደስ እዚያ ተገንብቷል:: ለጦርነት አምላክ ለአሬስ እና ለአፖሎ እዚያ መቅደስ ነበራቸው:: ሌሎች አሥራ ሁለት አማልክትም በአንድነት መቅደስ ተሠርቶላቸዋል:: ዛሬ የአጎራ ሙዝየም የሆነው አዳራሽ 21 ሱቆች በመደዳ የነበሩበት የገበያ ሥፍራ ነበር::

ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ታዋቂ የሆነው ግሪካዊው ፈላስፋ ዲዮጋን በጠራራ ፀሐይ መብራት እያበራ ሰው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍሊፕ የሠራው እዚህ የገበያ ሥፍራ ነበር:: «ምንድነው በጠራ ፀሐይ መብራት ታበራለህ?» ቢሉት «ሰው ፈልጌ ነው» አለ:: «ምንድነው እኛ ሁላችንስ ሰዎች አይደለንም ወይ» ብለው ጨምረው ሲጠይቁት ደግሞ «ሰው ሆኖ የተፈጠረ ሳይሆን ከልቡ ሰው የሆነውን ነው የምፈልገው» አለ ይባላል::

ፀሐይዋ እየከረረች ነውና ጉዞአችንን ብንቀጥል ይሻላል:: ፊ ለፊታችን ወደምናገኘው *አትራፓስ ኪሉማስ* ኮረብታ እንውጣ በዚያም የተበበ እድ ሞያተኞች እምሳክ የሆነውን የሄፓኢ *ተስጋ* መቅደስ እናያለን:: 34 አዕማድ ጣራውን ተሸክመው የ ዙት ይህ መቅደስ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በ5ኛው መክዘ የተ ገነባ ነው:: ዓምዶቹ በዘመናት ብዛት ካጋጠማቸው እርጅና በቀር ውበታቸው እንዳለ ነው:: ወደ ላይ ቀና ብለው ሲያዩ ቸው ከግዝፈታቸው የተነሣ በሰው ላይ ሊወድቁ ያዘመ ይመስላሉ:: ጣራው እንደ ሌሎቹ ሁሉ እብን በረድ የተ ሩበት ነው::

እኔን የሚገርመኝ በዚያ ዘመን በምን ቴክኖሎጂ ይህንን እ ዶን ሠሩት? እንዴትስ ከቦታው አንጉዘው እዚህ አመጡት? እንዴትስ አቆሙት? ጥርብ ጥርብ የሚያህለውን እብነ በረ እንዴት አድርገው ጣራ ላይ ሰቀሉት? የሚሉት ነገሮችን መ ብኩ ጊዜ ነው:: ያንን የሚያህል ግዙፍ መቅደስ ድንጋይ በ ንጋይ አድርጎ መገንባት፣ መጀመርያ መታሰቡስ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በአውግስጦስ በር በኩል አልፈን ከተንታተኛው የአቴና የገበያ ሥፍራ በስተ ምሥራቅ በኩል ብቅ አልን። እዚያም ከዘርሲቶስ ልደት በኋላ በመጀመሪያው መቶ የተገነባውን የሮማውያንን የገበያ ሥፍራ እናያለን። ንጉሥ አውግስጦስ ያስገነባው ይህ የገበያ ሥፍራ በውስጡ የንፋስን አቅጣጫ ለማመልከት የተሠራ «የንፋስ ማማ» የተሰኘ የአክታጎን ቅርጽ ያለው ሠገነት ይገኛል። ከሶርያ ቂሮስ በመጣው አስትሮኖመር በአድራኒቆስ የተሠራው ይህ ሠገነት ለሚትሮሎጂያዊ መረጃ ማሰባሰቢያ እና ለሰዓት መቁጠርያ እንዲውል የተሠራ ነበር። በጣራው ላይ የተተከለው የመዳብ ቀስት የንፋስን አቅጣጫ ያመለክታል።

በስምንት አቅጣጫዎች የሚገኙት ምልክቶች ሰሜን፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምሥራቅ፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ደቡብ ምሥራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ የተሰኙትን ስምንቱን የንፋስ አቅጣጫዎች እንዲያመለክቱ የታሰቡ ናቸው። በግንቡ ዙርያ በብረት ተሠርቶ ምልክት የተደረገበት ንጣፍ በፀሐይ ጊዜ ሰዓቱን ያሳያል። ፀሐይ በማትወጣ ጊዜ ደግሞ በሠገነቱ ውስጥ ያለው የውኃ ሰዓት ጥቅም ላይ ይውላል።

በሐድርያን በር በኩል እንዝለቅና ወደ ግሪክ አማልክት ንጉሥ ወደ ዜውስ ቤተ መቅደስ እንገሥግሥ። 18 ሜትር ከፍታ፣ 13 ሜትር ስፋት እና 2.30 ሜትር ውፍረት ባለው የሐድር



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ያን ትስት ስትዝቡ ዜውስ የሰውን ልጅ ፈጠረበት የሚባለው
ቦታ ታገኙታላችሁ:: እንደ ግሪክ ሚቶሎጂ ከሆነ አሁን የቆ
ከብት ቦታ ሰው ሆኜ የተፈጠርኩበት ቦታ ነው:: ከክርስቶ
ልደት በፊት በ6ኛው መክዘ መሠረቱ ተጥሎ በ2ኛው መ
ከክርስቶስ ልደት በኋላ በንጉሥ ሐድርያን አማካኝነት የተ
ናቀቀው የዜውስ ቤተ መቅደስ 250 ሜትር ርዝመት
130 ሜትር ስፋት አለው:: ከነበሩት 108 አዕማድ መካከ
ዛሬ 16ቱ ብቻ ቆመው ይታያሉ::

ብያችኋለሁኮ:: አቴናን በጥቂት ቀናት ጎብኝቶ መጨረስ አ
ቻልም:: የሙዝየሞቹን፣ የሐውልቶቹን እና የታሪካዊ ቦታ
ቹን ብዛት ባለቤቶቹ ይቁጠሩት:: አሁን ፀሐዩንም መቋቋ
አልቻልንም:: አቴናን ለጊዜው እዚህ ላይ እንሰናበታት:: በቀ
ማዩ ሰኞ ከተማዋን ለቅቀን በታሪካዊዉ የኤጅያን ባሕር ላይ
ለስድስት ሰዓታት ያህል በመርከብ እንጓዛለን:: ዮሐንስ ራእ
ዩን ወደጻፈበት ወደ ፍጥሞ ደሴት:: ረቡዕ ደግሞ ወደ ቆሮ
ቶስ ከተማ:: እግረ መንገዳችንንም ወደ ማራቶን ሜዳ:: ቸ
ግሬ እንሰንብትና አብረን ብዙ እናያለን:: ለበርግሊስ፣ አቴ

# ግማሽ ነው ሙሉ?

«**እዚህ** ሀገር እንደ መጣሁ የመጀመሪያ ሥራዬ አንዲት የስ ማንያ ዓመት ግሪካዊት ባልቴትን መንከባከብ ነበር:: ሴትዮዋ አንዲት ልጅ አለቻት:: በኛ ሀገር «ሊትሞት አንድ ሐሙስ የቀራት» የምትባል ዓይነት ናት:: ምግብ መመገብ፣ አልጋዋን ማንጠፍ፣ ገላዋን ማጠብ፣ መጸዳጃ ቤት መውሰድ እና ማስ ተኛት ሥራዬ ነው::

ታድያ መጀመርያ ቀን ስገባ ልጅቱ አንዳንድ የግሪክ ቃላትን በወረቀት ጽፈው ሰጥተውኝ ነበር:: አንድ ትእዛዝ ስታዝዝ ወረ ቀቱን አውጥቼ ማየት ነበረብኝ:: አንድ ቀን ታድያ ልጅቱ «ያያውን አምጭልኝ» አለችኝ:: ወረቀቱን ሳዬው ያያ ማለት ባልቴት ማለት ነው:: ግራ ገባኝና ዝም አልኩ:: ልጅቷ ያለ ችው ሁለተኛ ፎቅ ላይ ስለሆነ እንዴት አድርጌ እዚያ ድረስ ባልቴቷን እወስዳለሁ ብዬ አሰብኩ:: አሁንም በድጋሚ በግሪ ክኛ «ያያውን አምጭልኝ ጠረጴዛ ላይ አለልሽ አለችኝ:: እኔ ደግሞ ባልቴቷን ጠረጴዛ ላይ አድርገሽ አምጪት ያለች ስለ መሰለኝ ደብልቅ ግራ ተጋባሁ::

ለሦስተኛ ጊዜ እየጮኸች «ጠረጴዛው ላይ ያለውን ያያ ለምን አታመጭውም» አለችኝ:: እኔ ደግሞ ጠረጴዛ እና ባልቴት



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚሉትን ቃላት ብቻ ነው ወረቀቴ ላይ ያገኘኋቸው:: ምንም ማድረግ ስላልቻልኩ ባልቴቷን ጠረጴዛ ላይ አድርጌ ሰውነቴ እየተንቋቋ ወደ ሁለተኛ ፎቅ ደግሞ ወጣሁ:: የሚስተር ቢንን ፊልም የምሠራ ነበር የምመስለው:: ባልቴቷ ታቃስታለች:: እኔም እያረፍኩ እየተነሣሁ የመኝታ ቤቱን ያለችበትን በር ከፍቼ ስገባ ልጅቷ በድንጋጤ ወለሉ ላይ ተዘረረች::

ለካስ በግሪክ «ያያ» ማለት ባልቴት ብቻ አይደለም:: ከእነ ገሩ ላይ ትንሽ ለወጥ ቢልም መንጽር ማለትም ይሆናል:: ልጅቱ መንጽሬን ከጠረጴዛው ላይ አንሥተሽ አምጭልኝ ማለቷ ነበር ለካ:: አወይ አለማወቅ::

«አንድ ጊዜ ደግሞ ሌላ ሰው ቤት ተቀጥሬ ስሠራ ሰውዬው ብዙ ወፎች ነበሩት:: ለወፎቹ ልዩ ፍቅር አለው:: እናም ወፎቹን መመገብ እና ቤታቸውን ማጽዳት እንዲሠራዬ ነበር:: አንድ ቀን ምን እንዳቀበጠኝ አላውቅም የወፎቹን ቤት ከፈትኩት:: ወዲያውኑ አንዷ ወፍ በርራ ዛፍ ላይ ወጣች:: ዕጢዬ ዱብ ነው ያለው::

ወፏ የምትሰማኝ ይመስል እስኪበቃኝ ለመንኳት:: «ባንቺ ምክንያት ሥራዬን ከማጣ በናትሽ ተመልሰሽ ግቢ:: በኪዳነ ምሕረት ይገርሻለሁ:: ሌላ ጊዜ አይለምደኝም» እያልኩ እለምናት ጀመር:: ደባስ ብላ በረራ ጎረቤት ግቢ ውስጥ ገባች:: እሀል ውኃዬ አለቀ ብዬ ምርር እያልኩ ባለቅስ ለማችኝ መሰል ተመ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ልሳ መጥታ ጎጆዋ ውስጥ ገባች:: ይኼውልህ የኛ ሕይወት እንደዚህ ነው::»

እነዚህን ታሪኮች የነገረችኝ ከኢትዮጵያ ወደ ቤይሩት፣ ከቤይሩት ወደ ቱርክ፣ ከቱርክ ደግሞ ወደ ግሪክ የገባች እንዷት እኅት ናት::

ከአዲስ አበባ ቤይሩት በመኪና ወይንም ከአዲስ አበባ ቱርክ በአውሮፕላን ትገባላችሁ:: ከአዲስ አበባ በቱርክ በኩል አድርጎ ግሪክ ለመግባት ከሰባት እስከ አሥር ሺ ዩሮ ወይንም በኢትዮጵያ ብር ከ130 እስከ 180 ሺ ብር ድረስ ያስከፍላል:: ያለበለዚያም ደግሞ በዐረብ ሀገሮች ተቀጥሮ እንደሚሠራ ማንኛውም ሠራተኛ ቤይሩት ትገቡና ለጥቂት ዓመታት ሠርታችሁ ገንዘብ አጠራቅማችሁ ወደ ቱርክ ትሻገራላችሁ:: እር ሱም ቢሆን ግሪክ እስክትደርሱ ከ3000 እስከ 5000 ዩሮ ያስፈ ገኛል::

ቱርክ ከገባችሁ በኋላ አሸጋጋሪዎች አሉ:: የፖሊስ ኃይል የማ ይበረታባትን ሌሊት ጠብቀው ወደ ጥንቷ ሰርምኔስ ወይም ወደ ዛሬዋ ኢዝሚር ወደብ ያመጧችኋል:: ከዚያ በኋላ ያለው ጉዞ እንደ ዕድላችሁ ነው:: በቱሪስት ማጓጓዣ ጀልባ ወይንም ደግሞ በአየር በሚነፋ የላስቲክ ጀልባ ልትሳፈሩ ትችላላችሁ::

በቱሪስት ጀልባ የምትሳፈሩ ከሆነ ራሱን የቻለ ካፒቴን አለው:: እንደምንም ደብቆ በደረቁ ሌሊት ግሪክ የባሕር ዳርቻ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ያደርሳችኋል:: የማሪክ ጠረፍ ጠባቂዎች የሚደርሱባችሁ ከሆነ በግድ ያወርዳችሁና ባሕር ላይ ይጥሏችኋል:: ከዚያ በኋላ በሰበሳችሁት የመንሳፈፊያ ትጥቅ ተጠቅማችሁ ሕይወታችሁን ማትረፍ ነው:: የመርከቡ ነጅ እንዳይያዝ እየበረረ ወደ ቱርክ ማዛት ይገባል::

ከባዱ ነገር በአየር በምትነፋው በላስቲክ ጀልባ ከመጣችሁ ነው:: ከመካከላችሁ አንዱን ሥልጠና ይሰጡትና አቅጣጫውን አሳይተው ይሸኟችኋል:: ደግነቱ የባሕሩ መንገድ ቢበዛ ለሦስት ሰዓት ያህል የሚቆይ ነው:: ጭንቀቱ ግን የአንድ ዓመት ያህል:: መንገድ ሲጠፉችሁ የምትደውሉበት ስልክ ይሰጧችኋል:: ከዚያ ታሪክ ሰዳ የማለበት ለደተኛ ሾፌር የላስቲክ ጀል ባውን እየነዳ መንዝ ነው:: ጉዞው የሚደረገው ሌሊት ነው:: መንገድ ከተሳሳታችሁ ወዳሳፈሯችሁ ሰዎች ትደውሉና በስልክ ይመሯችኋል::

በድንገት የማሪክ የጠረፍ ጠባቂ ወታደሮችን ካያችሁ ያላችሁ አማራጭ ሁለት ነው:: ወይ ወደ ቱርክ መመለስ ያለበለዚያም ደግሞ ባላችሁበት መጠበቅ:: ገንዘቡን ከሰከሱ ከቱርክ የወጣ ለደተኛ በምንም መንገድ መመለስን አይመርጠውም:: እዚያው ቆማችሁ ከጠበቃችሁ ደግሞ በመጣችሁበት ጀልባ ይመልሷችኋል:: እናም ያለው አማራጭ አንድ ብቻ ይሆናል:: የተሳፈራችሁበትን በአየር የተሞላ የላስቲክ ጀልባ ማስተንፈስ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያ በመንሳፈፊያ ትጥቅ ባሕሩ ላይ ትጥኛላችሁ:: ወታደ ሮቹ የሚመልሱበት መርከብ ስለማያገኙ ወደ ግሪክ መሬት ያመጧችኋል::

ኢትዮጵያውያን በሊቢያ ሲከርሙ የሚያጋጥማቸውን ያህል ችግር ቱርክ ውስጥ እንደማያጋጥማቸው ስደተኞች ይናገ ራሉ:: ሕዝቡ ለስደተኞች ያዝናል:: ፖሊሶችም ቢሆኑ የባሰ ነገር ኢጋጥሟቸው ካልሆነ በቀር ስደተኞችን አያንገላቱም:: የባ ሕሩ ላይ ጉዞ ግን ለሰዓታት ያህልም ቢሆን አስጨናቂ ነው::

ነዳጅ አልቆባቸው በባሕሩ ላይ ተንሳፍፈው የቀሩ:: በዚህም ምክንያት በምግብ እና በውኃ እጦት እዚያው የሞቱ አሉ:: ጀልባዋ መንገድ ላይ ፈንድታ የያዘቻቸው ስደተኞች ሁሉም የሰመጡበት አጋጣሚ አለ:: መንገድ ላይ ሞተር ሊበላሽ ይች ላል:: እንዲያውም እኛ ከመምጣታችን ጥቂት ቀደመ ብሎ ሠላሳ ስደተኞችን የያዘች ጀልባ ሰምጣ ሁሉም የውኃ እራት ሆነው ቀርተዋል::

ከቤይሩት ተነሥተው የሚመጡት ኢትዮጵያውያን እንቶች ደግሞ ሌላም ፈተና አለባቸው:: መንገድ ላይ ገንዘባቸውን ለምግብ፣ ለሆቴል እና ለትራንስፖርት አውለው ይጨርሱትና ይቸገራሉ:: በዚህም ምክንያት እንደኔ እርሱ በቤይሩት በኩል አድርገው ከሚገቡት ከሱዳናውያን፣ ከባንግላዴሾች እና ከሌ ሎች አገር ወንዶች ጋር መጎዳኘት የግድ ይላቸዋል:: ይህቺ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በችግር ምክንያት የተጀመረች ጓደኝነት ግሪክ ከተደረሰ በኋላ ለብዙዎቹ የሕይወት ፈተና ትሆናለች።

በዚህ ዓይነቱ ጓደኝነት ውስጥ ያሉ ሴቶች በሀገራቸው ልጆች ዘንድ ይገለላሉ። ቤተሰቦቻቸው እንዳይሰሙባቸውም ያፈሩ ቃሉ። ለመለያየት ቢፈልጉም የተከፈለላቸውን ገንዘብ እስከ መለሱ ድረስ የወንዶቹን ውሊታ በሰውነታቸው የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

በጣልያንም ሆነ በግሪክ በኩል ወደ አውሮፓ ለሚገባ ስደተኛ አንዱ ፈታኝ ጉዞ ባሕሩን አልፎ ከወጣ በኋላ ከፖሊስ ተደብቆ ጨዋማውን የባሕሩን ጠረፍ ማቋረጥ ነው። በድካም እና በረሃብ ምክንያት የሚሞቱ ብዙ ናቸው። አንድ ልጅ ባሕሩን አልፈው የብስ ሲደርሱ ያጋጠመውን እንዲህ አጫውቶኛል።

«ከባሕር ወጥተን አሸዋማው ደረስንና በእግራችን መጓዝ ጀመርን። እግራችን ዝሏል። ምግብ አልበላንም። የውኃ ጥሙ ሊገድለን ነው። በመካከሉ አንድ ጓደኛችን ደከመ። ትንሽ እልፍ እንዳለም ተዝለፍልፎ ወደቀ። ለጭንቅ ቀን የያዝናትን ውኃ ብንግተውም የሚመለስ አልሆነም። ሰውነቱ ቀዝቅዞ ዓይኖቹ ተከደኑ። ምንም ማድረግ ስላልቻልን እያለቀስን አሸዋውን ቆፈር ቆፈር አድርገን ቀበርነውና የመስቀል ምልክት በእንጨት ሠርተን ጉዟችንን ቀጠልን። ሚስቱ አብራን ነበረች። ኀዘኗ ከባድ ነበር። ግን ምን ማድረግ ይቻላል። ስደት እንዲህ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ያደርጋል:: እንደምንም ብለን ሮማ ገብተን ጥቂት ጊዜ ቆየን:: አንድ ቀን ጠዋት ከምናድርበት ቤት ወጥተን በረንዳ ላይ ተቀምጠን እያለን ማመን የማንችለውን ነገር በዓይናችን አየን:: ያ የቀበርነው ልጅ እየመጣ ነው:: በድንጋጤ ሁላችንም ቆምን:: ሕልም ነው ወይስ ምትሐት? ሁላችንም ግራ ገብቶናል:: ፊቱ እና እጁ አካባቢ ጠባሳ ይታያል::: ሚስቱ በድንጋጤ ራሷን ሳተች::

ለካስ ያ ጓደኛችን አልሞተም ነበር:: በሞት እና በሕይወት መካከል ነበር:: እኛ ግን ወጣቶች ነን:: የሞተ እና ያልሞተ ሰው እንኳን መለየት አንችልም:: እንደዚያ ዓይነት ነገርም ገጥሞንም አያውቅም:: እርሱን ግን ትረፍ ሲለው ከቀበርነው ከሰዓታት በኋላ ነፍስ ይዘራና እጁን ሲያንቀሳቅስ እጁ ከአሸዋው ውስጥ ብቅ ይላል:: እንደ ድንገትም የአካባቢው በግ ጠባቂዎች እጁን ያዩትና ደንግጠው ሰው ይጠራሉ:: አሸዋውን ሲጠርጉለት ለካስ ነፍሱ አልወጣችም::

ወደ ቤታቸው ወስደው ጨው የበላውን ቁስሉን ያክሙታል:: ምግብ ይሰጡታል፤ ገላውን ያጥቡታል:: እየቆየ ራሱን እያወቀ ይመጣና ጤንነቱ ይመለሳል:: የሆነውን ነገር ሁሉ ያወቀው ያኔ ነበር:: ሌሎች ስደተኞች ሲመጡ ጠብቀው አብረው ላኩት:: እኛም አገኘነው:: የኢትዮጵያውያን ስደት በብዙ ታሪክ የተሞላ ነው::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ግሪክ ለሴቶች ስደተኞች እንጂ ለወንዶች የምትስማማ አይደ ለችም:: አንዳንዶቹ እንደ ሚሉት ወንዶች ሀገር ቤት በሴቶች ላይ የዋሉትን ግፍ የሚከፍሉበት ሀገር ናት:: ሚስት ሥራ ውላ ባል ምግብ ሠርቶ የሚጠብቅባት ሀገር:: ለወንዶች የሚ ሆን ሥራ አይገኝም:: ሴቶቹ ግን በሰው ቤት ተቀጥረው ደህና ደመወዝ ያገኛሉ::

እናም በአቴና ከተማ «እገሊት እገሌን አገባችው» እንጂ «እገሌ እገሊትን አገባት» ሲባል አትሰሙም:: እንዲያውም እንድ ልጅ ሴቶች የቤት እመቤት መሆናቸው ቀርቶ ወንዶች «የቤት አበቤት» የሆኑበት ሀገር ነው ብለውኛል:: ለዚያውም ባል የሚመረጠው ቁመናውና ወንዳ ወንድነቱ ታይቶ ብቻ አይደለም፣ ጠባዩ እና የቤት አያያዝ ሞያው ታይቶ ጭምር ነው:: ሚስት ሥራ ውላ ስትመጣ አረፍ ምግብ ሠርቶ፣ ቤት ጠርጎ፣ አልጋ አንጥፎ፣ ሰቃ አጥቦ የሚጠብቅ መሆን አለበት::

የአቴና ኢትዮጵያውያን ሴቶች ስለ ባሎቻቸው ሲጠየቁ ምን እንደሚሉ ታውቃላችሁ? «እንዴት ነው ባልሽ? ግማሽ ነው ሙሉ»? ይላሉ:: ግማሽ ማለት «ለሌሊቱ» ብቻ የሚሆን፣ «ሙሉ» ማለት ደግሞ የቀኑንም የጓዳ ሥራ መሥራት የሚ ችል ማለት ነው:: የሀገር ቤቶቹስ እንዴት ናቸው?

**አቴና፣ ግሪክ**



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ባለ ራእይዋ ደሴት



ከአቴና ወደ ፒራዎስ ወደብ በባቡር ነው ያመራ ነው:: ወደ አርባ ደቂቃ ያህል ይወስዳል:: መርከቡ ከላይ ተሳፋሪዎችን ከሥር ደግሞ የቤት እና የጭነት መኪኖችን እያስገባ ጠበቀን:: ወቅቱ የፈረንጆቹ የበጋ ወቅት በመሆኑ ሕዝቡም አካባቢውን ለቅቆ ወደ መዝናኛ ቦታዎች የሚጓዝበት ነው:: የመርከቡ መግቢያ በሰው ተጨናንቋል::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ለአሥራ አምስት ደቂቃዎች ያህል መንሥመራችንን ይዘን ከተንዘን በኋላ መርከቡ ውስጥ ገባን:: ውስጡ የጊዮርጊስ እና የቡናን ጨዋታ የሚያስተናግደውን የአዲስ አበባ ስታድዮም መስሏል:: በግራም በቀኝም ከሰው ውጭ ሌላ ነገር አይታይም::

እንደምንም ብለን መቀመጫ ካገኘን በኋላ ወደ መርከቡ ውጪኛው ክፍል ወጣን:: ቀዝቀዝ ያለ ነፋስ ስላለው እጅግ ደስ ይላል:: በጥንቱ የዓለም ታሪክ ግሪኮች፣ ሮማውያን፣ ፋርሶች እና ባቢሎናውያን ሲራወጡበት የኖሩት የኤጅያን ባሕር ፊት ለፊታችን ተዘርግቷል:: በውስጡ ከል የተበጠበጠ ይመስል መልኩ ጥቁር ነው:: ውኃው በነፋሱ ሲንቃነቅ ነው ባሕሩ የውኃ መልክ የሚይዘው:: «እስመ ነፋሳት ሕይወቶሙ ለማያት» ሲል ሊቁ የተናገረውን ባሕሩ ራሱ ይተረጉምለታል::

መርከቡ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ ተንቃነቀ:: እንደ ተነገረን ወደ ፍጥሞ ደሴት ለመድረስ 163ቱን ማይልስ ለሰባት ሰዓት ያህል መጓዝ ይጠበቅብናል:: መርከቡ ውኃውን ሲሰነጥቀው ባሕሩ የሳሙና አረፋ መልክ ይይዝ ጀመር:: ግሪክ አያሌ ደሴቶችን ያቀፈች ሀገር በመሆኗ በኤጅያን ባሕር ላይ እዚህም እዚያም በመብራት የደመቁ ደሴቶቹ የጨለማውን ግርማ ገሥውት ይታያሉ:: መርከቦቹም በሠገነታቸው ላይ ችቦ የመሰለ መብራት አብርተው በባሕሩ ላይ ላይ ይተራመሳሉ::

Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ አንድ ጊዜ ከ41 እስከ 44 ዲግሪ የሚደርሰውን የግሪክ ሙቀት ለመቋቋም ጎዞውን በሲሲት ማድረጋቸው ተገቢ ነው። ይሄ ሙቀት ሳይሆን አይቀርም የግሪኮችን የሥራ እና የዕረፍት ባሕል ከሌሎቹ የአውሮፓ ሀገሮች ባሕል የተየረው። በግሪኮች ዘንድ ከቀኑ ስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት በአፊሴል የታወቀ የዕንቅልፍ ሰዓት ነው። የትኛውም ቢሮ ሰው አያስተናግድም። በተለይ ደግሞ ማክሰኞ እና ኀሙስ ከሰዓት በኋላ ሥራ የለም፤ ዕረፍት ነው። ዓርብ ደግሞ ከሰዓት በኋላ ሰው በከተማ አይገኝም። እኔን የገረመኝ መቼ ሠርተው እንደሚኖሩ ነው። ምናልባትም የአውሮፓውያንን በሙሉ ዕረፍት ግሪኮች ሳያርፉት አይቀሩም።

ወደ መርከቡ የበረንዳ አጥር ተጠግተን አካባቢውን ስንቃኝ ግሪኮቹ ቀረብ ይሉና አንዳንድ መግለጫ ይሰጡናል። ይሄ ሰውን ለመርዳት ያላቸውን ፍላጎት ወድጄላቸው ነበር። ችግሩ ግን እናውቅም ማለትን ስለማያውቁ አንዳንድ ጊዜ የማያውቁትን ሁሉ ይነግሯችኋል አሉ። በተለይም አንድ ቦታ ጠፍቷችሁ አራት ግሪኮችን ብትጠይቁ አንዱ ወደ ሰሜን፣ ሌላው ወደ ደቡብ ሌላው ደግሞ ወደ ምሥራቅ፣ የቀረው ወደ ምዕራብ ነው የሚያሳዩዋችሁ። ይህንን ጠባይ ያወቁት ኢትዮጵያውያን አንዱን ግሪክ «ኦዶስ ማሞ» የት ነው ብለው ይጠይቁታል። «የማሞ መንገድ የት ነው?» ማለት ነው። እናውቅም



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የማያውቀው ጅማና በዚህ እና በዚያ አድርጋችሁ ታገኙታላችሁ ብሎ መራቸው ይባላል።

አሁን ሙሉ በሙሉ ጨልሞ አካባቢውን ጨለማ ወርሶታል። ቅዝቃዜውም እየጨመረ ነው። ሁላችንም ቀስ በቀስ እየገባን ተኛን።

ፍጥሞ ደሴት መድረሳችን በመርከቡ ጡሩንባ ተበሰረ። ከሊሊቱ ስምንት ሰዓት ሆኗል። እኛም ዕቃችንን ሸክፈን ወረድን። የደሴቲቱ ሰዎች በሩ ላይ ተሰብስበው ቆመው ለአልጋ ፈላጊዎች ማስታወቂያ ይናገራሉ። እነዚህኞቹ በወረቀት ጽፈው መቆማቸው ነው እንጂ. አዲስ አበባ ክፍለ ሀገር አውቶቡስ ተራ በምሽት የደረስኩ ነው የመሰለኝ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከእኛው ጋር ወደ ፍጥሞ ለሥራ የሄደች እንዲት እኅት ከአሠሪዋ ጋር አገናኘችን። እርሷ እዚህ የመጣችው በጋውን ለአንድ ሆቴል በመሥራት ለማሳለፍ ነው።

ለአሠሪዋ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ነው የሆነላት። ልጅቱን እና እኛን በአንድ ሌሊት አገኘ። ለአንድ ክፍል 35 ዩሮ እየከፈልን አልጋውን ተከራየን። እነሆ ሌሊቱ በጸጥታ አለፈ።

ጠዋት ሦስት ሰዓት ላይ ተነሣን። ከዚያም መጀመርያ ስካ ወደ ተባለው የደሴቲቱ ዋና የሰዎች መናኸርያ አመራን። እዚያ ጥቂት ቆየንና በታክሲ ከባሕር ጠለል በላይ 190 ሜትር ከፍ ወደሚለው የተራራው አናት ላይ ወጣን። ተራራው ላይ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ስትወጡ ደሴቲቱን በሚገባ ታዩዋታላችሁ:: ደሴቲቱ የተዘለለ ሥጋ ትመስላለች:: በሽንሿ በኩል አልፋችሁ ርዝመቷን ስትለኩት ወደ 15 ኪሎሜትር ይሆናል::

ደሴቲቱ በጠቅላላው 34 ኪሎ ሜትር ስኩዌር ስፋት ሲኖራት በውስጧ 3000 ያህል ነዋሪዎችን ይዛለች:: ደሴቲቱ በሠንሠለታማ ወለታማ ተራሮች የተሞላች ናት:: አብዛኛው ሕዝብ የሚኖረው የመርከቡ ወደብ ባለበት በስካላ አካባቢ ነው:: የተራራውን ግርጌ ይዘው የተነጠፉት የመዝናኛ ቤቶቿ ናቸው ከሃይማኖታዊው ቱሪስት ቀጥሎ ፍጥሞ እንድትወደድ ያደረጓት::

በጥንቱ የግሪክ የአማልክት አፈ ታሪክ መሠረት ዜውስ የተባለው የአማልክት ንጉሥ ፍጥሞን ፈጥሮ ለልጁ ለአርጤምስ ሰጣት:: በአካባቢው የተገኘው የአርጤምስ ምስል ዛሬ በቅዱስ ዮሐንስ ገዳም የአርኪዎሎጂካል ሙዝየም ውስጥ ይገኛል::

የታክሲ ትራንስፖርት በምድረ ግሪክ ከሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች በተሻለ ርካሽ ነው:: እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ አውቶቡስ ይወደዳል:: እኛም ወደ ተራራው ለወሰደን ታክሲ ለአራት ሰው አምስት ዩሮ ብቻ ነበር የከፈልነው:: መጀመርያ የተጓዝነው ወደ ቅዱስ ዮሐንስ ታሪካዊ ገዳም ነበር::

በፍጥሞ ደሴት በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ስም አንድ ቤተ ክርስቲያን ታንጾ ነበር:: ከአምስተኛው መካዘ በኋላ ግን ደሴቲቱ ምን እንደሆነች ሳይታወቅ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ነዋሪዎቿ ተተዋት ሄደዋል:: በአፈ ታሪክ እንደሚባለው የባሕር ዘራፊዎች ነዋሪዎቹን በማስቸገራቸው የተነሣ ነው ሕዝቡ አካባቢውን ጥሎ የተሰደደው::

በ1088 ዓም አባ ክሪስቶዶሉስ የተባሉ አባት ወደ አካባቢው መጥተው ዛሬ ድረስ የሚታየውን እና በተራራው አናት ዙሪያውን በተመሸገ አጥር የተከበበውን ገዳም መሠረቱ:: ገዳሙ አንድ ሺ ዓመታትን ያስቆጠረ ቤተ ክርስቲያን፣ የመነኮሳት መኖሪያ እና ሙዝየም አለው:: እኔን ያስቀናኝ በሚገባ የተደራጀው ሙዝየም ነው::

የአርኪዎሎጂ መረጃዎችን፣ ጥንታውያን ንዋያተ ቅድሳትን እና የወግ ዕቃዎችን፣ የብራና መጻሕፍትን እና ልዩ ልዩ መዛግብትን፣ ሥዕሎችን እና መስቀሎችን፣ በድንጋይ ላይ ተሠርተው የነበሩ የዘመኑ የሥነ ጥበብ ውጤቶችን እና የሐውልት ፍርስራሾችን በሚገባ ሠድረውና በግሪክ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ መረጃዎችን ጽፈው አስቀምጠዋቸዋል:: ሙዝየሙን ለመጎብኘት ስድስት ዩሮ ያስከፍላሉ:: አቀማመጡን እና የያዛቸውን መረጃዎች ለተመለከተ ክፍያው ያንሰው እንጂ የሚበዛበት አይሆንም::

ምናለ እነ አክሱም እና ላሊበላ፣ እነ ጣና ገዳማት እና እነ ጎንደር ይህንን ባዩ:: ያንን ሁሉ ታሪካዊ እና ሃይማኖታዊ ቅርስ ይዘው፣ በአንጻት ጠባብ ዕቃ ቤት ከምረው፣ የብል እና የም



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ስጥ መሙያዎች ከሚያደርጉት እና ታሪክ ከሚያሳጡን፣ እንዲህ እንደ ፍጥሞአውያን ሠልጠን ያለ ሙዝዬም ሠርተው ቢያሳዩን ምናለ:: እነርሱም ከልመና ይወጡ ነበር:: እያልኩ ተቆጨሁ::

ነገሩ እዚህ ያሉ መነኮሳት የዋዛ አይደሉም:: ሁሉም ቢያንስ አንድ ዲግሪ በአንድ ትምህርት የያዙ ናቸው:: አሁን ገዳሙን የሚያስተዳድሩት አባት እንኳን የመነኮሱት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተው ለብዙ ዓመታት ከሠሩ በኋላ ነው:: ከተሰሎንቄ ዩኒቨርሲቲ እኤአ በ1998 ዓም በዶክትሬት ዲግሪ የተመረቁ ሲሆን በየጊዜው በሚያሳትሟቸው የጥናት ወረቀቶች አማካኝነትም በ2000 ዓም [illegible] ከተሰኘ የሮማኒያ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ተቀብለዋል:: እስካሁን ድረስም አምስት መጻሕፍትን ጽፈዋል::

ስለ ደሴቲቱ እና ስለ ገዳሙ ታሪክ የሚገልጡ ፖስት ካርዶች፣ መጻሕፍት፣ ፊልሞች፣ ሥዕሎች እንደ ልባችሁ ታገኛላችሁ:: የቅዱስ ዮሐንስ ገዳም ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆን ኖሮ ቪዲዮ ለማንሳት ክልክል ነው የሚል ማስታወቂያ እንጂ የተነሣ ቪዲዮ አታገኙም ነበር::

በገዳሙ ካየኋቸው ነገሮች ሁሉ ልቤን የነካኝ በ15ኛው መክዘ ቱርኮች ደሴቲቱን በያዙዋት ጊዜ የቱርኩ ገዥ ገዳሙ እንዳይነካ፣ ወደ ውስጥም መነኮሳቱ ከፈቀዱለት ሰው በቀር ማንም እንዳይገባ፣ ግብርም እንዳይጠየቅ፣ ቅድስናውም ተጠብቆ እን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ዲኖር በማለት ያወጀው አዋጅ ነው። ዐዋጁ በሚጠቀሰል ብራና ተጽፎ እና ተፈርሞበት ግድግዳው ላይ ተሰቅሏል። የቱርኩ ገዥ ሃይማኖቱ ሙስሊም ነው። ነገር ግን የማላምንበት ነገር ሁሉ እያስፈልገኝም ባይል ለደሴቲቱ ፍጥሞ ገዳም ያደረገው ቸርነት እና ያወጀው ዐዋጅ 500 ዓመታትን ተሻግሮ ለዛሬ ትውልድ ትምህርት የሚሰጥ ነው።

የቅዱስ ዮሐንስን ገዳም ጉብኝት አጠናቅቀን ወጣን። በገዳሙ በስተ ጀርባ በኩል ወደ ታች የሚወርድ አውቶቡስ አገኘንና ተሳፈርን። እናም በጉጉት ወደምንጠብቀው ቦታ አመራን። ስንደርስ ከ800 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ገዳም ነው ያገኘ ነው። ዙርያው በነጭ ግንብ ታጥሮ ግጥምጥም ያለ ነው። አርባ ሁለቱን ደረጃዎች ወርደን ወደ ውስጥ ስንዘልቅ አንድ ዋሻ አገኘን።

እነሆ ደረስን፤ ቆምንም፤ ቅዱስ ዮሐንስ በ95 ዓም ራእዩን የጻፈበት ዋሻ ውስጥ ገባን። የዋሻው ግድግዳ ጥቁር መልክ አለው። የዋሻው ቁመት ከመካከለኛ የሰው ቁመት ትንሽ ከፍ ያለ ነው። ገባ እንዳላችሁ ወደ ቀኝ ስትዞሩ ዮሐንስ ራእዩን ያየበትን ቦታ በብረት ፍርግርግ ታጥሮ ታገኙታላችሁ። ከአጠገቡ ራእዩን እያየ ሲነግረው ደቀ መዝሙሩ አብሮኮሮስ ራእዩን የጻፈበት አትሮንስ የመሰለ ዐለት ይገኛል።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF



ዮሐንስ እየነገረው ለፕሮኮሮስ የጻፈበት ቦታ

ዓይናችሁን ዘቅዘቅ ስታደርጉ ከጸሎት በኋላ ያርፍበት የነበረው ሥፍራ ዐለቱን ወደ ውስጥ በመሠርሰር የተሠራ የአንገት መደ ገፊያ፣ ከመሬት ለመነሣት የእጆቹ መደገፊያ የነበረ ከዐለት የተፈለፈለ መያዥያ በብረት ምልክት ተደርጎበት ይታያል።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF



*ዮሐንስ ቢተኛ ለገድ ትራስ ይጠቀምበት የነበረው ቦታ*

በዓለም ክርስቲያኖች እና ተመራማሪዎች ዘንድ ከፍ ያለ ቦታ ያለው አስደናቂው የዮሐንስ ራእይ በድምጥያኖስ ዘመነ መንግሥት የተጻፈው እዚህ ነው፡፡ አቡቀለምሲስ ዮሐንስ ከኤፌሶን ከተማ ተይዞ በግዞት ወደዚህ ደሴት በመምጣት ለሁለት ዓመታት መቆየቱን የአካባቢው ድርሳናት ያሳያሉ፡፡

አካባቢው ጸጥ ረጭ ያለ ነው፡፡ ድምፅ የሚባል ነገር አይሰማበትም፡፡ የመጡ ጎብኚዎች ሁሉ በጸጥታ ነው በቦታው የሚቆሙት፡፡ ወደ ኋላ ለ2000 ዘመናት ያህል ትንንዱና አብራችሁ ራእይ ታያላችሁ፡፡ እኔም ምናለ የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ም



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሚሆን ራእይ ባየሁ ብዬ ተመኘሁ:: የመጣ እና የሄደ ሁሉ እንዲህ ትሆናለች እያለ በሌለ ተስፋ ከሚሞላን ቁርጥ ያለውን የነገ ዕጣ ፈንታዋን ዐውቀን በጊዜ ብንገላገል ምናለ:: ከዚህ ጥቁር ዐለት በነጭ ሰሌዳ ተጽፎ እንዳች ራእይ ቢታየኝ ምናለ::

ከዋሻው መግቢያ ከላይ ያለው ዐለት ለሦስት ተሰንጥቋል:: በቦታው የሚገኙ መዘግብት እንደሚሉት የሐንስ ራእዩን የገለጠለትን ድምፅ ሲሰማ ዘወር ባለ ጊዜ የተሰነጠቀ ነው:: የሰነጠቀውም የሰማው ድምፅ ነው ይላሉ::





Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህንንም ከምሥጢረ ሥላሴ ጋር ያገናኙታል::

በዚያ ቤታ ለሁለት በዓታት ያህል ቆየን:: ከዚያም ቃልኪ እና ጸጥታውን ተሰናብተን ወጣን:: ወደ አቴና ለመመለስ የምሽቱን መርከብ መጠበቅ አለብን:: ምን ችግር አለው እንደ ሀገራችን የተጠበሰ በቆሎ ከመንገድ ላይ ገዝተን ወደቡ አጠገብ ቁጭ አልን:: ደግነቱ እዚህ ሀገር ምቾ የሚባል ነገር የለም::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ተሳቢ



በቀደም ዕለት ነው:: በአንድ ትልቅ አውራ ጎዳና ላይ አንድ የጭነት መኪና ከነተሳቢው ይጓዛል:: እየሄደ ቆየና ድንገት ቆም አለ:: ሾፌሩም ከጋቢናው ወረደና ወደ ተሳቢው አመራ:: ሆድ ዕቃውን እና ዳሌውን ፈታተሸው:: ከሳቢው ጋር የተያያዘበትን ገመድም አየው:: ጎማዎቹን መታ መታ አደረጋቸው:: እኔ የሚያደርገውን እንጂ የሚያስበውን ለማየት አልታደልኩም::

ወደ ጋቢናው ተመለሰና መፍቻ ነገሮች ይዞ ወጣ:: አንድ ሌላ ሰውም ዓይኖቹን እየደባበሰ አብሮት ወረደ:: ምናልባት የደከመው ረዳት ይሆናል ብዬ ጠረጠርኩ:: ለሁለት ተጋግዘው ብረቱን ፈቱና ሳቢውን ከተሳቢው ለዩት:: የመሳቢያውን ብረት መሬት አስነከሱና ተሳቢውን ወደፊት ሳብ አደረጉት:: ከአካባቢው ብቅ ብቅ ያሉ ወጣቶች ልምድ ባለው አኳኋን ቀረቡና ለጥቢቃ ሥራ በገንዘብ ተደራደሩ:: ተስማሙ መሰለኝ:: ሾፌሩ እና ረዳቱ ጋቢና ውስጥ ገብተው መኪናውን እያስጓሩ ወሰዱት:: ምስኪኑ ተሳቢ ግን በቆመበት ቀረ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አይ ተሳቢ፣ አልኩ በልቤ:: የራሱ ጭንቅላት የለው፣ ራሱ ም... የለው፣ የራሱ ፍሬን የለው፣ የራሱ ጌጅ የለው፣ የራሱ ነዳጅ መ... የለው:: የራሱ ማርሽ የለው:: በሳቢው ላይ ተማግምጦ እና ሳቢ... ተከትሎ በሄደበት ይሄዳል፣ በቆመበት ይቆማል:: ከወሰደው ይሄ... ከጎተረው ይቆማል:: እርሱ እቴ ወዴት እንደሚሄድ አይወስ... የሚወስንለት ሌላ ነው:: እርሱ እቴ መንገዱን አይመርጥም፣ መን... የሚመርጥለት ሌላ ነው:: እርሱ እቴ መነሻ እና መድረሻውን አ... ውቅም:: ሌላው ካስነሣው ይነሣል:: ካደረሰው ቦታ ይደርሳል::

አይ ተሳቢ::

እኔም ጠጋ ብዬ «አንተ ግን እስከ መቼ በሌላ መኪና ጭንቅላ... ትመራለህ:: ከምትሳብ ለምን ራስህን አትችልም?» ስል ጠየቅኩት::

እኔስ መኪና ነኝ፣ ግን እንደ ሀገር ስንት ዘመን ተሳበናል:: ማርክ... እና ሌኒን ሳቢዎቻችን ሆነው ስንት ጊዜ ሳቡን:: የኢትዮጵያ ... ፈንታ በማርክሲዝም እና በሌኒኒዝም ካልሆነ በራስዋ አንወስ... ብለን ስንሳብ፣ ስንሳብ፣ ስንሳብ ኖርን:: ጎርባቾብ የሚባል አንድ ሰው መጣና የኮሚኒዝምን መኪና የሆነ ቦታ አቆማት:: እኛ... ቆምን:: ከዚያ እነርሱ መኪናቸውን አስነሥተው ጠፉን:: እኛ ተሳቢ... ዎቹ ወዴት እንሂድ:: ቀድሞም ለመሳብ እንጂ ለመሄ... አልተነሣንምና::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አሁንም ያው በሽታ አልለቀቀንም:: ክርክራችን እና አመለካከታችን «ለኢትዮጵያ የትኛው ይስማማታል፣ ኢትዮጵያዊ የሆነ አስተሳሰብ፡ ርእዮ እና መንገድ፣ ነገር ግን የምንፈልገው ቦታ ራሳችንን በራሳችን መርተን የሚያደርሰን የቱ ነው?» በሚለው ላይ አይደለም:: አንዱ ወደ ምዕራብ ወስዶን ኢትዮጵያን የአሜሪካ መኪና ይሳባት ይላል:: ሌላው ምሥራቅ ወስዶን ኢትዮጵያን የቻይና መኪና ይሳባት ይላል:: ሰንባብ ራሳችን መንዳት አንችልም ወይ?» አለና መለሰልኝ::

«ይህ ችግር ግን የአፍሪካውያን ሁሉ አይደለም ወይ?»

«ነው እንጂ:: እምቢ ማለት የሚችሉ የአፍሪካ ሀገሮችኮ በጣም ጥቂት ናቸው:: ለዚህ ነው አፍሪካ የአዳዲስ ሀሳቦች መሞከርያ የሆነ ችው:: በተለይም ቅኝ የተገዙ ሀገሮች የገዥዎቻቸው ተሳቢዎች ሆነው ቀርተዋል:: የትምህርት ሥርዓታቸው፤ የአኗኗር ጠባያቸው፤ የፖለቲካ መርሖአቸው፤ የባንክ ሥርዓታቸው ሁሉ የሚወሰነው በሳቢ ዎቻቸው ነው:: የራሳቸውን መንገድ እና ፖሊሲ ቀርፀው ከመጓዝ ይልቅ ሳቢዎቻቸው ወደሚወስዷቸው መጓዣን ይመርጣሉ::»

«ቆይ ግን ይህ ነገር ከስተት ነው አመለካከት ነው?» ስል ጠየቅኩት::

«እንደኔ ከስተት ሳይሆን አመለካከት ነው የሚመስለኝ:: እስኪ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ብቅ በል:: ኢትዮጵያን በተመለከተ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የውጭ ሰዎች የሰጡትን ትንታኔ፣ ድምዳሜ እና አቋም ያለ ምን ጥያቄ እንደ ወረደ ታገኘዋለህ:: ሌላው ቀርቶ ኢትዮጵያዊውን የቦታ የሰው እና የዕቃ ስም ፈረንጆች በሚጠሩበት አጠራር ሲጠራ ታገ ዋለህ:: እነዚያ የውጭ ሰዎች የሰጡት ትንታኔ እና መደምደሚ እውነት ይሆን? እኔ ከእነርሱ ይልቅ ለሀገሬቱ አቀርባለሁ? ብ መልስ የሚጠይቅ አታገኝም:: የተሳቢነት በሽታ ስላለ ዝም ብ በእነዚያ ሰዎች ጭንቅላት ብቻ መመራት ነው:: እነርሱ ቲዎሪያቸው ሲቀይሩ ትቀይራለህ፤ እነርሱ አዲስ መጽሐፍ ሲጽፉ ያው እርሱ ጠቅሰህ እንደገና ታስተምራለህ፤ እነርሱ ተሳስተን ነበር ካሉ አንተ ተሳስቼ ነበር ትላለህ:: እነርሱ መጻፍ ሲያቆሙም ያንተም የማስ ማርያ ኖት እዚያው እንደ ቆመ ይቀራል::»

«እንዲህ ካለከማ እዚህ እየኖረ አሜሪካ ላይ የሚታሰብለት ብ አይደል እንዴ?» አልኩት::

«በደንብ አይተኸዋል» አለኝ:: «የሚለብሱትን፣ የሚበሉትን፣ የሚ ሩትን፣ የሚጫሙትን ሁሉ የሚጠብቁት አሜሪካ እና አውሮፓ ከሚ ገኙ ዘመዶቻቸው ነው:: እነርሱ ኢትዮጵያ ተቀምጠው ምንም አያስ ቡም:: ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚዘንብ አሜሪካ ውስጥ ቢዘንብ ደስ ይላ ቸዋል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተፈጠረ ችግር ይልቅ አሜሪካ ውስጥ የተፈጠረ ችግር ያሳስባቸዋል:: ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ይልቅ ለአሜሪካ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ኢኮኖሚ ይጸልያሉ:: ከአራት ኪሎ ማርያም ይልቅ ለዲሲዋ ማርያም ይሳላሉ::

«በየቀኑ ከአሜሪካ እና ከአውሮፓ ስልክ እየተቀበሉ ስለየሀገራቱ መረጃ ይሰበስባሉ:: ከዚያም እዚያ የኖሩ ያህል ከጓደኞቻቻቸው ጋር ሲሆኑ ይተነትናሉ:: የመረጃ ምንጫቸው እዚያ ሀገር ያለው ጭንቅላታቸው ነው:: እርሱ ካኮረፈ ያኮርፋሉ፤ ከታመመ ይታመማሉ፤ ሎቢ ከረገጠ ይረግጣሉ:: ወደ ውጭ ስለመሄድ እንኳን ሲያስቡ አንድ ቀን ይህ ሰው ይወስደኛል ብለው በርግጠኛነት ያምናሉ::

«እነዚህ ሰዎች ናቸው ባለፈው ጊዜ የአሜሪካ ኢኮኖሚ ተናግቶ ጭን ቅላቶቻቸው ቀጥ ሲሉ እነርሱም ቀጥ ያሉት:: እየተንተቱ መሄድን ብቻ ስለሚያውቁ ወዴት ይሂዱ:: ሥራ መፈለግ እና ሥራ መሥራት አልለመዱም:: አንድ በዲግሪ የተመረቀ ሰው ከሚያገኘው በላይ በዶላር እየተላከላቸው ሲያገኙ የኖሩ ናቸው:: ልብሳቸው እና ጫማቸው ከባሕር ማዶ ነው የኖረው:: ታድያ አሁን መኪናው በድንገት ሲያቆም ምን ይዋጣቸው:: ያው እንደኔ መንገድ ላይ መገተር ነው እንጂ» አለ ፈገግ ብሎ::

«አንተ እነርሱን ትላለህ:: እዚህ ሀገር ሆነውስ ተሳቢዎች አሉ አይደለም እንዴ? አንድን ሀብታም፣ ወይንም ባለ ሥልጣን ተጠግተው፣ ሲስቅ እየሳቁ፤ ሲያለቅስ እያለቀሱ፤ ሲከሳ እየከሱ፤ ሲወፍር እየወፈሩ፤ የሚኖሩ ተሳቢዎች አሉኮ:: የት እንደሚሄዱ ፍጻሜያቸውን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እያውቁም:: ስለ ራሳቸው በራሳቸው አያስቡም:: የሚሄዱት ያ ሰ
በሄደበት ነው:: የሚያምኑት ያ ሰው የሚያምነውን ነው:: የጠላ
ይጠላሉ፣ የወደደውን ይወድዳሉ:: በትልቅ ዋርካ ሥር ያሉ ትን
ዛፎችን ታውቃለህ? እንደዚያ ማለት ናቸው:: ምግባቸውን የሚ
ኙት ከዋርካው ነው:: የሚጠለሉትም በዋርካው ነው::

«ታድያ ያ ሰው ቢከሥር፣ ከሥልጣን ቢወርድ፣ ወይንም ጊዜ
ዳው እነዚህ ተላቢዎች ግራ ይገባቸዋል:: የሆነ ቦታ ቆመው ይ
ሉና:: ያላቸው አማራጭ አንድ ብቻ ነው:: ሌላ የሚሰባቸ
መፈለግ::»

«ቲፎዞ ከመሆን በቀር የራሳቸው ሃሳብ የሌላቸው ሰዎችስ አታው
ቅም?» አለኝ::

«ልክ ነህ ዐውቃለሁ» አልኩት::

«እነርሱምኮ እንደ እኔ ተላቢዎች ናቸው:: እገሌ እንዲህ አለ ከማ
ለት በቀር እነርሱ ራሳቸው የሚሉት ነገር የሌላቸው:: እንብበው፣
ተምረው፣ ወይንም መርምረው ከማግኘት ይልቅ ከሌላ ሰው ሰም
ተው ብቻ የሚወስኑ አሉልህ:: እነርሱ ማሰብ አይፈልጉም፤ ማን
ብም አይፈልጉም፤ ማየትም አይፈልጉም:: ነገር ግን የሚሰባቸው
ሰው አላቸው:: ምን ጊዜም የሌላ ሰው ቲፎዞ ይሆናሉ እንጂ በራ
ሳቸው አይቆሙም::»



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«የአንድ ታዋቂ ዘፋኝ ወይንም የፊልም ተዋናይ ተሳቢዎች የሆኑስ አላየህም» አልኩት::

«እነዚህ የለበሰውን ለመልበስ፣ እንደ አካሄዱ ለመሄድ፣ እንደ ድምፅ አወጣጡ ለማውጣት፣ እንደ አቆራረጡ ለመቆረጥ፣ እንደ አነጋገሩ ለመናገር፣ እንደ ማይክራፎን አያያዙ ለመያዝ፣ መከራ የሚያዩ ወገኖ ቻችን ያሳዝኑኛል:: ለምን በራሳቸው ጭንቅላት አይመሩም:: ከሌላ ውኮ ጥቂት ወስደህ አዳብረህ፣ ካንተ ጋር አስማምተህ አዲስ ማንነት ትፈጥራለህ እንጂ እንዴት የሌላው ፎቶ ኮፒ ትሆናለህ:: ከሌላው መማር ነው እንጂ እንዴት ሌላውን እንዳለ ትቀዳለህ? እንደ አገሬ ነበዝ ነው ሲባል እንጂ፣ አገሬን ይመስላል ሲባልኮ ጥሩ አይደለም:: በራስ መመራት እንጂ መሳብኮ ደግ አይደለም::»

እንዲህ እየወጋን አንድ ተሳቢ የሌለው የጭነት መኪና መጣ:: ሾፌ ሩም ከመኪናው ወረደ:: መንገድ ላይ ወደ ቀረው ተሳቢም ተጠጋ:: ሆድ ዕቃውን ሲነካካው ቆየ:: ከዚያም ከሳቢው ጋር የሚገናኝበትን ገመድ ፈታታው:: የጭነት መኪናውን ወደ ተሳቢው አስጠጋና ገጠመው::

«እንዴ ከሌላ መኪና ጋር ልትሄድ ነው እንዴ?» ብዬ ጠየቅኩት:: የተሳቢ ነገር ይሄውኮ ነው:: የራስህ ጭንቅላት ከሌለህ ያገኘህ ሁሉ ይስብሃል:: ሳቢ ተሳቢውን እንጂ ተሳቢ ሳቢውን አይመርጥም ሲባል አልሰማህም::» አለኝ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«…ታድያ አሁን ወዴት ነው የምትሄደው»

«እንደምሄድ እንጂ ወዴት እንደምሄድ አላውቅም። ተሳቢ መሳቡን እንጂ መንገዱን አያውቅም።» አለ።

መኪናው አጓርቶ ተነሣ። ተሳቢውም ወደማያውቀው ቦታ ሄደ።?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ኮሞ ሳቫ

የዓለም ሀብት ከተከማቸባቸው ከተሞች አንዷ በሆነችው የስዊዘርላንድ ዋና የንግድ ከተማ በዙሪክ እምብርት ላይ ለስብሰባ ወደ አንዱ ሆቴል በረንዳ ስናመራ አገኛለሁ:: ሻሂ ለመጠጣት ወደ አንዱ ሆቴል በረንዳ ስናመራ እገኛለሁ:: ሻሂ ለመጠጣት ወደ አንዷ ሆቴል በረንዳ ስናመራ አብሮኝ የነበረው ልጅ አንዲት ወጣት አገኝና ሰላም ብሏት መጣ:: እርሱ ሲመለስ ለሌሎቹ ልጆች «ሰላም አትሏትም ነበር እንዴ?» አላቸው:: «ማናት? አላወቅኋትምኮ» አሉና ሌላው መለሰለት:: «ሳባ ኮ ናት» አለው ሰላምታውን የሰጣት ወጣት:: «ሳባ የቷ?» «ኮሞ ሳባ ናታ» «እሃ» አሉና ተሳሳቁ::

ህበሾች አንዲት ነገር እንሥተው ከሳቁ አንዳች ታሪክ ይኖራታል ብዬ ጠረጠርኩና «ኮሞ ሳባ» ምንድን ነው?» የሚለውን ጥያቄ ሰነዘርኩ::

«ይህች ልጅ እዚህ ሀገር እጅ ትሰጣለች:: ያው ለቃለ መጠይቅ ለመቅረብ ኬዝ ማጥናት ነበረባት:: በአስተርጓሚነት የሚሠራ አንድ አበሻ ያገኛትና ኬዝ በማዘጋጀት ይረዳታል:: በሳምንት ሁለት ሦስት ቀን እየተገናኙ ያስጠናትና በቀጠሮዋ ቀን ትቀርባለች:: ልጅቱ ሳባ ነው ስሟ:: ነገር ግን ለኬዝ ስትል



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አልማዝ ነኝ ብላለች:: የስደተኞች ቢሮው የነበረው ጅ
ነው:: እዚያ ደግሞ ብዙው ሰው ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ነው::

አስተርጓሚው ከልጅቱ ጋር እንደቀረበ ቃለ መጠይቅ ከሚ
ደርገው ሰው ጋር ስለሚተዋወቁ ሰላምታ ሲለዋወጡ «ኮ
ሳባ» ብሎ በፈረንሳይኛ ሲያወራ ትሰማለች:: ይኼኔ እውነተ
ስሟን ያጋለጠባት ይመስላትና «አይ አበሻ ምቀኛው፣ አስተ
ጉምልኝ ብለው ምሥጢሬን ያወጣብኛል» ብላ ትናደዳለች
ወዲያው ራሴን አመመኝ ትልና ተዝለፍልፋ ትወድቃለች
ቀጠሮው ተራዝሞ ሐኪም ቤት ይወስዷታል::

ከተሻላት በኋላ አስተርጓሚውን «ካንተ ጋር አልሠራም» ት
ዋለች:: ልጁ ግራ ገብቶት ለምን ይላታል:: «እንዴት ስሟ ሳ
ይባላል ብለህ ትነግራቸዋለህ?» ትለዋለች:: ያንጊዜ ይገባው
«ኮሞ ሳቫ ማለትኮ በፈረንሳይኛ ሰላምታ ነው» ብሎ ከት ብሎ
ይስቃል:: በዚያ ምክንያት ስሟ ኮሞ ሳባ ተብሎ ቀረ::

«ማን ነበር በናትህ አስተርጓሚዋ፣ እርሱ ልጅኮ ብዙ ታሪ
ያለው ልጅ ነው» አለው አንደኛው እየሳቀ:: «ሰሎሞን ቅን
ጅት ነዋ» «እ...ም» ከማለቱ «እንዴ ደግሞ ብላችሁ ብላችሁ
ሰሎሞን ቅንጅት፣ አበበ ኅብረት፣ ዓለሙ ግንቦት 7፣ አልማዝ
መድረክ ማለት ጀመራችሁ?» አልኳቸው:: «እርሱኮ የቅንጅት
አባል አይደለም፣ በረሃ ላይ የወጣለት የበረሃ ስሙ ነው:: እይ
ውልህ እዚያ ሱዳን እና ሊቢያ ትራንስፖርት ወይንም ገንዘብ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አጥተህ ብዙ ጊዜ ልትቀመጥ ትችላለህ:: ሦስትም አራትም ወር፡ ከዚያም እንደምንም ብለህ ጣልያን ብትገባም፤ ምግብ እንጅ ልብስ እና ጫማ ብዙም እንደልብህ አታገኝም::

«በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜ የምታደርገው ይኼ የጣት ማስገ ቢያው ወፍራም የሆነ የሱዳን ነጠላ ጫማ አለ:: ታድያ ያንን ጫማ ብዙ ጊዜ የምታደርገው ከሆነ የእግርህ አውራ ጣት እና ሌላው ጣትህ አይገጥምም፣ የV ቅርጽ ሠርቶ ነው የሚቀረው:: ልክ እንደ ቅንጅት የምርጫ ዓርማ:: እና በቃ እግራቸው እን ደዚያ የሆኑ ልጆች ካምፕ ውስጥ «እገሌ ቅንጅት» ይባላሉ::

«ቆይ ግን እዚህ ሀገር እንዴት ነው የሚገባው? ጣልያንስ በመ ርከብ ይገባል» አልኳቸው:: «ከጣልያን ወደዚህ ገንዘብ ተከፍ ሏቸው የሚያሻግሩ ልጆች አሉ:: ጣልያን ላይ ሥራ ስለሌለ ማንም እዚያ ለመኖር የሚፈልግ የለም:: ስለዚህ እንደምንም ብሎ ገንዘብ አጠራቅሞ ወይንም ከሰው ለምኖ መሻገር ነው::» «ከዚያስ? እዚህስ ሥራ ይገኛል? እንዴት ትኖራላችሁ?» «እዚህ ይሻላል፤ ኬዝ ታቀርባለህ፤ እስኪታይ ድረስ መኖርያና ምግብ ይሰጡሃል፡ ከተቀበሉህ ጥሩ ካልተቀበሉህም እየተከራከ ርክ ብዙ ዘመን ትሠራለህ፤ እዚህ ደግነቱ ይብዛም ይነስም ሥራ አታጣም::»

«ምን ዓይነት ኬዝ ነው የምታቀርቡት?»

«ያው የፖለቲካ ወይንም የአንደር ኤጅ ኬዝ ነዋ»



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«የአንደር ኤጅ ኬዝ ምንድን ነው?»

«አየህ አበሻ ሰውነቱ ተጠንፍቶ ቅጭም ያለ ስለሆነ የአርባ ዓመቱ ሰው አሥራ አምስት ዓመቴ ነው ብሎ እጁን ይሰጣል፡ ከዚያ ከሕፃናት ጋር መኖር ነው»

«እንዴት ትችሉታላችሁ ሃያ ሠላሣ ዓመት ቀንላችሁን»

«ከባድ ነው፤ ግን ያው አንዱ ሲያደርገው ስታይ አንተም ታደርገዋለህ፣ ጉዳቱ በኋላ ነው የሚታወቅህ፡ ጡረታ መውጣት አትችልም»

«አንዱ አበሻ ያደረገውን ልንገርህ» አለኝ::

«አገር ቤት ለአንዱ ክለብ ቦክሰኛ ሆኖ ሲጫወት የነበረ ነው:: አርባ ዓመት ሳይሆነው አይቀርም:: ፂሙን ሙልጭ አድርጎ ተላጭቶ አሥራ አምስት ዓመቴ ነው ብሎ እጁን ሰጠ:: ከዚያ ከአንደር ኤጆች ጋር ኪንደር ገባልህ:: እዚያ እንደ ፍላጎትህ የተለያየ ስፖርት ትመርጣለህ:: እርሱ ቦክስ መረጠ:: አጅሬ ፕሮፌሽናል ስለሆነ ገና የመጀመርያ ቀን ሲያዩት አሰ ልጣኞቹ ሁሉ ተገረሙበት:: በቃ ለስዊዘርላንድ የሚሆን ተሰፋ ተገኘ ተብሎ ሰሙ ገነነ::

«በኋላ ውድድር ላይ ልጆቹን ሁሉ ጧ፣ ጠብ፡ ጧ፣ ጠብ እያደረገ ፈጃቸው:: ከእርሱ ጋር ተጋጥሞ ሳይጎዳ የሚወጣ አን ድም ልጅ አልነበረም:: እንዴ ወዳጄ ይኼ የአርባ ዓመት ቡ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰኛ የሚጋጠመው ከአሥራ አምስት ዓመት ልጆች ጋር እክ ነው:: በኋላ ታድያ ልጆቹ ከእርሱ ጋር እንጫወትም አሉ:: አሠልጣኞቹም ግራ ገባቸውና እድሜውን ሲያስመረምሩት ራዛ ልቱ በአርባ እና በሠላሳ አምስት መካከል ነው ብሉ ቁጭ:: ወዲያው ተባረረ»

ሌሎቹ ተስተናጋጆች ምን መጣ እስኪሉ ድረስ አካባቢው በሳቅ ታጀበ::

«ቴዲ ታይታኒክ ነው አይደል እንዲህ ያደረገው» አለ አንዱ እንባውን እየጠረገ:: «አዎ እርሱክ ነው:: በኋላ ወረቀት ያላት ልጅ አግብቶ ነው መኖርያ ያገኘው» አለ የተረከው ልጅ:: እኔም እንደ ለመደብኝ «ደግሞ ታይታኒክ ምንድን ነው?» አልኳቸው::

«እዚህ ሀገር ያለው ስደተኛ በቱርክ በኩል ወይንም በሊቢያ በኩል ወደ ጣልያን፣ ከዚያም ስዊዝ የገባ ነው:: በሊቢያ በኩል የገቡትን ታይታኒኮች ይሏቸዋል::» አለና አብራራልኝ:: ጣል ያን ባሕር ኃይል የሚባሉት ናቸው እዚህ ታይታኒክ የሚባ ሉት ማለት ነው::

«እንዴት ግን፣ እነርሱስ አይጠረጥሩም እንዴ የአርባ ዓመት ሰው አሥራ አምስት ዓመቱ ነው ሲላቸው?»



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«በፊት በፊት አይጠረጥሩም ነበር፣ ገዝም ብለው ነበር የሚ
በሉሁ። በኋላ ግን መጠራጠር ጀመሩ። ያንን እንትናን እ
ተጫውተውበታል» አለና ትረካውን አቆመ።

«የቱን?» አልኩ እኔ ታሪኩን ለማወቅ ጓጉቼ።

«ሠመረ ቱቦን»

«ወይ እዚህ ሀገር የቅጽል ስሙ መብዛቱ። ደግሞ ቱቦ ም
ይሆን ይሆን?» አልኩ ሳሳስበው ድምጼን ከፍ አድርጌ።

«ቆይ ታሪኩን ይንገርህና ቱቦ ምን እንደሆነ እነግርሃለሁ» አ
ከጎኔ የተቀመጠው።

«ልጅ ወደ ሰላሣ አምስት ዓመት ይሆነዋል። ሂሙን ፈን
ይመጣና አሥራ አምስት ዓመቴ ነው ብሎ እጅ ይሰጣል
አገር ቤትኮ ሲታወቅ ክለብ እግር ኳስ ሲጫወት የነበረ ነው
እንትና ሲባል ሰምተህ አታወቅም?» አለና የታወቀ ስም ጠራ
ልኝ። ስሙን የሰማሁት ይመስለኛል።

«እነርሱ ግን ይጠራጠሩትና ተቀብለው ካምፕ ውስጥ አን
ቤት ለብቻው ሰጥተው ያስቀምጡታል። ለአንድ ሳምን
ከቤት እንዳይወጣ ፍሪጁን በምግብ ሞልተው በሩን ይዘጋሉ
በአካባቢው ምንም ዓይነት የጢም መላጫ አልነበረም። ታድያ
ከሳምንት በኋላ ቤቱ ሲከፈት አጅሬ እንደ ገና አባት ፂ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ተንዝርግኅልሃል:: ወዲያው የአሥራ አምስት ዓመቱ፡ ልጅ! ብለው አስወጡት::

«ቱቦ ምን መሰለህ» አለና ከጎኔ የተቀመጠው ልጅ ሻሂውን ፉት እያለ ቀጠለ:: እዚህ በሊቢያ የመጡት ታይታኖቹ እንደ ሚባሉት፣ እስራኤል ደግሞ ከግብጽ በድንበር በኩል እስራኤል የገቡት ቱቦ ይባላሉ:: በአንድ ወቅት በአሸጋጋሪዎች ምክንያት ከኢትዮጵያ ግብጽ፣ ከግብጽ ደግሞ ወደ እስራኤል መግባት ተጀምሮ ነበር:: የምትገባው በጋዛ በኩል በቱቦ ውስጥ አልፈህ ነው:: እስራኤሎች ከደረሱብህ እንዳይታወቅ ሌሊት ሌሊት ነበር ጉዞው:: የሚያስገርምህ ቱቦው ውስጥ ስትሄድ የምትጓዘው ፊትህን አዙረህ ወደ ኋላ ነው:: ምክንያቱም ወደ እስራኤል የገባ ሳይሆን የወጣ ነው ተብሎ እንዲጠረጠር:: አንደኛው አሻጋሪ ከኋላ ሆኖ ሲመራህ ሌላው ደግሞ ከፊትህ ሆኖ የእግር ኮቴ ያጠፋል»

«እንዲያውም አንድ ጊዜ ከኋላ ሆኖ ወደ ኋላ መጀመርያ የሚጓዘው ሰው በጣም ወፍራም ስለ ነበር ተንፋሽ አጠረውና ቆመ:: በምን እንሂድ:: አሻጋሪው ብቻውን ማውጣት አልቻለም:: ግዙፍ ሰውዬ ነው:: መንገዱን ጥቅጥቅ አድርጎ ዘጋው:: በስንት መከራ እያራገበለት ሊነጋጋ ሲል ነበር የደረሱት:: ከዚያ ቱቦው ፍልስጥኤም ማዛት ይጥልሃል፤ በመኪና እስራኤል ትገባለህ:: በዚህ መልክ የገቡትን ነው «ቱቦ» የሚሏቸው::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«ቆይ ከግብፅ ወደ እስራኤል ድንበር እንዴት ትሄዳላችሁ?»

«ማታ ማታ ነው የምንጓዘው:: ከሆነ ቦታ በፒክ አፕ መኪና ይጭኑህና ተኛ ተብለህ በላይህ ላይ ሸራ ይለብሳል:: ለማ መሰል ደግሞ ዘይት የተሞላበት ጀሪካል በላይህ ላይ ይጫ ናል:: አቤት ክብደቱ:: አየር መተንፈሻ አታገኝም:: በመኪ ናው ግራ እና ቀኝ በኩል በቀዳዳ የወጣ ቱቦ ለእያንዳንዳችን ይሰጠንና በርሱ እየተነፈስን ነው የምንጓዘው:: ልክ በቆም እና ጀሪ ፊልም ላይ ባሕር ውስጥ ሲገቡ እንደሚያደርጉት:: ከዚያ ድንበሩ ጋር ደርሰህ በቱቦው መንፏቀቅ ነው::

«አሁን እናንተ የውሸት ኬዝ አጥንታችሁ ነው የምትቀርቡት ቆይ ግን ቃለ መጠይቅ ሲያደርጉላችሁ ድንግርግር አይላ ችሁም::»

«ምን ጥሩ ነገር አለ መሰለህ፣ ከአስተርጓሚህ ጋር ነው አብረህ ኬዝህን የምታጠናው፣ አንተ ከተደናገረህ «ረስቼዋለሁ» ትለ ውና እርሱ ይመልስልሃል:: ያለበለዚያም በኮድ ትነጋገራለህ»

«እንዴት?»

«ያው ሰለሞን ሰለሞን እያልክ ነዋ» ሁሉም ሳቁ:: አንዳች የሚ ያስታውሱት ታሪክ ቢኖር ነው ብዬ ጓጓሁ::

«ሰለሞን ሰለሞን ነው ማለት ልክ መልሱን የሰጠህ አስመስለህ የአስተርጓሚውን ርዳታ መጠየቅ ማለት ነው::»



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«ለምን ሰለሞን ሰለሞን ተባለ?»

«ይህማ የመርካቶ ታሪክ እኮ ነው» አለና ተረከልኝ::

«በደርግ ጊዜ መርካቶ ውስጥ ሰለሞን የሚባል ልጅ ያላቸው አንድ ነጋዴ ነበሩ:: ያኔ ግብር የሚተመነው አገር ውስጥ ገቢ ይመጣና ሱቅህንና መጋዝንህን በማየት ነበር:: ታድያ አንድ ቀን ሱቃቸው ውስጥ ቁጭ ብለው ጠዋት ዳዊት ሲደግሙ አገር ውስጥ ገቢዎች ሳያስቡት ከች አሉባቸው:: ሱቃቸውን አስተካክለዋል:: ከመጋዝኑ ግን ዕቃ አልቀነሱም:: ሰውዬው በጸሎት ደጋሚነታቸው ስለሚታወቁ አገር ውስጥ ገቢዎቹ እስኪጨርሱ ብለው ቆም አሉላቸው:: እርሳቸውም ዳዊት የሚደግሙ መስለው አጠገባቸው ለቆመው ለልጃቸው ለሰለሞን

ሰለሞን ሰለሞን

እንጋቻቺ መጠሙኑ

ኸለፍም ኸለፍም ግብሪ እከላልተኑ

/ሰለሞን ሰለሞን፣ ጆቦቹ መጥተዋልና ሄደህ ዕቃውን አዘገጃጅ/ አሉት:: እርሱም ተነሥቶ ሄደና ዕቃውን ቀናነሰው:: ልክ ልጁ ሲመለስ እርሳቸውም ምራቃቸውን ትፍትፍ ብለው ለሰዎቹ በላምታ ሰጧቸው:: የኛም እንዲሁ ነው:: ***ሉሴርን፣ ስዊዘርላንድ***

# «የታሪክ እና ቅርስ ፓርቲ»



**ሉሁቻ** በጀርመን የንግድ ከተማ በፍራንክፈርት እምብርት
ኛለሁ:: እዚህ የመጣሁት ልቅሶ ልደርስ ነው:: ሕዝቡ
ዘሐ ዘጊ ወዲህ ወዲያ ሲል ነው የምታዩት:: በአንድ
የበጋው ዘፈን ደምቋል፤ በሌላ በኩል በየበረንዳው በጃምቦ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሞቶ የተሞላ ቢራ የጨበጡ ጀርመኖች ከወገባቸው በላይ ተራ ቁተው ያስነኩታል፡፡

አሁን ያለህበትን ቦታ የሀገሬው ሰዎች «ሀውት ኻት» ይሉታል፡፡ የከተማው አራዳ እንደ ማለት ሳይሆን ይቀራል? እዚያ ቦታ ላይ አንዲት ጥንታዊት የጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን አለች፡፡ ቅድስት ካትሪና ትባላለች፡፡ እዚህ የመጣሁት ከሦስት መቶ ዓመታት በፊት፣ ኢትዮጵያዊ ሳይሆን የኢትዮጵያን ጉዳይ ለዓለም ለማስተዋወቅ የደከመ፣ አማርኛን እና ግእዝን አጥንቶ ሰዋስው የጻፈ፣ የሀገሩ ሰው የሆነው ኤድዋርድ ሉልንዶርፍ «ኢትዮጵያን በተመለከተ እጅግ የሚያስደንቅ ዕውቀት ያለው ምስጉን ሰው» ብሎ የመሰከረለትን የጀርመናዊውን ሊቅ የኢዮብ ሉዶልፍን መቃብር ለመጎብኘት ነበር፡፡

ወደዚህ የመቃብር ሥፍራ ከመምጣቴ በፊት በፍራን ክፈርት ከተማ ያገኘኋቸውን ኢትዮጵያውያን እጠይቅ ነበር፡፡ «ለመሆኑ ኢዮብ ሉዶልፍ የሚባለው የአማርኛ እና የግእዝ ሊቅ፣ የኢትዮጵያን እምነት፣ ባሕል፣ ታሪክ እና ቋንቋ በተመለከተ ያጠና ፣ ኢትዮጵያን በተመለከተ እምብዛም በማይታወቅበት ዘመን፣ ከአሥር በላይ መጻሕፍትን የጻፈ፣ እንግሊዝ ድረስ ተጉዞ ከኢትዮጵያ ጋር የንግድ ግንኙነት ሊኖር ይገባል ብሎ የወተወተ፣ ሀገረ ነገዱ ትውልደ ሙሳዱ ጀርመን የሆነ፣ ያልተወለ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ደን ወገናችንን፣ የተቀበረበትን መቃብር ታውቃላችሁን?» የሚለው ጥያቄዬ ለአንድ ሳምንት ያህል ቀጥሎ ነበር።

እንኳንስ መቃብሩን የሚያውቅ፣ ኢዮብ ሉዶልፍ የተባለ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን በተመለከተ ብዙ የደከመ ፍጡር መኖሩን የሰማ አላገኘሁም ነበር። አንዳንዶቹም እዚህ ግኝነት ጠይቆ የቀረ ሐበሻ፣ ሌሎችም ከብዙ ዓመታት በፊት በጉዲፈቻ የመጣ ኢትዮጵያዊ ነበር የሚመስላቸው። በመጨረሻ ግን ሐምቡርግ የሚማረው መርሻ አለኸኝ መቃብሩ የሚገኝበትን አድራሻ አገኘና ገላገለኝ።

መቃብሩን ለማየት ሁለት ጊዜ ተመላልሻለሁ። በከተማዋ እምብርት ጭፈራው በመቅለጡ የተነሣ ይመስለኛል ቤተ ክርስቲያኑ ዝግ ነበር። ለሦስተኛ ጊዜ ስንመጣም ተመሳሳይ ዕጣ ፈንታ ነበር የገጠመን። አካባቢው በልዩ ልዩ ሀገሮች የባሕል ጭፈራ ሞቋል። ቢራ የሚጨልጡ ጀርመኖች ከፊሎቹ ቆመው ሌሎቹ ተቀምጠው አካባቢውን አጥለቅልቀውታል። ለአንድ ሰዓት ያህል ታግሠን ጠበቅን። ቤተ ክርስቲያኑ ግን አልተከፈተም። በመጨረሻ አካባቢውን ለቅቀን ልንወጣ ስንል በፊት ለፊት በኩል ያለው በር ተከፈተ። እኛም በጉጉት እየተጣደፍን ለመግባት በስተ ቀኝ በኩል ስናመራ ዓይኔ አንዳች ነገር ላይ ዐረፈ። «ኢዮብ ሉዶልፍ» የሚል በላቲን ፊደል የተጻፈ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የማድግዳ ጽሑፍ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተ ጀርባ፣ በቀኝ በኩል አየሁ::

ፋሚዩን ገታ አደረግኩና አተኩሬ ተመለከትኩት «ሚዋሪየ ኢዮቢ ሉዶልፊ» ይላል:: ጽሑፉ በላቲንኛ ነበር የተጻፈው:: ኢዮብ ሉዶልፍን የተመለከተ መሆኑ ገባኝ:: በውስጡ የተጻፈውን ግን ልረዳው አልቻልኩም:: እንዳች የሚገልጥልኝ ሰው ባገኝ ብዬ ወደ ቅድስት ካትሪና ቤተ ክርስቲያን ገባሁ::

ወደ ቤተ ክርስቲያኗ ስንገባ ያገኘነው አገልጋይ፣ አራት ጥቋቁር ሰዎች በፍጥነት ተግተልትለን ስንገባበት ጊዜ ነው መሰል ደንግጦ አለ::

«የኢዮብ ሉዶልፍን መቃብር ለማየት ነበር የመጣነው» አልነው:: ሰውዬው ግራ ተጋባ:: ከዚያም

«ኢዮብ ሉዶልፍ ማነው?» ሲል መልሶ ጠየቀን:: አልሰሜን ግባ በለው ማለት ይሄኔ ነው:: እየተቀባበልን ስለ ኢዮብ ሉዶልፍ የምናውቀውን ነገርነው:: በጣም የሚገርመው ግን፣ ይህ ሰው ለመጀመርያ ጊዜ ኢዮብ ሉዶልፍ ስለሚባል ሊቅ በመስማት ላይ ነበር::

«የምትሉትን ሰው አላውቀውም» አለንና አረፈው::

እኔም «ከቤተ ክርስቲያኑ ጀርባኮ ስለ እርሱ ተጽፏል» አልኩት በእስተርጓሚ:: በመገረም ነበር የሚያየኝ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«ርግጠኛ ነህ?» አለና ጠየቀኝ:: አብሮኝ የነበረውና ጀርመን የሚናገረው አብርሃም አሰፋ የተባለ ወዳጄ

«አሁን እርሱን አይተን ነው የመጣነው» አለና በሚገባ ቋንቋ አስረገጠለት::

«አሳዩኝ» አለ ሰውዬው:: ከዚያም ተከታትለን ወጣን:: ከቤተ ክርስቲያኑ ጀርባ ወዳለው ጽሑፍ ዘንድ ወሰድነው:: እየተደነቀ ከኛ እኩል ተመለከተው::

«ይቅርታ አድርጉልኝና አይቼው አላውቅም፤ የመጀመርያ ነው:: ለወደፊቱ ታሪኩን ለማወቅ እሞክራለሁ» አለን:: ሰውዬ ውም እንደኛ የላቲን ፊደል አያነብብምና በውስጡ ምን እን ተጻፈ ማወቅ አልቻልንም::

ሉዶልፍ ኤርፉት በተባለች የጀርመን ከተማ፣ ጁን 15 ቀን 1624 እኤአ ነበር የተወለደው:: በኤርፉት አካዳሚ እና በሌ ይደን የጥንታዊ ጽሑፎች ምርመራ የሆነውን ፊሎሎጂን ካጠና በኋላ በስዊዲን መንግሥት አማካኝነት በ1649 እኤአ ወደ ሮም ተጓዘ:: በሮም እያለ ከዚያ ዘመኑ አምሐራ፣ ከዛሬ ደቡብ ወሎ ከመጣው አባ ጎርጎርዮስ ከተባለ መነኩሴ ጋር ተገ ናኘ:: የግእዝ እና የአማርኛ ቋንቋን ጠንቅቆ የተማረው ከአባ ጎርጎርዮስ ነበር::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ለተወሰኑ ዓመታት በጥናት እና በሥራ ላይ ከቆየ በኋላ በ1684 እኤአ ወደ ፍራንክፈርት መጣና እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ሙሉ ጊዜውን ለኢትዮጵያ ቋንቋ፣ ታሪክ እና ባሕል ጥናት ሰጠ። የኢትዮጵያን የጥንት መጻሕፍት እና የኢትዮጵያን ታሪክ የተመለከቱ መጻሕፍትን አሳትሟል። መጻሕፍቱም ከላቲን በተጨማሪ በእንግሊዝኛ፣ በፈረንሳይኛና በደች ቋንቋ ለዓለም ተዳርሰው ነበር።

የአማርኛ ሰዋሰው፣ የአማርኛ እና ላቲን ሌክሲኮግራፊ፣ የግእዝ እና ላቲን ሌክሲኮግራፊ እንዲሁም የግእዝ ሰዋሰውን በተመለከተ ያዘጋጃቸው መጻሕፍት እጅግ ያስደነቁት እና ከእርሱ ዘመን በኋላ የተነሡ ሊቃውንት የኢትዮጵያን መጻሕፍት በሚገባ እንዲረዱ መሠረት የጣሉ ሥራዎቹ ናቸው። ይህንን ሁሉ አከናውኖ ኢዮብ ሉዶልፍ እፕሪል ስምንት ቀን 1704 እኤአ አርፎ፣ በፍራንክፈርት ቅድስት ካትሪና ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ።

ይህንን ሁሉ የሠራውን ሊቅ ነው እንግዲህ በተቀበረበት ቦታ ላይ የሚያገለግለው ጀርመናዊ አላውቀውም ያለኝ። መጀመርያ እጅግ ተናድጄ ከፉ ቃል ልናገረው ነበር። በኋላ ግን ብናገረውም በአማርኛ ወይንም በእንግሊዝኛ ነው። ያም ቢሆን እኔን የተሰማኝን ያህል እርሱን አይሰማውም። እኔም ብሆን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በእንግሊዝኛ እንጀቴን የሚያርስ አሪፍ አሪፍ የንዴት ቃል አይመጣልኝም ብዬ ተውኩት።

ደግሞምኮ «ባለቤት ያቃለለውን አሞሌ ባለ ዕዳ አይቀበለውም» ይላል የሀገሬ ሰው። ለነገሩ ኢዮብ ሉዶልፍን ማስታወስ ያለብን እኛ ነን ወይስ ጀርመኖቹ? ለመሆኑ ኢዮብ ሉዶልፍ የሠራው ለኛ ነው ወይስ ለጀርመን? እነዚህን ጥያቄዎች ነበር የማስበው በጽሑፉ ፊት ለፊት ቆሜ። ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ፣ አንዳንዶቹም ኢትዮጵያን በዓይኑ ሥጋ ሳያዩ፣ ጥቁር ሕዝብን ከሚንቁ ማኅበረሰቦች ተፈጥረው፣ ስለ ኢትዮጵያ የደከሙ፣ ታሪካችንን፣ ባሕላችንን፣ እምነታችንን፣ ቋንቋችንን፣ ቅርሶቻችንን ለማስተዋወቅ ለደከሙ። በዚያ ዘመን አፍሪካ የጨለማው አህጉር እየተባለች በምትጠራበት ጊዜ «በዚያ አህጉር ብርሃን አለ» ብለው በድፍረት የጻፉ አያሌ የውጭ ሰዎች አሉ። ከኢትዮጵያውያን በላይ ለኢትዮጵያ ባለውለታ የሆኑትን፣ በዜግነት የሌላ፣ በልባቸው ግን የኢትዮጵያ የሆኑትን ሰዎች እንዴት ያለ ቦታ ይሆን የምንሰጣቸው?

መቼ ይሆን እንወዳታለን የምንላትን ሀገር፣ ከኛ በላይ ለወደዱ ሰዎች፣ እንሞትላታለን ለምንላት ሀገር ከኛ በላይ ለሞቱ ሰዎች፣ እንሠራላታለን ለምንላት ሀገር ከኛ በላይ ለሠሩ ሰዎች ታሪካዊ ዋጋ ሰጥተን ታሪካዊ ውለታ የምንከፍለው? እነ ኢዮብ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሉዶልፍ ከተረሱ የንሲልቪ.ዮ ጋንክረስት እና ሪቻርድ ጋንክረ
ስት ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ነው?

እኔ ግን ሳስበው ደጋጎቹን ሰዎቻችንን እንድንረሳ ያደረገን
ቂም የመያዝ ልማዳችን ሳይሆን አይቀርም ብዬ ገመትኩ::
ቂመኛ ሰው የጎዳውን እንጂ የጠቀመውን አያስታውስምና::
ለልጅም የሚያወርሰው ቂም የያዘበትን እንጂ በጎ ያደረገለትን
አይደለም:: እኛም እነ ሞሶሎኒን፣ እነ ግራዝያኒን፣ እነ ጄኔ
ራል ናፒየሪን የምናስታውሰውን ያህል እነ ኢዮብ ሉዶልፍን
የረሳናቸው በዚያ ምክንያት ይመስለኛል:: ብዙዎቻችን ሀገሩ
ችንን ስለ ጎዱት ሰዎች ብዙ የምናውቀውን ያህል ስለጠቀሟት
ሰዎች ብዙ አናውቅም:: እናም ይህንን ጠባያችንን የሚያጠፉ
እንዳች መድኃኒት ሳያስፈልገን ይቀራል?

አውሮፓ ውስጥ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳይ አሳሳቢ እየሆነ ሲመጣ፣
የፖለቲካ ሰዎችም አብዛኛው ትኩረታቸው ሞቃት ወደሆኑት
ጉዳዮች እያጋደለ ሲሄድ፤ «አረንጓዴ ፓርቲዎች» የሚባሉ ፓር
ቲዎች ተመሠረቱ:: የእነዚህ ፓርቲዎች ዋና ዓላማ መንግ
ሥት መሥርቶ ሀገር ማስተዳደር ሳይሆን በሀገሪቱ ሕጎች፣ አሠ
ራሮች፣ አጀንዳዎች እና የዕለት ከዕለት ጉዞዎች ውስጥ የአካ
ባቢ ጥበቃ ቦታ እንዲሰጠው፣ እንዳይዘነጋ ማድረግ ነበር::

ኢትዮጵያ ውስጥም «የታሪክ እና ቅርስ ፓርቲ» ሳያስፈልግ
አይቀርም:: ለዚህች ሀገር ውለታ ውለው የተረሱትን፣ ሥራ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሠርተው የተዘነጉትን የሚያስታወስ፣ በሀገሪቱ ሕጎች፣ አሠራ ሮች፣ አጀንዳዎች እና መዋቅሮች ውስጥ የሀገሪቱን ባሕላዊ፣ ታሪካዊ እና ትውልዳዊ ቅርሶች፣ እሴቶች፣ አሻራዎች ቦታ እንዲያገኙ የሚታገል ፓርቲ:: ዓላማው መንግሥት መመሥ ረት አይደለም:: ነገር ግን የሚመሠረቱ መንግሥታት ለሀ ሪቱ ታሪክ፣ ባሕል፣ ቅርስ ተገቢውን ቦታ እንዲሰጡ የሚሟ ጉት እና የሚቀሰቅስ፣ ታላላቅ ሰዎች በብሔራዊ ደረጃ እን ሰየሙ፣ እንዲከበሩ፣ መታሰቢያ እንዲኖራቸውና ታሪኮ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ የሚሠራ ፓርቲ:: ( ርላማው ውስጥ ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት ቅርስ እና ታሪ የሚወክል::

በየዘመኑ፣ በየብሔረሰቡ እና በየሀገሩ ሊያሉ ሰዎች ታሪክ ተው አልፈው ተቀብረዋል:: እያሌ ቅርሶች ተከማችተዋ ሀገሪቱን የሚመለከቱ መታሰቢያዎች ተተክለዋል:: ትው አልፎ ትውልድ ሲተካ ግን ይረሳሉ:: ኢትዮጵያውያን ዶ ኞች ለደቡብ ኮርያ ነጻነት ለከፈሉት መሥዋዕትነት በኮሪ ምድር የተተከለ ሐውልት አለ:: ወደዚያ የተጓዙ ሰዎች እንደ ሚሉት ግን ከአዳዲሶቹ የኮርያ ትውልዶች ብዙዎቹ ያን ሐውልት አያስታውሱትም:: ነገሮች ተረስተው እና ተበላሽ ተው እንደ ኢዮብ ሉዶልፍ መቃብር ከመዘንጋታቸው በፊት መንቃት ያለብን ዛሬ ይመስለኛል:: «ፀጉርን ማሣመር ሳይረ ለጥ ነው» ይል የለ የሀገሬ ሰው:: [illegible]



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ይምርሃነ – ያልተጠናው ሥልጣኔያችን



***ከአዲስ አበባ*** በባሕርዳር፣ ጎንደር፣ ላሊበላ በኩል ወደ አክሱም የሚወስደውን የተለመደውን የቱሪስቶች የጉዞ መሥመር ተከትለን ነበር የተጓዝነው:: እኛ ላሊበላ ላይ ወርደን ጉዟችንን ወደ ይምርሃነ ክርስቶስ አደረግን::

ወደ ይምርሃነ ክርስቶስ ለመድረስ ከላሊበላ ወደ ሰቆጣ የሚወስደውን መንገድ ይዘን ለ30 ኪሎ ሜትር ከተጓዝን በኋላ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ብልብላ ከተባለችው ከተማ ደረስን:: ከዚያም ዋናውን መንገድ ትተን ወደ ምሥራቅ ተገነጠልን:: መንገዱ ወደ ይምርሃ ክር ስቶስ ቱሪስቶችን ለማጓጓዝ እንዲረዳ በአካባቢው መስተዳድ የተጠረገ መንገድ ነው:: ከብልብላ በኋላ 6 ኪሎ ሜትር እን ነዳን ጥንታዊውን የንጉሥ ይምርሃነ ክርስቶስ ከተማ በሩቁ አየናት:: አሁን ለምልክት ከሚታየው እና የኢያ ወሐና ማኅበር በብረት ፍርግርግ ለማስታወሻ ካሠራው ተኛ ጎጆ እና በዙርያው ካለው ዐጸድ በስተቀር ሌላ ም አይታይበትም:: ቀሪውን ስድስት ኪሎ ሜትር ስናጠናቅ ታችን ጥቅጥቅ ያለው ደን ገጭ አለ::

1526 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው እና በተራራው ላይ የ ጋው ጥንታዊ ደን በሀገር በቀል ጽድ እና ወይራ የ ነው:: መነኮሳቱ ደኑን የተከለው ንጉሥ ይምርሃነ ክር መሆኑን ይናገራሉ:: ከመኪና ወርደን ባሕል እና ቱሪዝም ራው የእግረኞች መንገድ በኩል ተራራውን መውጣት ጀ ርን:: ጸጥ ባለው አካባቢ የአእዋፍን ድምጽ ብቻ ነው የምት ሙት:: 1 ኪሎ ሜትር ያህል እየተጠማዘዛችሁ ተራራው ትወጣላችሁ::

የእግር መንገዱን አጠናቅቃችሁ ከተራራው ወገብ ስትደርሱ «ውግረ ስሂን» የሚባለውን ዋሻ ከሩቁ ታዩታላችሁ:: የወለ ስፋቱ 50 ሜትር በ38.75 ሜትር የሆነው ይህ ሰፊ የተፈጥ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ዋሻ ዙርያው በቋጥኝ የታጠረ ነው። በስተ ምስራብ በኩል የዋሻው ከፍታ እስከ 7.7 ሜትር ይደርሳል።



በስተ ምሥራቅ በኩል ዋሻውን ውስጥ ለውስጥ እስከ አቡነ የቤፍ ተራራ ጋር የሚያገናኝ የውስጥ ለውስጥ መንገድ እን ዳለው መነኮሳቱ ይናገራሉ። የገዳሙ ዲያቆናት ችቦ አብርተው የዋሻውን መጨረሻ ለማግኘት ገብተው ነበር። ውስጥ ለውስጥ አራት ሰዓት ተኩል ያህል ከተጓዙ በኋላ ችቦው እያለቀባቸው ሲመጣ ጊዜ መመለሳቸውን የአካባቢው ሰዎች ይተርካሉ። ከቅ ርብ ጊዜ ወዲህ የውስጥ ለውስጥ መንገዱ መግቢያ በደለል እየተደፈነ ይገኛል። በአስቸኳይ ጥናት ማድረግ ካልቻልን እንደተሠወረ የሚቀር ብዙ ታሪክ አለ።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ዋሻው የታጠረበትን የ1979 ዓም የብሎኬት አጥር አልፋችሁ ስትገቡ ዓይናችሁ ሊነቀልበት የማይችለውን የ12ኛው መክዘ ሥልጣኔያችንን ታያላችሁ።

የቤተ መቅደሱ ድንቅ ጥበብ በውኃ ላይ ከመሠራቱ ይጀምራል። ዋሻው ውስጥ ተዘርግቶ የነበረው ሐይቅ በላዩ ላይ በእንጨት እና በድንጋይ ተረብርቦ ነው ቤተ መቅደሱ የተሠራው። የኋላ ዘመን ትውልድ አያምነንም ብለው አስበው ይመስለኛል ከሥሩ የሚገኘውን የውኃ አካል ለማየት እንዲቻል ስትገቡ በስተ ግራ በኩል በእንጨት በር የሚዘጋ ጉድጓድ ትተውልናል። የአካባቢው ሰዎች እንደሚሉት እና በመጠኑም ማየት እንደሚቻለው በባሕሩ ላይ እንጨት፣ በእንጨቱም ላይ ሣር፣ በሣሩ ላይ ጭቃ፣ በጭቃውም ላይ ደረቅ አፈር፣ በአፈሩ ላይ ንጣፍ ድንጋይ ተደልድሎ ነው የተሠራው። ወደ መቅደሱ ገብታችሁ በባዶ እግራችሁ ከቆማችሁ ቅዝቃዜው ይሰማችኋል።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF



በባሕሩ ላይ የተረበረበው እንጨት በምን መሠረት ላይ ቆመ? በእውነትም እንጨት ከሆነ ለአንድ ሺ ዓመታት እንዴት ቆየ? ተመራማሪዎችን የሚፈልጉ ጥያቄዎች ናቸው::

የይምርሃነ ክርስቶስ ቤተ መቅደስ ውቅር አይደለም:: ጥንታዊው የኢትዮጵያውያን የሥነ ሕንፃ ጥበብ የተንፀባረቀበት ግንባታ ነው:: ውጫዊ ስፋቱ 12.22 በ9.54 ሲሆን ከወለሉ እስከ ጣራው ያለው ከፍታ ደግሞ 5.88 ሜትር ያህላል:: ከዕጽዋት፣ ከወጥ ድንጋዮች እና ከኖራ መሰል ነገር የተሠሩ 26 መስኮቶች ዙርያውን አስውበውታል:: እነርሱም በሰሜን 8፣ በምሥራቅ 6፣ በደቡብ 7፣ በምዕራብ 5 ናቸው::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠቢቡ አምስት ስድስት፣ ሰባት እና ስምንት ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸው የመረጠበት ምክንያት ምን ይሆን? ከ26ቱ መስኮቶች መካከል 22ቱ ሲከፈቱ አራቱ ግን አይከፈቱም:: የአንዱ መስኮት ዲዛይን ከሌላው መስኮት ዲዛይን ስለሚለያይ ለሃያ ሁለቱ መስኮቶች ሃያ ሁለት ዓይነት ዲዛይን ነው የምናየው:: የዘመኑ ጠቢባን ጥበባቸውን ለማሳየት ምን እንደተጠበቡ ያመላክታል::

ቤተ መቅደሱ ደቃቅ፣ መጠናቸው የተመጣጠኑ ጥቋቁር ድንጋዮች በጭቃ እየተጣበቁ ነው የተገነባው:: እንዴት ይሆን ጭቃ እና ድንጋዩን አቡክተው ያጣበቋቸው? የጭቃው ግንባታ ለ25 ሳ. ሜትር ያህል ወደ ላይ ከተጓዘ በኋላ በአራት መዓዝን የተጠረበ ወጥ እንጨት ይገባበታል:: እንዲህ እያለ ድንጋዩ፣ ጭቃ እና እንጨት በጥበብ ተስማምተው ይምርሃን ክርስቶስን ለሺ ዓመት ያህል አቁመውታል:: እኔን የገረመኝ ነገር ቢኖር ዛሬ ዛሬ በሲሚንቶ እና በድንጋይ የተሠሩት ሕንፃዎቻችን ዓመት ሳይሞላቸው ሲሰነጠቁ ጭቃውን ከድንጋይ እና እንጨት ጋር አዛምደው ይህንን ያህል ዘመን ያቆዩበት ጥበብ ምን ይሆን? የሚለው ነው:: እንዲህ እየተያያዘ የተገነባው ግድግዳ ኖራ በሚመስል ነጭ ነገር ከውጭ እና ከውስጥ ተለስኗል:: የልስኑ ንጣት እና የእንጨቱ ወርቃማ ቀለም ለቤተ መቅደሱ ውጫዊ ገጽታ ዓይን እንዳይነቀል የሚያደርግ ውበት ሰጥቶታል::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በምዕራብ እና በምሥራቅ ሁለት ሁለት ፎቆችን ያዘለው ሕንፃ ወለሉ እጅግ ለስላሳ በሆኑ ድንጋዮች ንጣፍ የተሠራ ነው:: እጅግ የሚያስደንቀውን ሌላ ጥበብ የሚያዩት ደግሞ ወደ በሩ ስትዞሩ ነው:: ከአንድ ወጥ እንጨት የተሠራው በር፣ ከግድግ ዳው ጋር አንድ ሺ ዘመን በሆናቸው ብሉኖች እየታሠረ በታ ጣፈ ብረት ተያይዟል:: በዚያ ዘመን እንጨት ሠርስረው የሚ ገቡ ብሉኖችን የመሥራት ጥበብ ነበረን ማለት ነው? በሩን ለመዝጋት ከእንጨት የሠሩት ጥንታዊ ቁልፍ እጅግ አስደናቂ ነው:: የቁልፉ መግቢያ ቀዳዳ እንደ ዘመናዊው ቁልፍ የተገ ለበጠ ቅል ቅርጽ አለው:: በዚያ ዘመን የነበረውን የቁልፍ ቴክኖሎጂ የታሪክ ምሥክር ሆኖ ያሳየናል::

የቤተ መቅደሱን ውስጣዊ ጥበብ ለማየት ከአንድ ወር በላይ ይፈጃል ባይ ነኝ:: የዘመኑ ጠቢባን ያለ ጥበብ ያለፉት አን ድም ክፍት ቦታ አይገኝም:: ጣራው፣ ግድግዳው፣ ወለሉ፣ ዓም ዶቹ በሮቹ እና መስኮቶቹ ሁሉ አንዱ ከሌላው የማይገናኝ ጥበብ ፈሰሰበታል:: የመቅደሱ መካከለኛ ቦታ ከተጠረበ እና ለስላሳ ከሆነ እንጨት የተገጣጠመ ሲሆን ክብ ሆኖ የታነፀ ነው:: ውስጡ በመንፈሳዊ ሥዕሎች ያጌጠ ሲሆን የሚዘጋው በመጋረጃ ነው::

የቤተ መቅደሱን ጣራ የተሸከሙት ዓምዶች በባለሞያ ከተጠ ረቡ ለስላሳ፣ ጠንካራ፣ ሰፋፊ እና ከባድ ከሆኑ የከበሩ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ድንጋዮች የታነጹ ናቸው:: እያንዳንዱ ዓምድ ልዩ በሆነ ቁረጣ
እና ሥዕል የተጌጠ ነው:: የአንዱ ዓምድ ዲዛይን በምንም
መልኩ ከሌላው ጋር አይያያዝም:: የቅድስቱ ጣራ በስምንት
ክፍል የተ ከፈለ ሲሆን እያንዳንዱ ጣራ የራሱ የሆነ ልዩ
ዲዛይን እና ሥዕል አለው:: አሁን አሁን ከአቧራ እና ከክብካ
እጦት የጣ ራው ላይ ድንቅ ሥዕሎች እና ቅርጾች እየደበዘዙ
ናቸው::

በጣራው ውስጣዊ ገጽታ ከጣራው ጋር ተያይዘው ወደ ታች
በወረዱ አራት መዓዝን በሆኑ ሁለት የእንጨት ገመዶች የተን
ጠለጠሉ ሰንቁዎች አሉ:: ከሁለቱ በአንደኛው ገመድ ላይ የተ
ንጠለጠሉትን ሰንቁዎች በ1986 ዓም አካባቢ ሌቦች የወሰዷ
ቸው ሲሆን ቶሉ እንዳይታወቅ ተመሳሳይ ነገር ተክተውበት
ነበር::

ውሳጣዊውን ክፍል ስታዩ በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች ዘጠና
አርባ አምስት እና አንድ መቶ ሰማንያ ዲግሪዎችን ጠብቀው
የጣራውን ክበብ፣ የዓምዶቹን መዓዝን እና የመስኮቶችን ቅርጽ
ለመሥራት የተጠቀሙበት የጂኦሜትሪ ጥበብ ምን ይሆን?
ምናለ ሕንፃውን እንዳገኘነው ሁሉ ጥበቡንም አብረን ባገኘው
ያሰኛችኋል:: ለመሆኑ ይህንን ሕንፃ ከማነፃቸው በፊት ዲዛይ
ኑን በምን ሠሩት? ጣራውን ሲያንፁ የተጠቀሙበት የመደ
ገፊያ እና የኮንክሪት ጥበብስ ምን ይሆን?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤተ መቅደሱ ውስጥ ሁለት ጥንታውያን የእንጨት ሳጥኖች ይገኛሉ:: ዛሬ ዛሬ ለዕቃ ማስቀመጫነት በሚጠቀሙባቸው እነ ዚህ ሳጥኖች ላይ የሚታየው ቅርጻ ቅርጽ እና በሕንፃው ጣራ ላይ የሚታየው ቅርጻ ቅርጽ ተመሳሳይነት አለው:: እንደ እኔ ግምት ከሆነ እነዚህ ሳጥኖች የሕንፃው ንድፍ የተቀመጠባቸው ሳጥኖች ይመስሉኛል:: ጠቢቡ ሕንፃውን ሲያንፀው ምናልባት በእንጨቱ ላይ የሠራውን ዲዛይን እየተከተለ ይሆናል::

ከቤተ መቅደሱ ጎን ያለው፣ ዛሬ በዕቃ ቤትነት የሚያገለግለው እና ይምርሃነ ክርስቶስ በቤተ መንግሥትነት ይጠቀምበት ነበር የሚባለው ሕንፃ ግን እጅግ ተጎድቷል:: ሌላው ቀርቶ አቧራ ውን እንኳን በዘመናዊው የአቧራ መጥረጊያ ማሽን በአንድ ቀን ማስለቀቅ በተቻለ ነበር:: በዚሁ ከቀጠለ ከአሥር ዓመታት በኋላ የምናገኘው አይመስለኝም::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF



ይምርሃነ ክርስቶስ በ939 ዓም አካባቢ ተወልዶ በ1036
አካባቢ ያረፈ የዛግዌ ሥርወ መንግሥት ንጉሥ ነው።
ሠው በ996 ዓም አካባቢ ሲሆን ቤተ መቅደሱን
በ1018 ዓም አካባቢ መሆኑ ይነገራል። የላሊበላ አብያተ
ደስ ተጠናቀቁበት ከሚባለው ዘመን 1193 ዓም ጋር
ያየው ቢያንስ የሰባ ዐመት ቅድሚያ አለው ማለት ይቻላል



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ይምርሃነ ክርስቶስን የሥነ ሕንፃ፣ የአርክቴክቸር እና የአርኪ
ዖሎጂ ባለሞያዎች ሊጎበኙት ለዛሬው ሥራችን የሚጠቅሙም
ሀገራዊ ጥበብ ሊሸምቱበት ይገባል ባይ ነኝ፡፡ የባለሞያዎችን
ጥናት እና ምላሽ የሚፈልጉ አያሌ ጥበቦች የፈሰሰበት ሕንፃ
ነው፡፡ በተለይም ቦታው ዋሻ ውስጥ በመሆኑ እና ከተራራ ግር
ጌም በመደበቁ ከብዙዎቹ የእርስ በርስ ጦርነቶች ተርፎ ታሪ
ኩን እንደያዘ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ከአካባቢው የተሻሉ መረጃ
ዎችን ይሰጣል ባይ ነኝ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለአካባቢው ታሪክ እና ቅርስ ትኩረት በመ
ስጠት መንገዱን ለማሠራት፣ አካባቢውን ለመጠበቅ፤ ለማስተ
ዋወቅ እና ለመከባከብ የክልሉ ባሕል እና ቱሪዝም የሰጠው
ትኩረት የሚደነቅ ነው፡፡



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ሯጭ እና አሯሯጭ

***በዘመናዊው*** የሩጫ ዓለም ፈጣን ሰዓት እና ሪከርድ መ
የተመልካቾችን ልብና የሚማርኩ እና የሩጫ አዘጋጆችን
ረትም የሚስቡ ሆነዋል:: በዚህም የተነሣ ለፈጣን ሯጮች
ለሪከርድ አሻሻዮች የሚሰጠው ሽልማት እየጨመረ፣ ሪከ
መስበርም ካለፉት ዓመታት ይልቅ እየተዘወተረ መጥቷል::

ለሩጫው መፍጠን እና ለሪከርዱ መስበር አስተዋጽዖ ካላ
ነገሮች አንደኛዎቹ አሯሯጮች ናቸው:: እነዚህ አሯሯ
ከሯጮቹ ጋር አብረው ጀምረው ዙሩን በማክረርና አት
ቹን ወደፊት በመሳብ ሩጫው በተሻለ ሰዓት እንዲካሄድ
ርጋሉ:: የእነርሱ ተልዕኮ የተወሰነላቸውን ያህል መጠን በ
ደበላቸው ፍጥነት በመሮጥ አትሌቶቹን ወደ ፊት በ
ከሳቡ በኋላ መውጣት ነው:: ሩጫውን መጨረስ አይ
ባቸውም::

ከእነዚህ ለየት ያለ አሉታዊ ተልዕኮ ያላቸው አሯሯ
ደግሞ በማንኛውም የኛ ሕይወት ውስጥ ይገኛሉ::

በአንዳንድ ውይይት ላይ እንኳን አሯሯጮችን አላ
ውም:: የሌለ ርእሰ ጉዳይ እና መከራከርያ ይዘው ገብ
ሰምቻለሁ፣ ፀውቀዋለሁ፣ ርግጠኛ ነኝ፣ በኔ ይሁንባችሁ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሩን ሁሉ ካከረሩት በኋላ ከውይይቱ ውስጥ ሳጥ ብለው የሚወጡ አሯሯጮች አሉ:: በጉዳዩ ላይ በቂ ዕውቀት ያላቸው ይመስል፣ ወይንም ደግሞ ተገቢ መረጃ የጨበጡ ይመስል በኃይለ ቃል ላይ ኃይለ ቃል፣ በሃሳብ ላይ ሃሳብ፣ በነገር ላይ ነገር እየጨመሩ፣ የውይይቱን ዙር ካከረሩ በኋላ ሌሎቹ በጉዳዩ ተስበው በውይይቱ ሩጫ ላይ ማከረራቸውን ሲያዩ፣ ሳጥ ብለው ይወጡና፣ ከተናጋሪነት ወደ አድማጭነት ታጠቅ ሳጥ ብለው ይዘዋወራሉ:: የተናገሩት እውነት መስሎት እነርሱን ተከትሎ ሲዉዉህ የነበረው ሁሉ ራሱን ያሳሰበው ዙር ላይ ተካርሮ ያገኘዋል:: እነዚያው ዙሩን ሲያካርሩ የነበሩትም ነገር ዓለሙን ሁሉ ረስተውት መልሰው አስታራቂ እና ሽምጋይ ሆነው ቁጭ ይላሉ::

በስብሰባው ላይ ከረር ያለ ነገር ሲነሣ ማስተዋል ያስፈልጋል፤ ሰውዬው ሯጭ ነው አሯሯጭ? የሚለውን ለመለየት እንዲቻል:: ነገርዬውን ወደ አንድ ጽንፍ ወስዶ እያከረረ፣ እኛም እውነት መስሎን የመጣው ይምጣ ብለን የልባችንን ስናወጣ፣ እጅሬ ሳጥ ብሎ ከሩጫው ሊወጣ ይችላልኮ:: ምናልባትም የርሱ ዓላማ እነማን የዚህ ሃሳብ አቀንቃኞች ናቸው? የሚለውን ዙሩን አክርሮ ማውጣጣት ሊሆን ይችላልኮ::

የትዳር አሯሯጮችስ ገጥመዋችሁ አያውቁም:: ባል እና ሚስቱ በሚችሉት ፍጥነት በራሳቸው ሰዓት የራሳቸውን ሪከ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ርድ በራሳቸው ፀትም ለማሻሻል ሲሮጡ፤ እያገባው ገብቶ ሳ ዱህ ሆነህ ነው የምትኖረው፣ እንዲህ ሆነሽ ነው የምትኖ ረው፣ እንዲህ አያደርግልሽም፣ እንዲህ አታደርግልህም፣ ሆነህ እንዲህ ሆነህ ትኖራለህ፣ ለመሆኑ አንቺ ሚስት ነሽ ወይስ አገልጋይ፣ እኛ እያለንማ እንዲህ አትሆንም/አትሆኚም/ ባል ከሆንህ ነህ/ ከሆንሽ ነሽ/ እንዲች ነገር ማድረግ አለብህ ማድረግ አለብሽ» እያለ የሰላማዊውን ትዳር ዙር አክርር ሮሮ፣ ባል እና ሚስቱ ከተለመደው ፍጥነት ወጥተው በጉ መካረር ሲጀምሩ ሜዳውን ለእነርሱ ጥሎ ላጥ ብሎ ያ ጣል:: አለሁ ሲል የነበረውና ነገር እያቀባበለ ዙሩን ሲያከ ረው የነበረው ሰውዬ ከጀግኑነት ወደ ተመልካችነት ይሸጋ ራል:: እነዚያው ባል እና ሚስቱ ግን «የት ይደርሳል የተባ ጥኝ ቁራ ተገኘ» እንደ ሚባለው፣ የት ይደርሳሉ ሲባሉ፣ ዙሩ ከርሮባቸው፤ እንኳንስ የትዳርን ሜዳልያ ሊያገኙ ቀርቶ፣ መሮ ጥም ይሳናቸውና እንጉል ሆነው ይቀራሉ::

ሰውዬው ሚስቱ ገበያ ሄዳ እርሱ የተሰጣ እህል ይጠብቃ ለ:: በመካከል ጓደኛው ሊጠይቀው ይመጣል:: «ምን እየ ራህ ነው? ለምን ወጣ ብለን አንድ ሁለት አንልም» ይለዋል፡ ባልም «አይ ባለቤቴ ገበያ ስለሄደች የተሰጣ እህል እየጠበቅ ነው» ይለዋል:: ጓደኛው በነገሩ ተናድዶ «እንዴት የወንድነ ክብር ታስደፍራለህ፣ ብለህ ብለህ ደግሞ የተሰጣ እህል ጠባ ሆንክ፣ ምነው አንተን ባደረገኝ፤ እንዲህ ታዋርደህ? የት



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሻልሃል፣ አሁን አንተ ባል ነህ ወይስ አሽከር» እያለ ልቡን ያንሟሙው ጀመር:: ባልም አስቦት የማያውቀውን ሁሉ ማሰብ ጀመረ::

«ምን ላድርግ ኑሮ ነው» አለው ባል:: «ቢሆንስ መኖር እን ደዚህ ነው እንዴ! ለምን አፍንጫዋ ላይ አትወረውር ላትም፤ አንተ ወንድ ሁን እንጂ ሚስት እንደሆነ አገሩን ሁሉ ሞልቶታል:: እንዲህ ሆነህ ከምትኖር ወዲያ ፍታትና ለኛም ላንተም የምትሆን አግባ::» እያለ ዙሩን ያከርርበት ገባ:: ባልም ልቡም እየሞቀ፣ ንዴትም እየተሰማው፣ ኑሮውንም እያ ማረረ፣ በሚስቱም ላይ ቂም እየያዘ ሄደ::

ጓደኛው አሁንም አሁንም እየደጋገመ «ወይኔ! ምነው እኔ በሆ ንኩ ኖሮ አሳያት ነበር» እያለ የተቀመጠበትን መደብ በቡጢ ይደበድባል:: ከገበያ መጥታ፣ በጓሮ በር ገብታ ይህንን ሁሉ ተደብቃ ትሰማ የነበረች ሚስት ፍልሟን ይዛ በድንገት ከች አለችና «እህ፣ አንተ ብትሆን ምን ታደርግ ነበር?» ብላ ጓደ ኛውን ስታፋጥጠው፣ እየተንቀጠቀጠ «እኔ ብሆንማ

*ለቆሞ ለቆሞ ወንዷቱ ጀግናይቱ*

*ለመከሸ ነይልኝ ሳይጀምር ሌሊቱ*

እያልኩ እየዘፈንኩ እህሉን ደኅና አድርጌ እጠብቅ ነበር» ብሎ ከከረረው ዙር በጊዜ ወጣ ይባላል::

ይኼው ስንቱን የሀገሬን ነጋዴ ከንግዱ ዓለም ያስወጡትኮ አሯሯጮቹ ናቸው:: የዕቃ ውን ዋጋ ካመጡበት በታች ይተ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ምንኛ፣ የገባውን ዋጋ ከዕቃው ዋጋ በላይ ይሰቅሉትና፣ ዕቃ እንደ እህል ተዘርቶ ይበቅል ይመስል ለየቸርቻሪው ያለ ሃሳብ በዱቤ ይበትኑትና፣ ለአሥር ሳንቲም ዕቃ የመቶ ብር ማስታወቂያ ያስነግሩና፣ የገበያውን ዙር ያለ መጠን ያከርሩታል። ደገኛው ነጋዴ ሀገር አማን ነው ብሎ በዚያው በለመደው ፍጥነት ዙሩን ለመጨረስ ሲሮጥ አጅሬዎቹ የሰዓቱን መንገድ በደቂቃ፣ የደቂቃውን መንገድ በሰከንድ አድርገው ይጠብቁትና ግራ ያጋቡታል።

ያን ጊዜ ጥቂቶች ብቻ አሯሯጮቹን ተከትለው ከሩጫው ዓለም ሳለመውጣት ሲሉ ብቻ ያለ ዐቅማቸው በከረረው ዙር ውስጥ ይፈተለካሉ። እንደሚያከስራቸው፣ እንደማያዋጣቸው እያወቁት የዋጋውን ሪከርድ ለመስበር ይታገላሉ። በዚህ መካከል አሯሯጮቹ ከገበያው ሩጫ በድንገት አቋርጠው ይወጣሉ። የዕቃው ዋጋ ቀንሷል፤ ያለ ሃሳብ በየቦታው ተበትኗል። ገበያውም ጥንቡን ጥሏል። በዚህ የተነሣ ለስንት መዓርግ የሚጠበቀው ነጋዴ ሁሉ እንኳን ለሜዳልያ ለሰርተፊኬትም ሳይበቃ ታሪኩ ተበላሽቶ ይቀራል።

ኧረ ምን ነጋዴውን ብቻ ተጋቢውን ሁሉ ልቡን አውልቀውት የቀሩት አሯሯጮች አይደሉ እንዴ። እነርሱ እንደሆን ማግባት እንጂ ትዳር መያዝ ዓላማቸው አይደለም። ደግሞም ሥርት እንጂ ጋብቻው አያስጨንቃቸውም። የሠርግን ወጭ፣ የድግስን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ዓይነት፣ የአዳራሽን ኪራይ፣ የመኪናን ዓይነት እና ኪራይ፣ የኬኩን መጠን እና ዋጋ፣ የሰሐን እና የብርጭቆን ዓይነት እና ዋጋ፣ የሠርግ ካርድ እና የከረሜላን ዋጋ እንኳን ሳይቀር፣ ዙሩን አክርረው አክርረው ይሄው ሰማይ ሰቀሉት። ምስኪን የሀገሬ ሰው በአሁኑ ጊዜ ሠርግን በፊልም እንጂ በአካል እንዳ ያገኘው አድርገውታል። «ሠርግ እና ሞት አንድ ነው»፣ ለምን ድነው ቢሉ፣ ሁለቱም ያስፈራሉና፣ የሚል ትርጓሜ አሰሰጥተ ውታል።

በተለይማ ከውጭ ሀገር እየመጡ እዚህ ሀገራችን የሚጋቡ ወገ ኖች ዋና አሯሯጮች እየሆኑ ነው። እንዴው ለመሆኑ ሀብ ታም ገለው ነው ወይስ ሠርተው ነው ገንዘቡን ያገኙት? ነጋ ዴው ከጠየቃቸው በላይ ዋጋ እየሰጡ፣ በነጻ እናገኘው የነበረ ውን ሁሉ ገንዘብ እየከፈሉ፣ የድግሱን ሪከርድ ሰባብረውት ሄዱ። በአትሌቲክሱ ለወንዶች እና ለሴቶች ተብሎ ሪከርዱ እንደ ሚነገረው ሁሉ፣ የዲያስፖራ እና የሀገር ቤት የሠርግ ሪከርድ ተለያየ። ዘመድ አዝማድ እንኳን ብሩ ከውጭ ይመ ጣል ከተባለ እህሉን ሳይከራከር ነው የሚገዛው። የሠርጉን ምንዛሪ እንደ ዶላሩ ይጨምረዋል።

የሚገርመው ነገር እነዚህ ሰዎች የሠርግን ዙር እንዲህ አክር ረው አክርረው እነርሱ ላጥ ብለው መውጣታቸው ነው። ወይ ከትዳሩ አለያም ከሕይወት ሩጫው ከመሥመሩ ሳይደርሱ ነው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙዎቹ የሚጠፉት፡፡ በጋብቻ «መሣ» ላይ ለመሮጥ ዝግጁ የነበረውን ሁሉ ተጋቢ «እይ እኔ በዚህ መጠን ልሮጥ አልችልም» እንዲል አድርገው ተስፋ ካስቆረጡ በኋላ፤ እነርሱ ራሳቸው ገና የሠርጉ ቋንጣ እንኳን ሳይደርቅ፤ የትዳርን ዙር አቋርጠውት ይወጣሉ፤ ያለበለዚያም ደግሞ ሕይወት እንደ ሠርጉ ዕለት አልመቻቸው ብሎ የተመደበላቸውን ሰዓት ጨርሰው ከድሉት ኑሮ አቋርጠው ቁጭ ይላሉ፡፡ ይኼው የሠርጉ ሬሌይ ተቀንባብሮ ከመላኩ በፊት የስንቶቹ የመለያየት ዜና ከውጭ ይመጣ የለ፡፡

እንዲው የዲያስፖራው ነገርማ ከተነሣ እነርሱኮ የሠርጉን ሩጫ ብቻ አይደለም እያከረሩ ያስቸገሩን፡፡ ለማዕድ ቤት እንኳን የማትበቃ መሬት በሚሊዮን ብር እየገዙ፤ እንዲው ደኅና ቀለም የተቀባ ከመሰላቸው ቤቱን በሺ ብሮች እየተከራዩ የቤትን ዋጋ ከሚሊዮን እንዳይወርድ ሰቅለውት የቀሩ እነርሱ ናቸው፡፡ የሚገርመው ደግሞ «አንድ ዲያስፖራ የሰቀለውን ሃምሳ ያገር ቤት ሰው አያወርደውም»፡፡ አሁን ይሄው ዕድሜ ለአሜሪካ ኢኮኖሚ፤ የዲያስፖራው አሯሯጮች ዙሩን አክረው አክርረው፤ ገንዘብ የለም ብለው አቋርጠው ወጡና ይህንን የተሰቀለ የዋጋ ሪከርድ ማን ይድፈረው? ሪል እስቴቱም፣ ሊዙም፤ የቤት ኪራዩም፤ የቤት ሽያጩም ዙሩ ከረረብን፡፡ እንኳን ለተራው ዜጋ ቀርቶ በፊት ሪከርድ ይሰብሩ የነበሩትም እንደ አውራ ዶሮው «ከዐቅሜ በላይ ነው» እያሉ ናቸው፡፡



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በፖለቲካውም መስክም ቢሆን ብዙ አሯሯጮች አሉ:: ዙሩን እንደማይጨርሱት ያውቁታል:: የእነርሱ ሥራ ማሯሯጥ እና ዙሩን ማክረር ነው:: ታድያ የዋሑ ሯጭ ዐቅሙን ሳይመዝን ሪከርድ እሰብራለሁ ብሎ እንዲሁ ሲከተላቸው፣ አሯሯጭ መሆናቸውን ያላወቀ ተመልካችም እንዴት ያሉ ጀግኖች ናቸው፣ መደገፍ እነዚህን ነው እያለ፣ ከመጀመርያው ጀምረው ዙሩን የሚመሩ እያለ ሲጠብቃቸው:: ሚናቸውን ባለማወቅም በኋላ ጭብጨባ ሲያጅባቸው፣ የቴሌቭዥኑ መስኮትም ፊት መቅደማቸውን እና ዙር ማክረራቸውን አይቶ እየደጋገመ ሲያሳያቸው፣ በመካከል ፈትለክ ብለው ይወጡና ሁሉንም ጉድ ይሠሩታል:: በሜዳው ላይ እነዚያው አትሌቶቹ ብቻ ይቀራሉ::

አንደኛ ወጡ ብሎ ሲያጨበጭብላቸው የነበረው ደጋፊም ዕጢው ዱብ ይላል:: ርግጥ ነው አንዳንዶቹም ለአሯሯጭነት ገብ ተው የሩጫውን ሁኔታ ካጠኑ በኋላ በዚያው ለሚዳልያ የሚወዳደሩ አሉ::

እናም በአሁኑ ዘመን ገዝም ብሎ መሮጥ ብቻ አያስፈልግም:: ሯጮችን ከአሯሯጮች መለየት ካልተቻለ፣ እግር በእግር ብቻ ተከትለን ስንፈተለክ፣ ላጥ ብለው ጥለውን ይወጡና ጉድ ይሠሩናል::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# የጃፓን ዕንቁራሪቶች

**እነሆ ጃፓኖች** እንዲህ ይተርታሉ::

በአንድ ወቅት አሳካ እና ኪዮቶ በተባሉ የጃፓን ከተሞች ውስጥ እርስ በርሳቸው ሳይተዋወቁ የሚኖሩ ሁለት ዕንቁራሪቶች ነበሩ:: እነዚህ ዕንቁራሪቶች ከሚኖሩባቸው ከተሞች በተቀር ሌላ ቦታ አያውቁም:: አንድ ቀን በድንገት ሁለቱም የሚኖሩበት ቦታ መረራቸው፣ ሰለቻቸው:: በሁለቱም ልብና ከሚኖሩበት ቦታ ወጥተው በአቅራቢያቸው የሚገኘውን ሌላ የተሻለ ከተማ የመጎብኘት ሃሳብ መጣባቸው:: ሳይመካከሩ እንዲሁ በድንገት ሁለቱም መንገድ ጀመሩ:: አንዱ ከአሳካ ወደ ኪዮቶ፣ ሌላው ደግሞ ከኪዮቶ ወደ አሳካ::

መንገዱ እንዲህ የዋዛ አልነበረም:: እጅግ አያሌ ቀናትን የሚፈጅ፣ ተጨማሪ ስንቅ የማይሸመትበት እና አድካሚም ነበር:: ከሁሉም የሚብሰው ደግሞ በመካከል አስቸጋሪ እና ረዥም የሆነ ተራራ መገኘቱ ነው:: ነገር ግን ሁለቱም ተስፋ ባለመቁረጥ ተጓዙ:: እያረፉ እየተነሡም ያንን ተራራ ከሁለት አቅጣጫ ተያያዙት:: በድንገት ጫፉ ላይ ሲደርሱ አንደኛው ሌላኛውን ተመለከተ:: ሁለቱም ተገረሙም፣ ደነገጡም:: አንዱ የሌላውን መኖር ፈጽሞ አያውቅም ነበርና::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ወዲያው ተቃቅፈው ከተሳሳሙ በኋላ አንዱ እሳካን ሌላው ደግሞ ኪዮቶን ለማየት በመንዝ ላይ መሆናቸውን ተጨዋወቱ:: ከተረፈቻቸው ስንቅ አውጥተው አብረው በሉ:: ግራ ላይ ጋደም ብለውም ጥቂት ዕረፍት አደረጉ:: በመካከል የእሳካው ዕንቁራሪት «እንዲህ ትናንሾች መሆናችን ምንኛ መጥፎ ዕድል ነው» አለ:: የኪዮቶው ዕንቁራሪት ደንግጦ «ምን ተገፃህ» አለው:: የእሳካውም «ትልልቆች ብንሆን ኖሮ እዚህ ተራራ ጫፍ ቆመን የምንሄድባቸውን ከተሞች በሩቁ ማየት እንችል ነበር፡ ከዚያም በእውነት እዚያ ድረስ መሄዳችን ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም የሚለውን ሳንለፋ እንወስን ነበር» አለው::

ያን ጊዜ የኪዮቶው ዕንቁራሪት ራሱን ከነቀነቀ በኋላ «ቀላል ነውኮ፤ ትልቅ መሆንም አያስፈልግም፤ ምን መሰለህ ሁለታችንም በኋለኛው እግራችን ብቻ እንቆማለን፤ በፊት እግራችን ደግሞ እንያያዛለን፤ ከዚያም ፊታችንን ወደ ምንሄድበት ከተማ አዙረን ማየት እንችላለን» አለ:: በሃሳቡ ሁለቱም ተደሰቱ::

ከዚያም ሁለቱም በኋላ እግራቸው ቆመው አንገታቸውን ቀና አደረጉና በፊት እግራቸው ተያያዙ:: አፍንጫቸውን ወደሚሄዱበት አቅጣጫ አዞሩት:: እናም ከተማው ታያቸው:: «ይገርማል» አለ የኪዮቶው ዕንቁራሪት:: እሳካ ከኪዮቶ ምንም አትለይም:: ፎቆቿ፣ መንገዶቿ፣ መብራቶቿ፣ መኪኖቿ ሁሉም



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ያው ናቸው:: ተመሳሳይ የሆነ ነገር ለማየትማ እዚያ ጉብ
ምን አለፉኝ፣ ለውጥ ላይመጣ ድካሙ ምንድን ነው፣ የኔ ዘሬ
ድረስ መሄድ ምን ለውጥ ያመጣል፣ ዙሮ ዙሮ እሳካ እንደ
ሆነች ኪዮቶ ማለት ናት:: ስሟ ብቻ ነው የተለወጠው» አለ።
የእሳካውም ተመሳሳይ ሃሳብ ነበር የሰነዘረው «ልክ ነህ ኪዮቶ
እንደ እሳካ ናት፣ ምንም ለውጥ የላትም:: ለካስ የትም ቢ
ቢሄዱ ተመሳሳይ ነገር ነው የሚገኘው፣ መንገደኞች ግን
ብለው ነው ለካ የሚደክሙት:: ትርፉ ድካም መሆኑን ባውቅ
ኖሮ ይህንን ሁሉ አልደክምም ነበር::» አለ::

የሁለቱን ሁኔታ እያየች ትስቅ የነበረች ጉንዳን «እናንተ ዕን
ራሪቶች ሞኞች ናችሁ ልበል፣ ወደፊት ብትቆሙም የምታ
ዩትኮ ወደ ኋላ ነው:: ስለ ቆማችሁ ብቻ ይታያችኋል ማለት
አይደለም:: ዋናው መቆማችሁ ሳይሆን አቋቋማችሁ፣ ማየታ
ችሁ ሳይሆን አስተያየታችሁ ነው» አለቻቸው:: ዕንቁራሪቶ
ቹም ተናድደው «ዞር በይ አንቺ ጉንዳን፣ አንቺ ከኛ በምን
በልጠሽ ነው፣ ድሮም እናንተ ጉንዳኖች የዕንቁራሪቶችን በ
አትመኙም፣ እኛ ያየነውን ለማየት ዕንቁራሪት መሆን ያስፈ
ልጋል» አሉና አባረሯት:: ከዚያም ከተያያዙበት ተላቀቁ እና
ማሩ ላይ አረፍ አሉ::

ሁለቱም ያልገባቸው ነገር ቢኖር፣ የኋላ እግራቸውን ዘርግተው
የፊት እግራቸውን ወደ ላይ አድርገው ሲቆሙ፣ አፍንጫቸ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ፊት ዓይኖቻቸው ግን ወደ ኋላ እንደሚያይ ነው:: ሁለቱም ወደ ፊት ያዩ መስላቸው እንጂ ያዩት የመጡበትን ከተማ ነው:: ሁለቱም የተስማሙት ተመሳይ ነገር አይተው አይደለም:: የሚያውቁትን ነገር ስላዩ ብቻ ነው:: ሁለቱም ከዚህ በፊት ቆመው በማያውቁበት ሁኔታ፣ ቆመው በማያውቁበት ቦታ ላይ ስለ ቆሙ አዲስ ነገር ያዩ መስላቸው እንጂ ያዩት የድሮውን ነው::

ካገቡ በኋላ ትዳር ከላጤነት ያለው ልዩነት አልታያቸው ብሎ፤ «ላጤነት ለብቻ፣ ትዳር ሁለት ሆኖ መኖር» የሆነባቸው፤ ያኔም እበላለሁ ዛሬም እበላለሁ፤ ያኔም እፈትራለሁ፣ ዛሬም እፈትራለሁ፣ ያኔም ምሳዬን ሆቴል እበላ ነበር፤ ዛሬም እበላለሁ፣ ያኔም እመሻለሁ፤ ዛሬም እመሻለሁ፤ ያኔም የቤት ወጭ እሰጣለሁ፤ ዛሬም እሰጣለሁ:: ትዳር ምንድን ነው? እያሉ የሚጠይቁ አሉ:: ርግጥ ነው አዲስ ቤት ገብተዋል:: እንደ ሁለቱ እንቁራሪቶች ተያይዘው ባል እና ሚስቱ ሆነው ቆመዋል፤ ትዳር በሚባለው ተራራም ላይ እስቸጋሪውን ውጣ ውረድ ሁሉ አልፈው ደርሰዋል፤ ግን ምናልባት ላጤነትን እያዩ ይሆን እንዴ ስለ ትዳር የሚናገሩት? እሳካም እንደ ኪዮቶ ነው፤ ኪዮቶም እንደ እሳካ ናት አሉ የጃፓን ሰንቁ ራሪቶች::

ከስንት ትግል በኋላ ተራራው ላይ መድረስ ብቻውን አዲስ ነገር ለማየት አያበቃም:: አዲስ ነገር የማየት ፍላጎት



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ብቻውንም አዲስ ነገር አያሳይም:: ተደጋግሮ ቀን ብሎ መቆም ብቻውንም አዲስ ራእይ አያመጣም:: እንዴት ነገ ወዴት ነው የምታየው? የሚለውም ወሳኝ ነገር ነው::

አንድ ሰው አዲስ ፓርቲ ስለ መሠረተ፣ በአዲስ ስም ስለ ተጠራ እና አዲስ ጽሕፈት ቤት ከፍቶ በዚያ ቦታ ላይ ስለ ቆመ ብቻ አዲስ ርእይ ሊኖረው አይችልም:: አዲስ ስም ይዘው፣ አዲስ አደረጃጀት መሥርተው፣ አዲስ ደንብ ቀር ጸው፣ አዲስ ዘመን ላይ ቆመው እነርሱ ግን አሁንም የጥንቱን ብቻ የሚያዩ ስንት የጃጁን ሰንቁራሪቶች አሉን? ምን አዲስ ነገር መጣ፣ እኛ የማናውቀው፣ እኛ ያላልነው፣ እኛ ያልሠራ ነው፣ እኛ ያልወጠወጥነው፣ ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ? ሁሉም ያው ነው፤ ብለው የሚያስቡ አሳካን እያዩ ስለ ኪዮቶ የሚናገ ስንት ዘመዶች አሉን መሰላችሁ::

አሁንም ከዚህ ሁሉ ልፋት በኋላ፤ ይህንን ሁሉ ተራራ ከወጣ ችሁም በኋላ፣ ከተደጋገፋችሁም በኋላ፤ አንድነት እና ግንባ ከመሠረታችሁም በኋላ ቢሆን እያያችሁ ያላችሁት የድሮውን ከተማ ነው:: አስተሳሰባችሁ፣ አካሄዳችሁ፣ አመለካከታችሁ ርእዮታችሁ፣ አደረጃጀታችሁ ያው እንደመጣችሁበት ያለ ነው» የሚል ካጋጠማችሁ ደግሞ አለመሆኑን ከማስረዳት ይልቅ «አንተ ጉንዳን እኛ ደግሞ ሰንቁራሪት ስለ ሆንን ነው:: የምናየውን ለማየት ሰንቁራሪት መሆን ያስፈልጋል» ይላሉ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በየመሥሪያ ቤቱ አሠራርን ለማሻሻል፣ ደንበኛን ለማስደሰት፣ ሥራን ለማቀላጠፍ፣ ገንዘብ እና ጊዜን ለመቆጠብ፣ እየተባለ ስንት ማሻሻያ ይጠናል፣ይተገበራል፣ ሥልጠና ይሰጣል፣ ይመከራል፣ ይገመገማል:: አንድ ሰሞን ሆይ ሆይታ ይሠመና ከዚያ በኋላ ደንበኛውም፣ ሠራተኛውም፣ ኃላፊውም «ምን አዲስ ነገር አለው ያው ነው» ማለት ይጀምራሉ:: ዝም ብለን ነው የለፋነው፣ የደከምነው፣ የሠለጠንነው፣ ኪዮቶ እንደ ሆነች እንደ እሳካ ናት፤ ምንም ለውጥ ላናመጣ ትርፉ ድካም ነው ይላሉ::

ችግሩ የሚመነጨው ግን ከሥርዓቱ፣ ከሥልጠናው ወይንም ደግሞ ከአተገባበሩ ብቻ አይደለም:: አዲስ የደመወዝ ደረጃ ስለ ተሠራ፣ አዲስ ኃላፊ ስለ ተመደበ፣ አዲስ ቢሮ ስለ ተቀየረ፣ አዳዲስ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች ስለተገዙ፣ አዳዲስ ስያሜዎች ስለመጡ፣ አዳዲስ የቢሮ ስሞች ስለ ተለጠፉ ብቻ ለውጥ የሚመጣ መስለን:: እኛም በየስብሰባው «እጅ ለእጅ ተያይዘን እና ተደጋግፈን ለውጥ እናመጣለን» እያልን ቃል ገባን:: ስንደጋገፍ ግን የመጣንበትን እንጂ የምንሄድበትን ማየት አልቻልንም:: ስለ ቆምን ብቻ የምናይ፣ የጥናቱን እና የምደባውን ተራራ ስለ ወጣነው ብቻ ማየት የምንችል መሰለን፣ ወደ ፊት ዞረን ቀመናል፣ ዓይኖቻችን ግን አሁንም የጥንቱን ብቻ ነው የሚያዩት::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በየአካባቢው፣ በየእምነት ተቋማቱ፣ በየመንደሩ ችግር እን ታለን፣ ለውጥ እናመጣለን፣ አሁን ካለንበት የተሻለ ዓለም አለ ያለን፣ እናሳይማለን ብለው የተነሡ ማኅበራት ነበሩ። እነዚ ማኅበራት ብዙ ታግለዋል። አስቸጋሪ ተራራዎችን ወጥተዋል። በተለያየ ቦታ ሆነው በየልባቸው በነበረ ስሜት ተነሣሥተው ጉዞ ጀምረዋል። ከዚያም ታሪክ እያገናኛቸው ተራራው ላይ ተገናኝተዋል። ታናሽነታቸውን ለማሸነፍ እና ታላቅ ሥራ ለመ ሥራት ሲሉም እርስ በርሳቸው ተደጋግፈዋል።

በመጨረሻ ግን አዲስ ራእይ ከማየት ይልቅ የመጡበትን ብቻ የሚያዩ፣ አዘውትረውም ስለመጡበት ታሪክ ብቻ የሚተርኩ ሆነዋል። የተሻለ ሀገር እንደርሳለን ብለው መጥተው፣ እንኳን የተሻለ ሀገር ሊደርሱ ኪዮቶ ናት እያሉ አሁንም የመጡበትን አሳካ ብቻ ነው የሚያዩት። አዲስ አሠራር፣ አዲስ ሃሳብ፣ አዲስ ርእይ፣ አዲስ ፍልስፍና፣ አዲስ ስሜት፣ አዲስ አመለ ካከት፣ አዲስ ጥበብ ማየት ትተው «ለካስ ቢሄዱ ቢሄዱ የው ነው» ወደ ሚለው የጃፓን ዕንቁራሪቶች ሃሳብ ተመልሰዋል። የኖሩበት ከተማ ስልችቷቸው ወጥተው፣ መልሰው ግን ያን እንዳዩት ዕንቁራሪቶች እናስተካክለዋለን፣ እናሻሽለዋለን፣ እና መዋለን፣ የተሻለ እናደርገዋለን ብለው የተቹትን አሠራር እና አካሄድ መልሰው ደጋግመውታል። እንደ ጉንዳኗ «ተው እያ ችሁ ያሳችሁት ወደ ኋላ ነው፣ ወደ ኋላ ማየት ከጀመራችሁ ደግሞ የምትሄዱት ወደ ኋላ ነው።» የሚል ካጋጠማችሁ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ደግሞ «አይ ድሮም ጉንዳኖች ዕንቁራሪቶችን ስለማትወዱን ነው» የሚለውን የተለመደ መዝሙር ይዘምራሉ።

አንዳንድ ጊዜ ኢትዮጵያን ገነት ብቻ አድርገው የሚያዩ ሰዎች አሉ፤ በተቃራኒው ደግሞ ሲዖል ብቻ ሆና የምትታያ ቸውም አሉ። ለአንዳንዶቹ እንደ ቻይና ተመንድጋለች፤ ለሌ ሎቹ በጣም እንጨቅረር ወርዳለች፤ ለአንዳንዶቹ ሀገሪቱ ለሌ ሎች የዕድገት ምሳሌ ትሆናለች፤ ለሌሎቹ ደግሞ የውድቀት አርአያ ናት፤ ለአንዳንዶቹ ዴሞክራሲ የሰፈነባት ናት፤ ለሌ ሎቹ ደግሞ የዴሞክራሲ ጠበል ሲረጭ እርሷ አልነበረችም።

ሁለቱ ዕንቁራሪቶች ኪዮቶ እንደ ኦሳካ፤ ኦሳካም እንደ ኪዮቶ ናት ያሉት የሚያነፃጽሩበትን ከተማ አይተውት አይደለም። ስለ ኦሳካ የሚያወሩት ኪዮቶን፣ ስለ ኪዮቶም የሚያወሩት ኦሳካን እያዩ ነው። እናም ስለ ኢትዮጵያ የምንናገረው ቻይ ናን፣ ሲንጋፖርን፣ ሕንድን፣ አፍጋኒስታንን፣ ሰሜን ኮርያን፣ አሜሪካን እያየን ይሆን እንዴ። ዕንቁራሪቶቹ ሌላ ሀገር እያዩ ስለ ሌላ ሀገር ያወሩ ነበር። እኛስ ሌላ ሀገር እያየን ይሆን እንዴ ስለ ኢትዮጵያ የምናወራው። አንዳንዱ ሀገሪቱን በመኮ ነን ይስማማል፤ ሌላው ደግሞ ሀገሪቱን በማወደስ ይግባባል። ምናልባት ግን የሁለቱም መግባባት የመጣው እንደ ዕንቁራ ሪቶቹ ያንኑ የምናውቀውን በማየታችን ምክንያት ከሆነስ?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ባሎችም ያረግዛሉ

**ውጭ ሀገር** የሚኖር ሐበሻ ደመወዙን እንጂ ሥራውን ቢጠ
ይቁት አይወድም ይባላል:: እኛ በልማዳችን «ሥራ» ለሚ
ባለው ነገር የምንሰጠው ትርጉም ትንሽ ሐዲዱን ሳይስት አይ
ቀርም:: መሐንዲስ፣ ሐኪም፣ ፓይለት፣ መምህር፣ ነጋዴ፣
ወዘተ ካልተባሉ በቀር ስማቸውን መጥራት የምናፍርባቸው
ሥራዎች አሉ:: ታድያ እነዚህን ዓይነት ሥራዎች ላይ የተሠ
ማሩ የሀገሬ ልጆች ለሀገር ቤት ዘመዶቻቸው መናገር አይፈ
ልጉም:: ተረቡንም፣ ሐሜቱንም፣ ወሬውንም መቋቋምና ማ
መን ያቅታቸዋል::

እናም እዚህ ካምፓላ ያገኘኋት አንዲት እኅቴን በዚሁ የሐበ
ልማድ መሠረት ስራ ስቸር በዙርያ ጥምጥም ምን እንደም
ትሠራ እንሣሀባት:: እርሷም ፈጠን ብላ «እዚህ ሀገርኮ ተምሬ
ነርስ ሆንኩልህ» አለችኝ:: እንዲህ ደፈር እና ፈጠን ብላ ከተ
ናገረች የምትኮራበት ነገር ላይ ተሠማርታለች ማለት ነው
አልኩና እኔም ለመቀጠል ተደፋፈርኩ::

«አንቺ በቃ ድሮ ጀምሮ የምትመኘውን ሕክምና አሳደገ
አሳደሽ ካምፓላ ላይ ደረስሽበት?» አልኳት:: ሳቅ አለችና



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«ለንገሩ አሁን በሕክምና ሞያ ላይ አልሠራም» አለችኝ።

«ደግሞ ሌላ ዓይነት ነርስነት መጣ እንዴ?» ስል ጠየቅኋት።

«የኔ ሥራ ባሎች እንዲያረግዙ መርዳት ነው» ብላ ሳቋን ለቀቀችው። የተናገረችውም፣ አሳሳቋም እኔን መልስ አሳቀኝ። አሁን የተናገረችውን ነገር የህገሬ እናቶች ቢሰሙት ስምንተኛው ሺ መግባቱን ለማወቅ የሚጠቅማቸው ምልክት ይሆናል ብዬ ገመትኩ። በዚህ በምዕራቡ ዓለም የማይመጣ ነገር የለም። ደግሞ የሚገርመው እነ ኡጋንዳ ሥልጣኔ መስሏቸው የዚያን ነገር እንዳለ መገልበጣቸው ነው። እያልኩ አሰብኩ።

«ቆይ እንጂ፣ ለመሆኑ እንዴት አድርገው ነው ባሎች የሚያረግዙት? ያውስ ደግሞ በእናንት ርዳታ ነው እንዴ የሚያረግዙት? እረ ለመሆኑ እንዴትስ አድርጋችሁ ነው የምትረዷቸው?» የጥያቄ እሩምታ አከታተልኩባት።

«እናቴም ስነግራት እንዳንተ ነበር ያለችኝ። እንዲያውም እርሷ በይ የኔ ልጅ ቶሎ ብለሽ ከዚህ ዓይነት ነገር ውጭ፣ ወይ ስምንተኛው ሺ ነበር ያለችው» አለችና መልሳ ሳቀች።

«እይውልህ በምዕራቡ ዓለም ሚስቶች ብቻ ሳይሆኑ ባሎችም ያረግዛሉ» ብላ ስትጀምር



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«እኮ እንዴት እንዴት አድርገው? እንደገና ማግበን አለ ብተው ነው? ለመሆኑ ምን ምን አድርገው ያረግዛሉ? አልኳት በአግራሞት::

«የባሎች እና የሚስቶች ርግዝና ይለያያል» አለች:: «እስ አሁን በተለመደው መንገድ ሚስት ብቻዋን ነበር የምታረግ ዘው:: የወንዶቹ ተግባር ሚስት እንድታረግዝ ማድረግ ብቻ ነበር:: አሁን አሁን ግን ርግዝናው የተሳካ፣ የተቃና እና ለእና ቲቱም ሙሉ ጤንነት እና ክብካቤ እንድታገኝ ባልም አብሮ ማርገዝ አለበት እየተባለ ነው»

«ወይ ግሩም! እኔስ ባል ማርገዝ አለበት ብለው ማሰባቸው አይደለም የገረመኝ:: እንዴት አድርጎ ማርገዝ ይቻላል የሚ ለው ነው ዕንቆቅልሽ የሆነብኝ» አልኳት::

«የባል እና የሚስት ርግዝና ይለያያል:: የሚስት አካላዊ ርግ ዝና ነው፤ የባል ደግሞ ማኀበራዊ እና ሥነ ልቡናዊ ርግዝና ነው:: እንዲት ሴት በርግዝና ወቅት በሰውነቷ ውስጥ በሚከ ለውጦች፣ የፍላጎት ለውጦች፣ የአመጋገብ ለውጦች፣ የአመለ ካከት ለውጦች የአኗኗር ለውጦች አሉ:: እነዚህ ለውጦች የሚ ያስከትሉት አዎንታዊ እና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ደግሞ ሴቲ ቱን ብቻ ሳይሆን ወንዱንም፣ ቤተሰቡንም ይነኩታል::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሴቲቱ እነዚህን ነገሮች በራስዋ ላይ ሲደርሱ ወይንም ደግሞ ከደረሱባት በኋላም ቢሆን በልምድ ታውቃቸዋለች። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ሴቶች ከሴቶች ጋር የሚያደርጉት ውይይት ወንዶች ከወንዶች ጋርም ሆነ ወንዶች ከሴቶች ጋር ከሚያደርጉት የተሻለ ነው።

«ወንዶች ሚስቶቻቸው ሲያረግዙ የሚከተለውን አካላዊ፣ ሥነ ልቡናዊ እና ማኅበራዊ ለውጥ ባለመረዳታቸው የተነካ ጊዜውን እንደ ችግር ወቅት የማየት፣ ሚስቶቻቸውን ከመርዳት ይልቅ የማማረር፣ ሁኔታውን የተሻለ ለማድረግ አስተዋጽዖ ከማድረግ ይልቅ በጠብ እና በጭቅጭቅ የማባባስ ሁኔታ ይታይባቸዋል። ከርግዝናው በኋላ ለሚመጣው ልጅም ሴቶቹ እንጂ ወንዶቹ ዝግጅት አያደርጉም። ለዚህ መፍትሔው ወንዶቹም እንደ ሴቶቹ እንዲያረግዙ ማድረግ ነው» አለችና አሁንም ሳቀች።

«ሃሳባችሁክ ገብቶኛል፤ እንዴት? ነው ጥያቄዬ።»

«እንዴት ማለት ጥሩ ትላለች አክስቴ። ለመሆኑ ርግዝና ማለት ምን ማለት ነው? በርግዝና ውስጥ ምን ምን ነገሮች ይፈጠራሉ? ከእርግዝና እስከ ወሊድ ድረስ በሴቲቱ ላይ የሚመጡት ለውጦች ምን ምን ናቸው? እያንዳንዱ ቀን፣ ሳምንት፣ ወር ምን ታስከትላለች? እናቲቱስ ምን ያስፈልጋታል? በመጨረሻስ ወሊድ ማለት ምን ማለት ነው? በወሊድ ጊዜ የወንዶች ድርሻ ምን መሆን አለበት? ለሚወለደው ልጅ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀድሞ መደረግ ያለበት ዝግጅት ምን ምን ናቸው? የሚሉትን ወንዶች እንዲሠለጥኑ እናደርጋለን።

«ትምህርት በተጨማሪ ቤተ ሙከራዎች አሉ። ለውጦቹን በቪዲዮ፣ በናሙና፣ በተግባር ልምምድ ያጠናሉ። ሆስፒታል ይሄዳሉ፤ የተለያዩ ርጉዝ ሴቶች እየመጡ ያጋጠማቸውን ነገር ገለጣ ያደርጋሉ። የኛ ተግባር ባሎች ያረገዙ ያህል እንዲሰማቸው ማድረግ ነው። ርግዝናውን እነርሱም እንዲሰማቸው፣ ስሜቱንም እንዲጋሩት ማድረግ ነው።

«ለምሳሌ በሚስቶቻቸው ላይ የመነጫነጭ፣ የማኩረፍ፣ ቶሎ የመቆጣት፣ በስሜት ስሱ የመሆን ነገሮች ሲያጋጥሟቸው ምን ማድረግ አለባቸው? ለመሆኑስ እነዚህ ነገሮች ለምን ይመጣሉ? ምን ምን ነገሮች በርጉዝ ሴቶች ሕይወት ላይ ሲለወጡ እነዚህ ይመጣሉ? በእያንዳንዱ ሳምንት ምን ይጠበቃል? ምን ለውጥስ ይኖራል? የአመጋገብ እና የአኗኗር ለውጥ ሲያጋጥም ቀድመው ምን ማድረግ አለባቸው? ይህንን ሁኔታ እናሠለጥናቸዋለን።

«የሚገርምህ ነገር ብዙ ወንዶች የሚስቶቻቸውን የርግዝና ጠባይ የሚረዱት ከተጋቡ በኋላ ነው። የጠባይ መለወጥ፣ የነገሮች መቀያየራቸው እንግዳ ነገር ይሆንባቸውና የአመል መቀየር አድርገው ይቆጥሩታል። ከዚያም ጠብ ይነሣል። ከጠብ በኋላ ነው ይህ ነገር በእርግዝና ምክንያት የተከሰተ መሆኑን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚረዱት፡፡ የሥለጠኑት ባሎች ግን አስተድመው ይገነዘቡታል፡፡ እንዲያውም ሚስቶቻቸውን ይህ ዓይነት ነገር ሊከሰት እንደሚችል ቀድመው ይነግሯቸዋል፡፡ ሲከሰትም ምክንያቱን ይረዱታል፡፡

«የርግዝና ወቅት ረዥም ጊዜ ነው፡፡ ዘጠኝ ወር ማለትኮ ዓመት ሊሞላ ምን ቀረው፡፡ ይህንን የሚያህል ጊዜ በየሰዓቱ በሰውነትህ ውስጥ ለውጥ እየተካሄደ፣ የሰው ልጅን «የመፍጠር» ያህል ኃላፊነት ተሸክመህ ብቻህን መጓዝ ከባድ ነው፡፡ ልጅ ከተወለደ በኋላ የሚያመጣው ደስታ ልዩ እና የማትጠብቀው በመሆኑ እንጂ የእርግዝና እና የምጥ ሰዓት ሲታሰብ ደግሞ የምትወልድ ሴት አትገኝም ነበር፡፡

«ይህንን ጊዜ ግን ልዩ የደስታ ትዝታ ጥሎ እንዲያልፍ ማድረግ ይቻላል፡፡ ለዚህ ደግሞ አንዱ ትልቁ መፍትሔ ቅድም እንዳልኩህ ባሎችም ከሚስቶች ጋር አብረው እንዲያረግዙ ማድረግ ነው፡፡ የርጉዝ ሴቶች የጠባይ መለዋወጥ በቤተሰቡ ውስጥ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያስከትለው ሁሉ ባሎች ተባባሪዎች፣ ሥልጡኖች እና በዘመኑ ቋንቋ የገባቸው ከሆኑ ግን የሳቅ እና የደስታ ጊዜ ማድረግ ይችላሉ፡፡

«ለምሳሌ እንዴት?» አልኳት፡፡

«ለምሳሌ በእርግዝና ወቅት የሚመጡ ነገሮችን ቀድሞ ዐውቆ በእኩል መነጋገር ትልቁ ነገር ነው፡፡ ሚስት የተሻለ ትወቀው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እንጂ ርግዝናዋን በተመለከተ ባልዋም በሚገባ ያወቀ ከሆነ ውይይታቸው የመረዳዳት ይሆናል። አብዛኛውን ጊዜ ግን ሚስት እስረጅ ባል ሰሚ ነው የሚሆኑት። ባል ለሚስቱ ምን ነገር መቼ መግዛት እንዳለበት? ጠባይዋ ምን ሲሆን ምን ማድረግ እንዳለበት? በየትኛው ወር ምን ሊከሰት እንደሚ ችል ዐውቆ ምን ዝግጅት ማድረግ እንዳለበት ከሠለጠነ፤ ቤተ ሰቡን ደስተኛ ያደርገዋል።

«በተለይ ደግሞ በወሊድ ጊዜ አይተህ ከሆነ ብዙ ባሎች ከመ ጨነቅ ያለፈ ድርሻ የላቸውም። እስተዋጽዖ ከማድረግ ይልቅ ኮሪደር ላይ በመንቆራጠጥ ነው የውስጣቸውን ጭንቀት የሚገ ልጡት። እኛ ግን በዚህ ሥልጠና የወሊድ ጊዜ እና ሰዓት መቃረቡን በምን በምን ምልክቶች ማወቅ እንደሚችሉ፣ መቼ ወደ ሐኪም ቤት መውሰድ እንዳለባቸው፣ በርግዝና ወቅት የሚከሰቱ ድንገተኛ ነገሮች ምን እንደሆኑ? ድንገት ምጥ ቢይ ዛት ምን ዓይነት ርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው? እናሠለጥና ቸዋለን።

«እንዲት የወለደች ሴት ምን ምን ያስፈልጋታል? አሁን እኛ በባህላችን የመጣልንን ልምድ ተከትለን ነው ለአራስ ምግብ የምናዘጋጀው። ነገር ግን በወሊድ ምክንያት ደም ለፈሰሳት፣ ዐቅሟን ላሟጠጠች፣ ወይንም ደግሞ በልዩ ልዩ መንገድ ለተጎ ዱች ሴት ምን ምን ዓይነት ምግቦች ናቸው የሚያስፈልጓት



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚለውን በውቀን አይደለም የምንዘጋጀው። አንዱ በሥልጠና የምንነግራቸው ይኼንን ነው። እርሷ ይህንን ሥሩልኝ ከምትል ባልዋ እያሰበ ቢገዛላት፣ ከቻለም ቢሠራላት፣ ካልቻለም ቢያሠራላት ለእናቲቱ ከሚፈጥርላት የደስታ ስሜት በተጨማሪ ጤንነቷንም ይጠብቀዋል።

«እስኪ እንዴው አያድርገውና በወሊድ ጊዜ የእናቲቱ ሕይወት ቢያልፍስ? ምንም ልምድ ከሌለ ባል ምንድን ነው የሚያደርገው? እንዴትስ ነው ኃላፊነቱን የሚረከበው? እያምጣው ብለን ብቻ ነው እንዴ የምናልፈው? ግን ካመጣውስ እንዴት ይደፈጋል? ለዚህ ሁሉ አእምሮን ማዘጋጀት ያስፈልጋልኮ። እሺ ይህንን ተወው መቼም ዶሮ ፊት ፈንግል አይወራም። ግን እናቲቱ በከባድ ሁኔታ ብትታመምና የልጇን ኃላፊነት ለመወጣት ዐቅም ቢያንሳትስ? በዚህ ጊዜኮ ከባልዋ የተሻለ ሰው ሊኖር አይችልም። ሌሎች የቤተሰብ አባላት የማይገኙበት አጋጣሚ ይኖራል። በተለይ በውጭ ሀገር እናት አባት፣ እኅት ወንድም፣ ዘመድ ጎረቤት ብዙ ጊዜ አይገኙም፤ እና ምን ታደርጋለህ?

«ይህ ሁሉ እሺ ይቅር። ልጁ በጤና ተወለደ፤ እናቲቱም ጤና ናት። ነገር ግን በተለይ በውጪ ዓለም እንደ ልብህ የሥራ እረፍት አታገኝም። ልጆች ደግሞ ቢያንስ እስከ ሁለት ዓመት የቅርብ ክትትል ይፈልጋሉ። ለመሆኑ ስንት ባሎች ልጅ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በትክክል ሳይደቀቅ ማቀፍ፣ ልጅ ማጠብ፣ ሽንት ጨርቅ መቀየር፣ ምግብ መመገብ ይችላል?

«ብቻ ምን ልበልህ፣ ባል ከጾታው በቀር በስሜቱ ሁሉ እንዲያረግዝ አድርገን ነው የምናሠለጥነው። ሚስት ስትወልድ የሚመጣውን ፍትፍት እየበሉ፣ አጥሚት እየጠጡ አመልማሎ መስሎ መውጣት ብቻ አይደለም። አንዳንድ ጊዜኮ አራሷ ማን ኖቸው ኖቸው ትላለህ አይደል? ያረገዘች እርሷ የወፈረ ሌላ፤ አሁን ግን ፍትፍቱን አብሮ ለመብላት ርግዝናውንም መጋራት ያስፈልጋል እያልንልህ ነው» እንደ ልማዷ ከት ብላ ሳቀች።

እኔ ግን አልሳቅኩም። ያገሬ በሴቶች ቅዝ ብለውኛል።

ትምፓላ / ሌጋዊ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ተራራው

**እዚህ አሜሪካ** በየቦታው የሚዘዋወር ሰው ኢትዮጵያውያንን በተመለከተ ከሚሰማቸው ወሬዎች አንዱ በተበላ ገንዘብ ስለ ተገዙ እና ስለ ተከፈቱ ነገሮች ነው። «ይህ ጋዝ ማደያ እገሌ የተባለው የዚህ ፖለቲካ ፓርቲ አመራር ይህንን ያህል ብር ሰብስቦ የገዛው ነው፤ ይህ የሽያጭ መደብር እገሌ የተባለው የእገሌ ፓርቲ አስተባባሪ ገንዘብ ሰርቆ የከፈተው ነው። እገሌ ይህንን ያህል ሺ ዶላር ይዞ ጠፋ፣ እገሊት ይህንን ያህል ብር በባንክ አካውንቷ አስገብታ ጠፋች»። አብዛኞቹ ስማቸው የሚነሣ ሰዎች የታወቁ ፓርቲዎችን በመወከል እና በመምራት ስብሰባ ሲጠሩ፣ ገንዘብ ሲያሰባስቡ፣ ሰልፍ ሲያስተባብሩ የነበሩ ናቸው። እውነት ይሁን ውሸት እግዜር ይወቅ።

የዚህ ነገር ሲገርመኝ ደግሞ ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ አንድ የቤተ ክርስቲያን የቦርድ አባል ምእመናኑ ሳያውቁ ቤተ ክርስቲያኑን በባንክ አስይዞ ገንዘብ በመበደር ሲጠቀምበት በመገኘቱ በምእመናኑ ውሳኔ ከሥልጣን መነሣቱ ይወራ ጀመር። የተሻሉ ናቸው ብለን ከመረጥናቸው በኋላ እንዴት ከኛ የባሱ ሊሆኑ ቻሉ?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እነዚህ ነገሮች ናቸው አስቴር ካግ /ከካናዳ/ የላከችልኝን ቀጥሎ ያለውን ታሪክ እንዳስታውስ ያደረጉኝ።

አንድ የሊባኖስ መነኩሴ ከሰው ተለይቼ ለብቻዬ በምኖርበትን ቦታ አባክህ ምራኝ ብሎ እግዚአብሔርን ይለምነዋል። እግዚአብሔርም ወደ ሊባኖስ ተራራ ጫፍ ይወስደዋል። የተራራው ጫፍ ከአካባቢው በጣም የራቀ እና በአካባቢው ከመንደራቸው የራቁ እረኞች ብቻ የሚገኙበት ነው።

መነኩሴው በተራራው ጫፍ ላይ ለጥቂት ጊዜ እንደኖረ የብርዱ ወቅት ይመጣል። ቅዝቃዜው ከዐቅሙ በላይ ሲሆንበት ከተራራው ወርዶ እረኞችን ብርድ ልብስ ይለምናቸዋል። እነርሱም አንድ ብርድ ልብስ ይሰጡታል። የተወሰነ ጊዜ ከተጠቀመበት በኋላ ብርድ ልብሱን አይጦች ይበሉበታል። እንደ ገና ከተራራው ወርዶ እነዚያን እረኞች ሌላ ብርድ ልብስ ይለምናቸዋል። እረኞቹም ብርድ ልብሱን ከለገሱት በኋላ አይጦቹን ለመከላከል ድመት ማሳደግ የተሻለ መሆኑን ይመክሩትና አንዲት ድመት ይሰጡታል።

እንደተባለው ድመቷ ስለመጣች አይጦቹ ድራሻቸው ይጠፋል። እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ አይጥ እየበላች የነበረችው ድመት አይጦቹ ሲጠፉ የምትበላው አጣችና መራብ ጀመረች። ያን ጊዜ ያ መነኩሴ ወደ እረኞቹ መጥቶ ወተት ለመ ናቸው። እነርሱም ወተቱን ሰጡት። በየጊዜው እንደዚ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የተመለከቱት እረኞች አንዲት እየተመሳሰለ ሁሉት መለመኑን ሳም ከነ ጥጃዋ ወስዶ ቢያረባ መልካም መሆኑን መከረው አንዲት ላም ከነጥጃዋ አበረከቱለት፡፡ እንደ ተባለውም ላሟን ከነ ጥጃዋ ወስዶ ማርባት ጀመረ፡፡

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የአካባቢው ማር ደረቀና ላሟ ተራበች፡፡ መነኩሲውም ወደ እረኞቹ ወርዶ ለላሟ የሚበላ ነገር ጠየቃቸው፡፡ እረኞቹም ለብዙ ጊዜ የምትበላው እህል ከሰጡት በኋላ ደግመኛ ከመመላለስ የእህል ዘር ወስዶ ቢዘራ የተሻለ መሆኑን መከሩት፡፡ እንደ ተባለውም የእህሉን ዘር ዘርቶ እካ ባቢው በእርሻ የከበረ እንዲሆን አደረገው፡፡ ነገር ግን እህሉን ማጨድ፣ መውቃት እና ለክፉ ጊዜ ማስቀመጥ ስለሚያስፈልግ እንደገና ተመልሶ የእርሻ መሣርያ ለመናቸው፡፡ እነዚያ እረኞችም ሳይመረሩ ከየትም ፈልገው ሰጡት፡፡

እንዲህ እንዲህ እያለ የተራራው ጫፍ የዘመናዊ የከብት ርባታና የእርሻ መናኸርያ ሆነ፡፡ ብዙ ሰዎችም ያንን ዘመናዊ እርሻ በአድናቆት ለመጎብኘት ይመጡ ነበር፡፡

አንድ ቀን አንድ ሰው እርሻውን ለመጎብኘት መጣ፡፡ በመነኩሲው ሥራ መደነቁን ከገለጠ በኋላ መነኩሴው ያንን ሰው ወደ ቢሮው ወሰደው፡፡ ያም ጎብኝ ቢሮው ውስጥ እንደገባ «ግን ወደዚህ ቦታ ያመጣህ ለዚህ ነበር እንዴ?» ሲል ጠየቀው፡፡ ለካ ያ ሰው እግዚአብሔር ኖሯል፡፡



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ተራራው ከወጡ በኋላ ዓላማቸውን የቀየሩ ወይም ሌሎች ኅሪቤት ዓላማዎችን የፈጠሩ ስንት ናቸው?

ትጻር ተራራ ነው:: ከላጤነት፣ ከልቅነት ብሎም ሁሉ አማረሽ ከሚባለው ሜዳ ርቆ የሚኖርበት:: ብዙዎች ወደ ተራራው ሲወጡ ይምላሉ፣ ይገዘታሉ:: ከእንግዲ አልለይም፣ ካንተ ይንጥለኝ፣ ለትጻሬ ታማኝ እሆናለሁ፣ «ቢጭኑኝ አህያ ቢለጉሙኝ ፈረስ» እሆናለሁ፣ ይህንን እና ያንን እተቀለሁ፣ እንደው በጠቅላላው በሜዳው ላይ ያሉትን ነገሮች ላይፈጽሙ ይመኑናሉ:: ተራራው ላይ ከወጡ በኋላ ግን ያገቡበትን ምክንያት ይረሱታል:: አሁንም አሁንም ወደ ሜዳው እየወረዱ አንዳንድ ነገር መቀስ ይጀምራሉ:: ከዚያም የ«ትጻር ጠሉችን» ፕሮጀክት በትጻር ተራራ ላይ ሲያካሂዱት ይታያሉ::

ወደ ሥልጣን ተራራ ለሕዝብ ነጻነት እና እኩልነት፣ ፍትሕ እና መብት ለመታገል ብለው ከወጡ በኋላ ዓላማቸውን ቀይረው ወደ ምቾት እና ቅንጦት፣ ራስን ብቻ ወደ መጥቀም እና ወደ ሙስና፣ በዘመድ አዝማድ ወደ መሥራት እና በሥልጣን ወደ መባለግ የተዘዋወሩ ስንቶች ናቸው::

ያ መነኩሴ የዚህ ዓለምን ነገር ጠልቶ እና ተጠይፎ ከዚያ ለመራቅ ነበር ወደ ተራራው ጫፍ የወጣው:: ነገር ግን እርሱ ራሱ በባሰ ሁኔታ ገባበትና ዐረፈው:: ከኑ እገሌ እንኳ ላለን፣ ይህንን ወይንም ያንን ነገር እንቃወማለን፣ መክራን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ማቱን፣ ሰቆቃን እናስቀራለን፣ ጭቆናን እና በደልን እናስወግ ዳለን፣ እምባገነንነትን እና ኢዲሞክራሲያዊነትን እንጸየፋለን፣ ዘረኛነትን እና ኮሙኒዝምን እንዋጋለን ብለው ትግል ጀምረው ወደ ተራራው የወጡ ነበሩ።

ከተጸየፉት በላይ ኮሙኒስት፣ ከታገሉት በላይ እምባገ ነን፣ ከተቃወሙት በላይ ጨቋኝ፣ ካስወገዷቸው በላይ ኢዲሞ ክራሲያውያን ሆነው ከተገኙ ግን ምን ዋጋ አለው። ወደ ተራ ራው መውጣት ብቻ ቁም ነገር የለውም። በተራራው ላይ ምን ይሠራል? የሚለው ነው ቁም ነገሩ።

መንፈሳውያን ነን ብለው የሚያስቡ አያሌ ሰዎች ወደ ተራራው የወጡበት እና በተራራው ላይ እየሠሩ ያሉት ሥራ ተለያይቷል። ለፈጣሪያቸው ታምነው፣ የፈጣሪን ሥራ ለመሥ ራት እና ከሥጋዊ ጥቅም ለመራቅ ብለው ወደ መንፈሳዊው የሥልጣን ተራራ ከወጡ በኋላ በተራራው ግርጌ ካሉት ይልቅ ብሰው የተገኙ ይኖራሉ። የገንዘብ ፍቅርን፣ ዘረኛነትን፣ ማን አለብኝነትን፣ ከንቱ ውዳሴን፣ ክብር ፈላጊነትን ትተው እና ንቀው ተራራው ላይ የወጡ ሲመስለን እነርሱ ግን በተራራው ጫፍ ላይ እነዚህኑ ነገሮች ሰብስበው ከተገኙ ምኑን መነኑት።

ጳጳስ፣ መነኩሴ፣ ቄስ፣ ሰባኪ፣ ባሕታዊ፣ ፓስተር፣ መጋቢ፣ ካርዲናል፣ ቃዲ፣ ዑላማ፣ ሐጂ፣ ሼክ፣ ወዘተ ለመ ሆን ሲነሡ የነበራቸው ዓላማ፣ የተናገሩት እና ቃል የገቡት፣



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የተጸየፉት እና የተቃወሙት፣ የናቁት እና ያወገዙት ነገ
አሁን በተራራው ላይ ሲኖሩ ተከትሏቸው ካልመጣ በአ
ናቸው:: እኛን እታድርጉ የሚሉንን ነገር አንድ አንድ እያ
ከተራራው ወርደው እየወሰዱ የሚያደርጉት ከሆነ ግን መ
ርያውኑ ለምን ወደ ተራራው መውጣት አስፈለጋቸው?

መማር ወደ ተራራው መውጣት ይመስለን ነበር:: በ
ሜት መስከን፣ አመክዝኖ መፍረድ፣ ግራ ቀኝ አይቶ መወሰ
ተቃራኒን ተከራክሮ መርታት፣ ልዩነትን መቀበል፣ ጠባብ
ትን ማሸነፍ፣ ይመስለን ነበር:: የተማረ የምንለው ወገናች
ዘረኛነቱ፣ ጠባብነቱ፣ ስሜታዊነቱ፣ እኔ ያልኩት ብቻ ትክክ
ነው ማለቱ፣ ከሚፈልገው ሃሳብ በስተቀር ሌላ ለመስማት አለ
መፈለጉ፤ ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት የተጻፉ መጻሕፍት በዛ
ቋንቋ ለምን አልተጻፉም ብሎ በጠባብነት መሟገቱ፣ በር
ብሶ አየነው:: ወደ ተራራው ከወጣ በኋላ የወጣበትን ምክንያ
ረሳው::

በተራራው ላይ ጸሎቱ ለሌሎች ይተርፋል ሲባል እር
ራሱ ሌላ ጸሎተኛ እንዳስፈለገው መናኝ የተማረ የምንለ
የኮሌጅ ተማሪ በአመለካከቱ፣ በሚዛናዊነቱ፣ በመቻቻሉ፣ በ
ግር ፈችነቱ እና የተሻለች ሀገር ለመፍጠር ባለው ራእይ ለ
ሎች ይተርፋል ሲባል እርሱ ራሱ ሚዳው ላይ ካለት በ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠብዞ፤ ካልተማሩት በላይ ሚዛኑ ተናግቶ፤ ችግር ከመፍታት ይልቅ ችግር ፈጣሪ ሆኖ፣ ከመቻቻል ይልቅ ቂም ተያይዞ ተራራው ላይ አየነው:: ከማይጠሩ የባሱ ጠባብ ምሁራን፣ ከተራራው የባሱ ግልብ ልሂቃን፣ ተራራው ላይ የወጡበትን ምክንያት የረሱ ናቸው::

ዛሬ በየቦታው የጎሳ ግጭቶች፣ የዘር ጥላቻዎች፣ መከፋፈሎች እና መሻኮቶች ይታያሉ:: ወደ ተራራው ወጥተን አልነበረም እንዴ! እነዚህ ከተራራው ግርጌ የነበሩ ነገሮች እንዴት ሊመጡ ቻሉ:: ወደ ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ ወደ መቻቻል እና መከባበር፣ ሀገራዊ እና ሁሉን ዐቀፍ ወደሆነ አመለካከት ገና አልደረስንም ማለት ነው? ያ ዘመን አልፏል፡ ሌላ ዘመን መጥቷል፤ ከዓለም ተምረናል ብለን ወደ ተራራው ወጥተን አልነበረም:: ታድያ ቀድሞውኑ ወደ ተራራው አልወጣንም ወይስ እነዚህን ነገሮች አብረን ይዘናቸው ወጣን?

ያንን መነኩሴ እምላኩ «ለዚህ ነበር እንዴ ወደዚህ ቦታ ያመጣሁህ» እንዳለው ሁሉ «ለዚህ ነበር እንዴ የታገልነው» «ለዚህ ነበር እንዴ የተሠዋነው» «ለዚህ ነበር እንዴ መከራ የተቀበልነው» የሚሉ አያሌዎች አሉ::

ወደ ተራራው ከወጣን በኋላ መልሰን ስንከፋፈል፣ ሰላማን ጥም ስንራኩት፣ በገንዘብ እና በጥቅም ስንባላ፣ ቃል የገባነውን ለራሳችን እንኳን ማድረግ አቅቶን የጠላነውን እኛው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ስናደርገው የሚያዩ ወገኖች «ለዚህ ነበር እንዴ ያን ሁሉ
ያደረግነው፣ ወደዚህ ቦታ ያመጣናችሁ ለዚህ ነበር እንዴ?»
ማለታቸው የት ይቀራል::

ተለይቻለሁ፣ ይህንን እና ያንን እቃወማለሁ፣ ይህ እና
ያ አያስፈልገኝም፣ እያሉ መዘርዘር እና ወደ ተራራው መው
ጣት በጣም ቀላል ነው:: ከባዱ ነገር የጠላናቸውን፣ የተቃወ
ምናቸውን እና የታገልናቸውን ነገሮች እኛስ ወደ ተራራው
ላለመውሰዳችን ምን ዋስትና አለን? የሚለው ነው:: እነዚህ
ነገሮች ወደ ተራራው የሚሰበሰቡት በአንድ ጊዜ አይደለም::
አንዱ አንዱን እየተከተለ፣ ወይም እያስከተለ ቀስ በቀስ ነው::

ያ መነኩሴ በተራራው ላይ ጸንቶ መኖር አለመቻሉን
ሲያውቀው «አልቻልኩም» ብሎ ከተራራው መውረድ እና በ
ቅሙ መኖር ነበረበት:: ያደረገው ግን በተቃራኒው ነው:: ወደ
ተራራው መውጣት አንድ ነገር ነው:: በተራራው ላይ በዓላማ
ጸንቶ መኖር ደግሞ ሌላ ነገር::

በተራራው ላይ በዓላማ ለመኖር ጽንዐት እና ቆራጥነትን
የግድ ይጠይቃል:: ወደ ተራራው ስንወጣ በዚያው በወጣንበት
በዓላማ ጸንተን ለመኖር ከፈለግን ለወጣንበት ዓላማ መጋደል
አለብን:: ያለበለዚያ ግን አለመቻላችንን አረጋግጠን
ከተራራው መውረድ ነው::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ግን ብዙ ጊዜ አይታይም። ድመቷን፣ ላሟን፣ ጥጃዋን፣ እርሻውን፣ ማረሻውን፣ መውቂያውን፣ የወተት ማለቢያውን፣ የቅቤ ማንጠሪያውን፣ የእድብ መሰያውን፣ በተራራው ላይ እያየነው ነው። እነዚህን ነገሮች ለማድረግ ተራራ ላይ መውጣት አያስፈልገንም ነበር። እዚያው ሜዳው ላይ ይገኛሉና።

[illegible]

# ዘገዩ

*ይህ ቀን ፈጣሪ* በምድር ላይ ለመፍረድ ተመልሶ የሚመጣበት ቀን ነው እንበል::

መለከት ተነፋና የሰው ዘር ሁሉ ተሰበሰበ:: እናም የየሀገሩ ሰዎች አንድ ላይ እየሆኑ ከመቃብር ተነሥተው ወደ መንግሥት ሰማያት ለመግባት ተሰልፈው ይሄዳሉ:: የአንዳንዱ ሀገር ሰዎች ብዙ ናቸው:: የሌሎቹ ደግሞ በጣት ይቆጠራሉ:: ከአንዳንዱ ሀገርማ ጭራሽ ሰው የለበትም:: መለከቱ ይነፋል:: ሙታንም እየተነሡ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ:: የመጨረሻው ሰዓት አበቃና የመንግሥተ ሰማያት በር ተዘጋ::

ከሰዓታት በኋላ እጅግ ብዙ፣ ለቁጥር የሚታክቱ፣ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሰዎች ዘና ብለው መጡ:: ወደ መንግሥተ ሰማያት ተጉዘው በሩ ላይ ሲደርሱ ተዘግቷል:: ግራ ተጋቡ:: እስካሁን የእነርሱን ያህል ብዙ ሰዎች እንዳልገቡ ርግጠኞች ናቸው:: ታድያ ለምን በሩ ተዘጋ:: አንኳኩ:: ደጋግመው አንኳኩ::

ከብዙ ማንኳኳት በኋላ አንድ መልአክ መጣና በሩን ከፈተው:: ከበሩ ውጭ እጅግ ብዙ ሰዎች ነጫጭ ልብስ ለብሰው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

መቆሚያቸውን ተመለከተና «ምን ፈልጋችሁ ነው?» ሲል ጠየቃቸው፡፡

«እኛ ከኢትዮጵያ የመጣን ሰዎች ነን፤ ለመግባት ፈልገን ነው» ሲሉ መለሱለት፡፡

«እስካሁን የት ነበራችሁ፤ የመግቢያ ሰዓቱኮ አለፈ፤ በሩኮ ከተዘጋ ቆየ» አለና እየገረመው መለሰላቸው፡፡ «ምን ያስቸኩለናል፣ ቀስ ብለን እንደርሳለን ብለን እኮ ነው፤ ደግሞም ሦስት ሰዓት ብቻ ነው ያረፈድነው» አሉት፡፡

«እዚህኮ አንድ ደቂቃም ቢሆን ማርፈድ አይቻልም፤ እናንተ ግን ዘገያችሁ፤ እናም በሩ ተዘጋ»

«ምናለ አስተያየት ቢደረግልን» አሉት ኢትዮጵያውያኑ፡፡ «እንዴ ስንት ጊዜ ነው አስተያየት የሚደረግላችሁ፤ ታሪካችሁ ሁሉኮ በአስተያየት የተሞላ ነው» አለ መልአኩ፡፡

«አሁን ከኛ የበለጠ ሃይማኖተኛ ተገኝቶ ነው ሌሎችን አስገብታችሁ በሩን የዘጋችሁት፤ ድሮም ጨዋ ቀስ ብሎ ነው የሚመጣው» አለ አንድ ሽማግሌ፡፡

«ልክ ነው እናንተ ኢትዮጵያውያን ሃይማኖተኛ ናችሁ፤ ጨዋ ናችሁ፤ ይህንን ማንም ያውቅላችኋል፤ ግን ሰዓት እጃችሁ ላይ አሥራችኋል እንጂ ሰዓታችሁ አይቆጥርም፤ ጥሎሽ ላይ ሰዓት



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ካልተጣለ ብላችሁ የምትከረክሩ ጀግኖች ሠርጉ ላይ ግን
ዘግይታችሁ ነው የምትመጡት::

በሥልጣኔ መንገድ ከዓለም ቀድማችሁ ሮጣችሁ፤ በኋላ ግን
የት እንደሄዳችሁ አይታወቅም፤ ጥንቸል እና ዔሊ ሩጫ ተወ
ዳደሩና ጥንቸል እንደ ጥይት ተተኩሳ ዔሊን ቀድማት ሄደች::
መካከል ላይ ጥንቸል ዘወር ብትል ዔሊ እየተጎተተች ነው::
ይቺ ቀርፋፋማ መቼም አትቀድመኝም ብላ ትንሽ ለማረፍ
መስኩ ላይ ጋደም እንዳለች ዕንቅልፍ ወሰዳት:: ከዕንቅልፏ
የተነሣችው የጭብጨባ ድምጽ ስትሰማ ነው:: ነገሩ አስደንጋ
ጭ ነበር ዔሊ ሩጫውን ጨርሳ ገመዱን በጥሳ ገብታ
ለች:: ጥንቸልን በዔሊ ያስቀደማት መተኛቷ ነው:: እናንተ
ምኮ ተኛችሁ፤ ዘገያችሁ፤ ለመሆኑ ከአኩስም ሥልጣኔ በኋላ
የት ሄዳችሁ? ከላሊበላ ሥልጣኔ በኋላ የት ገባችሁ? ከጎንደር
ሥልጣኔ በኋላ የት ተሸሸጋችሁ? ይሄው ከኋላችሁ የተነሡ፣
የሚጠቅሱት ታሪክ፣ የሚያሳዩት ቅርስ፣ የሚያስጎበኙት ታሪ
ካዊ ሥፍራ የሌላቸው ስንት ሀገሮች ከኋላችሁ እየተነሡ ቀድ
መዋችሁ ሄዱ::

ችግራችሁን በጊዜ አታምኑ፤ ስንት ጥፋት ከጠፋ በኋላ
ሊመለስ ከማይችልበት ደረጃ ስትደርሱ ነው መሳሳታችሁ
የሚገባችሁ፤ በጊዜ አትወስኑ፣ ዝናቡ አልፎ መሬቱ ከደረቀ
በኋላ ነው ለመዝራት የምትወስኑት:: በጊዜ አትጨርሱ፡



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እስቲ በጊዜው ያለቀ የትኛው ፕሮጀክታችሁ ነው? እነ ላሊበላ በለት ፈልፍለው አሥራ አንድ ቤተ መቅደስ ለመሥራት ከፈጀባቸው ጊዜ በላይ ነው ኮንዶሚኒየም ለመሥራት የሚፈጅባችሁ::

የተበላሸ ለመጠገን እና ለማስጠገን እንኳን መዘግየት ለምዶባችሁ በውትፍትፍ ጨርቅ ስታሥሩ፣ በፕላስተር ስትለጥፉ፣ በሽቦ ስትጠቀልሉ ኖራችሁ ኖራችሁ፣ መጠገን ከማይችልበት ደረጃ ሲደርስ እኮ ነው ለጥገና የምትኳትኑት:: በአንድ መርፌ የሚድነው፣ በአንድ ክኒን የሚፈታውን በሽታ እስኪ ቆይ፣ ይቆል ይደር፣ እያላችሁ ስትዘገዩ እኮ ነው ካንሰር የምታደርጉት:: በጊዜ የሚያስረክብ ሞያተኛ በሌለበት ሀገር በጊዜ መኖር እንዴት ይቻላችኋል:: ለመሆኑ መቼ ነው ተሟልቶላችሁ ቀጠሮ የምታከብሩት፤ መቼስ ነው በጊዜ የምትደርሱት?

«በኛ ባህል ቀደም ቀደም ማለት ነውር ነው» አሉ አንዷ እናት::

«እኔ እንኳን ባህላችሁ አይመስለኝም:: ባህላችሁ ቢሆን ኖሮማ ባሕር አቋርጣችሁ ሀገር በማሰስ ከሌሎች አትቀድሙም ነበር፣ ታሪካችሁን በራሳችሁ ፊደል በመጻፍ ከሌሎች አትቀድሙም ነበር፣ በደረቅ እና በባሕር ላይ ንግድ አትቀድሙም ነበር:: በሥነ ጽሑፍ እና በሥነ ሕንፃ ከሌሎች አትቀድሙም ነበር:: ማርፈድ ባሕላችሁ ሳይሆን ያላወቃችሁትና ያልታከማችሁት



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በሽታችሁ ነው:: 'የቸኮለ አፍሶ ለቀመ፣ አስቀድሞ የበቀለን ጆሮ በኋላ የመጣ ቀንድ በለጠው፣ አደጋም አትበል ቀዳሚ ቀዳም ያደርግሃል ዳኛም በዳኛ፣ አስቀድሞ የበቀለን ማገ ወፍ ይጠረጥረዋል' እያላችሁ ሥነ ቃሎቻችሁ እንኳን መቅ ምን ሳይሆን መዘግየትን ነው የሚያበረታቱት::

አንድ ልጅ ከማኅበረሰባችሁ ከቀደመ፣ ፈጠን ፈጠን ካለ የበ ዓይን ይበላዋል፣ የምቀኛ ዓይን ይወጋዋል ብላችሁ ነው የምታስቡት:: በስብሰባችሁ እንኳን ቀድመው የመጡት ሳይሆን የዘዩት ናቸው የሚጠበቁት:: የመጡትን አክብራችሁ ከመጀመር ይልቅ በዘገዩት ምክንያት ስብሰባ ትበትናላችሁ:: የማያረፍድ ሙሽራ እንደ ዋልያ ብርቅ በሆነበት ሀገር፣ የማያረፍድ ሠርገኛ በሥዕለት በማይገኝበት ሀገር እየኖራችሁ ዛሬ በማይ ታችሁ ብትመጡ አይገርመኝም::

ስትቀጣጠሩ እንኳን እኮ 'ነገ እንገናኝ፣ ከሳምንት በኋላ ደውልልኝ፣ ማታ ብቅ በል፣ በኋላ ላግኝሽ፣ ከአንድ ወር በኋላ ላድርስልሽ' የምትባባሉ ጀግኖች እኮ ናችሁ:: ለመሆኑ ነገ ሃያ አራት ሰዓት፣ 1440 ደቂቃ፣ 86400 ሰከንድ መሆኑን አታውቁም? ወይስ ለእናንተ እነዚህ ሁሉ ትርጉም የላቸውም? ሳምንት ማለትስ ለእናንተ ምንድን ነው? 168 ሰዓታት ወይም 10080 ደቂቃ መሆኑን ረስታችሁታል? የእናንተ አባቶች አበቅቴ፣ መጥቅዕ፣ ዐውደ ፀሐይ፣ ዐውደ ወርኅ፣ ኬክሮስ እያሉ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘመን ሲቆጥሩ ዘመንን መጠቀምን አብረው አላስተማሯ ቸሁም እንዴ?

ለመሆኑ በብዙ ሰዎች ቤት እና ቢሮ የተሰቀሉ የግድግዳ ሰዐቶች ይሠራሉ? አንዳንዶቹ ለሥርግ ስጦታ እንደተሰጣቸው በቀሉት እንጂ ሰዓቱ በጃፓን ይቁጠር በአሜሪካ አይተውት አያውቁም:: የአንዳንዶቹም የሰዓቱ ባትሪ አልቆ የሰኮንድ መቁጠሪያው ባለበት እየረገጠ ጢቅ ጢቅ ሲል ይሄው ስንት ዓመቱ? ለሌሎችም የግድግዳው ሰዓት የቤት እና የቢሮ ማጌጫ ከመሆን ያለፈ ጥቅም የለውም:: እንደ እናንተ እኮ በጊዜ የቀለደ የለም::

ያረፈደውም አንድ ሰዓት ዘግይቶ ሲመጣ ይቅርታ እንኳን አይ ጠይቅም፤ በመዘግየቱ አይሰማውማ፤ ፈገግ እያለ ጆብዱ እንደ ሠራ ሰው ይቀላቀላል:: ከሁሉ የሚገርመው ግን ጠባቂው ሰው ነው:: ይመጣል ብሎ ከአንድ ሰዓት በላይ መጠበቁ:: ሁለቱም ስለለመዱት ምንም አይሰማቸውም:: ይሉኝታ እንጂ ጊዜ አያስ ጨንቃቸውማ::

«እና ያንን ሁሉ ጽድቅ ስንሠራ ኖረን ዛሬ ሦስት ሰዓት አረ ፈዳችሁ ተብሎ ልንከለከል» አንድ ወጣት እያዘነ ጠየቀ::

'የዘገየ ፍትሕ የቀረ ያህል ነው' ትሉ የለም እንዴ! አንድ ነገር እኮ ጥሩ መሆኑ፣ ጽድቅ መሆኑ፣ ጠቃሚ መሆኑ ብቻውን አይበቃም:: በጊዜ መድረሱ፣ በጊዜ መገኘቱም ወሳኝ ነው::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

'እኔ የምሞት ዛሬ ማታ፣ ግብስ የሚደርስ ለፍልሰታ' ብላችሁ ትተርቱ የለም እንዴ! ምን ማለታችሁ ነው? ግብሱ ለፍልሰታ ቢትረፈረፍ እኔ ዛሬ በጊዜው ካላገኘሁት ምን ያደርግልኛል ማለታችሁ አይደል:: መፈክሮቻችሁ እንኳን እኮ ስለ 'ነገ' እንጂ ስለ ዛሬ አይናገሩም:: ዓለም ዛሬ እየሠራ እናንተ ስለማትጨብጡት ነገ ትፎክራላችሁ:: 'ሶሻሊዝምን እንገነባለን፣ ኢትዮጵያን የዳቦ ቅርጫት እናደርጋለን፣ ዲሞክራሲን እናሰፍናለን፣ ሙስናን እናጠፋለን፣ ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ጋር እንደምራለን' መቼ? የሁሉም መልስ 'ነገ' የሚል ነው::

ለመሆኑ ጊዜ በሌላው ዓለም ሌት ከቀን ሲያጣድፉት እና በአፍጢሙ ሲደፉት ሲደርሱ፣ ለምን ሃያ አራት ሰዓት ብቻ ሆንክ ብለው መከራ ሲያሳዩት እንደ ምንም ብሎ የዓመት ፈቃድ ወስዶ ይዝናና የነበረው እናንተ ሀገር መሆኑን ታውቃላችሁ? እንዲያውም ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ደርሶ የኢሚግሬሽን መኮንኑ «ለምን ያህል ጊዜ ትቆያለህ» ብሎ ጊዜን ቢጠይቀው «ለአንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት ወር» ብሎ መለሰለት:: የኢሚግሬሽን መኮንኑም ገርሞት «ቁርጥ ያለውን ጊዜ ንገረኝ እንጂ.» ብሎ ጠየቀው:: ጊዜም «ቁርጥ ያለ ጊዜ የሚገርበት ሀገር ቢሆንማ ኖሮ እኔስ ለዕረፍት መች እመጣ ነበር» አለው አሉ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ጊዜ ወርቅ ነው እያላችሁ ነው የተታለላችሁት:: ጊዜ ከወር ቅም ይበልጣል:: ከወርቅ ጋርም አይመሳሰልም:: ምክንያቱም በጊዜ ተጠቅሞ ወርቅን መግዛት ይቻላል:: በወርቅ ተጠቅሞ ጊዜን መግዛት ግን አይቻልም:: ነገሩ እናንተ ስለ ጊዜ ማወቅ መቼ ቸገራችሁ፣ መጠቀም እንጂ::

«እና አሁን መፍትሔው ምንድን ነው?» አንድ ሰው ጠየቁ:: «አይ አባቴ አሁንማ ምን መፍትሔ አለው:: ያው ወደ ሲኦል መውረዳችሁ ነው:: ያንን ሁሉ ጽድቅ ሠርታችሁ፣ ጽድቁ ሳያን ሳችሁ ማርፈድ የሚባለው በሽታ ጉድ ሠራችሁ:: «የማያድሩ በት ቤት አያመሻሹበትም ትሉ አልነበረም እንዴ? እንዴት እናንተ በማያዛልቅ ልማድ ኖራችሁ?

እናንተኮ መዘግየት ምን ያህል አጥንታችሁ ድረስ እንደ ገባ ያወቅኩት 'ዘገየ' ብላችሁ ለልጆቻችሁ ስም ማውጣታችሁን የሰ ማሁ ጊዜ ነው:: 'አትቸኩል ትደርሳለህ' የሚል ዘፈን ማውጣ ታችሁን ያወቅኩ ዕለት ነው:: አስተውለህ ንዳ፣ ሕግ አክብረህ ንዳ፣ በተገቢው ፍጥነት አሽከርክር ይባላል እንጂ 'አትቸኩል ትደርሳለህ' እንዴት ይባላል:: መድረሱማ የት ይቀራል? መቼ ነው የሚደርሰው? የሚለውኮ ነው ወሳኙ:: አንድ ፊልሙኮ ሩጫ ውን መጨረሱ አይደለም ዋናው ነገር፣ ስንተኛ ሆኖ መቼ ጨረሰ? ነው ጥያቄው:: በስታዲዮም የነበረው ሰው ሁሉ ቤቱ ከገባ በኋላ ስታዲዮም ቢደርስ ምን ይጠቅመዋል? የጥበቃ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሠራተኞው 'ስትጨርስ ዘግተህ ና' ብሎ ቁልፍ ካላስተማረበት በቀር።

«ሴቱ ወጣቶቹ አዝናለሁ። እዚህ ይሉኝታ የለም። በጊዜው መጀ ረስ ነበረብኝ። ግን ዘገያችሁ። የማይድልዉ ሌማይ ለምኞ ጎዶችሁ። ከእሱን በኋላ ስማችሁ ይቀየራሉ።» አለና ፊታቸ ገልበጥ ገልበጥ አደረገ።

«ምን ተባለ» አለና አንድ ወጣት ጠየቀው።

«እኔ ዘንዶ» ትብላችሁ።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# የዶክተር ውሳኔ

አንድ የወታደር ሐኪም ነበር አሉ። የሚሠራው ጦር ግንባር ላይ ነው። ወታደሮች ሲቆስሉ እንዲታከሙ፣ ሲሞቱም እንዲቀበሩ መርምሮ የሚወስነው እርሱ ነበር። ያለ እርሱ ውሳኔ የሞቱትን መቅበር እና ቁስለኞችን ማሳከም፣ ታመምን የሚሉትንም ወደ ሆስፒታል መላክ አይቻልም ነበር።

አንድ ጊዜ ጦርነቱ በጣም ኃይለኛ ሆነና የሞተው እና የቆሰለው በዛ። እያንዳንዱን እየመረመረ ይኼ ሞቷልና ቅበሩት፣ ይህም ቆስሏልና አክሙት ማለቱ ለዚያ ሐኪም ከዐቅሙ በላይ ሆነ። በዚያ የጦር ግንባር ላይ ብቸኛው ሐኪም እርሱ ብቻ ነበርና ያንን ሁሉ ወታደር አንድ በአንድ እያየ መወሰን ከበደው። የጠላት ጦር እየገፋ፣ ሙትና ቁስለኛውም እየበዛ መጣ። ያም የወታደር ሐኪም ደከመው።

በመጨረሻ እያሌ ወታደሮች ወደ ወደቁበት ቦታ ሄደና አይቶ «እነዚህ በሙሉ የሞቱ ስለሆነ ይቀበሩ» ብሎ በጅምላ ወሰነ። የታዘዙት ቀባሪዎችም የወደቁትን እያነሡ መቅበር ጀመሩ። በመካከል ላይ አንድን ወታደር አንሥተው ሊቀብሩት ሲሉ «የት ልትወስዱኝ ነው?» ብሎ ጠየቃቸው። ቀባሪዎቹም «ልን ቀብርህ ነዋ» አሉት። «እንዴት በሕይወት እያለሁ ትቀብሩ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ኛላችሁ» ሲል ጠየቃቸው:: «አይ ዶክተሩ ሞተሃል ብሉናል መቀበር አለብህ» አሉና መለሱለት:: «እንዴ በሕይወት ሌን እያያችሁ፣ በዓይናችሁ እያረጋገጣችሁ፣ እያነጋገርኳችሁ እንዴት ሞተሃል ትሉኛላችሁ፡ ዶክተሩ ቢሳሳት እንኳን እናንተ አርሙት እንጂ» አለ ወታደሩ ገርሞት::

«እየሀ» አለው አንዱ ቀባሪ «ዋናው ነገር የኛ አለመሞትህን ማረጋገጥ ወይንም ያንተ አለሁ ማለት አይደለም፤ የዶክተሩ ውሳኔ ነው:: ዶክተሩ ሞተሃል ካለህ ሞተሃል፡ አለህ ካለህም አለህ፡ አንተ ከዶክተሩ ልትበልጥ አትችልም፤ እኛም የዶክተር መመሪያ ልናፈርስ አንችልም፣ የተመደብነው ያለውን እና የሞተውን እየመረመርን ልንለይ አይደለም፡ ወይንም ደግሞ ያለሞቱ ሰዎችን አቤቱታ ለመስማትም አይደለም:: የተመደብነው መመርያ ለማስፈጸም ነው:: ውሳኔ ለማስተግበር ነው:: እናም ሞተሃል ተብሎ ስለተወሰነ የግድ መቅበራችን ነው» ብሉ ነገሩን ወስደው ቀበሩት::

የዶክተር ውሳኔ:: ሀገር የሚገድል፣ ሀገርም ሲገድል የኖረ ሀገርም እየገደለ ያለ::

በመጀመርያ ያ ሁሉ ጦርነት በሚደረግበት ቦታ፤ ሙት እና ቁስለኛ በሚበዛበት ቦታ፡ አንድ ሐኪም ብቻ የሺዎችን ሕይወት እንዲወስን መደረጉ ነው ችግሩ:: ሞተሃል፣ አልሞትክም፣ ታመሐል አልታመምክም ብሎ የሚወስነው ዶክተር



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ በሆነበት ቦታ:: የሰዎች ህልውና በአንድ ሐኪም ብቻ በሚወሰንበት፣ የእርሱ ትጋት እና ድካመት፣ የርሱ ደግነት እና ክፋት፣ የርሱ ሰውቀት እና ማይምነት፣ በብቸኛነት የሰዎችን ሕይወት በሚወሰንበት ቦታ፣ ይህንን መሰሉ ታሪክ መፈጠሩ አይገርምም::

ሁለተኛው ችግር ደግሞ ሌሎቹ ሰዎች የማሰቢያ አእምሮ፣ የማስተዋያ ኅሊና፣ የመመርመርያ ልቡና የሌላቸው ይመስል፣ ቲዎሪ ከነባራዊው ጉዳይ፣ መመርያም ከእውነታው ይበልጥ ይመስል፣ ትእዛዝ እና መመርያ፣ ውሳኔ እና መግለጫ ለማስፈጸም ብቻ መቀመጣቸው ነው:: ለምን? እንዴት? ትክክል ነው ወይ? እንደገና መመርመር አለበት ወይ? ብሎ የሚጠይቅ ኅሊና ሲጠፋ፣ «ከላይ የወረደ ሁሉ ትክክል ነው» የሚል እምነት ሲሰፋ፣ እለሁ ማለት፣ መተንፈስ እና መንቀሳቀስ፣ የደም ዝውውር እና የሕዋሳት ንቅናቄ ብቻ መኖርን ሊያመለክት አይችልም::

ዶክተሩ አድገናል ካሉ አድገናል፣ አላደግንም ካሉ አላደግንም:: አሽንፈናል ካሉ አሽንፈናል፤ አላሸነፍንም ካሉም አላሸነፍንም:: ከታች ያሉትም ያንኑ ከመፈጸም እና ከማስፈጸም በቀር አእምሯቸውን አይጠቀሙብትም:: ይኼው «አንድምታ» የሚለውን ቃል ባለሥልጣናቱ «እንድምታ» ብለው ተሳስተው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለተናገሩት የዶክተር ውሳኔ ሆነና ማጼ.ያውም፣ ምሁሩም፣ ደራሲውም ይናገረው የለ?

ለምሳሌ «ሙስና» የሚለው የግእዝ ቃል «ኮራፕሽን» ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል መተርጎሚያ ውሏል:: በሃሳብ ይመሳሰሉ:: በጎጃም ገበሬ ዘንድ ግን

**የደረቷ ቅላት የአንገቷ ሙስና**

**እንኳን ያፈቀረን ሙት ያስነሣል ገና**

የሚል ሥነ ቃል አለ:: ታድያ የዚያ አካባቢ ሕዝብ «ሙስና» የሚለው ቃል «ውበት፣ ቁንጅና» ማለት ነው ብሎ ቢከራከር መመርያ ማስከ፣ ሕግ አፈረስከ፣ ዶክተሩን ተቃወምክ ነው የሚባለው ወይስ ለካስ ያልታየ ነገር አለ ብሎ የሚቀበለው አለ?

በፖለቲካው ዘንድ ብቻ ሳይሆን በዕውቀቱ መስክም እገሌ የተባለ የምዕራብ ታሪክ ፀሞቂ፣ የሥነ ልቡና ሊቅ፣ የፍልስፍና ምሁር፣ የአርኪዎሎጂ መርማሪ፣ የባሕል ባለሞያ አንድ ጊዜ ከተናገረ እርሱን ተከትሎ ማስተጋባት፣ እና የርሱን መጽሐፍ እየጠቀሱ መከራከር እንጂ ሊሳሳት ይችላል፣ ያላወቀው ነገር ሊኖር ይችላል፣ ደግሞም እኔም ከርሱ የተሻለ ሳውቅ እችላለሁ ብሎ የሚያስብ ያለ አይመስልም::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሃምሳ ዓመታት በፊት ወደ ጣሊያን ተጉዞ ፓስታ እያበላ እዚያ ሁለት ዓመት የቆየ መምህር ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ስለ ምግብ ሲያስተምር «ምግብ ማለት ከሱፐር ማርኬት የሚገዛ፣ የሚቀቀል፣ ስጎ የሚጨመርበት፣ ከዚያም በሹካ የሚበላ ማለት ነው» አለና ተማሪዎቹን አስተማረ።

ከዚያም ተማሪዎቹን አንድ ነገር ጠየቀ «እንጀራ ከሱፐር ማርኬት ይገዛል» «አይገዛም» አሉት። «እንጀራ ይቀቀላል» «አይቀቀልም» «ስጎ ይጨመርበታል» «አይጨመርበትም» «በሹካ ይበላል» «አይበላም» «እንግዲያውማ እንጀራ ምግብ አይደለም ማለት ነው» አላቸው ይባላል። ለርሱ እንጀራ የፓስታን መመዘኛ እስካላሟላ ድረስ ምግብ አይደለም። ምክንያቱም የዶክተሩን ውሳኔ የሚሽረው የለማ።

ለምን እንጀራ በፓስታ መመዘኛ ይመዘናል? ለምን ለእንጀራ የራሱ መመዘኛ አይኖረውም? ለመሆኑስ የጣሊያኑ መምሬ እንጀራን ያውቁት ነበር? ብሎ መጠየቅ አያስፈልገውም። የርሱ ድርሻ የዶክተሩን ውሳኔ ማስፈጸም ነውና።

ዛሬ ዛሬ ስለ ሀገራችን የሚነገሩ ነገሮች በአብዛኛው ምዕራብ ቀየድ የሆኑት በዚህ ምክንያት ይመስለኛል። የኢትዮጵያውያን ተረቶች በአውሮፓ ተረቶች መመዘኛ ነው የሚመዘኑት፣ ሥነ ቃሎቻችንም በአውሮፓ ሥነ ቃል መመዘኛ ነው የሚተነትኑት። ለምን ኢትዮጵያውያን በራሳቸው መመዘኛ አይታ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍያም? ኢትዮጵያውያን ለራሳቸው ባህል እና ወግ፣ ታሪክ እና ኑሮ እንዲስማማ፣ ችግራቸውን እንዲፈታ እና ሕይወታቸውን እንዲያበለጽግ ሲሉ እነዚህን ነገሮች ሠሯቸው እንጂ ከአውሮፓ እና አሜሪካ ጋር ለመመሳሰን ብለው አይደለም። ነገር ግን በአንድ ወቅት ይህንን ጥናት የጀመሩት አውሮፓውያን፣ በሚያውቁት በራሳቸው መመዘኛ እየመዘኑ ምሁሮቻችንን ስላስተማሯቸው፣ እነርሱም የጾከተሩን ውሳኔ ተከትለው ከመንዝ በቀር ለምን? ብለው መጠየቅ አልፈለጉም።

ከዚህም በላይ የሚከፋው ደግሞ የአፍሪካውያን ታሪክ እና ፍልስፍና ተጽፎ ካላየነው በቀር «ታሪክ እና ፍልስፍና» ለመባል አይችልም እያልን መሮከራችን ነው። አፍሪካውያን ከብዙ ሺ ዓመታት በፊት ጀምረው ታሪካቸውን፣ ባሕላቸውን እና ፍልስፍናቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፉ የኖሩት በትውፊት ነው። ይህም ትውፊት በነገር እና በክዋኔ የሚገለጥ ነው። ሽማግሌዎች ይተርካሉ፣ ጎልማሶች ደግሞ በተግባር ተውኔታዊ በሆነ መልኩ በክዋኔ ይገልጡታል። እፍሪካ ይህች ናት።

ጽሑፍ መልካም ቢሆንም የግድ ታሪካችሁን ጽፋችሁ ካላመጣችሁ በቀር ከታሪክ አይቆጠርላችሁም፣ የግድ ባህላችሁ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በመጽሐፍ ተጽፎ ካላገኘነው በቀር ከህልዉ እንቆጥረውም ያለው ማነው? ወይስ የዶክተሩን ውሳኔ የሚለውጠው የለም?

የአፍሪካን ፍልስፍና በፕላቶ እና በሶቅራጥስ ፍልስፍና መነጽር ማየት ለምን ያስፈልጋል? አፍሪካውያን ለመፈላሰፍ እና ፕላቶን ማወቅ ለምን ያስፈልጋቸዋል? ድሮምኮ የተፈላሰፉት ሕይወትን ለመረዳት እና ለመራቀቅ እንጂ ከፕላቶ ጋር ለመነጻጸር ወይንም ለመወዳደር ብለው አልነበረም::

እንግሊዛውያን የሥለጠኑ እና ዴሞክራሲ የበፈነባቸው ከሚባሉ ሕዝቦች ወገን ናቸው:: የመንግሥት አሠራራቸው፣ የፓርላማ ጠባያቸው ግን እንግሊዝ እንግሊዝ ይሸታል እንጂ አሜሪካ አሜሪካ አይሸትም:: የፓርላማ አለባበሳቸው የጥንቱን ባህላቸውን እንጂ የሴኔቱን ገልብጠው አይደለም:: እነርሱ እንደ አሜሪካ ለመሆን ካልተገደዱ፣ እኛ እንደ እንግሊዝ ለመሆን ለምን እንገደዳለን:: ልብስ ለሰውነት ይሰፋል እንጂ ሰውነት ለልብስ አይሠራም::

ምዕራባውያን ስለኛ መመራመራቸው፣ መጻፋቸው፣ ማስተማራቸው እና ትኩረት መስጠታቸው ያስመሰግናቸዋል:: እነርሱ ይህንን ሥራ ባይሠሩልን ኖሮ ልናገኛቸው የማንችል ብዙ ነገሮችም አሉ:: ይህ ማለት ግን እነርሱ ያሉት ሁሉ ትክክል ነው፣ ወይም ደግሞ አብነቶቹ እነርሱ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም:: ትልቁ ችግር እነርሱ አለ ካሉ አለ፣ የለም ካሉ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የለም፣ ልክ ነው ካሉ ልክ ነው፤ ልክ ነው ካላሉ ግን ልክ አይደለም የሚለው አስተሳሰብ ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ነገር አለ? ተብሎ ሲጠየቅ «የለም» ብሎ አፍን ሞልቶ ለመናገር ምዕራባውያን የጻፉትን ብቻ ማገላበጥ በቂ አይደለም:: የኢት ዮጵያን ብሔረሰቦች ሥነ ቃሎች፣ ባሕሎች እና ወጎች፣ ዋሻ ዎች እና ገዳማት፣ ከርሰ ምድር እና ጥንታዊ መዛግብት ማየ ትንም ይጠይቃል:: «ዶክተሩ የለህም ካሉ የለህም» ዓይነቱ አሠራር አያዋጣም::

አብዛኞቹ ምሁሮቻችን ዕውቀታቸውን በሀገርኛ ቋንቋ ከመግለጥ እና ትውልዱን ከማስተማር ይልቅ በምዕራብ ሀገሮች ፀውደ ጥናቶች እና ሴሚናሮች ወረቀት ማቅረብ ብቻ የሚ መርጡት ያለ እነርሱ ቡራኬ ዕውቀት ዕውቀት ስለማይመስ ላቸው ይሆን? ለመሆኑ በሀገር ቤት መጽሔቶች እና ጋዜጦች፣ በሀገር ቋንቋ፣ ምሁራን የሚጽፉት ነገር፣ በሌላ ቋንቋ በሌላ ሀገር እንደሚጽፉት ነገር ተቆጥሮ ለሹመት ለሽልማት የማያ በቃቸው ለምንድን ነው? ፕሮፌሰር ለመሆን በአማርኛ መጻፍ ነጥብ ያስቀንሳል እንዴ?

በእንግሊዝኛ የተጻፉ እና የታተሙ ሃያ ሠላሳ ጥናቶች ያሏቸው ምሁሮቻችን በሀገርኛ ቋንቋ ጽፈው ትውልድ የማስተማር ግዴታቸውን ለምን አልተወጡም? የገንዘብ ችግር እንዳይባል ከነርሱ የባሰ ችግር ያለበት ወጣት ነው ብዙ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ አይሳተም ያለው። ያውም እነርሱስ በደኅና ጊዜ፣ በደኅና ዋጋ የቀበሌያም ቤት አግኝተዋል፤ ነጻ መሬትም ተመርተዋል፤ ከቀረጥ ነጻም መኪና ይዘዋል፤ ልጆቻቸውን አሳድገዋል። እንግዲህ ምን ይጠብቃሉ። ለምን ታድያ ትውልዱን ይወቅሳሉ?

አንድም ዶክተሩ አንድ ብቻ አይሁኑ፤ አንድም ዶክተሩ ያሉት ሁሉ እና ብቻ ምንጊዜም ትክክል ነው ብለን አናስብ፤ አንድም ዶክተሩ ያላዩት ነገር ሊኖር ስለሚችል እርሱን እንመርምር።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ወንደኛ አዳሪዎች

***ቤተኛ አዳሪነት*** ካልጠፋ ማኅበረሰባችን ኢች አይ ቪ ኤድ ስን ከመሳሰሉ አደጋዎች ሊወጣ አይችልም ብሎ ነበ የሚ ያስበው:: እናም ይህንን በተመለከተ አንድ ጥናት ሊያደርግ ተነሣ - ጋዜጠኛው:: ከዚያም መረጃ የመሰብሰብ ሥራውን ከራሳቸው ከቤተኛ አዳሪዎቹ መጀመር አለብ ብሎ ሄደ:: በቤተኛ አዳሪነት ትተዳደራለች ብሎ ወዳሰበት ወደ አንዲት ለጋ ወጣት ቤት አመራ:: እንኳኗ እና ግ መጀመርያ ለሌላ ነገር የመጣ ነበር የመሰላት:: በኋላ ግ ሐሳቡን አስረዳት::

«እኔ በቤተኛ አዳሪነት ላይ ጥናት እያደረግኩ ነው:: ለመሆ አንቺ ቤተኛ አዳሪነት እንዲጠፋ ምን መደረግ አለበት ትያለሽ?» አላት::

«ቀላል ነው» አለችው ፍልቅልቅ እያለች:: «ወንደኛ አዳሪነትን ማጥፋት ነው መፍትሔው» ይህንን ቃል ያለ ዛሬ ሰምቶት አያውቅም::

«ወንደኛ አዳሪነት ደግሞ ምንድን ነው?» ሲል ጠየቃት::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«አሁን እኔን '*ሴተኛ አዳሪ*' ብለህ ከሰየምከኝ ከእኔ ጋር የሚያድረው ወንድ ደግሞ '*ወንደኛ አዳሪ*' ነው ማለት ነው» አለችና ከት ብላ ሳቀች::

«አንቺኮ ዝሙትን ሕይወትሽ እና መተዳደርያሽ ስላደረግሽው ይመስለኛል *ሴተኛ አዳሪ* ተብለሽ የተጠራሽው:: ሴትነትሽን ተጠቅመሽ ገንዘብ ትሰበስቢያለሽ እንደ ማለት ነው:: የወንዶቹ ግን እንዴት ሊሆን ይችላል?» አላት::

«አየህ የማንዛቤ ስሕተት አለብህ:: ነገሩ ወንድ ስትሆን እንዲህ ነው የምትረዳው:: ይህንንም እኮ ስያሜ የሰጡን ወንዶች ናቸው:: ከዚያም መልሰው ሴተኛ አዳሪነትን የሚያወግዝ ሕግ የሚያወጡት ወንዶች ናቸው:: ራሳቸውን ነጻ ያወጡ እየመሰላቸው:: ለመሆኑ ከሴተኛ አዳሪነትና ከወንደኛ አዳሪነት መጀመርያ የተጀመረው የቱ ይመስልሃል?»

«መረጃው የለኝም፣ የምታውቂው ከሆነ ለምን አንቺ አትነግሪኝም» አላት::

«ቀላል እኮ ነው:: መጀመርያ የተጀመረውማ ወንደኛ አዳሪነት ነው:: እስኪ አስብ፤ ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ሴቶች ሀብት ንብረት እንዲኖራቸው በማይፈቀድበት ዘመን:: ነገር ዓለሙ ሁሉ በወንዶች ይተዳደር እና ይመራ በነበረበት ዘመን፣ ወንዶቹ ኃይላቸውን እና ሀብታቸውን ተጠቅመው ወደ ሴቶቹ ሊሄዱ ይችላሉ እንጂ ሴቶቹ በምን ዐቅማቸው ወደ ወንዶቹ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሄዳሉ? ወንዶቹ ከትዳራቸው ሌላ ወይንም ደግሞ እንዲህ መዝናናት አማራቸውና ይህንን ሕይወት አስጀመሩት:: እናም ሴቶቹ ለወንዶቹ ሊከፍሉ አይችሉም፤ ምክንያቱም ሀብቱ ያለው በወንዶች እጅ ነበርና:: ጉዳዩን ግን ከሴቶቹ በላይ ወንዶቹ ይፈልጉታል:: የእነርሱ ፍላጎት ባይኖርበትማ በወቅቱ እንደ ነበራቸው ኃይል እና ሥልጣን፣ ሕግ ማለት ወንድ ማለት በነበረበት ዘመን እንደ መኖራቸው፣ ሴተኛ አዳሪነትን ያጠፉት አልነበር?» ትንታኔዋ ገርሞት ዝም ብሉ ያዳምጣት ጀመር::

«ለመሆኑስ ወንዶቹ ለኛ ገንዘብ የሚከፍሉት ለምን ይመስለሃል?»

ዝም አላት::

«ከኛ ለሚያገኙት ነገር መሰለህ? አይደለም:: ስማቸውን ለመጠበቅ እኮ ነው የሚከፍሉት»

«እንዴት?» አለ ገረመውና::

«ይህ ድርጊት ቦታ እና ጊዜ ያስፈልገዋል:: 'ድርጊት፣ ቦታ እና ጊዜ' ካሉ ደግሞ ታሪክ አለ ማለት ነው:: ታሪክ ካለ ደግሞ ባለ ታሪክ አለ:: ድርጊቱን ታውቀዋለህ፤ ባለ ታሪኮቹ ደግሞ እኛ እና ወንዶቹ ነን:: እኛ ሴቶቹ ኢኮኖሚያዊ ዐቅም ስለሌለን ገንዘቡን ፈለግነው:: ወንዶቹ ደግሞ ገንዘቡ ስላላቸው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ስማቸውን ፈለጉት:: ስለዚህም 'ቢተኛ አዳሪነት' የሚለውን ስም እኛ ተሸከምንላቸው:: ቦታው እና ድርጊቱ በኛ ስም ሆኑ፡ ተለይቶ መታወቅን እኛ ወሰድነው፤ ተደብቆ መከፈልን ደግሞ ወንዶቹ ወሰዱ::

«ኅብረተሰቡ ራሱ ደህንን አሠራር ስለ ተቀበለው ወንደኛ አዳሪዎችን ሳይሆን ቤተኛ አዳሪዎችን ነው የሚያገልለውም፣ የሚቀጣውም:: እስቲ በየቤተ እምነቱ ሂድ:: ከኛ ጋር ያደረው ወንደኛ አዳሪው ማንም ስለማያውቀው ቀጥ ብሎ ቤተ ክርስቲያን ይገባል:: ማን ከልካይ አለበት:: እኛ ግን አንዷ ስለታወቅን ጥግ ነው የምንቆመው:: እኛን ለዕድር እና ለዕቁብ፣ ለኮሚቴ እና ለምርጫ ማን ከቁም ነገር ይቆጥረናል:: ወንደኛ አዳሪው ግን ስሙን እኛ ስለደበቅንለት መብቱ ተጠብቆ፣ ስሙም ተከብሮ ይኖራል:: አንዳንድ ሰዎች ቀብር ላይ ተገኝተን «አቶ እገሌ ጨዋ፣ ሥነ ምግባር የነበራቸው፣ ትዳራቸውን አክባሪ፣ ታማኝ እና ሃይማኖተኛ ነበሩ» ተብሎ ታሪካቸውን ስንሰማ፣ ምናለ ደህንን የሕይወት ታሪክ የመጻፍ ዕድል ባገኘን እንባለንክ::

«ደግሞምኮ ቤተኛ አዳሪዎች የምንባለው ሴቶች ቢበዛ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ጨርሰን የተቀመጥን ነን:: ወንደኛ አዳሪዎቹ ግን ፕሮፌሰሮች፣ ዶክተሮች፣ ባለ ሥልጣናት፣ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ ምሁራን፣ ሊቃውንት ጭምር ናቸው:: እኛ በአብ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩት የቀደሙት ወንደኛ አዳሪዎቹ ግን የናጠጡ ናቸው። ዛኛው ድኸች ነን። ወንደኛ አዳሪነት ላይ ይመስለሃል? እሀ እና ስታየው፣ ችግሩ ከሴተኛ አዳሪነት ላይ ይመስለሃል? ... ያውን ፈርቶ ደውላውን ካልሆነ በቀር። እስኪ አስበው ሴተኛ አዳሪዎች የምንባለው ሴቶች ቁጥራችን ትንሽ ነው። ወደ እኛ የሚመጡ ወንዶች ግን ቁጥራቸው የት የለሌ ነው። ትንሽ ኢኮኖሚክስ አልወሰድክም። ፍላጎት ከአቅርቦቱ በላይ ሲሆንክ ሸማቹ ያንን ነገር እጅግ አጥብቆ ይፈልገዋል ማለት ነው። ደግሞም አቅርቦቱን ማሳደግ ካልተቻለ ያ ነገር ሕልው የሆነው በሸማቹ ከመጠን ያለፈ ፍላጎት እንጂ በራሱ አስፈላጊነት አይደለም ማለት ነው። እኔም ለዚህ ነው ሴተኛ አዳሪነት ሕልው የሆነው በጀማሪዎቹ በወንዶች ፍላጎት እንጂ በሴቶቹ አይደለም የምልህ።»

«ቆይ አንቺ ሴተኛ አዳሪነት መኖር አለበት ብለሽ ነው የምታ ምንኛው ማለት ነው?»

«ወንድሜ ዋናውኮ የኔ ማመን አለማመን አይደለም፣ ነበረ ተሰቡ ያለ ሴተኛ አዳሪዎች መኖር ይችላል ወይ? ነው ጥያቄው።

«መኖር አይችለም ብለሽ ታምኛለሽ»

«አምና! እነዚህ ሁሉ ሃይማኖቶች፣ ባሕሎች፣ የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች፣ ሕጎች እና ነውሮች በሞሉበት ሀገር ሴተኛ አዳሪነት እንዴት ይህንን ሁሉ ተቋቁሞ ሊኖር ቻለ? ብለህ እስኪ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠይቅ:: ኅብረተሰቡ ስለሚፈልገው ካልሆነ በቀር:: እኛ በድር ጊቱ እናፍራለን፡ ወደን የምናደርገውም አይደለም:: ኅብረተሰቡ ግን በሁለት መንገድ ያስገድደሃል:: አንደኛ ድህነትህን ተጠቅሞ ያስገድድሃል፡ እንደገናም ጥቃት ያደርስብህና ወደዚህ ኑሮ ይልክሃል::

«ለመሆኑ እኛ ኅብረተሰባችንን ከስንት መከራ እንደታደግነው ታውቃላችሁ?»

«እስኪ ንገሪኝ»

«እነዚህ ሁሉ እኛ ጋር መጥተው እንስሳዊ ጠባያቸውን የሚያሳዩት፣ በሕይወታችን የሚቀልዱት፤ ስሜታቸውን መቆጣጠር አቅቷቸው በሰው ላይ የማይፈጸም ግፍ የሚፈጽሙብን ወንዶች እኛ ባንኖር ኖሮ የት ሊሄዱ እንደሚችሉ አስባችሁት ታውቃላችሁ?»

«የት ይሄዱ ነበር?»

«ለመሆኑ የትኛዋ ሚስት ጨዋ ሆና ትኖር ነበር? የትኛዋ ልጃገረድስ ድንግልናዋን ጠብቃ በመንገድ ትተላለፍ ነበር? የትኛዋስ ተማሪ ትማር ነበር? የትኛዋስ እናት በሰላም ትኖር ነበር? እነዚህ እኛ ዘንድ የሚመጡት አራዊት ወደ እነዚህ ቤቶች ነበር የሚዘምቱት:: ሕግ ካላገዳቸው፣ በሕል ካልገራቸው፣ ሃይማኖት ካልያዛቸው ማን ነበር የሚያግዳቸው? እነ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ዚህ ሁሉ ሴቶች በሰላም ውለው የሚገቡትኮ እኛ ሽክማቸውን ስለተሸከምንላቸው ነው:: ፈውዝ ታውቃለህ:: ይሄ ሶኬት ላይ የሚገጠመው ነገር:: ፈውዝ ራሱ ይቃጠልና ሌሎች ዕቃዎችን ከመቃጠል ያድናቸዋል:: መቃጠሉን ፈልጎት አይደለምኮ:: ነገር ግን የሌሎችን ቃጠሎ ነው እርሱ የሚቃጠለው::

እናቶቻችን ጉንዳን ቤታቸው ሲመጣባቸው፣ በየቦታው የተበ ራውን ጉንዳን በምን እንደ ሚሰበስቡት ታውቃለህ? አንድ ቦታ ላይ ሥጋ ይጥላሉ:: ያን ጊዜ ጉንዳኖቹ እያሸተቱ ወደ ዚያ ሥጋ በራሳቸው ጊዜ ይሰበሰባሉ:: ከዚያ ጠርገው ያወጡ ታል:: እኛም እንደዚያው ነው:: ወደ ኅብረተሰቡ ሲዘሩ የነበ ሩትን ጉንዳኖች ነው ሰብስበን የያዝንላችሁ:: ልታመሰግኑን ይገባል» አለችና ሳቀች::

«አሁን አንቺ ስለራስሽ እንዴት አድርገሽ ነው የምታስ ቢው?»

«እኔ በኅብረተሰባችን ውስጥ ያለው ችግር መገለጫ እንጂ በራሲ ችግር አይደለሁም ብዬ ነው የማስበው:: የሚያበሳጭ ነገር ሲያጋጥምህ ራስህን ያምሃል:: ምናልባት የራስ ሕመሙን ለማሻል ፔይን ኪለር ትወስድ ይሆናል:: ለጊዜውም ይለቅሃል:: ብስጭትህን የሚያመጣውን ነገር ካላስወገድከው ግን ለራስ ምታቱ ብቻ መድኃኒት በመውሰድ ችግርህን መፍታት አትች ልም:: አንተ ችግሩን ሳይሆን የችግሩን መገለጫ ነው ልታስ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ወገድ የምትሞክረውና፡፡ ራስ ምታቱ ሳይሆን ራስ ምታቱን የመጣብህ ብስጭት ነው ችግሩ፡፡ ለራስ ምታት የምትውጠው መድኃኒት ብስጭትህን አያስወግድልህም፣ ለብስጭትህ የምትወስደው መፍትሔ ግን ራስ ምታትህን ያስወግድልሃል፡፡

«አሁንም 'ቤተኛ አዳሪነት' 'ወንደኛ አዳሪነት' የተባለው የኅብረተሰብ በሽታ መገለጫው፣ የበሽታው ምልክት እንጂ በራሱ በሽታ አይደለም፡፡ ሴቶች በቤተኛ አዳሪነት እንዳይሰማሩ ብትከለክል ቤተኛ አዳሪነትን አታጠፋውም፡፡ ወንዶች በወንደኛ አዳሪነት እንዳይሰማሩ ካደረግክ ግን ቤተኛ አዳሪነት አይኖርም፡፡ ጀነሬተሩ ከጠፋ አምፖሉ በምን ይበራል ብለህ ነው? ወሎ የነበሩ እንትቶቼ በንጉሥ ሚካኤል ዘመን ምን እንዳሉ ታውቃለህ? ንጉሡ ቤተኛ አዳሪነትን ለማጥፋት '*የቤተኛ አዳሪ ቤቶች ሁሉ ይዘጉ*' ብለው ሕግ ያወጣሉ፡፡ ይህንን የሰሙት ቤተኛ አዳሪዎች ታድያ

*ይዘጋ ካሉማ መርሐባ ይዘጋ*
*አዳራሹም በሊጋም አልፍኙም በቀጋ*

ብለው ገጠሙ፡፡ አዳራሹ እና አልፍኝ ካሉት ወንደኛ አዳሪዎች ይጀመር ነው ነገሩ፡፡

«እኔ የቤተኛ አዳሪነት ፍቅር ኖሮኝ አይደለም ይህንን ያህል የምከራከረው፡፡ ነገር ግን አሉሉውን ወደ እኛ ብቻ መወርወሩ ይቅር፡፡ ድንጋዩ የተቀመጠበት ቦታ ድረስ ሄዶ በእግሩ አየ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ነሪት፣ ሰው ለንቅፋት መታኝ ይላል። እንቅፋቱን እንመታው ነው ወይስ ይመታናል? ገንዘብ ጠፋብኝ ሲባል አይገርምህም? አጠፋነው ወይስ ጠፋብን? እያሁ ኃላፊነትን የመውሰድ ችግር አለ ማለት ነው። ስለ እኛ ሲታገቡ ከመውቀስ እና ከመክሰስ ከመጠየፍ እና ከማነወር፣ ከመፍረድ እና ከመፈከን አቁሙ። ከዛሬ ጀምሩ። ችግሩ የራሳችሁ መሆኑን ከማወቅ ጀምሩ።

ጋዜጠኛው ተሰናብቷት ሲወጣ የጥናቱን ርእስ መቀየር እንዳለበት ገባው።

«ወንደኛ አዳሪነትን ለማጥፋት ምን ማድረግ አለብን?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ጠጠሮቹ

ሰሞፌሰው ዓሣ አጥማጁ ነው። እናም ለዓይን ያዝ ሊያደርግ
ሲል ጀልባውን እየቀዘፈ ወደ ወንዙ ገባ። ጸጥ ብሎ በሚፈ
ስሰው ወንዝ መካከል መረቡን አመቺ ቦታ ላይ ጣለው። ከዚ
ያም ወደ መረቡ የገቡትን ዓሦች ጠዋት መጥቶ ለመውሰድ
እያሰበ ወደ ወንዙ ዳር ተመለሰ። ጀልባውን ወንዙ ዳር ጥሎ
ወደ ቤቱ መንገድ ሲጀምር አንዳች ነገር እግሩን መታው።
ጎንበስ ብሎ ቢመለከት በእራፊ ጨርቅ የተቋጠረ ነገር ነው።
አነሣና ፈታው። ብዙ ጠጠሮች በእራፊው ጨርቅ ተቋጥረ
ዋል። ድክም ስላለው ጠጠሮቹን ይዞ መጣና ዋርካው ሥር
ተቀመጠ።

ሕሁን ምናለበት መረቤ ሙሉውን ዓሣ ቢይዝልኝ። ደግሞም
ዛሬ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው እንደዚሁ መረብ ሙሉ ዓሣ ቢኖ
ረኝ። ይሆንን ወንዝስ ሌላ ሰው ባይሻማኝና እኔ ብቻ ዓሣ ባስ
ግርበት ምናለበት። አቤት እንዴት ሀብታም እሆን ነበር»
አለና መንገድ ላይ ካገኛት እራፊ ጨርቅ ውስጥ ከተቋጠሩት
ጠሮች አንዱን አንሥቶ ወደ ውኃው ውስጥ ወረወረ። ጠጠሯ
የረፈችበት ቦታ ክበቦች እየሠራ ዘና አደረገው።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«መጀመሪያ ቤቱን አቀይር ነበር:: ፎቅ ነበር የምሠራው:: ያውም በማንብ ግጥም አድርጌ:: እንኳን እኔ ሁለቱ አሁኖቹ እንኳን ያልፍላቸው ነበር:: መረቤ እና እኔ አብረን መተኛታችንም ይቀር ነበር:: ይኼው ቤቱ ሁሉ የሞተ ዓሣ የሚሸተው ማደርያውም፣ ሰቃ ማስቀመጫውም፣ መሠገቢያውም፣ አንድ ስለሆነ አይደል:: ይኼ ሁሉ ይቀር ነበር::

አሁንም አንድ ሁለት ጠጠር አውጥቶ ወረወረ::

«እንደ አቶ ዘመናይ ያለች መኪና ገዝቼ የሠፈሩን ሰው እቀይረዋለሁ እንጂ:: "ከኒያ መኪና ካላቸው ሰውዬ ቤት አጠገብ" መባል አለበት:: ታድያ የማንንም ቡትቶ ለባሽ ማሳፈር የለብኝም፤ እየመረጥኩ ነው:: እርግጥ አልፎ አልፎ የተከበሩ ሰዎች ሲያገቡ መኪናዬን ላከራያቸው እችላለሁ:: ከዚያ ውጭ ግን እንኳን እነርሱ እኔም ዝም ብዬ የትም አልሄድባትም:: የተከበረ ቦታ ከሆነ ብቻ ነው በመኪና የምሄደው:: ሌላውን በእግሬ እሄዳለሁ::

ከእራፊው ጨርቅ አንድ ሦስት ጠጠሮች አወጣ፤ ከዚያም ወደ ወንዙ ወረወረ::

«የምጠጣበትም ቤት ለየት ማለት አለበት:: ይኼ ማንም ከሚገባበት ቦታ መግባቴ ይቀራል:: ከመጠጡ አጠጣጡ፤ ከአ ጠጣጡ አቀማመጡ ይባል የለ:: ዋናው ምን ጠጣ? አይደለም፤ የት እና ከነማን ጋር በስንት ብር ጠጣ? የሚለው ነው ወሳኙ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እንጂ መጠጡማ የትም ይገኛልኮ:: ሰዎቹ ናቸው የትም የማይ ገኙት:: "እርሱን እዚህ ቤት አየነው" ሲባልኮ ነው ግርማ ሞገሱ፣ "ይህንን ያህል ብር ከፈለ" መባሉ እኮ ነው ዝናው::

ሌሎች ተጨማሪ ጠጠሮች ወረወረ::

ብዙዎቹ ስጠሩ አጠራሩ ከድሮው ለየት ማለት አለበት:: አሁን ሌሎች ሲሰጡ ማጨብጨብ ይቀራል፣ ሰጥቶ ማስጨብ ጨብ ይጀመራል:: "እርሱ ይህንን ያህል ብር አዋጥቶ እኛ እንዴት ዝም እንላለን" እያለ አዳሚ መጨነቅ አለበት:: መቼም ለስም እና ላለመጠቆር እንጂ ለኀሊና ሲባል ማዋ ጣት እየቀረ ነው:: ይኼው አንዳንዱ እወደድ ባይ ገንዘብ ሰብ ሳቢዎቹ ያላሰቡትን ሁሉ፣ ራሱን ኮሚቴ አድርጎ፣ "አሁን እን ዴት ዝም ይባላል" እያሰኘ ስንቱን ያለውዴታው በግድ አስወ ጣው አይደል:: ታድያ እስከ መቼ በሰው ኮሚቴ አዋጣለሁ:: እኔ ራሴ ኮሚቴ ሆኜ መሰብሰብ ነው እንጂ:: ዋናው ነገርኮ ማን አዋጣ? መሆኑ ቀርቶ ማን ሰበሰበ ሆኗል::

እንደገና አንድ ጠጠር አውጥቶ ወደ ወንዙ ወረወረ::

‹አቤት የልጄን ሠርግ እንዴት አድርጌ ይሆን የምደግሰው:: "አሁን ይኼ ሠርግ ነው ወይስ የበጎ አድራጎት ግብዣ ነው" እስኪባል ድረስ:: ካርዱ ካናዳ ይታተማል፣ ብርጭቆው ከሆ ንግ ኮንግ ይመጣል፣ ስሑኑን ከታይላንድ አገዛለሁ:: ቬሎው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ከእንግሊዝ ይሻናል። አራት ሊሞዚን አስልፋለሁ። እኔ ያለን ሁሉ ካደረግኩ ተስማምቶ መኖር እና አለመኖር የተጋቢዎቹ ጉዳይ ነው። እኔኮ መደገስ እና መዳር እንጂ ማስማማት እና ማኖር አይጠበቅብኝም። ደግሞምኮ "የእገሌ ሠርግ" ተብሎ ይነገራል እንጂ "የእገሌ ልጆች ትዳር" እየተባለ አይነገርም። ስለ ሠርግ እንጂ ስለ ትዳር የሚያወራ ማን አለ።

ጠጠሯ አሁንም ተወረወረች።

"ፓሪስን አየናት ከእግር እስከ ራሷ፣

ኒውዮርክን አየናት ከእግር እስከ ራሷ፣

ዱቢንም አየናት ከእግር እስከ ራሷ" እያሉ መዝፈን አሁን ነው። አሁንማ ማንም ኤምባሲ ቪዛ አይከለክለኝም። ሀብታም ሄዶ አይቀርም ማን እንዳላቸው አላውቅም። ንግድ ፈቃድ የጠየቋቸው ይመስል ኤምባሲዎች ሁሉ ብር አሳዩን ይላሉ። ለት ርዳም ቢሆን አንድ ሁለት ሚስት ጨምሬ መቅረብ ነው። ይኸው በቀደም ያ ጎረቤቴ "ወደ ሀገርህ መመለስህን ለማረጋገጥ እዚህ ሀገር ትዳር መያዝክን፣ ልጅ መውለድክን ማስረጃ አምጣ" አሉት። አምስት ሚስቶቹን እና አሥራ ስምንት ልጆቹን ይዞላቸው ሄደ። ምንድን ነው? ቢሉት "አንዲት ሚስት ላገባ ቪዛ ከተሰጠው እኔ አምስት ሚስት ላገባሁትማ ሊሰጠኝ ይገባል" አላቸው። "መቼም አንዲት ሚስት ገቦ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመቅረት አምስት ሚስቶች ጥሎ መቅረት ያስነብዳል" አላቸው አሉ።

አሁንም ጠጠር ሊጥል ከጨርቁ ሲያወጣ አለቀበት። የቀረችው የመጨረሻዋ ነበረች። እርሷንም ሊጥላት ሲል አንዳች ብርሃን ብልጭ አደረገችበት። ወደ ልቡ ተመለሰና ነገበስ ብሎ አያት። አሁንም የብርሃን ፍንጣቂ ከጠጠሯ ሲወጣ ተመለከተ። አንዳች ተአምራዊ ነገር መሰለውና ለሦስተኛ ጊዜ ተመለከታት፣ አሁንም ብርሃን ትፈንጥቃለች።

በሐሳብ መንጎ ዱን ተወና ተስፈንጥሮ ተነሥቶ ወደ ገበያ ሮጠ። መሐል ገበያ ካለው ሱቅ ገባና ለባለ ሱቁ አሳየው። ባለ ሱቁ ወደ ጓዳ ጠጠሯን ይዟት ገባና ጥቂት ቆይቶ ተመለሰ። ጥርሱ ብቻ ሳይሆን መላ ሰውነቱ ይስቅ ነበር።

«የት አገኘኸው?» አለው ባለ ሱቁ በጉጉት።

«ወንዝ ዳር» ዓሣ አጥማጁ መለሰ።

«ምን እንደሆነ ዐውቀህዋል?»

«አላወቅኩትም፤ ብቻ አንዳች የሚያበራ ነገር ነው»

«የከበረ ድንጋይ እኮ ነው። ሌላም አለህ? ይህኮ ሚሊየነር የሚያደርግህ ነው። ካለህ አምጣው እባክህ?» አለና ባለ ሱቁ ለመነው።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እርሱ ግን ያደረገው ነገር ሁሉ ሲታሰበው፣ ጭውውው አለበትና አዙሮት ወደቀ፡፡ ነፍስ ሲዘራ ጠጠሯን ተቀብሎ ወደ ወንዙ በድጋሚ ሮጠ፡፡ ወንዙ በደራሽ ውኃ ሞልቶ ሲንዶለዶል ብቅ ባለችው ጨረቃ ይታያል፡፡

«ምን ዓይነት ሞኝ ነኝ፡፡ እንዴት አላስተውልም፡፡ እንዴት ገንዘብ እወረውራለሁ፡፡ ልቤን የት አድርጌው ነበር፡፡ ዝንጀሮ ሆኜ ነበር እንዴ፡፡» የጥያቄ መዓት በራሱ ላይ ደረደረ፡፡

«አንተ ብቻ አይደለህም» አለው ከሥሩ ተቀምጦበት የነበረው ዋርካ፡፡ «ብዙዎች እንደ አንተ ናቸው፡፡ እኔ ይኼውልህ እዚህ ከተተከልኩ ከሺ ዓመታት በላይ ሆኖኛል፡፡ እንዲህ እንዳንተ ያሉ ብዙ የዚህች ሀገር ሞኞች አያሌ በእጆቻቸው የገቡ ዕድሎች ሲያመልጧቸው ታዝቤያለሁ» አለው፡፡ ዓሣ አጥማጁ ቀና ብሎ ዋርካውን አየው፡፡

«ያላገኘኸውን እያለምክ ያገኘኸውን ትጥል ነበር፡፡ ያልያዝከውን በመመኘት የያዝከውን ትወረውር ነበር፡፡ ስለ ሚሊዮን ብሮች እየቃዠህ ሚሊዮን ብሮችን ከእጅህ እየወጣህ ትበትን ነበር፡፡ ይኼ ያንተ ችግር ብቻ አይደለም፡፡

«እያሌ ፖለቲከኞች የዚህችን ሀገር መዓት ዕድል ያበላሹት በእጃቸው የገባውን እድል እየወረወሩ በእጃቸው ያልገባውን ሲያልሙ ነው፡፡ በእጃቸው የጨበጡትን ተጠቅመው በእጃቸው ወዳልጨበጡት መንገዝ ሲችሉ፡፡ የያዙትን እየወረወሩ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ያልየዙትን ይናፍቁ ነበር፡፡ አንተ የከበሩ ድንጋዮችን እንደዋዛ ስትወ ረውር እንደነበርከው ሁሉ እነርሱም ስንት የከበሩ ዕድሎችን እንደ ዋዛ እየወረወሩ አበሳሹ መሰለህ፡፡ በዚህች ሀገር ታሪክ ስንት የለውጥ እና የዕድገት ዕድሎች አመለጡ፡፡ ስንት የከበሩ አጋጣሚዎች ወደማይገኙበት ጥልቅ ተወረወሩ፡፡

ዐበእጃቸው የገባውን ዕድል ተጠቅመው የሀገሪቱን ችግር መፍ ታት ሲችሉ የማይጨበጠውን ሶሻሊዝም እና ኮሚኒዝም ሲና ፍቁ፤ በእጃቸው የገባችውን ኢትዮጵያ ትተው በእጃቸው የሌለ ችውን ኩባን እና ሶቪየትን ሲቃኙ፤ የዚህች ሀገር ልጆች እንደ ከበሩ ድንጋዮች ውድ የሆኑ ስንት አጋጣሚዎችን አባከኑ፡፡

ዐንቱ ወጣትስ እንዲህ ያለ ሥራ ካልሆነ አልሠራም፤ ይህንን ያህል ደመወዝ ካልተከፈለኝ በቀር ሥራ የሚባል አያሳየኝ፡፡ ይህንን ያህል ካላተረፈኝ በቀር ንግድ የሚባለውን አላየውም እያለ በእጁ የገባውን ስንት የከበረ ጠጠር ወርውሯል መሰለህ፡፡ በእጁ የገባውን ዕድል ተጠቅሞ በእጁ ያልገባውን ዕድል እንዴት ላግኘው? የሚል የለም ከ፡፡ ዕንቁላሉን ካገኘህ እስፈልፍለህ ዶሮ ለማድረግ ተጠቀምበት፤ ከዚያ ዶሮዋ ብዙ ዕንቁላል ትጥልልሃለች፤ መልሰህ ደግሞ ዕንቁላሎችን ዶሮ ታደረጋቸዋለህ፤ ከብዙ ልፋት በኋላ ደግሞ የዶሮ ማርቢያ ትከፍታለህ፡፡ ከዚያም የዶሮ ሥጋ መሸጫ ይኖርሃል፡፡



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲህ እንዲህ እያልክ ያሰብከውን ብልጽግና ታገኘዋለህ ማለት ነው:: የዕንቁላል ፋብሪካ ካልከፈትኩ እያልክ ለምን እጅህ ውስጥ የገባችውን ዕንቁላል ትሰብራታለህ?

«የተፈጠረችውን ማግባት ትተው እንደ ልብስ ማስት በዕውቅ ለማሠራት ሲሞክሩ፤ ከጎናቸው ያለችውን ጓደኞቻቸው እየነጠቁ ሲያገቡባቸው፤ አስመጭና አከፋፋይ ይመስል ወደ እነርሱ የቀረበውን ሁሉ ወደ ሌላ ሲያሻግሩ፣ የሰንቶቹ ዕድሜ ገፋ፣ የሰንቶቹ እድልስ ተበላሸ:: ከምድር የተገኘችውን ጽጌረዳ ትተው ከማርስ የምትመጣ አደይ አበባ ሲመኙ፤ ከኢትዮጵያ የተገኘውን ከበደ ትተው ከአሜሪካ የሚላከውን ከቢኾ ሲቋምጡ እንዲህ እንዳንተ ሰንቶች በእጃቸው የያዙትን አጡ::

«እና ወንድሜ መጀመርያ የያዝከውን አጠንክረህ ያዝ፤ እርሱን ተጠቀምበት፤ ስታልምም እየሠራህ አልም፤ እየወረወርክ አታልም:: ከመሰላሉ ጫፍ ትደርሳለህ፤ መቼ? ከመጀመርያው እንጨት ጀምረህ በደንብ ጨብጠህ እየተንጠላጠልክ ከተጓዝክ:: ዘልዬ መጨረሻው ላይ እርፋለሁ ካልክ ግን ትሰበራለህ:: ሩቅ ማሰብ ጥሩ ነው:: ግን የቅርቡን እየተጠቀሙ ከሆነ ነው::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ኳሱን አትንኩብን



*«መጣቱ* በአውሮፓ እግር ኳስ ነፍሱ ሊወጣ ነው:: የሀገሩን እግር ኳስ እና የሀገሩን ጉዳዮች ከመከታተል ይልቅ በእንግሊዝ፣ በጣልያን እና በስፔይን የእ ግር ኳስ ተጨዋቾች ልቡ ተነድፏል:: ሚዲያዎችም ቢሆኑ እን ዴው ለአመል ያህል የሀገራችንን ኳስ ነካ ነካ ያደርጉና እጥፍ ጥፍ ብለው ወደ አውሮፓ ይሻገራሉ» እያላችሁ ታሙናላችሁ አሉ::

ወገኞች ናችሁ እንዴው:: የጨዋታውን ዓይነት፣ የግቡን ልዩ ነት፣ የታክቲክ እና የቴክኒኩን ነገር ተውት ይቅር ግዴለም:: የተጨዋቾቹን ዝና እና ታዋቂነት፣ የሚያሳዩትን ምትሐት ተውት አይነኣ ግዴለም:: አሁን እኛ ሀገር በእግር የሚመታ ኳስ እንጂ እግር ኳስ አለ ይባላል? እንኳን የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽንን ከመሠረቱት ሦስት ሀገሮች አንዱ ልንመስል እግር ኳስ ከአውሮፕላን ተወርውሮ የነጠረባት ሀገር



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እንመስላለን? ለመሆኑ እኛ ሀገር ስለ ተጨዋቹ እና ስለ ጨዋታው ከሚነገረው በላይ ስለ ቡድኖቹ ሽኩቻ እና ስለ ፌዴሬሽኑ ውዝግብ የሚነገረው አይበልጥም?

ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከንቢያው ቋጠጥ ሲባል አልሰማችሁም፡፡ ኳሱ መከራ እያየ፣ እኛ ማን ሥልጣን ላይ ይውጣ የሚለው ነው የሚያወዛግበን፡፡ መጀመርያ ኳሱ ሲኖር እኮ ነው ፌዴሬሽን እና የፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት የሚያስፈልገው፡፡ ጥርስ የላት ቅወቀር አግራት አሉ፡፡ የኢትዮጵያን እግር ኳስ አሁን ካለበት ደረጃ ለማድረስ እኮ ግዴለሽነት እና ክፋት እንጂ ፌዴሬሽን አያስፈልግም ነበር፡፡

ስንት ዋንጫ እየሳሙ፣ ስንት ውጤት እያመጡ፣ ስንት ታሪክ እየሠሩ ዓለምን የሚያናውጡ ቡድኖች ያሏቸው ፌዴሬሽኖች ሳይወዛገቡ እኛ ፊፋ ድረስ ሄደን እንካ ሰላንታ፡፡ ቅቤ አንጓሪዎ ተቀምጣ ጎመን ቀንጣሿን ምች መታት አሉ ወይዘሮ ዘርፌ፡፡ ፊፋስ ቢሆን «ማስረጃችሁን አምጡ፣ የፊፋ ሕግ አልተከበረም፣ መተዳደርያው ተጥሷል» እያለ ያለ ደረጃችን ደረጃ ከሚሰጠን መጀመርያ እስኪ ስታዲዮም ግብቼ ስትጫወቱ ልያችሁ፣ እስኪ ቡድኖቻችሁ እንዴት እንደተደራጁ አሳዩኝ፣ እስኪ ስንት ስታዲዮም ገነባችሁ፣ እስኪ ቢሮአችሁ እንዴት እንደ ተደራጀ ልይ» ቢል ኖሮ ውዝግቡ ይህንን ያህል ዘመን መች ይፈጅ ነበር፡፡ በሌላ ነገር እኮ ነው መከራ የምናየው፡፡



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የጎል ቁጠር ቢሉት ማፈያ እንድ አለ የተባለው ደረሰና ለምን ሮጎ ነው ኳሳችሁ የማያድገው? ተብለው ሲጠየቁ «ሕዝቡ የአውሮፓ እግር ኳስ ስለሚያይ ከስታዲየም ስለ ጠፋ ነው። ስለዚህም የአውሮፓ ጨዋታ የማይታይበትን መንገድ እንፈልጋ ለን» አሉ አሉ። ለሠራነው ስሕተት ራሳችንን ተጠያቂ የምናደርግበት? ይህ ነገር ሊከሰት የቻለው ምን ስሕተት ስለሠራሁ ነው? ብለን የምንጠይቅበት ዘመን መቼ ይሆን የሚመጣው። እንደዉ እድሜ ልካችንን ለችግራችን ሁሉ ውጫዊ ምክንያት እንደፈለግን ልንኖር ነው?

የጤፍ ነጋዴ ፓስታ በብዛት ስለተመረተ ገበያ ጠፋብኝ ብሎ ያውቃል? የቢራ ፋብሪካ እዚህም እዚያም ቢከፈት የሀገሬ ጠጅ ቤቶች መች ንቅንቅ አሉ። እነ ገደል ግቡ ጠጅ ቤት ይሄው ጢም እንዳሉ ናቸው። ሌላውን ተውት የሀገሬ ሰው በፊልሞቹ ላይ የሚሰጠውን ያንን ሁሉ ትችት እየሰማ እንኳን፣ ሰው በዐቅሙ ነው የሚጸድቀው ብሎ ከውጭ ሀገር ፊልሞች እኩል እንዲያውም በላይ፣ የሀገሩን ፊልም እያየ አይደለም እንዴ?

ለመሆኑ ሕዝቡ የአውሮፓ እግር ኳስን ለምን እንደሚወድ ደው ያውቁታል። የጨዋታውን ጣዕም እና የቡድኖቹን የብቃት ደረጃ አላነፃፀሩም። እንዳላስገነመጃቸው ብዬ። እረ ሌላ ሌላውን። ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ አንድ ቡድን፣

ተጨዋቾች፣ የቡድን አሰላለፍ፣ የአሠልጣኞች ሁኔታ፣ የክለብ ባለቤቶች እንቅስቃሴ፣ የገቢ እና ወጪ ጉዳይ ለማውራት መረጃ ይገኛል? የተጠናከረ ዌብ ሳይት ያለው ቡድን አለ? የተደራጀ ሙዚየም ያለው ቡድን አለ? የአንድ ተጨዋች ታሪክ፣ የገባ ቸው ግቦች፣ መቼ እንዳገባ፣ የት ላይ እንዳገባ በመዝገብ ይያዛል? በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ በዛሬው ዕለት የዛሬ ሠላሳ ዓመት ምን ተደርጓል? ተብሎ ቢጠየቅ መልስ ያለው ክለብ እና ፌዴሬሽን አለን?

በሐሜት ከሚነገረው በዘለለ የተጠናቀረ፣ ሁሉም ሊያውቀው የሚችል እና የሰሚውን ልቡና ሊያረካ የሚችል መረጃ አለ? ስለ አውሮፓ ቡድኖች፣ ፌዴሬሽኖች፣ ተጨዋቾች፣ አሠልጣኞች እኮ ከሚፈለገው በላይ የመረጃ ጎርፍ ይፈስሳል። ምን በሉ፣ ምን ጠጡ፣ የት ዋሉ፣ የሚጫማ ቱጥሪቸው ስንት ነው፣ የቤተሰባቸው ሁኔታ እንዴት ነው ተብሎ ቢጠየቅ፣ በደቂቃ መረጃ ማግኘት ይቻላል:: የማያውቁት ሀገር አይናፍቅም ሲባል አልሰማችሁም፣ ታድያ የማናውቀውን እግር ኳሳችንን እንዴት እንውደደው::

አንዳንድ ባለሥልጣናት እኮ መረጃ መስጠት የሚመስላቸው ጋዜጠኛ ጠርተው የሚያስቡትን እና የሚፈልጉትን መናገር ነው:: ይሄኮ ሐሳብን መግለጥ እንጂ መረጃ መስጠት አይደለም:: መረጃ መስጠት ማለትማ መረጃ መሰብሰብ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊገኝ በሚችልበት ቦታ እና መንገድ ማስተመጥ፣ በልዩ ልዩ የመረጃ ማስተላለፊያ መንገዶች ወደ ተጠቃሚዎቹ ማድረስ ነው:: ደግ ሞምክ እኛ የምንፈልገውን እና የምንወደውን ብቻ እንዲ ታወቅ የምናደርግ ከሆነ መረጃ መስጠት ሳይሆን ስንቀልል ሎሽ ነው የሚሆነው::

ደግሞስ መረጃ ቢኖርስ ነጻነቱ የት ይገኛል:: የአውሮፓ እግር ኳስን እኮ ብንፈልግ ስለ ተጨዋቹ፣ ብንፈልግ ስለ አሠልጣኙ፣ ብንፈልግ ስለ ክለቡ ባለቤት፣ ብንፈልግ ስለ ቡድኑ ገቢ እና ወጭ፣ ብንፈልግ ስለ ፌደሬሽኑ የዕለት ውሎ በንተች፣ ስንተነትን፣ ስንከራከር ብንወል ማን ተቆጭ አለን:: ጋዜጠኞቹ እንኳን ዘና ብለው መዘገብ የሚችሉት የሀገራቱን ዘገባ ጨርሰው ሜዲትራንያንን ሲሻገሩ ነው:: የሚቆጣቸው ፌዴሬሽን፣ የሚያ ስፈራራቸው ባለሀብት፣ የሚሰድባቸው ደጋፊ፣ የሚዝትባቸው ክለብ የለ:: እኛ ሀገርክ ኳሱ ለትንታኔ አይመችም፣ የኳሱም ሰዎች ለትንታኔ አይመቹ::

ስለ ጊዮርጊስ ከተቾህ «ፀረ ጊዮርጊስ» ትባልና መቆሚያ መቀመጫ ታጣለህ:: ስለ ቡና ከተናገርክ «ፀረ ቡና» ትባልና ምስህ ዱላ ይሆናል:: እንኳንስ ስትተቸው ስታመሰግነው እንኳን «ሦስት ጊዜ ምስጋና እንዱ ለነገር ነው» ብሉ በሚጠራጠርህ ሰው መካከል ሆነህ እንዴት ነው ስለ ሀገራችን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ክለቦች የምት ጨኔቀውና የምትደግፈው:: «ድጋፍ ተቃውሞን ካልፈቀደ፣ እንጀራ እርሾን ካልወሰደ» ምን ያደርጉልናል::

ሁለት የአውሮፓ ኃያላን ቡድኖች ከመጋጠማቸው በፊት እዚህ አዲስ አበባ ሆነን አሰላለፋቸውን እናውቀዋለን:: አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ማን ለማን እንደተሰለፈ በግልጽ ይታወቃል? በዛሬ ጨዋታ ለአርሴናል የተሰለፈው በቀጣዩ ጨዋታ አሠልጣኙ እንኳን ሳይሰማ ለማንቸስተር እየተሰለፈ መከራ አየንኮ:: እዚህ አዲስ አበባ ሆነን የተጨዋቾች የዝውውር መስኮት ሲከፈት ማን ወደ የትኛው ቡድን ሊሄድ እንደሚችል በግምትም፣ በፍ ንጭም፣ በመረጃም እንናገራለን:: መሄድ አለበት፣ የለበትም እያልን እንከራከራለን::

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም መስክ ማን ወደ የትኛው ቡድን ለመቀላቀል እንዳሰበ፣ እነማን ማንን እንዳስፈረሙ፣ ማን ከነማን ጋር ለመፈራረም ውስጥ ውስጡን እየመከረ እንደሆነ ማወቅ፣ ካወቁስ በኋላ ሃሳብ መስጠት ይቻላል? ይኼው ስንቶቹ መቼ እንደ ተነጋገሩና፣ መቼ ሃሳባቸውን እንደቀየሩ ሳናውቀው ለሌላ ቡድን ሲጫወቱ አገኘናቸው አይደል እንዴ:: አንዳንዶቹም ጭራሽ የነበሩበትን ቡድን ለቅቀው፣ እንዲያውም አብረዋቸው ከተጫወቱት ጋር ተጋጭተው፣ የሌላ ቡድን አሠ ልጣኝ ሲሆኑ ያየናቸው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በድንገት ነው:: የአውሮፓ ኳስ ቢሆን ኖሮ ቢያንስ ለመገመት በቻልን፣ ከተቻለም ፍንጭ ባገኘን ነበር:

ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ማንንም ሳይፈሩና ሳይሰቀቁ እንደ ልብ ሊያወሩበት እና ሊከራከሩበት የሚችሉት ጉዳይ የአውሮፓ ኳስ መሆኑን ታውቃላችሁ:: ብንደግፍ፣ ብንቃወም፣ የደገፍነውን ቡድን ዓርማ ብናውለበልብ፣ ማሊያውን ብንለብስ፡ ስለ እያንዳንዱ ነገር እያነሳን ብንፈልጥ ብንቆርጥ ማን ተቆጭ አለን:: እና እንደዚህ በነጻነት የሚወራ ጉዳይ ከየት ይገኛል ጃል:: አቦ ተውና::

ደጋፊም ተቃዋሚም መሆን እዚህ ሀገር ሰዳ ነው:: የመንግሥት ደጋፊ ነኝ ካልክ ገልማጭህ ብዙ ነው:: ተቃዋሚም ነኝ ካልክ የሚያጉረጠርጥብህ በዚያው ልክ ነው:: የአንዱን ማልያ መልበስ ቀርቶ ልትገዛ ስታገላብጥ ከታየህ መከራ ነው:: እን ኳንስ ስለ ተጨዋቾቹ እንሥቶ ለመነጋገር እና ለመተቸት ይቅር እና በቴሌቭዥን ሲቀርቡ እንኳን እነርሱን ትኩር ብለህ ካየህ አንዱ «ምን ታፈጣለህ» ይልሃል ሌላው ደግሞ «ምነው ሙድ ያዝኸርሳ» ብሎ ይተርብሃል:: በአውሮፓ ኳስ ግን ብት ደግፉ ተለጣፊ፣ ብትቃወሙ አደናቃፊ የሚላችሁ የለም::

ደግሞስ ደጋፊ እና ተቃዋሚ በአንድ አዳራሽ የሚሰ በሰብበት ይህንን የመሰለ ነገር ከየት ይገኛል:: ከመተራረብ፣



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመተቻቸት ያለፈ ሌላ ነገር የለ:: ርግጥ ነው እግር ኳስን በፖለቲካው መንገድ ለማስኬድ የሚፈልጉት እንዳንዶች ብጥብጥ እያነሡ ተቸግረን ነበር:: አሁን ግን ጋብ ብለዋል:: በኳስክ በዚ ህኛው ጨዋታ ካሸነፋችሁ እየጨፈራችሁ ቤታችሁ ትገባላችሁ፣ አንድ ሳምንት ትተነትናላችሁ፣ ከዚያ በኋላ ለቀጣዩ ጨዋታ መዘጋጀት ነው:: ትናንት አሸነፋችሁ ማለት ነገም ታሸንፋላችሁ ማለት አይደለም:: ብትሸነፉም ለጊዜው ትናደዱና እንደ ገና ለማሸነፍ መሥራት ነው:: ቴክኒክ እና ታክቲክ መቀየር፣ ሥልጠናውን ማጠናከር ብቻ ነው:: ትናንት ለምን እንዲህ ሆነ ብሎ መዝዝ ማለት የለም:: ሌላ ሌላውንማ ሲያሸንፍና ሲሸነፍ ምን እንደሚመስል እየነውክ::

ኧረ ለመሆኑ የእውሮፓ ኳስ ባይኖር ስለ ምን እናወራ ነበር:: ሰው ቋንቋ ኖሮት እንዴት ሳያወራ ይኖራል? ምሳ ሲበላ፣ ሻይ ሲጠጣ፣ ቡና ሲፈላ፣ በታክሲ እና በአውቶቡስ ሲኬድ ታድያ ምን ይወራ? ሁሉም ነገር ፖለቲካ በሆነበት ጊዜ ታድያ ምን እናውራ:: ጤፍ ተወደደ ፖለቲካ ነው፣ጤፍ ረከሰም ፖለቲካ ነው:: ሀገራችን አደገች ማለት ፖለቲካ ነው፣ ሀገራችን ወደ ኋላ ቀረች ማለትም ፖለቲካ ነው:: እገሌ ተሳስቷል ማለት ፖለቲካ ነው፣ ልክ ነው ብሎ መናገርም ፖለቲካ ነው:: ታድያ ምን እንበል?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ምን አባል ይሆናሉ? ማን ስምቶኝ ይሆናል? ተብሎ በሚጠራበት በዚህ ጊዜ እንደ ልብ የሚጠራ ነገር ማግኘት ቀላል ይመስል እንዴ! እኛ ተመልካቾች በሂደት አንድ የጥናት ውጤት አግኝተናል። ቢያንስ ስለ አውሮፓ አገር ኳስ ስታወራ የትኛውም የፓርቲ አባል እንደማይቆጣ:: አውሮፓውያን አትዮጵያውያን ቢሆኑ ኖሮ በስፔን ቡድን ላይ ትንት ስትሰነዝር የስፔን ኤምባሲ፣ በእንግሊዝ ቡድን ላይ ስትወርድበት የእንግሊዝ ኤምባሲ፣ የጣልያንን ቡድን ስታነሣ ጣልያን ኤምባሲ ኢያስቀ ምጡንም ነበር። አቦ እንኳን ኢትዮጵያውያን አልሆናችሁ፣ ተመችታችሁናል።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምን አደረግናችሁ?

*«ተመልከት፣ ተመልከት»* አለች ርግብ:: «ምኑን ነው የምመለከተው» ቁራ ነበር የመለሰላት:: «እነዚህ ሕፃናት የሚውሩትን አየህ?» አለችው:: ከዚያም ቀጠል ችና «አሁን ወሮቹ ምን አደረጓቸው? ለምን በወንጭፍ ያባርሯቸዋል፣ ለምንስ ይገድሏቸዋል? አሁን እነዚህ ሕጻናት ገና ከልጅነታቸው መግደልን ነው ወይስ ርኅራኄን ነው ባህል አድርገው ማደግ የነበረባቸው:: የሚገርመው ደግሞ በጎናቸው የሚያልፉት ዐዋቂዎች ምንም አይሏቸውም» ርግብ የኀዘን እና የንዴት ነበር ንግግሯ::

«ምን ብለው ነው የሚናገሯቸው:: እነርሱም እንዲሁ እየገደሉ ነው ያደጉት ከ:: «መግደል ያባቴ ነው» የሚል ዘፈን አልሰማሽም:: በእንስሳት መተረት ነው እንጂ ለእንስሳት ማዘን የሚባል ነገር እዚህ አገር ያለ አይመስለኝም:: እንጂ አሁን ምን አደረግናቸው? ለምን ይጨክኑብናል? ማንም ሰው መንገድ ሲሄድ ወይንም ቤቱ በር ላይ ሲቀመጥ ወይም ሲተክዝ ወፎ ችን ፊት ለፊቱ ካያቸው ድንጋይ እንሥት ማባረር ነው ቶሎ የሚመጣለት፣ ለምን? የጭካኔ ስሜት በሁሉም ውስጥ አለ ማለት ነው?» የቁራውን ንግግር መሬት ላይ ሆነው ሥጋ የሚ ሊቃቅሙ ውሾችም ሰሙት::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«ምን አደረግናቸው? እሌክ አውነትም ምን አደረግናቸው? እስቲ ተመልከቱ እንድ ምስኪን ውሻ አጥንት ፍለጋ፣ ማንንም ሳይተናኮል ዝም ብሎ ሲያነፈንፍ ቢገኝ፣ ያየው ሰው ሁሉ ድንጋይ እንሥቶ ለምን ያባርረዋል? ምን አደረገ? የሚሰሙኝ ወይም የሚናከስ ቢሆን ኖሮ ፈርተው ነው ይባላል፣ ነገር ግን ውሻ በመሆናችን ብቻ ለምን እንመታለን? ሰዎች ስለራሳቸው የመኖር መብት ብቻ ነው የሚያስቡትና የሚከራከሩት ማለት ነው? ደግሞም የሚገርመው፣ ይህ ጠባይ በልጁም በዐዋቂውም መኖሩ ነው?»

የውሻውን ንግግር ሣር የሚግጡ አህዮች እና ፈረሶች ሰሙት። አህያም በኀዘን «አህያ ሲያዩ ሰዎች ለምን ዱላ ትዝ ይላቸዋል? ምን አደረግናቸው? ይህችን ሀገርኮ ከእነርሱ ጋር አብረን ሠርተናል። መኪና የሚባል ይህችን ሀገር ከመርገጡ በፊት እህል አንግዘናል፣ ዛሬም እናጓጉዛለን። ለዚህች ሀገር ስንል ጦርነት ተዋግተናል፣ በጦርነት ሞተናል ቆስለናል። በርግጥ እኛ ምን ያህል እንደ ሞትንና እንደቆሰልን የሚመዘግብልን የለም እንጂ። ይህ ሁሉ ተረስቶ ግን ለምን ይጨክኑብናል። ዐፄ ምኒልክ እንኳን የአድዋ ጦርነትን ሲያውጁ «ዐመልክን በጉያህ፣ ስንቅህን በአህያህ ይዘህ ተከተለኝ» ነበር ያሉት። ዐዋጁ እኛንም ይመለከት ነበር። እኛም አብረን ዘምተናልኮ። ያ ሁሉ ስንቅ በምን ተጫነ? ያ ሁሉ መሣርያ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በምን ተማኒን? ያ ሁሉ ቱስለኛስ በምን ተማኒን? በኛ አልነበረም ወይ?» አለች ።

ወዲያው ፈረስ ቀበል አድርጎ «ካመጣሽውማ ጥሩ አድርገሽ አምጭው እንጂ። በአድዋ ጦርነትኮ አጤ ምኒሊክ 12 ሺ ፈረሰኛ፣ እቴጌ ጣይቱ 6 ሺ ፈረሰኛ፣ ራስ ሚካኤል 12 ሺ ፈረሰኛ ይዘው ነበር የዘመቱት። የሌሎቹን እግዜር ይወቅ። እነዚህ ሁሉ ፈረሶችኮ ለዚህች ሀገር ነጻነት እና ለቅኝ ግዛት አለመንበርከክ ዋጋ ከፍለዋል ማለት ነው። አራዳ መሐል ላይ ያለ ውን የዳግማዊ ምኒሊክ ሐውልት አታይም። እኛም አለንኮ። ከኛ ሥር ጉንጉን አበባ እያደረጉ እኛን ግን ይደበድባሉ።

ለመሆኑ ምን አድርገን ነው ያለ ርኅራኄ የምንደበደበው፣ ያለ ርኅራኄ ከዐቅማችን በላይ የምንጫነው፣ ከዐቅማችን በላይስ የምንጎትተው? የሰውን ያህል ባይሆንም መኖር የሚባለው መብት እኛን አይመለከተንም ወይ? አባ ዳኘው፣ አባ ዋጠው፣ ጠቅል፣ እየተባለ ለባላባቱና ለጀግኖቹ የፈረስ ስም ሲወጣ እንዳልነበር የፈረስ ውለታ እንዴት ይረሳል?»

«የቆሰለ አህያ እንዳይጫን ኮ እዚህ ሀገር ዐዋጅ ወጥቶ ነበር» አለች አህያ። «የት እዚህ ኢትዮጵያ» ፈረስ ጠየቀ። «አዎ እዚህ ኢትዮጵያ። ከ1660 እስከ 1674 ዓም የነገሡት ዐፄ ዮሐንስ ወይም ጻድቁ ዮሐንስ ስለ አህዮች ያወጡት ዐዋጅ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ንጉሡ በቤተ መንግሥታቸው በር ላይ አንድ ደወል ነበር:: ንጉሡ በቤተ መንግሥታቸው በር ላይ አንድ ደወል ነበራቸው አሉ:: ፍርድ የተጓደለበት፣ የተበደለና አቤት የሚል ሁሉ ያለ አጋፋሪ መጥቶ ደውሉን ይመታል:: ንጉሡም ወጥተው ጉዳዩን ያዩለታል::

ከዕለታት አንድ ቀን ደወሉ ተመታና ንጉሡ አሽከሬቻውን "ወጥተህ ተመልከት" አሉት:: ቢወጣ ሰው የለም:: "እረ ማንም የለም" አላቸው:: ደውሉ ግን መልሶ ተመታ:: "እስቲ በደንብ ተመልከት" ብለው መልሰው ሰደዱት:: ቢወጣ አሁንም ማንም ሰው የለም:: ንጉሡም "ታድያ ደውሉን ማን እየ መታው ይሬጭኸል" አሉት:: አሽከሩም "እንዲት አህያ እየታከከችው ነው ብሎ መለሰላቸው:: "እስቲ እምጣት እርሷምኮ በደል ይኖራታል" ብለው ላኩት:: ቢያመጣት ጀርባዋ የቆሰለች አህያ፣ ሌጣዋን እንደ ተሸከመች ትቷት፣ ባለቤቷ መጠጥ ቤት ገብቷል:: ንጉሡም "ታድያ ከዚህ በላይ በደል የት ይገኛል" ብለው ዐዋጅ በወጁ ይባላል::

«ምን የሚባል ዐዋጅ ነው ያወጁት?» አለ ፈረስ ገርሞት:: «"ከዛሬ ጀምሮ ጀርባውን የቆሰለ አህያ የሚጭን፣ የአህያውን ቍንት ሳያወርድ ወደ ቤት የሚገባ ሰው ይቀጣል" ብለው ነዋ»



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«ጽድቱ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ አሉ ሰዎች» ዶሮ ነበረች:: «እና ንተ ደግሞ እንዴው ምኑ ምኑ ያምራችኋል እቴ:: ዶሮ እንደ ከሰል በአይሱዙ መኪና ተደርድሮ ሞልቶ ሲጫን አላያች ሁም? ነገሩ ሰውም እንደዚያ ሲጫን ስላየሁ በዚያ አጽናና ለሁ:: ተምሯል የምትሉት ሰው እንኳን ከገበያ ገዝቶ ሲያመ ጣንኮ ቀና አድርጎ አይይዘንም:: በእናታችን ዘቅዝቆ እያስቃየ ነው የሚወስደን:: ጻሩ "እግር ወደላይ ትእዛዝ ከበላይ" እየተባለ የኖረ ማኅበረሰብ:: ሰውን በእናቱ ዘቅዝቆ ቶርች መምታት ታሪኩ የሆነ ማኅበረሰብ እኛ ዶሮዎችን እንደዚያ ማድረጉ ብዙም ሳይደንቅ ይችላል::

«አንዳንድ ጊዜማ ለኛም ለድመቶችም ዲቪ ቢኖር ምናለ እንላ ለንኮ፤ በዚያኛው ሀገር የድመት መብት ከሰው መብት ይበል ጣል እያሉ ያስቀኑናል:: እንዴው ከተኛንበት በድንጋይ እና በዱላ የሚቀሰቅሱን፣ ያየን ሁሉ "ሂጅ ብስ" እያለ የሚያባር ረን፤ ሕፃናቱ እንኳን ሲያድጉ ብትር ይሰጣቸውና "ሂድና ድመቷን ካ አድርጋት" ነው የሚባሉት:: መራራትን እና መክ ባከብን ሳይሆን መምታትን ነው የሚያስተምሯቸው:: በድሮ ጊዜ አይጥ የቤተ ክርስቲያኑን እና የቤተ መንግሥቱን ስታ እየበላ እንዳያስቸግር ድመት ለሚያረባው ሰው የሚሰጥ "የድ መት መሬት" የሚባል ነበር ይሉናል:: እኔ የዛሬውን ሳይ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እውነት እውነት አይመስለኝም፡፡ ለነገሩ እንኳን የኛ የሰንቱ መሬት ተወስዶ የለ»

«እንስሳቱን ብቻ አይደለምኮ» አለች ደግሞ መንገድ ዳር የበቀለች አበባ፡፡ «ያልለፋበትን፣ ያላስቸገረውን አበባ እና ዛፍ መንገድ ላይ ስላገኘው ብቻ ቆርጦ የሚሄድ ሰው አላጋጠማችሁም? አሁን ምን አደረግናቸው? ሲሆን መትከል የአባት ነው፣ መትከል ካልተቻለ ደግሞ ሰው የተከለውን መከባከብ ነው፣ ያም ካስቸገረ ደግሞ ቢያንስ አለማጥፋት ነው፡፡ እኔ ግን ሳስበው ሰው በውስጡ የአጥፊነት መንፈስ ተጠናውቶታል፡፡ ገና ለማላጋውን ዛፍ ምንም ሳያደርገው እንዲሁ ቆርጦ በእጁ እያወዛወዘ ይዞ መሄድ አሁን የጤና ነው ትላላችሁ?»

«አንዳንድ ጊዜኮ የዚህ ሀገር ሰዎች ማድነቅ ስለማይወዱ ነው መግደል የሚያምራቸው» ወሬውን ስትሰማ የነበረች ቢራቢሮ ነበረች ወደ ጨዋታው የተቀላቀለችው፡፡ የወፎቹን አፈጣጠር፣ የቢራቢሮዎቹን ቀለም እና ጠባይ ማድነቅ አይችሉበትም፡፡ ለልጆቻቸውም ማድነቅን አላስተማሯቸውም፡፡ አንበሳ ገዳይ፣ ነብር ገዳይ፣ ዝሆን ገዳይ እየተባሉ በመግደል ጀግንነትን የለመዱ ሰዎች እንዴት አድርገው ለእንስሳት ይራራሉ፡፡ "በለው፣ ግደለው" ብለው ለልጆቻቸው ስም የሚያወጡ እንዴት ለኛ ይራራሉ፡፡ ሕፃናቱ እንኳን ቢራቢሮ እና ንብ ሲያዩ ሁኔታችንን ተመልክተው ከማድነቅ ይልቅ በእጃቸው ይዘው ማሰቃየት፣



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በእግራቸው ረግጠው መግደል ይተናቸዋል:: ጠላጆቻቸው አሏ ነገሯቸውማ::»

«ይሄው በየትምህርት ቤቱ ዕጽዋቱን ዘር እያቀባበሉ የሚያሬ ቡት፣ አበቦችን የሚያወራርሱት ወፎች እና ነፍሳት ናቸው እየ ተባለ ትምህርት ይሰጣል:: የተለወጠው ግን በጣም ጥቂቱ ነው:: ምክንያቱም ቤት ውስጥ የሚነገረው ሌላ ትምህርት ቤት የሚነገረው ሌላ:: አንዳንድ ጊዜኮ ለሰው ልጆች ሕይወት የግድ አስፈላጊዎች መሆናችንን ያወቀልን ያለ አይመስለኝም:: እዚህች ምድር ላይኮ ተናንቀንና ተጨፋጭፈን ሳይሆን ተጋግዘን ነው መኖር የምንችለው:: አንድ ተረት ልንገራችሁማ»

«ምን?» አሉ ሲሰሟት የነበሩት ሁሉ::

እዚህ ደብረ ማርቆስ ውስጥ ደጃዝማች በሐዩ የሚባሉ ሰው ነበሩ ይባላል:: ጀግና የሥራ ሰው ናቸው አሉ:: ጎበዝ አርበኛ:: እዚያው ከተማ ውስጥ ደግሞ አለቃ ምሥራቅ የሚባሉ አካሏ ጉዳተኛ ሊቅ ይኖሩ ነበር:: አለቃ ምሥራቅ በዕውቀታቸው የሚመኩ ይህ ቀራቸው የማይባሉ የዘመኑ ሊቅ ነበሩ:: ታድያ አለቃ ምሥራቅ እና ደጃዝማች በሐዩ አይዋደዱም ነበር አሉ:: አለቃ ምሥራቅ «ይህ ከመግደልና ከመፎከር በቀር ምንም የማ ያውቅ ጨዋ» እያሉ ይነንቋቸዋል:: ደጃዝማች በሐዩም «ይሄ ግና ብዙ የሚቀረው፣ ወንዶች ከዋሉበት ውሎ የማያውቅ ደብ ተራ» እያሉ ይናገሯቸዋል::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሄ መንናኛ እየባስ መጣና ደጃዝማች ዐሐዩ እገባለሁ ብለው ተነሡ:: አለቃ ምሥራቅም "ድርም መገደል ነው የሚያውቀው" አሏቸው:: በመካከል ገላጋይ ገባና ደጃዝማች ዐሐዩን "ይተዋቸው እርሳቸውን ገድለው ጀግና ሳይባሉ ዝም ይበሏቸው" ብለው ዝም አሰኟቸው:: ደጃዝማች ዐሐዩ ለብዙ ጊዜ አለቃ ምሥራቅን ርግፍ አድርገው ረሷቸው:: በዚህ ጊዜ አለቃ ምሥራቅ በዝምታ መሸነፋቸው ገባቸውና የሚከተለውን ቅኔ በወረቀት ጽፈው ለደጃዝማች ዐሐዩ ላኩባቸው ይባላል::

«እኔም አንተን ሳከብር
አንተም እኔን አትናቅ
ተጣልተው አያውቁም ዐሐይና ምሥራቅ» ሰሚዎቹ ሁሉ የማርምት ሳቅ ሳቁ::

«ከዚያስ»

«ከዚያማ አለቃ ምሥራቅ የደጃዝማች ቤተኛ ሆነው ተከባብረውና ተፋቅረው ኖሩ ይባላል::»

«እና የቅኔው ሐተታ ምንድን ነው» አለ ፈረስ

«እኛም የሰውን ልጅ አክብረን፣ እርሱም እኛን ሳይንቅ ነው መኖር የምንችለው፣ በእን ስሳት እና በዕጽዋት ላይ መጨከን ይብቃ፣ እንተጋገዝ እንከባበር ነው»

«ይበል ይበል ይበል» ሁሉም አጨበጨቡ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# እውነት ይሆን እንዴ?

***ባለፈው ሳምንት*** ሳንዲያጎ በሚባለው እና በፓስፊክ ውቅያኖስ ዳርቻ «ቤይ ኤርያ» በተሰኘው አካባቢ፣ በሚገኝ ከተማ ነበርኩ። አንድ ከኬንያ በቅርብ ጊዜ የመጣ ወዳጄን አገኘሁና ስለ አንድ ሰው ጠየቅኩት። እጅግ ትክዝ ብሎ «እርሱንማ አስ ጠቆሩትክ» አለኝ። በሀገሩ ይትበሃል «ፕሮሰሱን አበላሹበት» ማለቱ ነው።

እኔም ደንግጬ «እንዴት» ስል ጠየቅኩት «አብሮት የሚኖረውን አገሬ የሚባለውን ልጅ ታውቀው የለም? ሲማሉ ጊዜ አሳይለም የጠየቀው ውሸቱን ነው። እርሱ እንዲህ እና እንዲያ ነው ብሎ ተናገረ፤ እስኪ ማራ ድረስ ብለው አዘገዩበት» ሲል መርዶ ነገረኝ። ያ ልጅ ሁሉም ነገር አልቆለት የበረራ ጊዜ ውን ብቻ እየጠበቀ መሆኑን ኢትዮጵያ እያለሁ ደውሎ ነግሮ ኛል። አሁን ምን ይጠቀማል? ፕሮሰሱን እርሱ አይድንዝበት? ይህንን የመሰለው ምቀኝነት ምን ያደርጋል? እያልኩ በውስጤ ማሰቡን ቀጠልኩ።

ይህንን የመሰሉ ታሪኮችን ዱባይም፣ ኬንያም፣ ደቡብ አፍሪ ካም እያለሁ እሰማ ነበር። እዚህ አሜሪካም ይህንን መሰሉን እርስ በርስ በምቀኛነት የመጠፋፋቱን ነገር እሰማማለሁ።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲያውም አንድ ሰው ኬንያ እያለሁ የነገረኝ ታሪክ ትዝ አለኝ:: ኬንያ የሚገኙ ስደተኛ ተቀብለው ወደ ተለያዩ ሀገሮች የሚ ልኩ ድርጅቶች ስደተኞች የሞሉት የፖለቲካ ጥገኝነት ጥያቄ እውነት መሆኑን የሚያጣራ ሰው ለየሀገሩ ስደተኞች ይመድባሉ::

ይህ ሰው ከሕዝቡ ጋር አብሮ እየዋለ ምን እንደሚወራ እያጣራ ለድርጅቶቹ መረጃ ይሰጣል አሉ:: ታድያ ለኢትዮጵያውያን ተብሎ የተመደበ ሰው የለም:: ለምን አልመደባችሁም? ሲባሉ «ኢትዮጵያውያን የእንዱን ጉዳይ አንዱ ስለማያጋልጠው ራሳቸው ሥራውን ሳንከፍላቸው ይሠሩልናልና መቅጠር አያስፈልገንም» አሉ እየተባለ ሲነገር ሰምቼ ነበር::

አንዳንድ ጊዜ ላለማደጋችን እና አንድ ሆነን ችግሮቻችንን በጋራ ላለመፍታታችን አንዱ ምክንያት ይህ የምቀኝነት አስተሳሰብ ይሆንን? እላለሁ:: አሁን እዚህ አሜሪካን አስቀድመው በአንድ መሥሪያ ቤት ረዥም ጊዜ ያገለገሉ ሰዎች ሌሎችን ሰዎች ለሌላ የሥራ ቦታ እንዲጠቁሙ ኃላፊዎቹ ዕድል ይሰ ጣሉ:: አሜሪካኖች በሰው በኩል «ሪኮሜንዴሽን» በሚቀጠር የሰው ኃይል ይተማመናሉ:: ይህንን መንገድ ሕንዶች፣ ቻይናዎች፣ ስፓኒሾች ተጠቅመውበታል:: ኢትዮጵያውያን ግን ሌላውን የሀገሩን ልጅ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠቂሞ ለማስቀጠር እንደማይፈልግ በየእት ባለሚው የምስማው ሮሮ ነው።

በሦስት ሺ ዘመን ታሪካችን ውስጥ እንድም እንኳን ሰረኛም ዘመን የኖረች ጠንካራ ከተማ ያጣነው ምናልባት ለዚህ ይሆን? ክርሱ ቀዳማዊ የሆነው መንግሥት ወይም ንጉሥ የሠራው ነገር እንዳለ ተቀምጦ ሰሙን ሲያስጠራው ከማየት፣ በዚያም ላይ ጨምሮ ከመሥራት ይልቅ የቀድሞውን አጥፍቶ፣ ርዝራዡ እንኳን እንዳይኖር አድርጎ ሌላ የራሱን ስም ማስጠሪያ መጀመር። አክሱምን ትተን ወደ ሮሐ፣ ሮሐን ትተን ወደ መንዝ፣ መንዝን ትተን እንጦራንዝ፣ እንጦራንዝን ትተን ጎንደር፣ ጎንደርን ትተን እንኮበር፣ እንኮበርን ትተን አዲስ አበባ ስንንከራተት ለምን ኖርን? ምናልባት እንዱ ያንዱን ካላጠፋ ወይንም ካልተወ፣ ካላስረሳ የማይረካበት የምቀኛነት ቁራኛ ይዞን ይሆን?

ልጅ ኢያሱ ያሠሩት የቀጨኔ መድኃኔዓለም የስማቸው መጠሪያ ሆኖ እንዳይኖር በዒ ኃይለ ሥላሴ የባይተዋር መቃብር እንዲሆን አድርገው ነበር። ለምን ቢባል የልጅ ኢያሱ ስም በምንም መንገድ በበጎ መጠራት ስለሌለበት፣ አሁንምኮ በፖለ ቲካችን ውስጥ የምንቃወማቸው ሰዎች ወይንም ድርጅቶች ስም በምንም ዓይነት በበጎ ሲጠራ የማየት ፍላጎቱ ያለን አይመስልም። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የምንቃወመው ወይንም የምንጠላው አካል ተለውጦ እና ተሻሽሎ፤ ወይንም የኛን ሀሳብ ተቀብሎ ከማየት ይልቅ ወድቆ እና ተንኮታኩቶ ማየቱ የሚያ ስደስተን ይመስለኛል::

አሁን በቀደም ዕለት እንዲት መናኛ፣ ነገር ግን ይህንን ጠባያችንን የምታሳይ ታሪክ ከአንዲት እኅት ሰምቼ ነበር:: ሁለት በፍቅረኛነት የከረሙ ወዳጆች ሳይስማሙ ቀርተው ተለያዩ:: ካልተስማሙ መለያየት ባሕል ሆኖ የለ:: ታድያ ወንዱ ሌላ ጓደኛ ይይዛል:: ፍቅረኛውም ያችን ጓደኛውን እየደወለች መከራ አሳየቻት:: እንዴት ከርሱ ጋር ትጀምሪያለሽ፣ ለኔ ያል ሆነ ላንቺ አይሆንም፣ ብትተይው ይሻልሻል፣ ወዘተ እያለች ትጨቀጭቃት ጀመር:: በወዳጅ በሽማግሌ ብታስለምናት ከርሱ ካልተለያየች አልተዋትም አለች:: በመጨረሻም በፖሊስ ኃይል እንዳትደውል ተወሰነባት::

ለምን ብዬ ጠየቅኩ:: በርግጥ በሰዎች ፊት በእኅትነት እና በወንድምነት አብረው ለመኖር ተስማምተው መለያየታቸውን ሽማግሌዎቻቸው ነግረውኛል:: ታድያ ለምን ይህንን አደረገች? ከምክንያቶቹ አንዱ ሊሆን የሚችለው ከርሷ በመለየቱ ሲወድቅ፣ ሲያዝን፣ ሕይወቱ ሲበላሽ የማየት ጉጉት ነው:: የኔን ትክክለኛነት የምመዝነው በነገሩ በራሱ ሳይሆን በተቃወመኝ ወይም በጠላኝ ሰው ውድቀት ነው ማለት ነው::

ትክክለኛነትነ የሚረጋገጠው ትክክለኛ አይደለም ያለኩት ሰው ሲወድቅ በማሳየት አይደለም። ነገሩን በማስረጃ እና በአመክንዮ በማቅረብ ነው እንጂ። እኔ እገሌ አልተስማሙምነ ተለያዩ፣ ተበታተኑ፣ ሊፈርሱ ነው፣ ገንዘባቸው ተበላ፣ ተጣሉ፣ ወዘተ ሲባል በዚያኛው ወገን ሆኖ ይቃወም የነበረው ሁሉ «አላልኩም ነበር» ለማለት ይዘጋጃል። ጥሩ ተሠራ፣ አደጉ፣ ተመነደጉ፣ ተባበሩ፣ አሸነፉ፣ ወዘተ ሲባልም ይከፋዋል። ከዚያም ወይ ውሸት ነው ይላል ያለበለዚያም ነገሩን መካድ ቢያቅተው እንኳን ያ የሆነው ነገር ሊጠላበት የሚችልበትን መንገድ ይፈልጋል። ለምን? ብንል የአውሬዎች ኮሚዴ በተባለ የጥንት መጽሐፍ ላይ፣

> አንድ ነገር ሲያምር ያዩሁት እንደሆን
> ያንን ካላጠፋሁ ከቶ ምንም ቢሆን
> እረፍት አላገኝም ዕንቅልፍ አይወስደኝም
> ቅን ነገር አይቼ እኔ አያስችለኝም፣

የተባለው ደርሶብን ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል።

እንዳንዴኮ የምናደንቃቸው ሰዎች፣ አርአያ የምናደርጋቸው ጀግኖች ያጣነውም በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም። ኅብዝ ነጋዴ ሲሆን አጭበርባሪ ነው፤ የማይሳደብ ጋዜጣ እና መጽሔት ሲሆን ተሞዳሙዶ ነው፣ ከመንግሥት ጋር የሚሠራ ባለሞያ ካለ የነ እገሌ አባል ሆኖ ነው፣ ኅብዝ ደራሲ ካለ ከውጭ ሰርቆ ነው፣ እያልን ስም እንሰጠዋለን እንጂ በርታ፣



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበዝ ማለት እናውቅበትም:: የሐዲስ ዓለማየሁን እና የበዓሉ ግርማን ስም እንኳን በክፉ የሚያነሡ ምሁራን ተተመውኛል::

የሙሉ የትምህርት ዕድል ከማግኘት በላይ ከኮሌጁ ባለሥልጣናት የትብብር ደብዳቤ ማግኘት ለምን ይከብዳል? ቢባል ከመተባበር ይልቅ ምቀኛነቱ እያየለ ነው:: ገንዘቡን ከየትም አምጥቶ ፋብሪካውን ከመገንባት ይልቅ የአንድን ባለሥልጣን ፊርማ ማግኘቱ ኢንቨስተሩን የከበደውኮ ጉቦው ብቻ አይደለም:: «ሊያልፍለት ነው አይደል» የሚለው ክፉ ሐሳብ ቀድሞ ስለሚመጣ ነው:: አንዳንድ ጊዜኮ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የም ርጫ ቦርድን ዕውቅና ከማግኘት የሌሎች ፓርቲዎችን ዕውቅና ማግኘቱ ይከብዳቸዋል:: ለምን ቢባል ሌሎቹ ወድቀው እኔ ካልቀረሁ ጉብዝናዬ ታድያ በምን ይለካል?

ሲያል ውስጥ የየሀገሩ ዜጎች በየራሳቸው ጉድጓድ ነው የሚገቡት አሉ:: ታድያ የሁሉም ጉድጓድ ሮጠው እንዳያመልጡ ሲባል ጠባቂ ተመድቦለታል:: የኢትዮጵያውያን ጉድጓድ ግን የለውም:: ለምን ቢባል «እኔ እነርሱ ጋ አንዱ እወጣለሁ ሲል ሌላው ጎትቶ መልሶ ስለሚያስገባው ጠባቂ አያስፈልጋቸውም እርስ በርሳቸው ይጠባበቃሉ ተብሎ ነው አሉ:: እውነት ይሆን እንዴ?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ቁንጮን ሲያታልሏት፣ ፓንክ ብለው ጠሯት

***አንድ የግብርና ባለሞያ*** የነገረኝን ታሪክ ባጫውታችሁ ደስ ይለኛል። ሰውየው የአንድ የግብርና ዩኒቨርሲቲ የታወቁ ተመራማሪ ናቸው አሉ። ታድያ የተሻለ ምርት የሚሰጥ የገብስ ዝርያ በምርምራቸው ያገኙና በባለሞያዎች እና በሚመለከተው አካል አስጸድቀው ወደ ገበሬው እንዲወርድ ይደረጋል። ገበሬውም የተሻለ ምርት የሚሰጥ ዘር በማግኘቱ ተደስቶ ዘራው። በቀጣዩ ዓመት ግን ገበሬው ዘሩን ተቀብሎ ለመዝራት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ።

ባለሞያዎች እና ባለሥልጣናት ተሰብስበው ወደ ገበሬው በመውረድ ለመዝራት ለምን ፈቃደኛ እንዳልሆነ ገበሬውን ጠየቁት። «የተሻለ ምርት የለውም?» አሉት። «አለው» አለ ገበ ሬው። «ታድያ ለምን አንዘራም አላችሁ» አሉና ጠየቁት። «ምርቱን ባልጠላነው ነበር። ነገር ግን የቀድሞው ገብስ በዘለላው ጫፍ እሾኻማ ነገር ስላለው ወፉን ይከላከልልን ነበር። ይኼኛው ግን የለውም። እናም እብዝተን ብናመርት ወፉ ተሻምቶ ከበላው ምን ዋጋ አለው? ብሎ መለሰ። ይህ ምርምር



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ የጎደለው ነገር መኖሩ የታወቀው ያኔ ነበር። ገበሬው ምን ዕውቀት እንዳለው አለመጠየቁ።

ዕውቀት በትምህርት ቤት ብቻ የሚገኝ፣ በዲፕሎማ ዲግሪ እና ዶክትሬት ብቻ የሚለካ አይደለም። መለኪያ ያልተገኘ ለት በትውልድ ብዛት የተከማቸ፣ ከመከማቸቱም በላይ በብዙ ትውልዶች ተፈትኖ ያለፈ ነባር ዕውቀትም አለ። የመመረቂያ ጽሑፍ ያልተሠራለት፣ በሳይንሳዊ ዘዴ ያልተተነተነ። በትወራ ያልተብራራ ነባር ዕውቀት አለ።

የብዙ ሀገሮች የዕድገታቸው መነሻ ይህ ነባር ዕውቀት ነው። ሌላ ነገር ከመደረጉ በፊት ያለው ነባር ዕውቀት በምርምር ይፈተሻል። ያለው እና የሚጎድለው ይታወቃል። ያለው ይዳብራል፣ የጎደለው ይሞላል። ከዚያ በፊት የነበረ የሰው ዘር ሳያስብ የኖረ ይመስል፤ ወይንም ደግሞ ዕውቀት በኛ ዘመን የተ ጀመረ ይመስል ያለፈው ሁሉ ተንቆ እና ተዋርዶ እንዲሁ ሁሉም ነገር ከአዲስ አይጀመርም።

አሜሪካን ሀገር እያለሁ ይቅርታ የጠየቅኩት አንድ ፍጡር አለ። ጤፍ ይባላል። የኢትዮጵያን ምሁራን፣ ጋዜጠኞች እና ተራቀቁ ትውልድ ወክዬ ነው ይቅርታ የጠየቅኩት። «ምንም ዋጋ የለውም፣ ሣር ብቻ ነው፣ ወደ ኋላ ያስቀረን እርሱ ነው» እየተባለ ከትውልድ ሀገሩ ከኢትዮጵያ ይሰደድ ዘንድ ግፊት ይደረግበት የነበረው ጤፍ አሜሪካ ገብቶ ሲከበር አየሁት። በታላላቅ ገበያዎች «ሊተካ የማይችል የብረት ማዕድን ያለው»



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሊበላ የሚገባው ጥንታዊ ምግብ» እየተባለ በ«እን ላይን» ገበያዎች ሲሸሞንሞንና አፍርንጅ ሲሻማበት ሳየው፣ «ወይ የጤፍ ግፍ የት ያደርሰን ይሆን» ነበር ያልኩት::

ሌላም ላንሣ እናቶቻችን ልጆቻቸውን በቤት ውስጥ ሆነው ማሳደጋቸውን እንደ ኋላ ቀርነት ነበር የቆጠርነው:: የቤት እመቤት መባል እና ማለት የሚያሳፍር እስኪሆን ድረስ በየስብሰባው ይሰበክ ነበር:: ዛሬ ግን ምዕራባውያን ልጆች ያለ ወላጆች ሱታፌ ሲያድጉ ምን እየሆኑ እንደሆን ገባቸውና እናቶችን «እባካችሁ ሠርታችሁ የምታገኙትን ያህል እንክፈላችሁ ቤት ተቀምጣችሁ ልጆችን አሳድጉ» አሉ:: ጉድ ነው::

በሀገራችን ምሁርነት እና ዐዋቂነት ላይ አንድ ክፉ በሽታ የገባ ይመስለኛል:: እኛ ጋ ያለ፣ ከወላጆቻችንም የወረስነው ሁሉ በወጭ ሀገር ሰው እና በውጭ ቋንቋ ካልተቀረበ በቀር ኋላ ቀር፣ ጎታች፣ ጥቅም አልባ ነው ብሎ ማሰብ:: ማሰብ ብቻ ሳይሆን በየአጋጣሚው መለፈፍ:: ምርምር ሳያደርጉ፣ ጥቅም እና ጉዳቱን ሳይተነትኑ እንዲሁ በእንግሊዝኛ የተጻፈ መረጃ ስለሌለው ወይም ደግሞ ፈረንጅ ስለማያውቀው ብቻ መተቸት:: አንዳንዴ እንዲያውም ሀገር በቀል ነገርን መናቅ የምሁርነት መለኪያ የሚመስልበትም ጊዜ አለ::

ዛሬ ዛሬ እንደ አዲስ ግኝት በውበት መጠበቂያ ቤቶች የምናገኘው አንድ ነገር አለ:: እኅቶቻችን ውኃ መልሶ የታጠበ እግራቸውን እንዳይነካው የእግር ማስቀመጫ ያለው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

መታጠቢያ / መዘፍዘፊያ:: ይህ ዓይነቱ መዘፍዘፊያ ከ1900 ዓመታት በፊት የአኩስም ሰዎች በሸክላ ሠርተው ይጠቀሙበት እንደ ነበር በአኩስም ሙዝየም የተቀመጠው የቁፋሮ ግኝት ያስረዳል::

ሙዝየሙ ከተከፈተ ከሠላሳ ዓመታት በላይ አልፈዋል:: አያሌ ባለሞያዎች ጎብኝተውታል:: ፈረንጆች ሠርተው እስኪያመጡት ግን አንድም ኢትዮጵያዊ ያንን ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የደፈረ የለም:: ለምን? ለኔ እንደሚመስለኝ የኛ የሆን ሁሉ ያለ ምርምር ስለሚጣጣል ነው::

ሰው በምድር ሲኖር ሳያስብ አይኖርም:: የአካባቢውን ችግር ለመፍታት እና የተሻለ ዓለም ለማየት ሲል ይመራመራል:: በዚህ ምርምሩም የራሱን ግኝት ያገኛል:: እነዚህንም ለትውልድ በልዩ ልዩ መንገድ ያስተላልፋል:: ያ ትውልድ የኖረበትን መንገድ፣ ያገኛቸውን ነገሮች እና የሚጠቀምባቸውን ሀብቶች ከራሱ ከባለቤቱ አግኝቶ፣ ምን እንደሚያስብም ሰምቶ እና ተረድቶ፣ መርምሮ እና ተንትኖ ይህ ይሳሳል ይህ ደግሞ ይጠቅማል ብሎ መነሣት እንጂ እንዴው ዘመናዊ ትምህርት ያል ተማረ፣ እንግሊዝኛ ያልተናገረ፣ ገጠር ተወልዶ ያደገ ሁሉ ኋላ ቀር ነው ብሎ ማሰብ ራሱ ኋላ ቀርነት ነው::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ትግራይ ውስጥ የተፈጸመ አንድ ታሪክ በውቃለሁ። ከመሐል ሀገር የሄዱ መሐንዲሶች መንገድ እየሠሩ ነው። በመንገዱ ማለፊያ ላይ በበጋ የሚደርቅ በክረምት የሚሞላ አነስተኛ ወንዝ ይታያል። ባለሞያዎቹ መጠነኛ የሆነ ቱቦ ቀብረው ድልድይ ሳይገነቡ ለማለፍ ወሰኑ።

ገበሬዎቹ ግን «ይህ ወንዝ በክረምት ዓባይን ያስንቃልና እርኝ ችንን ታጠፉብናላችሁ» ብለው ተሟገቱ። የተቀበላቸው አልነበረም። አንዳንድ የአካባቢው ባለሥልጣናት ተጨምረውበት በጫና ቱቦው ተቀበረ። በክረምቱ ወቅት ገበሬዎቹ እንዳሉት ከደጋ የጣለው ኃይለኛ ዝናብ አካባቢውን አጥለቅልቆ በለመ ደው መንገድ ሊያልፍ ሲመጣ እንደ ዜና ማርቆስ አጣብቂኝ የጠበበ ቱቦ ይገጥመዋል። መጀመርያ በአካባቢው ከተንሰራፋ በኋላ መንገዱን ሰብሮት ተጓዘ። ያኔ ነበር ባለሞያዎቹ ገበሬ ዎቹ ትክክል መሆናቸውን ያመኑት። እነዚህ ገበሬዎች በዚያ አካባቢ ተወልደውበታል፣ ኖረውበታል፣ አካባቢያቸው የሕይወታቸው አካል ነው። ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ የተቀበላቸው ግን አልነበረም። አዳፋ ልብስ ስለለበሱ፣ ምናልባትም ባለሞያዎቹ በሚናገሩበት ቋንቋ ስለማይናገሩ፣ ወይንም በ«ሳይንሳዊ» መንገድ ስላልተነተኑ አያውቁም ተባሉ። ነገሩ ለወገናችን ክብር አለመስጠት፣ የማያስብ እና የማይጠቅም አድርጎ የመገመት አባዜ ውጤት ነው።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ዲክተር ፈቃደ እዚህ ሥነ ቃል ሲያስተምረን የተናገረውን እዚህ ላይ ብነሳው ቅር አይለውም:: «ሰሜን ሸዋ ለአንድ ጥናት ሄደን ነበር» አለ:: «እዚያም ከተለያዩ ሰዎች መረጃ ለመሰብሰብ ስለፈለግን ገበሬዎችን ሰብስበን «ከሁላችሁም መረጃውን መሰብሰብ ስለማንችል ከመካከላችሁ 'ራንደምሊ' ሰዎችን እንወስዳለን» ብለን ነገር ናቸው::

ገበሬዎቹ ግን 'ራንደምሊ' ማለት ምን ማለት ነው ብለው ጠየቁን:: እኛም በብዙ ምሳሊ ለማስረዳት ደከምን:: በመካከልም አንዱ ገበሬ «በ ብዲግ ብዲግ ማለታችሁ ነው እንዴ» ብሎ ትክክለኛ የአማርኛ ትርጉሙን ነገረን» ብሎን ነበር::

የምዕራብ ዓለም ሰዎች ከሚቸገሩበት ነገር አንዱ ጭንቀት ነው:: ይህም ማኅበራዊ ርካታ እና የአእምሮ ፋታ ካለማግኘት የሚከሰት ነው:: በተዘጋ ቤት ያለ ማኅበራዊ ተራክቦ የሚኖርበት የምዕራብ ሥርዓተ ኑሮ ከፈጠራቸው አሉታዊ ነገሮች አንዱ ጭንቀት ነው:: በተለይም ታምመው የተኙ ሕሙማን ጠያቂ ስለሌላቸው ከሕመሙ ጭንቀቱ ይብሳቸዋል:: በዚህ የተነሣ ለጠያቂ ተከፍሎ እንዲጠየቁ እስከመደረግ ተደርሷል::

ለንበቴያችን፣ ዕድራችን እና የቡና ሥርዓታችን ለማኅበረሰባችን የሰጠውን ጥቅም የተረዳሁት ያኔ ነበር:: በአንድ ብር ቡና ሠፈር ጎረቤቱ ተጠራርቶ የአካባቢውን ጉዳይ ተወያይቶ፣



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ተጫውቶ እና ተዝናንቶ፣ ጭንቀቱን አራግፎ እና ድህነቱን ረስቶ መለያየቱ ፈውስ ነበር ለካ::

በቡናው ሥርዓት ሐሜት ካለ ሐሜቱን እናጥፋ እንጂ ይህንን ታላቅ ማኅበራዊ ሥርዓት አብረን ለምን እናጠፋዋለን? ተባይ በፀጉር ውስጥ አለ ተብሎ አንገት ተቆርጦ ይጣላል እንዴ?

ከዓለም ወደ ኋላ የቀረን፣ ዕድገታችንም ገና የሚያዘግም፣ ራሳችንንም በሚገባ መመገብ ያልቻልን እንሆን ይሆናል:: አሁንም ለራሳችን ዋጋ ሰጥተን ያለንን እና የሌለንን መለየት ካልጀ መርን:: ለቀደምቶቻችንም ዋጋ ካልሰጠን ወደፊት መሠልጠናችን ቀርቶ በትክክልም ወደ ኋላ መሄዳችን ያጠራጥራል:: ያለፈውን ሁሉ እንዳለ አፈራርሶ እንደ አዲስ መገንባት፣ የቀደ ምቱን በደምሳሳው አቃልሎ መሠረት አልባ ሥልጣኔን መና ፈቅ፣ ያሳደገው ሀገርም ሆነ ያሠለጠነው ሕዝብ የለም::

ይኼው እኛ ያቃለልነው የገና ጨዋታ የኦሎምፒክ ስፖርት ሆነ:: እኛ ትኩረት የነፈግነው የትግል ጨዋታ ለቻይና የሚ ዳልያ መዓት መሰብሰቢያ ሆናት:: «ቁንጮን ሲያታልሏት ጉንክ ብለው ጠሯት» እንዳሉት ያራዳ ልጆች የገጠር ናት ተብላ የተናቀች ቁንጮ ጉንክ ሆና ስትመጣ ሁላችንም ተረባ ረብንባት:: ታድያ ሌላው ሀብታችንም እንድንቀበለው አው ሮፓ እና አሜሪካ እየደረሰ መመለስ አለበት ማለት ነው?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ዝምታ ወርቅ አይደለም

ሰውየው ከሚስቱ ሌላ አንዲት ሴት ወደደና እፍ ክንፍ አለ:: ልጁን እና ሚስቱን እየተወ ከዚህችኛይቱ ጋር ማምሸት፣ ብሎም ማደር ጀመረ:: በመጨረሻም አንድ ቀን ወደ ሚስቱ መጣና ድንገተኛ የሆነ ጥያቄ አቀረበ:: «እኔ እና አንቺ እንድ ንፋታ እፈልጋለሁ፤ ለምን ብለሽ ምክንያቱን አትጠይቂኝ:: መፋታት ብቻ እፈልጋለሁ:: ደግሞም ሌላ ቀን አይደለም፣ ነገ እንዲሆን እፈልጋለሁ» አላት:: ሚስቱ በሁለት ነገሮች ተጨነቀች:: በአንድ በኩል ምንም ነገር አትጠይቂኝ ብሏታል:: በሁ ለተኛ ነገር ልጇ ወደ ዩኒቨርሲቲ የመግቢያ ፈተና ልትቀመጥ ጥቂት ቀናት ቀርቷታል::

«ባልፈልገውም፣ ባልስማማበትም፤ ካልክ የግድ እቀበለዋለሁ:: ነገር ግን በኛ ምክንያት ልጃችን መጎዳት የለባትምና የአንድ ወር ጊዜ ያህል እንታገሥ::» አለችው:: እርሱም አሰበና «ጥሩ አንድ ወር መታገሥ አያቅተኝም፤ ነገር ግን በዚህ አንድ ወር ውስጥ ሽማግሌ መላክ፣ ምክንያቱን መጠየቅ የለም፤ ስለ ፍቺው ማናችንም ምንም ነገር ማንሣት የለብንም፤ በዚህ ቃል ግቢ» አላት:: እርሷም «እስማማለሁ፤ ግን አንተም የምነግርህን ለመፈጸም ከተስማማህ ነው፤ ታድያ በዚህ አንድ ወር ጠዋት



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠዋት ከዕንቅልፉ ስነሣ፣ ማታ ማታም ወደ አልጋዬ ስሄድ ያኔ የሡርጋችን ዕለት አቅፌህ እንደ መሰድከኝ አድርገህ አቅፌህ ትመስደኛለህ» ስትል ጠየቀችው:: ነገሩ ያልጠበቀው እና ያልተለመደ ዓይነት ቢሆንበትም፣ ቀላል እና ሊያደርገው የሚችል ስለሆነ እሽ ብሎ ቃል ገባላት::

አንዱ ወር ተጀመረ::

ጠዋት ጠዋት ከዕንቅልፏ ስትነሣ አቅፎ፣ ከፍ አድርጎ፣ ወደ በረንዳ ካደረሳት በኋላ ወደ ሥራው ይሄዳል:: ማታ ማታም እንዲሁ አቅፎ ወደ አልጋዋ ይመስዳታል:: ስለ ፍቾው አይነጋገሩም:: እየዋለ እያደረ ሲሄድ የሰውነቷ ጠረን፣ የምትለብሳ ቸው ልብሶቿ፣ የዓይኖቿ እና የፀጉሯ ሁኔታ፣ የገላዋ ልስላሴ እና የአካሏ ቅርጽ እየሳቡት መጡ:: በየቀኑ እያቀፈ ሲያወጣት እና ሲያስገባት ሰውነቷ እየቀለለው፣ እርሷን አቅፎ መሸከሙም እንዳች እንግዳ የሆነ የደስታ ስሜት እየፈጠረለት መጣ::

ከራሱም ጋር መጣት ጀመረ:: «ለምንድን ነው እንዲታ ያልኳት፣ አሁን የሚሰማኝን ስሜት ያህል ስሜት ከአዲሷ ወዳጄ ጋር ለምን አይሰማኝም? ለምንስ ነበር ይህንን ነገር እንዳደ ርገው ቃል ያስገባችኝ? ይህን የመሰለውን ገላዋን፣ እንዲህ የሚማርከውን ጠረንዋን፣ እንዲህ የሚያስደስተውን ፈገግታ ዋን፣ እንዲህ የተዘናፈለውን ፀጉሯን፣ እንዲህ ልዩ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የሆነውን እካሷን እንዴት እስከ ዛሬ አላስተዋልኩትም? እርሷ ናት ከኔ ጋር የነበረችው ወይስ እኔም ከርሷ ጋር ነበርኩ?»

የወሩ መጨረሻ እየደረሰ መሆኑን ሲያውቅ ከእርሷ መለየቱ ጨነቀው:: እንዲያውም ይህ ሁኔታ የፈጠረበትን እንግዳ ስሜት እየወደደው መጣ:: ነግቶ እና መሽቶ እርሷን አቅፏት እስከሚወስዳት በጉጉት መጠበቅ ጀመረ:: በሌላም በኩል ደግሞ በዚህ ድርጊቷ በውስጡ ያሳደረችበትን ስሜት እያሰበ ያደንቃትም ጀመር:: ብልህነቷን፣ አስተዋይነቷን እና በቀላል ድርጊት ቀልቡን ልትገዛው መቻሏን ሲያስበው «ምን ዓይነት አስገራሚ ሴት ናት?» ይላል::

ወሩ ሊያልቅ ሁለት ቀን ሲቀረው የመፋታቱን ሃሳብ በውስጡ መረመረው:: ነገር ግን አላገኘውም:: በዚህ ሁኔታ መፋታቱ ደግሞ ለሕይወቱ የማይፈታ ዕንቆቅልሽ እንደሚሆንበት እያሰበ ተጨነቀ:: በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ አንድ ወር ውስጥ ፍቅን በተመለከተ ባለመነጋገር ቃል ተግባብተዋልና እንዴት እድርጎ ይናገር:: ዛሬም በደስታ ስሜት አቅፎ ከአልጋዋ እንደወሰዳት ሁሉ ማታ ወደ አልጋዋ መለሳት፣ ከበፊቱ እጅግ በጣም ቀለለ ችው፤ አላዘነችውም::

በወሩ መጨረሻ::

ወደ አዲሲቱ ወዳጁ ዘንድ ሄደና «የፍችውን ሃሳብ ሠርዤ ዋለሁ:: እኔና ባለቤቴ ፍቅር የሌለን መስሎኝ ነበር:: እኛ ግን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ለካስ ፍቅር አላጣንም:: ያጣነው ሁለት ነገሮች ብቻ ነው:: መነጋገር እና መቀራረብ:: ለዚህ ያደረሰንም መቀራረባችን እና አለመነጋገራችን ብቻ ነው:: አሁን ግን መነጋገር ባንችል እንኳን መቀራረብ ግን ችለናል:: ዛሬ ደግሞ መነጋገር እንችላለን:: ስለዚህ ሌላ የሚሆንሽን ፈልጊ» አላት::

ሲትዮዋ ተናደደችና በጥፊ መታችው፤ ከአጠገቧ የነበረውንም ውኃ ቸለሰችበት፤ «ይሄ ለብዙው ኃጢአቴ የተከፈለ ቅጣት ነው» እያለ ወጥቶ ሄደ:: ከዚያም ወደ አበባ መሸጫ ሱቅ ውስጥ ገባ:: ያኔ ሲጋቡ የገዛላትን ዓይነት አበባ ገዝቶ ወደ ቤቱ ከነፈ:: «ጓደኛዬ ትዳር ማለት አግብተው የሚኖሩት ሳይሆን በየጊዜው የሚጋቡት ነው ያለው እውነቱን ነው:: ትዳር እንደ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ፈተና አንድ ጊዜ አልፈውት ሰርተፊኬቱን የሚሰቅሉት አይደለም ያለው እውነቱን ነው:: ትዳር እና ተክል ክብካቤ ይፈልጋሉ:: እንዲሁ ቢያድጉ ይደጉ ተብለው የሚተው ነገሮች አይደሉም::

«ልክ እዚህ ሀገር ችግኝ የመትከት፣ የማጠጣት፣ የመንከባከብ እና የማሳደግ እንጂ የመትከል ችግር እንደ ሌለብን ሁሉ እኛም ጋር የመጋባት ችግር የለም:: ፍቅር ግን ማግባትን ብቻ ሳይሆን ማጠጣትን፣ መኮትኮትን፣ ማረምን፣ ከብት እንዳይበላሸው አጥር ማጠርን፣ በየጊዜው ማዳበርያ መጨመርን ጭምር ይፈልጋል:: በርግጥ በዕድሉ የሚበቅል ዛፍ እንዳለው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉ በእድሉ የሚኖር ትዳርም ይኖር ይሆናል:: ይህ ግን ሕይወትን ለራስ ጥረት ሳይሆን ለአጋጣሚዎች ብቻ አሳልፎ መስጠት ነው» ያለው እውነቱን ነው:: እኔ አልሰማሁትም እንጂ እርሱስ ተናግሮ ነበር::»

መኪናውን አቆመና ወደ ግቢው ውስጥ ገባ:: በረንዳ ላይ ትጠብቀው የነበረችው ባለቤቱ የለችም:: በሩንም አንኳኳ:: የሚከ ፍት ግን አልነበረም:: ደግሞ ሲያንኳኳ ገርበብ ብሎ የተዘጋው በር በራሱ ጊዜ ተከፈተ:: ባለቤቱ ግን በዚህች በወሩ ሠላሳኛ ቀን ሳሉንም የለችም:: እየተገረመም፣ ግራ እየተጋባም ወደ መኝታ ቤቱ ዘለቀ:: አልጋው ላይ ፊገግ እንዳለች ጋደም ብላ ለች:: አበባውን እንደ ያዘ ጠጋ አለና በእጁ ጉንጯን ነካው:: ቀዝቅዟል:: በቁልምጫ ጠራት:: መልስ ግን አልነበረም:: ግራ ተጋብቶ ዓይንዋን ገለጥ አደረገው:: ሊገለጥለት ግን አልቻ ለም፤ በርከክ አለና ሰውነቷን ደባበሰው፤ ቀዝቅዟል::

«የመጨረሻው ቀን ነው፤ ደህችን ቀን ማየት አልፈልግም፤ ለልጄ ስል እስከዛሬ ታግሻለሁ፤ በቃኝ» የሚል ጽሑፍ ራስጌዋ ላይ አገኘ::

እርሷ ፍችውን አትፈልገውም፤ ስለዚህም ሳትፋታ ሞተች:: በርሱ ውስጥ የነበረውን የሐሳብ ለውጥ አላወቀችም፤ እርሷ ምክንያቱም ሳይነጋገሩ ቃል ተግባብተው ነበርና::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የዛሬዋን ቀን በስጋት እና በጭንቀት ነበር የጠበቁቻት። የመለያያቸው ቀን፣ የሕይወቷን ግማሽ የምታጣበት ቀን። የማትፈልገውን ነገር የምታደርግበት ቀን ናትና። እርሱ ግን የዛሬዋን ቀን በጉጉት ነበር የጠበቃት። የሚነጋገሩባት ቀን፣ ፍችውን እንደ ተወው የሚነግርባት ቀን፣ ፍቅሩን የሚነግርባት ቀን፣ ይቅርታ የሚጠይቅባት ቀን፣ ለፍቅሩ ሲል ትንሽም ብትሆን ቅጣት ከፍሎ የመጣባት ቀን፣ በእርሱ እና በባለቤቱ መካከል የመነጋገር እና የመቀራረብ እንጂ፣ የመዋደድ እና ስሜት ለስሜት የመስማማት ችግር እንደሌለ መረዳቱን የሚገልጥባት ቀን ናትና። ግን ምን ያደርጋል፣ ሁለቱም ይህንን በየልባቸው ያው ቁታል እንጂ አልተነጋገሩም፤ ሃሳባቸውንም በሌላ መንገድ አል ተለዋወጡም። በዚህ የተነሣም በችግሩ መፍቻ ቀን ዋናው ችግር ተፈጠረ።

ሁለት የትዳር ነቀርሳዎች:- አለመቀራረብ እና አለመነጋገር። አብረው አንድ አልጋ ላይ እያደሩ፣ አብረው እየበሉ፣ አብረው እየኖሩ የማይቀራረቡ ባል እና ሚስት አሉ። አንድ አልጋ ላይ የሚተኙት አንድ አልጋ ላይ መተኛት ስላለባቸው ብቻ ነው፣ ከመጋባታቸው በፊት የነበራቸው ጉጉት እና ናፍቆት አሁን የለም። ሳይተኙ እንቅልፍ ይወስዳቸዋል። አብረው ይበላሉ፣ በአንድ ማዕድ መሆኑ፣ አንድ ጠረጴዛ ላይ መሆኑ እንጂ ያኔ በፊት ለምሳ ሲገባበዙ የነበረው ናፍቆት እና ጉጉት የላቸውም። ዝም ብሎ መብላት ብቻ።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እያንዳንዷን ቀን ልዩ፣ ደስታ የሚፈጠርባት እና ከትናንት የተለየች ለማድረግ አይጥሩም:: ዛሬም እንደ ትናንቱ፣ ነገም እንደ ዛሬ ነው::

*ወትሮ ለመኖ ወትሮ ጥየቃ፣*
*ወትሮ ደጅ ጥናት ወትሮ ጥበቃ፣*
*ከንግዲህ ምን ቀረሽ አግብተሽ በቃ፣*

እንደተባለው ይሆንባቸዋል:: አገባኋት በቃ፣ አገባሁት በቃ፣ ከንግዲህ ምን ቀረ? ብለው ያስባሉ:: ሰው ተፈጥሮ አባለቀም:: በየጊዜው ነው የሚፈጠረው:: ፈጣሪም ሰውን እንደ ተወለደ እንዲያልቅ አላደረገውም:: በየቀኑ፣ በየሰዓቱ፣ በየደቂቃው ባለተዋለው ሰው እንግዳ ፍጥረት ነው፤ አዳዲስ ነገር ይታይበታል:: ይህ ግን መቀራረብን ይጠይቃል:: ባል እና ሚስት ከተቀራረቡ ሳይፋቱ በየቀኑ ይጋባሉ፤ ጋብቻቸው እየታደሰ ይሄ ዳል:: የትናንቷ ሚስት ከዛሬዋ ትለያለች፤ የዛሬው ባልም ከትናንቱ የተለየ ነው:: ለውጥ፣ ዕድገት፣ ብስለት፣ አለ:: መል ክም ተለውጧል:: ግን ቀርቦ የሚያየው ያስፈልገዋል::

የዚያ ባል ችግሩ ሚስቱን አግብቷት እንጂ ቀርቧት አያውቅም ነበር:: አብሯት ይኖራል እንጂ ከርሷ ጋር አይኖርም ነበር፤ ምድር በፀሐይ ዙርያ ስለምትዞር ይመሻል ይነጋል እንጂ በእነርሱ የተለየ የሕይወት ጉዞ ምክንያት አይመሽም አይነጋም:: በማክሰኞ እና በረቡዕ መካከል ከስሙ በቀር በሕይወታቸው ውስጥ ልዩነት የለውም::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሌላው ችግር ደግሞ ያለ መነጋገር ነው:: መነጋገር ማለት በማያውቁት ቋንቋ ማውራት ማለት አይደለም:: እርሱንማ ከብትም ሲገናኝ እምቧ እምቧ ይባባላል:: ይህ ግን መነጋገር አይደለም:: በየጊዜው፣ በየሰዓቱ፣ ሁለመናን መለዋወጥ ማለት ነው:: ካልተነጋገሩበት የምሥራች፣ የተነጋገሩበት መርዶ ይሻ ላል:: ካልተነጋገሩበት ፍቅር የተነጋገሩበት ጠብ ይበልጣል:: ካልተነጋገሩበት ስጦታ የተነጋገሩበት ንጥቂያ ይሻላል::

ባል እና ሚስቱ ባለመነጋገራቸው ችግሩን በሁለት አቅጣጫ ፈቱት:: የሁለቱም ፍላጎት ችግሩን ላንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ መፍታት ነበር:: የሁለቱም ፍላጎት ፍቺ የሚባለውን ነገር ላለ ማየት ነበር:: የሁለቱም ፍላጎት ሠላሳኛዋን ቀን መገላገል ነበር:: ነገር ግን ባለ መነጋገር ምክንያት በሁለት አቅጣጫ ሆነ:: እርሷ ሞትን መረጠች፣ እርሱ ደግሞ ይቅርታን መረጠ:: ችግሩ የመጣው በዚህ ጉዳይ ላለመነጋገር ሲወስኑ ነው:: እርሷ በጉዳዩ ትጨነቃለች፤ ለምን ይሆን ከኔ መለየት የፈለገው? የሚለው ጥያቄ ያሳስባት ነበር:: በሃሳብ ብዛትም እየከሳች ሄዳ ነበር:: ለዚህም ነበር በየቀኑ ሲያቅፏት ትቀልለው የነበረው:: እርሱ ግን መቅለሷን እንኳን ለመጠየቅ ፈራ:: እርሱ ከራሱ ጋር እንጂ ከእርሷ ጋር አይነጋገርም ነበር::

እናም አንዳንድ ጊዜ አስፈላጊ ቢሆንም እንኳ፤ በትዳር ውስጥ ግን ዝምታ ወርቅ አይደለም::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# 171ኛው ሆስፒታል

በዓለም በደረጃው 171ኛ በሆነው ሆስፒታል ውስጥ ነው ከዚህ የሚከተለው ታሪክ የተፈጸመው:: ይህ ሆስፒታል ዛሬ አንድ መቶ ሰባ አንደኛ ይሁን እንጂ እጅግ ገናና የሆነ ታሪክ እና ዝና የነበረው ነው:: እያሌ ከባድ በሽታዎችን ድል እየመታ፣ ታላላቅ ሰዎችን እያፈራ፣ ለአንድም ቀን በበሽታ ላይ ደፈር የኖረ ሆስፒታል ነው – 171ኛው ሆስፒታል::

አንድ ቀን የሆስፒታሉ አምስት ሠራተኞች ሻሂ እየጠጡ የቆጥ የባጡን ይጨዋወቱ ነበር:: በመካከል ላይ «እኛ ለብዙ ዓመታት በዚህ ሆስፒታል ውስጥ እየሠራን ነው፤ ሆስፒታላችን ግን እናውቃለን በ^ሚሉ ጥቂት ዶክተሮች የተያዘ ነው:: እነዚህ አምስት እና ስድስት ዶክተሮች ብቻ ናቸው ቀዶ ሕክምና እያደረጉ የሚያከሙት:: በዚህ ምክንያትም ገንዘብ፣ ስም እና ዝና ያገኙት እነርሱ ብቻ ናቸው:: ይህ የጥቂት ዶክተሮች አስተዳደር ማብቃት አለበት:: ሁላችንም ይህ ዕድል ያለ አድልዎ ሊሰጠን ይገባል» የሚል ሐሳብ አነሡ:: ይህ ሐሳብ እንደ ሰደድ እሳት በሆስፒታሉ ውስጥ በአንድ ጊዜ ተነዛ:: የጥበቃ ሠራ ተኞች፣ ጸሐፊዎች፣ የጤና ረዳቶች፣ መገንገብ ቤቶች፣ አትክል ተኞች፣ ምግብ ቤቶች፣ ፋርማሲስቶች፣



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የጥገና ባለሞያዎች፣ ማኅሮ ነፍሶሎች፣ ሌሎችም በመደገፍ ተነሡ:: «ከዚህን በኋላ የጥቂት ዶክተሮች ሐሳቡን ዘመን ማብቃት አለበት» የሚለው መፈክር ይስተጋባ ጀመር::

በሦስተኛው ቀን ሠራተኞቹ ማኅበር አቋቋሙ:: የማኅበሩ ሊቀ መንበርም የሆስፒታሉን ባልደረቦች ለስብሰባ ጠራ:: «ዛሬ የተሰበሰብነው ለለውጥ ነው:: ይህ ሆስፒታል ከተቋቋመ አያሌ ዘመናት ተቆጥረዋል:: እስካሁን ሕመምተኛውን ቀደ ሕክምና እያደረጉ ስም እና ዝና ያተረፉት፣ ዳጎስ ዳጎስ ያለ ደመወዝም የሚያገኙት ጥቂት ዶክተሮች ናቸው:: ይህ ሁኔታ ማብቃት አለበት:: እኛስ በምን እናንሳለን:: ሁላችንም የሆስፒታል ሠራተኞች መባላችን ካልቀረ ዕድሉ ሊሰጠን ይገባል:: ለዚህ ነው የጠራናችሁ» በማለት ሰብሳቢው ሲናገር አዳራሹ በጭብጨባ ተናጋ::

እነዚያው ጥቂት ዶክተሮች ሃሳብ ለመስጠት እጃቸውን ቢያወጡም የሚሰማቸው አላገኙም:: አንድ በጥበቃነት ሲያገለግሉ የኖሩ ሰውዩ ተነሡና:: «ይህንን ባሰባችሁት ዕድሜ ይስጥልን:: ለብዙ ዘመናት ሲያንገበግበን የኖረ ነገር ነው:: እኔ ለምሳሌ በሳሳ ስምንት ዓመት አገለግያለሁ:: እስካሁን ግን አንድ በሽተኛ አክሜ፤ አንድም መድኃኒት አዝዤ አላውቅም:: ለስሙ ግን የሆስፒታሉ ሠራተኛ ነኝ:: በሽተኞችም እየመጡ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሐኪም እንዴ የሉም?" ነው የሚሉት፡ ይህ አሠራር "ግቶም አለበት» ብለው አስጨበጨቡ::

በዚህ ጊዜ እንደኛው የቀዶ ጥገና ሐኪም በንዴት መፈጠ ተነሡ:: «አራት ደቂቃ ብቻ» አሏቸው ሰብሳቢው:: «ሕክምና ምየ ነው:: ማከም ከፈለጋችሁ ተማሩ:: ብዙ ሐኪሞችን ከፈለ ግን ብዙ የሕክምና ኮሌጆችን መክፈት እንጂ ተሰብስቦ መወሰን አይደለም መፍትሔው:: ሞያ በመማር እና በመለመድ እንጂ እንደ ጠበል በመረጨት አይገኝም:: ችግራችንን ከድጡ ወደ ማጡ እንዳትከቱት» ሲሰሟቸው የፈለጉ ጥቂቶች ናቸው::

«ዋናው ነገር ትምህርት ነው የምትሉት እድሚያችሁን ለማራዘም ነው:: ሕዝብ ካመነብኝ እንኳንስ ሐኪም ሊቃም መሆን ይቻላል:: እኔኮ ለዚህ ሆስፒታል ታማኝ ሆኜ ሃያ አምስት ዓመት አገልግዬአለሁ:: ዋናው ለማኅበራችን ያለን ታማኝነት ነው::» እንዲት በጽዳት ሠራተኛነት ያገለገሉ እናት ለንዴቱ በንዴት መልስ ሰጡ::

«እኔ ሐሳብ አለኝ» አሉና አንድ የመዝገብ ቤት ሠራተኛ ተነሡ:: «ነዚሁን በኋላ አንድ በሽተኛ ሲመጣ በር ተቆልፎ ዶክተሩ ብቻቸውን የሚያነጋግሩበት አሠራር መቅረት አለበት:: ለምንድን ነው ሁላችንም የማንሰማው? ይሄ እኛ እንዳናውቅ የሚደረግ ሤራ ነው:: ስለዚህም እዚሁ አዳራሽ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እየመጣ በሽተኛው ይጠየቅ:: ሁላችንም የመመርመር እድሉን እናግኝ:: በሽ ታው ምን እንደ ሆነ አንድ ዶክተር ብቻውን በአምባገነንነት መወሰንም የለበትም:: እዚሁ አዳራሽ ውስጥ በድምጽ ብልጫ መወሰን አለበት» ተጨበጨበ::

«ተጨማሪ» አሉ የሆስፒታሉ ሾፌር «ባቦራቶሪ የሚባል የሰው ደም የሚጨርስ ነገር መቅረት አለበት:: እኛ እንዳናውቀው እየጫኑ ሐኪሞቹ ይልካሉ፤ እየጫኑ ባለ ባቦራቶሪዎች ይመልሳሉ:: መቅረት አለበት:: ባቦራቶሪ ከሕዝብ ድምፅ አይበልጥም:: ደግሞም ከሁን በኋላ ጥቂት ዶክተሮች ለብቻቸው ቀዶ ጥገና የሚያደርጉበት አሠራር ቀርቶ ማን ቀዶ ጥገና ማድረግ እንዳለበት እዚሁ በስብሰባ መወሰን አለበት» አሁንም ተጨበጨበ::

እምስቱም ዶክተሮች እጃቸውን አወጡ:: «ሥነ ሥርዓት» ይላሉ ደጋግመው::

በስንት መከራ ለአንዱ ተፈቀደላቸው:: «ሕክምና ሞያ ነው:: ሕመምተኛም እዚህ የሚመጣው ባለሞያ ፈልጎ እንጂ ለስብሰባ አይደለም:: ያለ ባቦራቶሪ እንዴት ነው በሽታን ልንለይ የምንችለው? በምን አሠራር ነው ሁላችሁም ልታክሙ የምትችሉት? መግደል ነው እንዴ የምታስቡት::» ሐኪሙ ሳይጨርሱ አንዲት የጤና ረዳት ተነሡና «ይህ ንቀት ነው:: ንቀት ነው:: ዕውቀት ሁለተኛ ነገር ነው:: የመጀመርያው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሆስፒታሉ የሠራተኞች ማኅበር ታማኞች ነን አይደለንም? ነው:: ቀጣዩ ደግሞ ሕዝብ መርጦናል ወይስ አልመረጠንም ነው:: የቀረው ነገር ፍሬ ከርስኪ ነው» ተሳቀ፣ ተጨበጨበ:: በስብሰባው መጨረሻ በወጣው የአቋም መግለጫ ስድስት ውሳኔዎች ተወሰኑ::

1. ማንኛውም በሽተኛ ወደ ሆስፒታሉ ሲመጣ ወደ ስብሰባው አዳራሽ ገብቶ፣ በግልጽነት፣ በሁሉም ሠራተኞች ፊት እየተጠየቀ እንዲመረመር፣ በድብቅ ዶክተሩ ብቻውን መመርመሩ እንዲቀር
2. ነበራቶሪ፣ አልትራሳውንድ፣ ራጅ፣ የመሳሰሉት ለብዙኃን አሠራር ስለማይመቹ እንዲቀሩ:: ደግሞም ከመላው ሠራተኛ ድምፅ እነርሱ አይበልጡም::
3. ማንኛውም በሽተኛ ምን እንዳመመው በድምፅ ብልጫ እንዲወሰን፣
4. ቀዶ ጥገና የሚያስፈልገውን በሽተኛ ማን ቀዶ ጥገና ማድረግ እንዳለበት በድምጽ ብልጫ እንዲወሰን፣ ዶክተሮች እንደማንኛውም ሠራተኛ ድምፅ ካገኙ ያክማሉ::
5. ቀዶ ጥገና አድራጊ ማን ማድረግ እንዳለበት ሲወሰን መጀመርያ ለሠራተኛ ማኅበሩ ያለው ታማኝነት፣ ቀጥሎ ከዚህ በፊት ዕድሉን ያላገኘ መሆኑ፣ እንዲታይ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

፩. ቀዶ ጥገና አድራጊዎች ከልዩ ልዩ የሆስፒታሉ ክፍሎች ያላቸው ተሞክሮ እንዲመጣጠን፡

ተጨበጨበ።

የመጀመርያው በሽተኛ ይግባ ተባለ። በሽተኛዋ ተጠሩ። «ወ/ሮ ሀገሬ ይግቡ» ወ/ሮ ሀገሬ ገቡ። በተሰብሳቢው መካከል አልፈው መድረክ ላይ ተቀመጡ። ቀድሞ ከሚያውቁት ስለተለዩባቸው ግራ ገባቸው። ሰብሳቢው ጥያቄ ጀመረ።

«ምንዎን ነው የሚያምዎት?»

«ራሴን»

«ከጀመረዎ ምን ያህል ጊዜ ነው»

«ብዙ ዓመት ሆኖታል»

«ዕረፍት ያደርጋሉ»

«አዩ ልጄ ምን ዕረፍት አለኝ»

«ይበቃል» ተባሉ።

«ብሉ በሽታቸው ምን ሊሆን ይችላል? በሚለው ላይ ሐሳብ ስጡና በድምፅ እንወስን» አሉ ሰብሳቢው።

«ጨጓራ ነው» «የለም ኩላሊት ነው» «የለም የለም ጉበት ነው» «ፈጽሞ፣ ይህማ መጋኛ ነው» «የለም ደንቃራ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ተደርጎባቸው ሳይሆን አይቀርም» ሐሳቦቹ ከያቅጣጫው መጡ:: እሁንም ዶክተሮቹ እየተነሡ ሮጡ:: ይህ ማን 171ኛው ሆስፒታል ነውና ሰሚ አላገኙም:: «በሽታ እንዴት በድምፅ ብልጫ ይወሰናል፡ በቂ ምርመራ ተደርጎ፣ አስፈላጊ የሆኑ ባክቴሪያ የአልትራ ሳውንድ፣ የመሳሰሉት ውጤቶች ሳይታዩ እንዴት ብዙ ሰው ስለተናገረ ብቻ ሊወሰን ይችላል:: ለምን ታማሚውን እንገድለዋለን» ማን ይስማ::

«ድምፅ ስጡ» ተባለ::

ከአምስት ተቃውሞ በቀር በብዙኃኑ ድምፅ «በሽታው ኩላሊት ነው» ተብሎ ተወሰነ:: ሕመምተኛዋ ወ/ሮ ሀገሬ ተቃወሙ «እኔ ኩላሊቴን ደኅና ነኝ:: ተውኝ እባካችሁ:: እንዲያውም መታከም አልፈልግም:: ይቅርብኝ እንዲሁ ብኖር ይሻለኛል:: "ትሻልን ስድጂ ትብስን አመጣሁ" አሉ እያቴ:: በቃኝ አልፈልግም» ተንገበገቡ::

«የለም የለም፤ ይህንን ያህል ጊዜያችንን አባክነውማ አልታከምም ማለት አይችሉም:: አሁንማ ድምፅ ተሰጥቶ፣ ተወስኖ፣ የግድ ነው፤ ይታከማሉ» ሰብሳቢው ተቆጣ::

«ቀዶ ጥገና ያስፈልገዋል አያስፈልገውም?» ሰብሳቢው ጠየቀ:: ከአምስት ተቃውሞ በስተቀር «ያስፈልገዋል» ተብሎ ተወሰነ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«እሺ ማን ቀዶ ጥገና ያድርግ» ስብሳቢው መጠየቅ ሲጀምር አንዱ ዶክተር ዘለው ተነሡ «ኧረ ስለ ፈጠራችሁ፣ ሰው መቀለጃ አይደለም:: እስቲ ይዋል ይደር በሉ»

ይህ ግን 171ኛው ሆስፒታል በመሆኑ የሰማቸው የለም:: ጥቆማዎች ቀረቡ:: በመጨረሻም የሆስፒታሉ አትክልተኛ ሆነው ለሠላሳ ዓመታት ያገለገሉትና አሁን ዓይናቸውን የጋረዳቸው አቶ እንዳለ ተመረጡ:: ጭብጨባው አስተጋባ::

አቶ እንዳለ ወደ መድረኩ ሲወጡ «ወ/ሮ ሀገሬ ይቅርብኝ አልታከምም» እያሉ ይጮኻሉ:: ይህ ግን 171ኛው ሆስፒታል መሆኑ የገባቸው አልመሰለኝም::

«ለዚህ ዕድል በመመረጤ ፈጣሪዬን አመሰግናለሁ:: እናንተ ካመናችሁብኝ ገና ብዙ ኦፐሬሽን አደርጋለሁ:: ዋናው መማር ሳይሆን መመረጥ ነው:: የተማሩ ብዙዎች የመሚመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው:: በሉ በሽተኛዋን እዚህ ጠረጴዛ ላይ አስተኙና ዓይኔን ጋረድ ስላደረገኝ ቢላዋውንና መቀሱን አስይዙኝ:: ደግሞም ኩላሊት የት እንደሚገኝ በእጄ አስጨብጡኝ፤ የቀረውን ነገር ለኔ ተውት»

ዶክተሮች ሊከላከሉ ይታገላሉ፤ ወ/ሮ ሀገሬ ይጮኻሉ፤ ይህ ግን 171ኛው ሆስፒታል በመሆኑ የሚናገር እንጂ የሚሰማ አላገኙም::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ቅኝ አልተገዛንም?

አባት ሁልጊዜ ለልጁ ስለ ሀገሩ ታሪክ እና ወግ ይነግረዋል:: በተለይም አንድ ነገር ደጋግሞ ያነሣለት ነበር:: «ኢትዮጵያ ከሁሉም የአፍሪካ ሀገሮች ተለይታ ቅኝ ያልተገዛች፣ ራስዋን ችላ የኖረች ሀገር ናት:: የራስዋ ፊደል፣ የራስዋ የዘመን አቆጣጠር፣ የራስዋ ባሕል ያላት ናት» ይለዋል:: አንድ ቀን ታድያ ልጁ ጥያቄ አነሣ:: «ኢትዮጵያ ግን በእውነት ቅኝ አልተገዛ ችም?» የሚል:: እናም አባቱን መሞገት ጀመረ::

«አባዬ ግን በእውነት ኢትዮጵያ በአውሮፓውያን ቅኝ አልተገዛችም? ወይስ ለሞራሌ ብለህ ነው ነጻነቷን ጠብቃ የኖረች ሀገር ናት እያልክ የምትነግረኝ» አለው ልጁ::

አባትዬውም ደንግጦ «ምነው ልጄ ምን አዲስ ነገር ተገኘ? ይህኮ እኔ የፈጠርኩት አይደለም:: ዓለም በሙሉ የሚያውቀው እውነት ነው:: የትኛውንም መጽሐፍ አገላብጥ፣ የትኛውንም ሊቅ ጠይቅ፣ ይህንኑ ብቻ ይነግሩሃል» አለው::

ልጁም «ይህ ከሆነማ ሆኗል ተብሎ የሚታሰበውና የሚታየው ነገር ይለያያል» አለው::

«እንዴት ማለት» አለ አባት::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«ኢትዮጵያ ቅኝ አለመገዛቷ ሆኗል ተብሎ የሚታሰበው ነገር ነው፣ የሚታየው ነገር ግን ቅኝ ተገዝታ የኖረች ብቻ ሳይሆን አሁንም ቅኝ እየተገዛች መሆንዋን የሚያሳይ ነው»

አባት ግራ ገብቶት ልጁን ትኩር ብሎ አየው:: «መቼም የዛሬ ልጆች ተፈላሳሚዎች ናችሁ:: የማታመጡት ነገር የላችሁም:: እኛ አሜን ብለን የተቀበልነውን ነገር ሁሉ መጠራጠር አመላችሁ ሆኗል:: ምን አግኝተህ ነው ይህንን ያልከው?» ሲል ጠየቀው::

«ለምሳሌ በቀደም ዕለት እኔና አንተ እዚያ ቢሮ ሄድን:: ታስታውሳለህ?» አለው ልጁ::

«አዎ እና ምን ተፈጠረ?» አለው አባት::

«በር ላይ የተፈጠረውን ታስታውሰዋለህ?» ልጁ መልሶ ጠየቀ::

«ምን ተፈጠረ? ተፈተሸን ገባን:: አለቀ» አለው አባት::

«በጣም ጥሩ እኔ እና አንተ ተፈትሸን ገባን:: ከእኛ አጠገብ የነበረው ፈረንጅ ግን ሰላምታ ብቻ ቀርቦለት ገባ፣ ለምን? እኔ እና አንተ ግብር ከፋይ የዚህች ሀገር ዜጎች ነን:: እኔ እና አንተ አጥንታቸውን ከስክሰው፣ ደማቸውን አፈሰው እያልን ዘወትር የምናነሣቸው አባቶቻችን ልጆች ነን:: ነገር ግን እኛ አንታመንም፣ ስለዚህ ተፈተሸን:: ፈረንጁ ግን ታማኝ ነው፣ እናም ሳይፈተሽ በጥሩ ፈገግታ ገባ:: እኛ አደጋ ሊያደርሱ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ይችላሉ ተብለን እንጠረጠራለን፣ ፈረንጁ ግን ንጹሕ ነው ተብሎ ይታመናል::

«ሆሆ» አለ አባት:: «እና ይሄ ከቅኝ ግዛት ጋር ምን አገናኘው?»

«ቆይ ቆይ ታገሠኝ:: እዚያ ቢሮ ብቻ አይደለምኮ:: ታላላቅ በዓላት ሲከበሩ በየአደባባዩ ሐበሻ ሆነህ ፎቶ ግራፍ ላንሣ፣ ፊልም ልቅረጽ ብትል ጠባቂው አያሳልፍህም:: ፈቃጁም በመከራ ነው የሚፈቅድልህ:: እርሱም ቢሆን ዘመድ ካገኘህ:: ፈረ ንጅ ከሆንክ ግን መልክህ ብቻ ይበቃል:: የፈለግከውን ብትቀ ርጽ፣ የፈለግከውን ብታነሣ ማን ጠያቂ አለህ:: እስኪ ወደ ታሪ ካዊ ቦታዎች ሂድ፣ ለሐበሻ ያልተፈቀዱ ቦታዎች ለፈረንጅ ክፍት ናቸው:: አንተ የማታገኘውን መረጃ ፈረንጅ በቀላሉ ያገኘዋል::

«አንቴ ከውጭ ሀገር የመጣ ጊዜ ትዝ ይልሃል? ምሳ ሊጋብዘን እዚያ ሆቴል ገባን:: እኔ መጀመርያውኑም እንዲህ ያሉ ፈረንጅ የሚያዘወትሩቸው ሆቴሎች መሄዱን አልፈለግኩትም ነበር:: ደግሞም ተናግሬያለሁ:: ግን ከሄድን በኋላ ያልኩት ነው የደረሰው::

«ምን ተፈጠረ፣ ነብርኩ አይደለም እንዴ?»



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«አዎ ነበርኩ:: ነገር ግን አንተ ቅኝ ግዛትን መሬት ላይ ነው የምትፈልገው፣ እኔ ደግሞ ሰው ላይ:: አንተ ስለ ድንበር የምታስበው በምዕራብ፣ በምሥራቅ፣ በሰሜን፣ በደቡብ እያልክ ነው:: እኔ ደግሞ ድንበሩን ከመካከላችን ነው የምፈልገው::

«እኛ ነበርን ወደ ሆቴሉ ቀድመን የገባነው:: ወንበር ይዘን የተቀመጥነው:: ነገር ግን አስተናጋጆቹ ሁሉ ፈረንጆቹን ለማስተናገድ ነበር ሽር ጉድ የሚሉት:: እኛ ተቀምጠን ከኋላችን የመጡት ፈረንጆች ቀድመው ተስተናገዱ:: አጎቴ ነገሩ ስላል ገባውና የአስተናጋጆቹ ንዝህላልነት ብቻ ስለመሰለው ከራሱ ሀገር ጋር አወዳድሮ ተናደደ:: በኋላም በመከራ ነው የታዘዙን::

የሚገርመው ነገር የምግብ ዝርዝሩን ሳየው አንድም ኢትዮጵያዊ ምግብ አላገኘሁም:: ለኔ አልገረመኝም:: እዚያ ቤት የሚጠበቀው ፈረንጅ እንጂ ሐበሻ አይደለም:: አንተም እንድ ትሄድ የሚጠበቅብህ ፈርንጀህ ነው:: ተወው ምግቡን:: ምግቡ የተጻፈበት ቋንቋ እንግሊዝኛ እና ፈረንሳይኛ ብቻ ነው:: አንዳች የሀገርህ ቋንቋ የለውም:: ከምግብ ዝርዝሩ ውስጥ ምን የሚል የእንግሊዝኛ ቃል እንዳየሁ ታውቃለህ?

«ምን አየህ ደግሞ? ዛሬ ለጉድ ነው መቼም አመጣጥህ» አለው አባቱ እየሳቀ::

«ታንግ ኢንድ ሰንበር ይልልሃል ምግቡ»



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«ታንግ ኢንድ ሰንበር ደግሞ ምንድን ነው?»

«አይውልህ ምላስ እና ሰንበር የሚለውን ለመግለጥ ነዋ:: ምግቡን ሲያፈረንጁት እኮ ነው:: ምናለ መጀመርያ በአማርኛ፣ ከዚያም ስሙን በእንግሊዝኛ፣ ቀጥሎ ስለ ምግቡ ባሕል እና ይዘት መጠነኛ ማብራርያ ቢሰጡ:: አይ ቅኝ ያልተገዛ ሕዝብ::

«ቋንቋ አለን ግን አንጽፍበትም:: ቁጥር አለን ግን አናስብበትም፤ ባሕል አለን ግን አንከራበትም:: እስኪ ቻይናን እያት:: መላውን ዓለም በቻይና ምግብ ቤት ሲታጥለቀልቀው:: የሠራተኞቹ አለባበስ፣ የምግብ ቤቱ ስም፤ ስሙ የተጻፈበት ቋንቋ፣ የምግቦቹ ስያሜ፣ ስያሜያቸው የተጻፈበት ቋንቋ፣ ግድግዳው ላይ የተጻፈው እና የተሳለው ነገር፣ የሚቀርብበት ዕቃ ምኑ ቅጡ ቤጂንግ ያለህ ነው የሚመስልህ::

«እስኪ ዘመዶችህን እያቸው አባዬ፤ ኢትዮጵያዊውን ስምኮ ድራሹን እያጠፉት ነው:: በግእዝ፣ በአማርኛ፣ በትግርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በወላይትኛ፣ በሲዳምኛ ስሞች መጠራት እየቀረ ነው:: የአሁኑ ዘመን የስም ፍልስፍና «ቢቻል የልጆችህ ስም ከአራት ፊደል ያልበለጠ፣ ለቁልምጫ የሚያመች እና ያልተለመደ ይሁን» የሚል ነው::

ይህ አይደለም ግን ችግሩ:: እነዚህን ነገሮች ለማሟላት እየተረባረብን ያለነው የፈረንጅ ስሞች ላይ ነው:: ልክ ቅኝ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የተገዙ አፍሪካውያን የሀገራቸውን ነባር ስሞች እየዘነጉ በቅኝ ገዥዎቹ ስሞች እንደተጠሩት እኛም ያንን መንገድ ሳንወረር እየተከተልነው ነው::

«የነገው ትውልድ የሚወጣባቸውን ትምህርት ቤቶችንስ ታያለህ? የሚያስተዋውቁትኮ ብቁ ኢትዮጵያዊ መምህር አለን ብለው ሳይሆን አንዳች ፈረንጅ እኛ ትምህርት ቤት ያስተምራል እያሉና እርሱን በቴሌቭዥን እያሳዩ ነው:: ምን ያድርጉ ይህ ቅኝ ያልተገዛ ሕዝብ ይህንን ነው የሚወደው:: ማንዴላ *ለነፃነት የተደረገ ረዥሙ ጉዞ* በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ፣ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ፣ አስተና ጋጆቹን እና ፓይለቶቹን ኢትዮጵያውያን ሆነው ሲያገኟቸው የተሰማቸውን ስሜት ይህ ቅኝ ያልተገዛ ሕዝብ አያውቀውም::

«እስኪ የትምህርት ቤቶቹን ስሞች እይ፤ አጸደ ሕፃናቱም፣ አዳዲስ የግል ኮሌጆቹም በአብዛኛውኮ ኢትዮጵያዊ ስም የላቸውም:: እነዚህ ሦስት ሺ ዓመት በነጻነት ኖረች በምትባል ሀገር የተከፈቱ፣ እነዚህ ፈረንጆች ሳይደፍሯት በነጻነት ኖረች ተብሎ በሚዘመርላት ሀገር የሚያስተምሩ፣ እነዚህ ቅኝ ሳንገዛ ድንበራችንን አስከብረን ኖርን እያሉ ልጆቿ በሚፎክሩላት ሀገር ያሉት ትምህርት ቤቶች ፈረንጅኛ ስያሜን በፈረንጅኛ ካልሰጡ ያደጉ አይመስላቸውምኮ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመሻ ገና ይልቅ የፈረንጅ ክሪስማስ የሚያከብሩት ትምህርት ቤቶቻችን በርግጥም ቅኝ ግዛት ያልነካን መሆናችንን ይመሰክራሉ።

የቻይናን፣ የጃፓንን እና የሕንድን ፊልም ያየ ሰው ሰዎቹ ኢትዮጵያውያን ሆነው ቢሠሩት እንኳን የቻይና፣ የሕንድ እና የጃፓን ፊልም መሆኑን ማወቅ ይችላል። እዚያ የሚያየው ባሕል እና ኑሮ፣ እዚያ የሚታየው ሥርዓት እና ወግ፣ እዚያ የሚደረገው ድርጊት፣ ሃሳቡ እና አመለካከቱ የቻይና፣ የሕንድ፣ የጃፓን ነው። እስኪ እባኮ ብዙዎቹን የኛን ሀገር ፊልሞች ተመልከት። ሰዎቹ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ባናውቅ ኖሮ የኢትዮጵያ ፊልም መሆኑን እንዴት እናውቅ ነበር?

ደግነቱ ብዙዎቹን የፊልም ተዋንያን በድራማ እና በቴሌቭዥን ማስታወቂያ አስቀድመን ማወቃችን ጠቀመን እንጂ፣ ተቀጥረው ለሌላ ሀገር የሚሠሩ ነበር የሚመስለን።

አለባበሱ፣ ቤቱ፣ መኪናው፣ ባሕሉ፣ ጠባዩ፣ ምኑ ነው ኢትዮጵያዊ? ሐሳቡ እንኳን ሳይቀር የፈረንጅ ሐሳብ ነው። ፈረንጅ መንገድ ለመንገድ የሚታኰስ ፊልም ስለሠራ እኛም በሰላም ሀገር፣ ለዚያውም ከስንት ዓመታት በኋላ ባገኘናት ቀለበት መንገድ ላይ የሚታኰስ ፊልም መሥራት አለብን?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የፍቅር ፊልሞቻችን እንኳን የፈረንጅን የፍቅር ጠባያት ነው የሚያሳዩን፤ ሐበሻ አያፈቅርም? ሐበሻ የፍቅር ዘፈን የለውም?

በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣ በሶማልኛ፣ በአፋርኛ ፍቅር የለም? ለመሆኑ ሐበሻ ሃሳብ የለውም፤ ተረት የለውም፤ ጉዳይ የለውም፤ ለፊልም የሚበቃ ኑሮ የለውም፣ ለፊልም የሚበቃ ታሪክ የለውም? ቅኝ ሳንገዛ ሦስት ሺ ዓመት በነጻነት ኖረን፣ ድንበር አስከብረን፣ ለፊልም እንኳን የሚበቃ ነገር እንዴት አሳተረፍንም?

«ይሄ ዘርፋፋ ከናቴራ ለብሶ፣ ቀበቶ የሌለው በርፋፋ ቡሬ ሶርቶ፣ እንደ ባሕታዊ ሠንበለት ታጥቆ የሚሄደው የሀገሬ ወጣት እውነት ቅኝ ያልተገዛ ነው? አሜሪካውያን ጥቁሮች ለምን ይህንን ዓይነት ልብስ እንደለበሱ ያውቀዋል? በዚያ የባርነት እና የልዩነት ዘመን ቀበቶ እንዳያደርጉ፣ ዘርፋፋ ልብስ እንዲለብሱ ለምን ይደረግ እንደነበር ይገባዋል?

እነማን ከትውልድ ሀገራቸው በሠንሠለት ታሥረው ለባርነት እንደ ተዳረጉ? እነማንስ በተወሰዱበት ሀገር በሠንሰለት ታሥረው በከባድ የጉልበት ሥራ እንደ ተሰቃዩ ያውቀዋል? እነዚያ ለሦስት መቶ ዓመታት የነበረባቸውን ስቃይ ለማስታወስ ያደርጉታል፤ ሌላውን ባህላቸውን አጥፍተውባቸዋልና ይህንን ባህላቸውን ያጠፋባቸውን ታሪክ በመከራ ይሰቡታል።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ቃድሮ! ቅኝ አልተገዛም ያልከው ወገኔ ይህንን ሲሰብስበውስ ምን ማለቱ ነው?

«እና አባዬ ምናልባት መሬቱ ቅኝ አልተገዛ ይሆናል:: እርሱም ሲሆን ያጠራጥረኛል:: መሬት ማግኘቱ አንዳንዴ ከሀገሬ ሰዎች ይልቅ ለውጮቹ ሲቀናቸው እያለሁና:: የርሱም አመለካከት ተቀይሮ ይሆናል:: እኛ ሰዎቹ ግን ልባችን ቅኝ የተገዛ ይመስለኛል:: ይልቅ ሆኗል ብለን በምናስበውና በሆነው መካከል ያለ ውን ልዩነት ማስተዋል እንጀምር:: ምናልባት እየሆነ ያለው ሆኗል ብለን ከምናስበው የተለየ እንዳይሆን::»

አባት ትኩር ብሎ ነበር ልጁን የሚያየው:: እርሱም በልጁ ላይ ሆኗል ብሎ የሚያስበውና እየሆነ ያለው ተለያይቶበት::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# «ቦሎ» ለትዳር»

***ይህ ስምን*** ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ ምርመራ አድርገው የተሽከርካሪነት ፈቃዳቸውን የሚያ ሳድሱበት ወይንም ደግሞ በተለመደው ቋንቋ «ቦሎ የሚያወጡ በት» ስምን ነው:: እኔ ደግሞ ይህንን ሳስብ ሌላ ነገር መጣብኝ::

ትዳር እንደ ቦሎ በየዓመቱ የሚታደስ ቢሆን ኖሮስ?

አሁን ለትዳር የቴክኒክ ምርመራ እየተደረገ ነው እንበል:: ለመሆኑ የስንቱ የተስፋ መብራት ይሠራል? ከአንዳንዱ የመኪና መብራት ይህች ሊሊት ሊሊት የምታበራው ትል ትሻላለችኮ:: በአንዳንዱ ትዳርስ የተስፋው መብራት ደብዝዞባቸው ወደፊት በትዳር እንቀጥላለን ወይስ መብራቱ ይጠፋል የሚለውን መለየት ያልቻሉ አሉ:: የስንቱ ፍሬን ጭቅጭቁን እና ንትርኩን ለማቆም ይሠራል? ይሄው ፍሬን ይገፔ አቆማለሁ ብለው ሲታገሉ እየተንሸራተተባቸው የስንቱ ትዳር መንገድ ለቀቆ አደጋ ደረሰበት መሰላችሁ:: የኔ ዓለም፣ የኔ ሆድ፣ ፍቅሬ፣ ልቤ፣ አንጀቴ፣ ማሬ፣ ወለላዬ፣ ውዴ፣ እንትኔ፣ እንትኔ ሲዋዛበት የነበረው የትዳሩ ዘይት አልቆ የስንቱ የአን ጀት ሽራ መጤስ ጀምሯል? ከተጋቡ በኋላ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳች የማገርሽ ለውጥ ያላደረጉ ወይ በአንደኛ ማገርሽ ባላቻቸውን/ሚስታቸውን እያስጨነቁ ያለበለዚያም በዜሮ ማገርሽ ቁልቁል እየተንደረደሩ የሚነዱትስ?

ያኔ በተገናኙ ጊዜ ምን ይባባሉ እንደ ነበር፣ እንዴት ይፋቀሩ እንደ ነበር፣ ምን ዐቅደው እንደ ነበር ወደ ኋላ ለማየት እንዳይችሉ በሥኪዮአቸው የተሰበረባቸው ስንት ባለ ትዳሮች አሉ? እነርሱ «እንፋቀራለን፣ እለን ባለ ትዳሮች ነን፣ ከኛ ወዲያ ትዳር ላሳር» እያሉ፣ ነገር ግን የትዳር ነዳጃቸው ማለቁን ለመለየት ያቃታቸው የነዳጅ ጌጃቸው የማይሠራ ባለ ትዳሮች መኖራቸውን ውስጥ ዐዋቂ ምንጮች እየጠቆሙ ነው:: አዘርፈው ያቆሙትን የትዳር መኪናዎቻቸውን እንደገና ለማስነሣት እንዳይችሉ ይቅር የሚለብት የልብ ባትሪያቸው ሞቶ ትዳርን ያህል መኪና የትም እንደገተሩት የቀሩትስ? የትእግ ሥት ራዲያተራቸው ተበላሽቶ የጠባይ ውኃቸው አሁንም አሁንም እየፈላ የሚያስቸግራቸውስ?

እንዲው ለመሆኑ ለትዳር ዓመታዊ በሎ የሚወጣለት ቢሆን ኖሮ የስንቶቻችን ትዳር ምርመራውን አልፎ ፈቃዱ ይታደ ስለት ነበር? በትዳር ውስጥኮ ተፋትተው ነገር ግን መፋታታ ቸውን ያላወቁ፣ ወይንም ያላወጁ:: ተጋብተው ነገር ግን ተፋትተው በአንድ ቤት የሚኖሩ፣ በአንድ አልጋ የሚያድሩ:: በየቀኑ እየተፋቱ በየቀኑ ሲጋቡ የሚኖሩ:: ይሉኝታ ስለያዛቸው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ወይም ደግሞ አንድ ጊዜ ትዳር ስለያዙ ብቻ፣ አለያም ለሥርግ ያወጡት ገንዘብ እየቆጫቸው፣ ወይም ደግሞ የሃይማኖታቸው ሕግ ስለሚያስገድዳቸው፣ ባስም ሲል ዕድሜያቸው ስላለፈባቸው ብቻ የግድ የትዳሩን መኪና የሚነዱት ሰዎች፣ በሉአቸው የሚታደስ ቢሆን ኖሮ በእድሳቱ ቀን ምን ይሉ ነበር?

አንደኛው መብራቱ ብቻ እየበራ፣ ጎማው በወላይቲኛ ዜፈን እየተሟወተ፣ የተቀጣጠሉ ገመዶች፣ የተሠበሩ መስተዋቶች፣ የጨለመ ዳሽ ቦርድ፣ የሚንተፋተፍ ጭስ መውጫ፣ በየቀኑ የሚገፋ ሞተር፣ እዚህም እዚያም በገመድ የታሠረ ብረት ያለው መኪና ገጥሟችሁ አያውቅም? በተለይ ከአዲስ አበባ ወጣ ስትሉ:: እነዚህ መኪኖች በምርመራ ወቅት እስማት ያደርጋሉ ወይስ ፎርጅድ መኪና አሠርተው ያቀርባሉ? አትሉም? ያመረታቸው ፋብሪካ እንኳን ቢያያቸው ሊያውቃቸው የማይ ችል፣ በትክክልም ምን ዓይነት መኪና እንደሆኑ ሺ ዳቦ ቢቆ ረስ እንኳን ስማቸውን ለማውጣት የማይቻል ስንት የሀገራችን መኪኖች አሉ መሰላችሁ? ሞተራቸው ካንዱ፣ ፍሬኑ ከሌላው፣ መብራቱ ከዚህኛው፣ መስተዋቱ ከዚያኛው፣ ወንበሩ ከእገሌ፣ ፖርቶ መጋላው ከእገሊት ተዋጥቶ የተሠራ የመቀረጫ መኪና:: አሁን እንዲህ ያለውም መኪና «መኪኖች እጃችሁን አውጡ» ሲባል መኪና ነኝ ብሎ እጁን ያወጣ ይሆናል::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲህ ያለ ትዳርስ የለም ትላላችሁ? የፍቅር ባትረጡ አለሠራ እያለ በየቀኑ በሽማግሌ እና በጓደኛ ሲገፋ የሚውል፣ በየቀኑ በሚፈጸም የቃለ መሐላ ገመድ እዚህም እዚያም የታሠረ፤ የሙሽሪት አባትም፣ የሙሽራው እናትም፣ የርሷ ጓደኛም፣ የርሱ እንትም ትዳሩ ውስጥ ገብተውበት ትዳሩ የማን ኛቸው እንደሆነ ለመለየት የሚያስቸግር አልገጠማችሁም? አሁን የቦሌው ምርመራ ቢኖር ኖሮ ምን ዓይነት ትዳር ተብሎ ይታደስለት ነበር? ከንግድ ሚኒስቴር የ«አክስዮን ማኅ በር» ፈቃድ ካላወጣ በቀር:: እንዲያውም ሀገራችን ውስጥ የማ ያጠራጥረው የሻንሲ ቁጥር ነው እየተባለ የሚመዘገበው እርሱ ነው:: ካጠራጠረ ደግሞ መንገድ ትራንስፖርት ተልኮ ይለይ ሊታል:: የሻንሲ ቁጥራቸው የጠፋባቸውን ባለ ትዳሮችስ ምን እናደርጋቸው ነበር?

ፕሮፌሰሩ በመርሳት የታወቁ ነበሩ አሉ:: አንድ ቀን መንገድ ላይ አንዲት ሴት አገኟቸውና «እንዴት ዋሉ ፕሮፌሰር» አለቻቸው:: እርሳቸውም የሰላምታዋን መልስ ሰጧት:: ሴት የዋም «ረሱኝ እንዴ ፕሮፌሰር?» አለቻቸው:: «ይቅርታ ማን ነበርሽ?» አሏት ፕሮፌሰሩ:: «የጥንቷ እጮኛዎ ነኝኮ» አለቻ ቸው ሳቅ ብላ:: «አወ ይቅርታ» አሉ ፕሮፌሰሩ:: ከዚያም መነጽራቸውን ወረድ አድርገው «ለመሆኑ አገባሁሽ ወይስ ሳላገባሽ ቀረሁ? ረሳሁትኮ» አሏት ይባላል::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የሻንሲው ቁጥር ሲጠፉ እንዲህ ያደርጋል። ስንት ባለትዳሮች መሰላችሁ በፍቅረኛነት ይቅሩ፣ ከዚያ በኋላ ይሰርጉ፣ ከሰርጉ በኋላ ይጋቡ፣ ወይስ ተፋትተው ረስተውት እየኖሩ ይሆን ትዝ የማይላቸው። የጋብቻ ወረቀታቸው እንጂ ልባቸው የሻንሲ ቁጥሩ ጠፍቶበት፤ በሚስታቸውና በሌላኛዋ ሴት፣ በባላቸውና በሌላኛው ወንድ መካከል ያለው ልዩነት ምን እንደ ሆነ የጠፋባቸው ስንቶች መሰሏችሁ። ሻንሲው ጠፍቷል እና የት እንላካቸው?

መኪና የገዙ እንጂ መኪና ያልነዱ አሉ ይባላል። ሳያስቡበት በድንገት፤ ወይንም እንደሌው ለጉራ ያህል፣ ቀላል አይደለንም ለማለት፣ ከማን አንሼ በሚል ስሜት ያለ ጥናት ገንዘባቸውን ላጥ አድርገው ይገዙና በኋላ «መኪና ነው ወይስ የራስ ምታት ነው የገዛሁት» የሚሉ አሉ አሉ። በየቀኑ ሰቃ ሲቀይሩ፣ ጋራጅ ሲገትሩ፣ ሲያስጠግኑ እና ቶርኖ ቤት ሲያሠሩ የሚውሉ። ሰቃ ሰበረ፣ ዘይት ጨረሰ፣ ነዳጅ በላ እያሉ ሲያማርሩ የሚውሉ። መጀመርያውኑ መኪና ለመግዛት እንጂ በኋላ እን ዴት እንደሚነዱት አላሰቡበትም መሰለኝ። እንደዚሁም ሁሉ የሠርጉ እንጂ ያልተጋቡ ስንቶች አሉ መሰላችሁ። መሠረግና መጋባት መቼም ይለያያሉ። መሰረግ አንድ ጊዜ መጋባት ግን በየቀኑ ነው። «ሰርግ እና ሞት አንድ ነው» ይባል የለ። ሰርግ ሥነ ሥርዓት፣ መጋባት ግን ሂደት ነው።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ባል እና ሚስት በአንድ ጊዜ ተጋብተው ሊጨርሱ አይችሉም፡፡ እናቶቻችን «ትዳር እና ጠጅ ይበልጥ ሲቆይ ይበልጥ ይቆጣለታል» ይላሉ፡፡ ባለትዳር ማለት እየተጋቡ፣ ይበልጥ እየተጋቡ፣ በተሻለ ሁኔታ እየተጋቡ፣ በጣም ይበልጥ እየተጋቡ፣ እጅግ በጣም እየተጋቡ የሚሄዱ ጥንዶች ማለት ነው፡፡ ሰርጉ ጋብቻው የሚጀመርበት ቀን ነው፡፡ ሰርግ ተጋብተውና እየተጋቡ ለመኖር በሕዝብ ፊት ቃል የሚገባበት ቀን ነው፡፡ ሰርግ ዐዋጅ ነው፡፡ ጋብቻ ግን ትግበራ፡፡ ያለ ጋብቻ ሰርግ የለም፤ ያለ ሰርግ ግን ጋብቻ ሊኖር ይችላል፡፡

ባለ ትዳሮች ልጅ ብቻ አይደለም ማሳደግ ያለባቸው፡፡ በፍቅር ቀን ተፀንሶ በሠርግ ቀን የተወለደውን ትዳራቸውንም እያሳደጉት መንዝም አለባቸው፡፡ እንዳንዶቹ እንዲያውም ሰርግ ከሰርጉ ከብዙ ዓመታት በኋላ የሚጋቡ አሉ፡፡ ጭቅጭቁ፣ ኩርፊያው፣ መሰለቻቸቱ፣ ጀርባ መሰጣጣቱ ሁሉ ያልፍና ታይቶ የማይታወቅ አዲስ ፍቅር ይጀምራቸዋል፡፡ ካረጀች በኋላ ሙሉ ሰርቪስ ተደርጋ እንደወጣች መኪና፡፡ አዲስ የተጋቡ እስኪመስላቸው ድረስ ይፋቀራሉ፡፡ ታገል ሰይፉ በአንድ ወቅት «አሁን እንደገና እንጋባ» ብሎ እንደ ጻፈው ማለት ነው፡፡ ይሄ እንግዲህ የቴክኒክ ምርመራው ዘግይቶ ሲጀመርና እድሳቱ ዘግይቶ ሲከናወን ነው፡፡



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙ ጊዜ ግን ተጋቢዎቹ ስለ ሰርጋቸው እንጂ ስለ ጋብቻቸው ሲጨነቁበት አይታዩም:: እነ ማን ይጠሩ፣ የት ይሁን፣ ምን ዓይነት ልብስ፣ መኪና፣ ጌጣጌጥ፣ አዳራሽ፣ ባንድ፣ መዝሙር፣ ኬሉ፣ ኬክ፣ እያሉ የሚተነትኑትን እና ለጥቃቅኗ ነገር ሁሉ የሚጨነቁትን ያህል ለትዳራቸው አያስቡለትም:: ሰይጣኑ ያለው ደግሞ ዝርዝሩ ውስጥ ነው::

አንዳንድ ጊዜ በሰርግ ወቅት ሙሽሮቹ ኬክ ቆርሰው ከረሜላ እየበተኑ ታዳሚውን ይሰናበታሉ:: ፕሮግራም መሪዎቹም «አሁን ሙሽሮቹ ታዳሚውን ስለሚሰናበቱ ተቀበሏቸው» ይላሉ:: እኛም እያጨበጨብን የታዘዝነውን እናደርጋለን:: አሁን አሁን ሳስበው ግን አንዳንዶቹ ለካ የምራቸውን ነው የተሰናበቱን:: «ከዚህ በኋላ በዚህ መልኩ አምሮብን አታገኙንም፤ እንዲህ ደስ ብሎን ፈገግ እያልን አታዩንም» ማለታቸው ነበር ለካ:: ለካስ ስንብቱ የምር ኖሯል:: እናም ከዚያ በኋላ በዚያ መልኩ አላየናቸውም:: ሰርጋቸው የፍቅራቸው መጨረሻ ሆኖባቸው ቀርተዋል::

ባለሞያዎች እንደሚመክሩት መኪናን በተበላሸ ቁጥር ከማሠራት አስቀድሞ ጥንቃቄ ማድረጉ መልካም ነው:: ዘይቱን በየ ጊዜው ማየት፣ ባትሪውን ማስመርመር፣ ሞተሩን ማሳየት፣ ጎማውን ማስፈተሽ፣ ማርሽ እና ፍሬኑን ማስመርመር፣ ውኃ መሙላት፣ የመኪናው ዕድሜ ይቀጥልለታል:: ፍጥነቱን ያሳምረዋል፤ ውበቱን ይጨምረዋል::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አገልግሎቱን ያቀላጥፈዋል:: ትዳርም እንዲህ እኮ ነው:: ሞተር ከነከሰ በኋላ ሺ ሺ ማግሌ ስብስቦ የተበላሸውን ትዳር ለመሥራት ከመሞከር ቀድሞ ነው መጠንቀቅ::

የመተሳሰብ ዘይቱን፣ የትእግሥት ውኃውን፣ የፍቅር ሞተሩን አዘውትረው ካዩለት:: የጠብ እንጉልፋቶውን ከጠረጉለት፣ ትዳር እድሜው ረዥም ነው:: አንዳንዴምኮ የጢስ ማውጫው ሲበላሽ ንዴቱንና ብስጭቱን ማብረድ ያስቸግራልና ከተለመደው ኑሮ ወጣ ብሎ ዘና ማለቱ «ሴፍቲ ቫልቭ» ይሆናል::

አንዳንዱ መኪናኮ ሲበላሽ ድምፁ ይቀየራል:: እንዴት ነው የትዳራችሁ ድምፅ ቀየር አላለባችሁም:: ንግግሩ፣ የፍቅር አጠራሩ፣ መልስ አሰጣጡ፣ ለየት ሲልባችሁኮ አንዳች ነገር ተበላ ሸቷል ማለት ነው:: ጉዳቱ ባስ ካለማ የሞተሩ ጉልበት ይቀን ባል:: እስቲ የትዳራችሁን ፍጥነት፣ እድገቱን፣ ሕይወቱን ቃኙት ቀነስ አላለም?

እንዴው ግን ትዳር ቦሎ ቢኖረው ኖሮ ስንቱ ባለትዳር ከአምስት፣ ዐሥር፣ አራት፣ ሃያ ዓመት በፊት ያሳደሰበት ቦሎ በተገኘበት ነበር:: ስንቱስ ምርመራውን ማለፍ አቅቶት በየጋራጁ በተንከራተተ ነበር:: ስንቱ ደግሞ የመኪናው በየጊዜው መበላሸት አስመርሮት ቦሎ ከመድረሱ በፊት ሶማሌ ተራ በትኖ በሸጠው ነበር?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ኑ እንፍጠር

**ግሪኮች** እንዲህ ይላሉ:: በድሮ ዘመን የአቴና ሰዎች መልካም መሪዎችን በማጣታቸው ምክንያት ይማረሩ ነበር:: አንድ ቀን ወደ ኦሊምፐስ ተራራ ወጥተው የአማልክት ንጉሥ የሆነውን ዜውስን ለመኑት:: «እባክህ ከመንደራችን እስከ ሀገራችን ድረስ ባሉት ቦታዎች በመልካም የሚያስተዳድሩ መሪዎችን ስጠን» አሉት:: ዜውስም «ፊንቄያውያን መጥተው ይግዟችሁ ሁን?» ሲል ጠየቃቸው አቴናውያንም «አንፈልግም» አሉ:: «ካርታጎዎች መጥተው ይግዟችሁን?» አላቸው ዜውስ አሁንም «በቅኝ መግዛት አንፈልግም» አሉ:: እንደገናም «ሮማውያንን አምጥቼ በላያችሁ ልሹምባችሁን?» ሲል ጠየቃቸው:: አቴና ውያን በዚህም ሊስማሙ አልቻሉም::

ዜውስ ባቢሎናውያንን፣ ፋርሶችን፣ ኬጢያውያንን እና ጢሮሳውያንን አምጥቶ በአቴና አውራጃዎች ለመሾም ፈቃዳቸውን ጠየቃቸው:: አቴናውያን ግን ፈጽሞ አይሆንም አሉ:: በዚህ ጊዜ ዜውስ «ታድያ ከየት አምጥቼ ነው መልካም መሪዎችን የምሰጣችሁ?» ሲል ጠየቃቸው:: «ከመካከላችን ስጠን» ብለው መለሱለት:: በዚህ ጊዜ ዜውስ እንዲህ አላቸው:: «ጥሩ በሬ ለማግኘት ጥሩ ጥጃ፣ ጥሩ ጠቦትም ለማግኘት ጥሩ ግልገል፣ ጥሩ ወፍ ለማግኘት ጥሩ ጫጩት፣



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥሩ ደረጃ ለማግኘት ጥሩ ዕንቁላል ያስፈልጋል። እናንተ በመልክም የሳሳደጋ ችጓቸውን ልጆች እኔ እንዴት አድርጌ በመልክም እሾማችዋ ለሁ። እኔ ሰውን ፈጠርኩ፣ መሪዎቻችሁን ግን እናንተ ፍጠሩ።»

መሪን ግን ይፈጥረዋል? ፓርቲ? ድርጅት? ትግል? በሳማዊ ለልፍ? ንግግር? ምርጫ? ወይስ ሌላ? እንደ ዜውስ ምክር ከሆነ ሕዝብን እምላክ፣ መሪን ግን ሕዝብ ይፈጥረዋል። መሪዎች የሕዝቡ ሥዕሎች ናቸው። ከተወለዱበት ቀን እስከ ተሾሙበት ቀን ድረስ በማኅበረሰቡ መካከል ሲኖሩ ሕዝቡ በእን ድም በሌላም መልኩ የሳለባቸውን ሥዕል ነው በሥልጣን ወን በር ላይ ሆነው የሚያሳዩን።

መሪዎቻችን የተረቶቻችን፣ የዘፈኖቻችን፣ የአባባሎቻችን፣ የእምነቶቻችን፣ አመለካከቶቻችን፣ የአኗኗራችን የአበባላችን እና የአጠጣጣችን ውጤቶች ናቸው።

ወላጅ ሳሉን ሲመገብ ጓዳ ውስጥ ግቡ ይባሉ ከነበሩ ልጆች ግልጽነትን መጠበቅ፣ ከወላጆቻቸው ጋር በአንድም ጉዳይ ሳይወያዩ እና በሐሳብ ልዕልና ለሙሳኔ ሳይበቁ ከሚያድጉ ልጆች ተወያይቶ መግባባትን እና ከኃይል እና ከሥልጣን ይልቅ በሐሳብ ልዕልና መተማመንን መጠበቅ፣ ልጅ እና ፊት እየበርደውም እየተባሉ ከሚያድጉ ልጆች መካከል የሕፃናትን መብት የሚያከብሩ መሪዎች መመኘት፣ ወላጆቻቸው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ችግሮቻቸውን ተነጋግረው፣ ተከራክረው እና ጊዜ ወስደው ከመፍታት ይልቅ በትንሽ በትልቁ ሲደባደቡ እና ሲፋቱ እያዩ ካደጉ ልጆች መካከል የክርክር እና የውይይት ባሕል ያለው፣ ልዩነቱን አቻችሎ የሚኖር፣ ጊዜ ወስዶ ችግር ችን የሚፈታ እና በትንሽ በትልቁ ፓርቲውን ጥሎ የማይ ወጣ መሪ መጠበቅ፣ ሴቷ ልጅ በቤት ሥራ ስትጳፋ እያየ እርሱ ሲራገጥ ከሚውል ልጅ መካከል የጾታ እኩልነትን የሚያ ሰፍን መሪ መሻት፣ ከየቢሮው እና ከየፋብሪካው፣ ከመንግሥት ካዝና እና ከቤተ እምነት ሙዳየ ምጽዋት፣ ከግብር እና ከቀረጥ፣ በተመነተፈ ገንዘብ ከሚያድግ ልጅ መካከል የህገሩን ገንዘብ የማይበላ መሪ መፈለግ፣

በቤተሰቡ መካከል በሚነገሩ አባባሎች እና ተረቶች፣ ስድቦች እና ርግማኖች አንዱ ብሔረሰብ ከሌላው ተለይቶ ሲሳቅበት እና ሲቀለድበት፣ ሲተረትበት እና ሲሾፍበት፣ ሲናቅ እና ሲንቋሸሽ እየሰማ ያደገን ልጅ አድገህ የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነት የምታሰፍን መሪ ሁን ብሎ ያለ ዐቅሙ ማሸከም፣ አስተማሪውን እያንጓጠጠ፣ እየተደባደበ እና በትምህርት ሰዓቱ እየቀለደ የሚያድግን ልጅ ማይፃሃነትን ከሀገር የምታጠፋ መሪ ሁን ማለት፣

ታናናሽ ወንድሞቹን እና እኅቶቹን እያንቋረጠጠ፣ የሠፈር ቤቶችን መቆሚያ መቀመጫ እያሳጣ፣ ለምን ቀና ብላችሁ አያችሁኝ ብሎ የሸሚዙን እጅጌ እየሰበሰበ ያደገን ልጅ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ዴሞክራሲያዊ መሪ እንዲሆን መመኘት ያልዘሩትን ማጨድ ነው።

በሀገራችን ጀግንነት ስለሚደነቅ፣ ጀግናም ስለሚከበር፣ አንበሳ እና ሊጋዝን፣ ነብር እና ዝሆን መግደል ስለሚያሸልም፣ በበሳዊው ትምህርት ፈረስ ጉግስ እና ጦር ውርወራ፣ ሽመል ሰንዘራ እና ጋሻ ምከታ፣ ውኃ ዋና እና ዝላይ ከልጅነት ጀምሮ ይሰጥ ስለነበር ሀገራችን እያሌ የጦር ሜዳ ጀግኖችን አፍርታለች። በጠላት ላይ አስደናቂ ድል የሚቀዳጁ፣ ድንበራቸውን ለአፍታም የማያስደፍሩ፣ ጀግንነት ከነጭ እና ቀይ የደም ሴላቸው ጋር ሦስተኛ ሕዋስ የሆንላቸው አርበኞችን አፍርታለች።

ነገር ግን የአመራር፣ የአስተዳደር እና የአሠራር ጀግኖችን፣ የዴሞክራሲ እና የሰብአዊ መብት ጀግኖችን፣ የክርክር እና የውይይት ጀግኖችን ገና አላፈራችም። የመቻቻል እና የመደማመጥ፣ ተቃራኒን ሃሳብ፣ የማንደሰትበትን ውሳኔ፣ የምንጠላ ውን አመለካከት እንደ በጎ የሚቀበሉ መሪዎችን ገና አላገ ኘችም። አንድ ሰው እንዳለው «ኮምፒውተሩ ባልተጫነበት ሶፍት ዌር ሊሠራ አይችልም»።

ስለሆኑ፣ ከሠፈር እድር እስከ ቤተ መንግሥት፣ ከቀበሌ እስከ ፓርላማ፣ ከአንደኛ ክፍል እስከ ዩኒቨርሲቲ ኢትዮጵያ የምትፈልጋቸውን ዓይነት መሪዎች ለማፍራት የሚያስችል



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘፈን፣ ተረት፣ አባባል፣ ጨዋታ፣ ብሂል፣ ወግ፣ ባህል፣ ሥርዓት አለንን? እንደ ኢትዮጵያ ባለች ሚዲያ እና ንባብ፣ ትምህርት እና ለዘመናዊ ሥልጣኔ መጋለጥ ውሱን በሆነባት ሀገር፣ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜያቸውን ከአካባቢያዊ ባህላቸው እና ወጋቸው ጋር ነው በሚያሳልፉባት፣ ካነበቡት መጽሐፍ የሰሙት ተረት፣ ከተማሩት ትምህርት የበለጠ ድግስ ከተከታተሉት ሚዲያ የዋሉበት ጨዋታ፣ ካገኙት ሥልጠና ያመሹበት የልቅሶ ድንኳን፣ በሚበዛበት ማኅበረሰብ ውስጥ፣ ኅብረተሰቡ የሚፈልጋቸውን መረጃዎች ለመፍጠር የሚያስችል ባሕል አለውን?

አባቱ አንድም ቀን ጋዜጣ ሲያነብ ያላየው፣ እንዲያነብም ያላደረገው፣ በቤታቸው ውስጥ ከትምህርት መጻሕፍት በቀር ሌላ መጽሐፍ ሲገዛ አይተው የማያውቁ፣ እናቶች ከብበው ቡና ላይ፣ አባቶች ከብበው ጠጅ ቤት እና ልቅሶ ቤት ሲያወሩ እንጂ መጽሐፍ ሲያነብቡ፣ ባነበቡት እና በተረዱት ነገርም ሲከራከሩ ያልሰማን ልጅ፣ ነገ አድጎ ስለ ፕሬስ ነጻነት ዘብ ይቆማል የሚለው ማን ደፋር ነው?

ስሞቻችን እንኳን «በለው፣ቆረጠው፣ ፍለጠው፣ እንቆራጠው፣ ግዛቸው፣ ቀኛቸው»፣ በሆነበት ሀገር፣ መሪነትን ሲያስብ ጉልበትን የማያስብ መሪ ከየት እናመጣለን?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤተሰቦቻችን፣ እድሮቻችን፣ ዕቁቦቻችን፣ የትምህርት ክፍሎቻችን፣ የጽዋ ማኅበሮቻችን፣ ሰንበቴዎቻችን፣ መጅሊሶቻችን፣ የእምነት ተቋሞቻችን፣ የወጣት እና የሴት ማኅበሮቻችን፣ የሞያ እና የሲቪክ ማኅበሮቻችን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶቻችን፣ ምን ዓይነት መሪዎች አሏቸው? ስለ ፓርላማው እና ስለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ስለ ካቢኔው እና ስለ ምክር ቤቱ ከመነጋገራችን በፊት በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ታላቁን ቦታ ስለሚይዙት ስለ እነዚህ ተቋማት አሠራር፣ አመራር፣ የመሪዎች አመራረጥ፣ ድምጽ አሰጣጥ እስኪ እንነጋገር::

ለመሆኑ በዕድር እና በዕቁብ የምረጡኝ ዘመቻ አለ? የክፍል ኃላፊን ስም ጠሪ መምህር ይመርጠዋል ወይስ ሃሳቡን አቅርቦ ብትመርጡኝ ለክፍላችን እንዲህ እና እንዲያ አደርጋለሁ ብሎ ተማሪው ይመርጠዋል? ለመሆኑስ በክፍል ኃላፊ ምርጫ ተማሪዎች በኮርጆ ውስጥ ድምጽ ይሰጣሉ? በእድር እና በዕቁብ ሊቀመንበር እና ሰብሳቢ ምርጫ ጊዜ ድምጽ እንዴት ነው የሚሰጠው፣ ምርጫው ዲሞክራሲያዊ፣ግልጽ እና የማይጭበ ረበር ነው?

የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶች፣ ዲኖች፣ የዲፓርትመንት ሊቃነ መናብርት ሃሳባቸውን አቅርበው፣ ምረጡን ብለው፣ ተወዳድረው፣ የምረጡን ዘመቻ አድርገው፣ ተከራክረው ብደመፅ አሰጣጥ ሥርዓት ተመርጠው የሚመሩበት ዘመን መቼ ነው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚመጣው? ተማሪዎችስ የተማሩ ምክር፡ ቤቶችን መሪዎች፣ የፓርር ላማ አባላት በሚመረጡበት ሥርዓት የሚመርጡት እና ለወደ ፊቱ የፖለቲካ እና የመሪነት ሕይወታቸው ልምድ የሚቀ ሰሙት መቼ ነው?

ታድያ እነዚህን ሁሉ እንደዋዛ ዘልለን የሀገር መሪ ከየት እናገኛለን። ዘውስ እንጻለው እኛ ያልፈጠርነውን መሪ ፈጣሪ ከየት ያመጣዋል? ከአፍሪካ? ከአውሮፓ? ከአሜሪካ? ከቻይና? ወይስ ከላቲን አሜሪካ? ለምን መንደራችንን በተገቢው መንገድ ከማ ስተጻር እንጀምርም። በኮንዶሚኒየም ሕንፃዎች፣ በራል እስቴት መንደሮች፣ በአፓርትመንቶች፣ ግልጽ ምርጫን፣ እንዳች የለ ውጥ ዕቅድ ይዞ ተመርጦ መሥራትን፣ በየጊዜው ሪፖርት ማድረግን፣ ተሰብስበን ሥራን መገምገምን፣ በሚገባ የሠራውን መሸለምን፣ በሚሰጠን አኅዛቢያዊ ሐላፊነት ያለ ቸልታ ማገልገ ልን ለምን እንጀምረውም? መሪዎችን ለምን እንፈጥርም? መሪ ነት ፓርላማ ከገቡ፣ ከተሾሙ እና ሥልጣን ከያዙ በኋላ እን ዴት ይጀመራል? ሰዎች እየመሩ ቆይተው ወደ ሥልጣን መምጣት አለባቸው እንጂ ወደ ሥልጣን መጥተው መሪነትን መማር የለባቸውም።

የዕድሩ ሙሴ ከተመረጡ ስንት ጊዜያቸው ነው? ሥልጣናቸውስ ገደብ አለው? የዕቁቡ ዳኛ ለስንት ዓመት ነው ከዓመት አንድ ዕጣ እየበሉ የሚኖሩት? የሥልጣናቸው ገደብ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እነበ መቼ ነው? የሰበካ ጉባኤው ምክትል ሊቀ መንበር፣ የአካባቢው መጅሊስ ሊቀ መንበር፣ የወጣቶች ማኅበር ሰብሳቢው፣ የሴቶች ማኅበር ሊቀ መንበር፣ የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት፣ የኮሚቴው ሊቀ መንበር፣ የክለቡ ፕሬዚዳንት፣ የድርጅቱ ፕሬዚዳንት፣ የሥልጣናቸው ገደብ ይታወቃል? እዚያ በታስ ከተቀመጡ ስንት ጊዜ ሆናቸው? የሚተካቸው ሰው ስለጡ ነው? እርሳቸው ተቀብተው ነው የተቀመጡት? ለመሆኑስ እንዴት እንደሚቆዩ እያሰቡ ነው የሚኖሩት ወይስ ተሩ ሥራ ሠርተው እንዴት ለሌላው እንደሚያስረክቡ? ታድያ በጊዜ ገደብ ሥልጣን ላይ የሚወጡ፣ ጊዜያቸው ሲደርስ ሪፖርታቸውን አቅርበውና የሚገባቸውን ሠርተው ወንበራቸውን ለሌላው የሚ ያስረክቡ መሪዎች ከየት ነው የምናገኘው? ከመካከላችን ያልፈ ጠርናቸውን ከየት እናስመጣ?

ኑ በየአካባቢያችን የነገ መሪዎቻችንን እንፍጠር:: ሕዝብ ነው መሪውን በአርአያው እና በአምሳሉ የሚፈጥረው:: መሪ በአንድ ቀን ምርጫ፣ በአንድ ስሞን ንግግር አይፈጠርም፡ መሪ በሂደት የሚገኝ ነው:: ባሕሩ ያልያዘውን ዓሣ መረቡ አያጠምደውም:: ከሩንችት ተዘርቶ በለስ፣ እሾህ ተዘርቶም ወይን የሚያበቅል መሬት የለም:: ***የሌ ትምህርት ለወርማዛንያ በሬፊ 707፣ ወደ አዲስ አበባ***



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ድንጋይ ሰድብ ነው ወይ?

***አንዳንድ*** ጊዜ በተለምዶ የተቀበልናቸው፣ እኛም ሳንመረምር ዝም ብለን የምናደርጋቸው እና የምንናገራቸው ነገሮች፣ የያዙት እውነታ ከሚታወቀው በተቃራኒ ሆኖ የሚገኝበት ጊዜ አለ። ትምህርት የማይገባውን፣ ሰነፉን እና ደደቡን፣ ሥራ ጠሉን እና ዘረጦውን ለመግለጥ «እገሌ ድንጋይ ነው» እንላለን። የሌላውን ሀገር አላውቅም እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን እንዲያ ብሎ መሳደብ እና ድንጋይን ለውጥ ለሌለው፣ ለሰነፍ እና ለሥራ ጠል አእምሮ ምሳሌ ማድረግ የምንችል አይመስለኝም።

ስለ ኢትዮጵያ ፊደል አመጣጥ ሊጠየቅ የሚችለው መረጃ ድንጋይ ነው። ቀደምት ሳባውያን ታሪካቸውን እና የኑሮ ዘገባቸውን፣ ንግግራቸውን እና እምነታቸውን ጽፈው ያስቀመጡት በድንጋይ ላይ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ የምንጠቀምበት እና የምንኮራበት ፊደል እንዴት እና ከየት ተገኘ ብለን ብን መረምር የመረጃው ባለቤት ድንጋይ ነው። ፊደላችንን ብቻ ሳይሆን በወቅቱ የነበሩትን የጥበብ መሣሪያዎቻችንን፣ የጦር መሣሪያዎቻችንን፣ የእህል ዓይነቶቻችንን፣ የምንጠቀምባቸውን ከብቶች፣ የዛፎቻችንን እና



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የማሰድናት ሁብቶቻችንን እንኳን የምናገኘው ከድንጋይ ላይ መረጃዎቻችን ነው::

የኢትዮጵያ የጥንቱ ግዛት ከየት ተነሥቶ የት ይደርስ እንደ ነበር፣ ማን ማን የተባሉ ሕዝቦች በአክሱም መንግሥት ሥር ይተዳደሩ እንደ ነበር፣ የትኞቹ ቦታዎች በጦርነት ገብረው እንደ ነበር፣ የትኞቹ ቦታዎች ወርቅ፣ የትኞቹስ ቦታዎች እልማዝ፣ የትኞቹስ ቦታዎች ሰንቁ ይገብሩ እንደ ነበር የጥንቱን መረጃ የያዘው የድንጋይ ላይ ጽሑፍ ነው::

ለመሆኑ የኢትዮጵያን የብዙ ሺ ዓመታት ታሪክ የድንጋይ ያህል አሟልቶ የሚያውቀው አለ? ለቅድመ ጽሑፍ ታሪካችን ምስክሩ የአክሱም እና የደቡብ ትክል ድንጋዮች ናቸው፤ ለአክሱም ዘመን ታሪካችን ምስክሩ በአክሱም አካባቢ እና ባሕር ተሻግሮ በየመን የተገኙት የድንጋይ ጽሑፎች ናቸው:: በዘመኑ የተጻፈ የታሪክ መረጃ የለም ተብሎ በባለ ታሪኮች ዘንድ «የጨለማ ዘመን» እየተባለ ስሙ የጠፋው የዛግዌ ሥርወ መንግሥት ታሪካችን እንኳን ሕያው ምስክሩ የድንጋይ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፤ ከዛግዌ ሥርወ መንግሥት በኋላ ለመጣው የመካከለኛው ዘመን ታሪካችንም ከጦርነት የተረፉን መረጃዎቻችን በየዋሻዎቹ የምናገኛቸው መዛግብቶቻችን ናቸው፤ የጎንደር ዘመንም አሻራዎቹ ከድንጋይ የተሠሩት ግንቦቻችን ናቸው:: ሐረር ለነበረው ሥልጣኔ እና ታሪክ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሕያው ምስክራችን ከድንጋይ የተሠራው የሐረር ግንብ ነው:: እናም ሦስት ሺም እንበለው ሰባት ሺ የኛን ታሪክ ከድንጋይ በተሻለ ማን ያውቀዋል::

በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን የክርስ ቲያን ሙስሊም ጦርነት በተመለከተ እንኳን በሁለቱም ወገን ከተጻፉት ታሪኮች ሌላ ምስክር የምናገኘው በድንጋይ ላይ ነው:: የት የት ቦታዎች ጦርነቱ ተደረገ? በወቅቱ የድል በለስ እየቀናው የመጣው የኢብን ኢብራሂም አሕመድ አልጋዚ ወታደሮች እና ተከታዮች የት ቦታ ላይ ተቀበሩ? በመጨረሻም አሕመድ አልጋዚ የት ቦታ ድል ሆነ? እያልን ብንጠይቅ በወቅቱ የነበረውን ታሪክ የምናገኘው «የግራኝ» ድንጋይ በመባል ከሚታወቁት እና በወቅቱ ከተተከሉት ትክል ድንጋዮች ይመስለኛል::

ሀገራችን በጦርነት ስትታመስ፣ ሕዝቦቿም ራሳቸውን እና ሀገራቸውን ሲከላከሉ የኖሩ ናቸው:: አብዛኛው ታሪካችንም የጦር ነት ታሪክ ነው ይባላል:: በዚህም የተነሣ እያሌ ታሪካዊ መዛ ግብትን አጥተናል:: መጻሕፍቱ፣ ሥዕሎቹ፣ ደብዳቤዎቹ፣ ንዋ ያቱ እና የወግ ዕቃዎቹ እየተቃጠሉም፣ እየተዘረፉም፣ በአፈር እየተበሉም አልቀውብናል:: የተረፉትም ቢሆኑ ዕድሜ ለድን ጋይ በየዋሻዎቹ ተደብቀው፣ ከአፈር መበላት እና ከእሳት፣ ብሎም ከቀበኛ የተረፉልን ናቸው:: እነዚህ የድንጋይ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ምሰሶ እና የድንጋይ ወጋግራ ዘርግተው የተፈጠሩ የድንጋይ ቋሻዎች ባይኖሩ ኖሮ፣ አሁን የምንኮራባቸውን የብራና መጻሕፍት፣ ንዋ ያት እና የወግ ኢቃዎች አጥተን ተረት ብቻ ወርሰን በቀረን ነበር።

እነዚያ የድንጋይ ዋሻዎች ንብረቶቻችንን ብቻ ሳይሆን በእነዚያ የጦርነት እና የመከራ ጊዜያት እናቶቻችንን እና አባቶቻችንንም አስጠልለው አትርፈዋል። በሰሜን ሸዋ ተራሮች ሥር የሚገኙት እና «ዋሻ እግሌ» እየተባሉ የሚጠሩት ለቁጥር የሚታክቱት ዋሻዎቻችን፣ የባሌው ሰብስቤ ዋሻ እና የጋሞጎ ፋው የቦረዳ ዋሻ ለዚህ ምስክሮቻችን ናቸው።

ቀደምቶቻችን ሰማይ ሰማዩን ብቻ ሲያዩ አልኖሩም። ምድር ንም በሚገባ ዐውቀዋት ነበር። ከሰሜን እስከ ደቡብ የምናገኛቸውን የድንጋይ ጥበቦቻችን የተሠሩባቸው ዐለቶች ተመሳሳይ ጠባይ ያላቸው ናቸው። እነዚያ ጠቢባን ድንጋዮቹን በሁለት መመዘኛ ነው ሲመርጧቸው የኖሩት። ቅርጽ ለማውጣት የሚ ያስችል እና ረዥም ዘመን ለመኖር ዐቅም ያለው። በሁለቱም ተሳክቶላቸዋል። የሚገርመው ግን እነዚህን መመዘኛዎች የሚ ያሟላውን ድንጋይ ለማወቅ የሚጠይቀውን የጂኦሎጂ ዕውቀት ከየት አገኙት? የሚለው ነው።

አንድ ሊቅ «ኢትዮጵያውያን ማለት ድንጋይ ሲያናግሩ የኖሩ ሕዝቦች ናቸው» በማለት የተናገረው እውነቱን መሆን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አለበት። መረቡን ፈልገው፣ ድንጋዩን አጥንተው፣ መርጠው እና አለዝበው ዘመናትን የሚሻገር የሥልጣኔ አሻራ መተው የቻሉት ድንጋይ የማናገር ችሎታ ስለነበራቸው መሆን አለበት። እነዚያን ድንጋዮች ቤት ብቻ አይደለም የሠሩባቸው። መሠዊያቸውን፣ መስቀሎቻቸውን እና ደወሎቻቸውንም ሠርተውባቸዋል። በወሎ፣ በጎንደር እና በጣና ገዳማት የምናገኛቸው የድንጋይ ደውሎች ድምፃቸው ከመዳብ እና ከብረት ደውሎች ይበልጣል። ለዚህ የተስማማውን፣ ድምፅ ሊያወጣ የሚችለውን የድንጋይ ዓይነት በምን ዐወቁት? ወይስ ያን ጊዜ የጂኦሎጂ ትምህርት ነበረ እንዴ?

ምናልባትም ቀደምቶቻችን የተፈተነ ሕይወትን የሚወድዱ ሳይሆኑ አይቀሩም። በቀላሉ ከእንጨት፣ ሣር እና ቅጠላ ቅጠል ሊሠሯቸው ይችሉ የነበሩትን ነገሮች ከባድ ከሆነው እና ልዩ ችሎታን እና ቴክኖሎጂ ከሚጠይቀው ከድንጋይ ለመሥራት የፈለጉት ተፈጥሮን ለመፈተን፣ ዕውቀትንም ለመገዳደር ይመስለኛል። የጀግንነታቸው አንዱ መገለጫም ጠላትን በመቋቋም ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮን ተፈታትነው በማስገበርም ጭምር እንደሆን ሳያስቡ አልቀሩም። በዚህ መልኩ መከራን ተቋቁሞ ማለፍን አስቀድመው ከተፈጥሮ ጋር ባደረጉት ትግል ስለ ለመዱት ሳይሆን አይቀርም እነዚያን ክፉ ጊዜያት ታሪክ እና ቅርስን ጠብቀው ለማሳለፍ የቻሉት።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ክርስቲያንም ሙስሊምም ያልነበሩት ቀደምት የዳአማት
መንግሥታት ታሪካቸውን ያቆዩት በድንጋይ ነው፤ በክርስትና
ቸው የታወቁት የዛግዌ ንገሥታት እና ሕዝቦችም ታሪካቸ
ውን ያቆዩት በድንጋይ ነው:: ሙስሊም የተነበሩት ግዛቶቻ
ችን እና ሕዝቦችም ታሪካቸውን ያቆዩት በድንጋይ ላይ ነው::
በትግራይ፣ በላስታ እና በጎንደር ከ3000 በላይ ውቅር አብያተ
ክርስቲያናትን እናገኛለን:: በአርጎባ «ራሳ» አካባቢ ደግሞ
አርጎባዎች «ቱሉል» ብለው የሚጠሯቸው ወደ 3000 የሚጠጉ
በባለሞያ የተቀረጹ የድንጋይ ምስሎች እናገኛለን:: እናም፣
ምንም በሃይማኖት ብንለያይም ሥልጣኔያችን ግን በድንጋይ
ላይ ሠፍሮ አንድነታችንን ይመሰክርብናል::

ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለውን የኢትዮጵያውያንን አንድነትስ ቢሆን ከድንጋይ በተሻለ ማን ይመሰክረዋል:: አንድ ሰው እንዳለው «እስክስታ እና ድንጋይን ያህል የኢትዮጵያን ሕዝቦች አንድነት የሚያሳይ ባሕላዊ ገጽታ የለም»:: ትግራይ ላይ ከወደ አንገት እና ትከሻ የጀመረው እስክስታ፣ አገው እና አማራ ላይ ሲደርስ አንገትን ከትከሻ ያያይዝና፣ ኦሮሚያ ላይ አንገትን፣ ትከሻን እና ወገብን ከእጅ እንቅስቃሴ ጋር ያዋሕዳል:: ወላይታ እና ሐድያ ላይ ሲወርድ ደግሞ ወገብን ታክኮ ወደ ዳሌ ዝቅ ይላል:: ከዚያም ደቡብ ጫፍ ሐመሮች ላይ ሲገባ እስክስታው በእግር ይጨርሳል:: ያኔም ኢትዮጵያ አንድ ሰው ሆና ትታያለች ማለት ነው::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ድንጋይም እንዲሁ ነው:: ከሰሜን አኩስም እስከ ባሌ ተራሮች፣ ከምዕራብ ኦጋዴን እስከ አሰሳ፣ ኢትዮጵያ በታሪካዊ የድ ንጋይ ሐውልቶች የተሞላች ናት:: በጣም የሚገርመው ደግሞ እነዚህ የድንጋይ ሐውልቶች ከመቃብር እና ከታሪካዊ ሁነቶች ጋር የተያያዙ መሆናቸው ነው::

የአኩስም ሐውልት በታላላቅ የአኩስም ነገሥታት መቃብር ላይ መታሰቢያ ሆኖ ቆሟል:: ከአዲስ አበባ ደቡብ 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ጀምሮ በሲዳማ፣ ወላይታ፣ ሐድያ፣ ስልጢ፣ ከምባታ፣ በሰሜን በአዋሳ ሐይቅ፣ በምዕራብ ደግሞ በአባያ ሐይቅ ተከብቦ የሚገኘውና ከ150 በላይ ታሪካዊ ሥፍራዎችን የያዘው የድንጋይ ሐውልቶች ስብስብ፣ እንደ ሰሜኑ ሁሉ የመቃብር ሥፍራዎችን እና ታሪካዊ ሁነቶችን መሠረት ያደረገ ነው:: በኦሮሚያ ክልል በተለይም በአርሲ እና ባሌ የምናገ ኛቸው ሐውልቶችም ይህንኑ የሰሜን እና ደቡብ እሴት ተጋ ርተው፣ እንድነታችንንም መስክረው ይሄው ዛሬም ይታያሉ::

ድንጋይ ሥልጣኔያችንን ብቻ ሳይሆን ጀግንነታችንንም ሲመሰክር የኖረ ነው:: መሣርያ እንደ ልብ ባልነበረበት በዚያ ዘመን ሉዓላዊነታችን ታፍሮ፣ ድንበራችን ተከብሮ፣ የኖረው በድን ጋይ ጭምር ነው:: ቆንጥር ለቆንጥር መወርወር፣ ተራራ ለተ ራራ መኖር የለመደው ሐበሻ በተራሮች ጫፍ መሽጎ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ይስቅቀው በነበረው ናዳ ያስቀውን ጠላት ያህል ሲላው መሣርያ ችን መጨረሱን እጠራጠራለሁ:: ከሚደማ አካባቢዎች ይመጡ የነበሩት አብዛኞቹ የውጭ ጠላቶች ከመሣርያችን በላይ መቋ ቋም ያቃታቸው ለሀገሩ ልጅ ብቻ ይበገር የነበረውን መልክዐ ምድራችንን ነው::

እናም ድንጋይ የታሪካችን፣ የፊደላችን፣ የሥልጣኔያችን፣ የእምነታችን፣ የቀጣይነታችን፣ የአንድነታችን፣ የኅብረችን መገ ለጫ ከሆነ «ድንጋይ» እንዴት ስድብ ይሆናል?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ፈረንጆቹ

አሜሪካ ሚኒሶታ ያሉ ኢትዮጵያውያን ልጆቻቸው አማርኛ ቋንቋ እንዲያውቁ ፊደልና ትምህርት ቤት አዘጋጁ:: የሁሉም ፍላጎት ቋንቋ ማሳወቅ እንጂ እንዴት ማሳወቅ እንደሚቻል ልምዱ ያለው ሰው አልተገኘም:: በኋላ በአንድ ሰው ጠቋሚነት ጥንት ለመሠረተ ትምህርት ማስተማርያ ያገለግል የነበረው የማስተማርያ መጻሕፍ ተገኝና እርሱ ነጭ ሰሌዳ ላይ እየተገለበጠ ትምህርቱ እንዲሰጥ ተወሰነ:: ታድያ ተማሪዎቹ በተሰበሰ በብት በመጀመርያው ቀን ነበር ትምህርቱ ፈተና የገጠመው::

መምህሩ በነጩ ሰሌዳ ላይ ከመሠረተ ትምህርት ማስተማርያ መጽሐፍ ገለበጠና በመጠቆሚያ እንጨት እያመለከታቸው «አበበ በሶ በላ» በሉ አላቸው:: ተማሪዎቹ ግን «who cares» ነበር ያሉት:: እንደ ደነገጠ ወደ ሁለተኛው መሥመር ሄደና «ጫላ ጩቤ ጨበጠ» አላቸው:: ክፍሉ ውስጥ ውውውው ውውው የሚል የተቃውሞ ድምጽ ተፈጠረና አንዲት ሕፃን ተነሥታ «this is very dangerous, they should report it to the police» አለችው:: እናም መምህሩ ከዚህ በላይ መቀጠል አልቻለም::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በአሁኑ ጊዜ በልጆች እና በወላጆች መካከል የአስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን የፍላጎት፣ የዕውቀት እና ለነገሮች ያላቸው የተጋላጭነት መጠን ልዩነት ተከስቷል:: እንዳንዶቻችን ቴሌቭዥን ያየንበትን እድሜ ልጆቻችን ካዩበት ዕድሜ፣ ኮምፒውተር የነ ካገነበትን እድሜ ልጆቻችን የኮምፒውተር ትምህርት ከሚወ ስዱበት እድሜ ስናነፃፅረው በቀላሉ ልዩነቱን እንረዳዋለን:: እንዳንድ ጊዜ እንዲያውም እኛ ስለ እነርሱ ያለን አስተሳሰብ የዘገየ የሚሆንበት አጋጣሚም አለ:: እንድ ወዳጄ ዘመዱ ቤት ሄዶ የሰማውን ብነግራችሁ ይህንን የሳያችኋል ብዬ አስባለሁ::

ቀደም ብሎ ነው:: የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን የአራት ሰዓት ተከታ ዜና በሚያሰማበት ጊዜ:: ከዜናው በኋላ ስለሚኖረው ፊልም እና ፊልሙን ማየት የሚችሉት እነማን እንደ ሆኑ ማስታወቂያ ይናገራሉ:: የርሱ፣ የእኅቱ፣ እና የአክስቱ ልጆች ሳሎ ኑን ሞልተው ቴሌቭዥን ያያሉ:: አስተዋዋቂዋ የፊልሙን ርእስ ተናገረችን «እድሜያቸው ከአሥራ አምስት ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ማየት አይችሉም» አለች:: ያን ጊዜ ወላጆች ከስ ተር ብለው «በሉ ሂዱና ተኙ፤ ይኼ ለእናንተ የሚሆን አይ ደለም» አሏቸው:: ልጆቹ ግን ቅር እላላቸውም እየሳቁ «ባለ ፊው ጊዜ ኮ ያየነው ፊልም ነው» እየተባባሉ ወደ መኝታ ቤታቸው ሲገቡ፤ ወላጆች በድንጋጤ ክው ብለው ቀሩ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሥርዓተ ትምህርታችን በየጊዜው በመቀያየሩም የተነሣ እኛና ልጆቻችን የተማርናቸው ነገሮች በአቀራረብ ብቻ ሳይሆን በመሠረታዊነት ተለያይተዋል። አንዳንዱን ጉዳይ ደግሞ የተማር ነውም ቢሆን ረስተነዋል። ዛሬ ዛሬ እኛ ላይ ክፍል የተማር ናቸውን እነርሱ የመጀመርያው ሳይክል ላይ ይማሩታል፣ እኛ ፈጽሞ ሰምተናቸው የማናውቃቸውን አዳዲስ መሠረተ ሃሳብ ችም በትምህርታቸው ይደስሷቸዋል። አንዳንዶቻችን ደግሞ ጥሎብን አልፎ አልፎ ጋዜጣ እናነብ ካልሆነ በቀር ለጠቅላላ ዕውቀት የሚሆን ነገር ማንበብም መስማትም አንወድም። ሌላው ቀርቶ ልጆቻችን ምን ይሆን የሚማሩት? ብለን እንኳን መጽሐፋቸውን አናገላብጥም።

ከጥንት ጀምረው ኢትዮጵያውያን ወላጆች እነርሱ ያላገኙትን ልጆቻቸው እንዲያገኙ መድከም ልማዳቸው ነው። «እስመ ጽሙዐን ለትምህርት ብሔረ ኢትዮጵያ ኄራን» እንዲል ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በመጽሐፈ ብርሃን። ሳይማሩ ያስተምራሉ አይደል የምንላቸው? በርግጥ ሳይማሩ ማስተማር በጥንቱ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ እምብዛም ጉዳት አልነበረውም። ተማሪዎች ከክፍል ወጥተው የሚሠሩት የቤት ሥራ ካልሆነ በቀር ከወላጆ ቻቸው ጋር የሚያገናኝ ነገር እምብዛም የለውም ነበር። ቢበዛ ረባሽ ተማሪ ሲያጋጥምና ወላጅ አምጣ ሲባል መሄድ ነው። እርሱም ቢሆን መንገድ ላይ የተገኘ የቆሕ ሰው ወላጅ ነው ተብሎ የሚወሰድበት ዘመን ነበር።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን በየትምህርት ቤቱ ያሉት አዳዲሶቹ መምህራን ግን «ሳይማር ያስተማረ» የሚባለውን ወላጅ ረስተውታል መሰለኝ:: ለልጆቹ የቤት ሥራ ሲሰጧቸው «ወላጆቻችሁን ጠይቁ» ይሏቸዋል:: ምን ይሄ ብቻ፤ ልጆች ክፍል ውስጥ የሠሩትን ሥራ ተመልክተው ወላጆች እንዲፈርሙ ከየደብተሩ ግርጌ «የወላጅ ስም እና ፊርማ» እያሉ ያውም በእንግሊዝኛ ጽፈው ይልካሉ:: ኧረ እንዲያውም አንዳንድ ትምህርት ቤቶችማ ለወላጆች ማስታወሻ የሚልኩት በእንግሊዝኛ ብቻ ነው፤ ልጆች ደግሞ «የወላጅ ፊርማ» ከተባለ «የወላጅ ፊርማ» ነው የሚያውቁት:: አንዳንዱ ወላጅኮ እንኳንስ ሳይማር ቀርቶ ተማርኩ የሚለውም የልጆቹ ትምህርት እርሱ ከሚያውቀው ተቀይሮበታል:: በተለይም በአሁኑ ጊዜ «የኛ ሙሽራ ኩራቸው፣ በእንግሊዝ እናግ ሪያቸው» የሚለው የጥንቱ የሠርግ ዘፈን በትምህርት ቤቶቻችን በሚተገበርበት ዘመን፤ በአማርኛ ያልተማርነውን በእንግሊዝኛ ለልጆቻችን ማስረዳቱ ችግር ሆኗል::

አንድ ዘመዳችን ልጆቹን ምርጥ የተባለ ትምህርት ቤት ያስገባል:: ያ ትምህርት ቤት ደግሞ የሚታወቀው ልጆቹን በእንግሊዝኛ እንዲቀብጡ በማድረግ ነው:: እናም ልጆቹ አለባበሳቸው፣ አበላላቸው፣ አካሄዳቸው፣ የፀጉር አሠራራቸው ሁሉ በእንግሊዝኛ ሆነ:: ማታ ማታ ሲገቡ የቤት ሥራቸውን ጠረጴዛ ላይ ይዘረግፉና «ዳድ ይህንን እንደርስታንድ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አላደረግኩትም» ይሉታል። እርሱ ደግሞ አራተኛ ክፍል ላይ ያቋረጣ ትን ትምህርት ልጆቹ በጸደ ሕፃናት እያሉ ነበር አልፈዋት የሄዱት። «እናታችሁን ጠይቋት» እያለ ያልፋቸዋል። እናት ታስረዳለች።

በኋላ ግን ሊያዋጣው አልቻለም «የነ እገሊት ዳድ አኮ ያስጠናቸዋል፤ የነ እገሊት ፋዘርኮ በእንግሊዝኛ ነው የሚያዋራቸው፤ ደግሞ ቲቸር ፋዘራችሁን ጠይቃችሁ ኑ ነው ያለን» እያሉ አላ ስቀምጠው አሉ። እርሱ ሁለት ችግር ነው የገጠመው። እንዳ ንጹን ነገር ጭራሹኑ ስምቶት አያወቅም፤ የሚያውቀውን ደግሞ ለማስረዳት እንግሊዝኛ የሚባለውን ቋንቋ ከየት ያም ጣው። አንድ ቀን ልጆቹ «ስቶሪ ቡክ» አንብብልን ብለውት በዚያች በሚያስታውሳት እንግሊዝኛ እየሰባበረም ቢሆን ሊያነ ብባቸው ሲሞክር ልባቸው እስኪፈርስ ስቀው «እንዴ ዳድ! በምን ቋንቋ ነው የምታነብልን» ያሉትን ሲያስበው ከአድ ሚው እየቀነሰ ተቸግሮአል። እናም በየጊዜው መሽወዱ አላ ዋጣ ሲለው፣ ሥራ አለብኝ እያለ ልጆቹ ከተኙ በኋላ መግባት ጀመረ አሉ። መሽት ሲል ባለቤቱ ጋ ይደውልና «እንዴት ነው ፈረንጆቹ ተኙ?» ይላል አሉ።

ልጆች ወላጆቻቸውን አያውቁም ብለው ከገመቱ ሁለት አደጋ ዎች አሉት። የመጀመርያው የሚቆጣጠረኝ የለም ብለው እንዲገምቱና ከመጠን በላይ እንዲዝናኑ ያደርጋቸዋል።



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ልጆቻቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር በየጊዜው መሥራት አለመሥራታቸውን ወላጆች ማረጋገጥ አይችሉም:: ደብተሩን ገለጦ የተቀመጠ ልጅ ሁሉ ያጠና ሊመስላቸው ይችላል:: ሁለተኛው አደጋ ደግሞ ልጆች በወላጆቻቸው እንዳይተማመኑ ያደርጋ ቸዋል:: በየጊዜው ወደ ትምህርት ቤት ወላጆቻቸው ተጠሮ ተው ከመምህራኑ ጋር በጉዳዮች ላይ በእኩልነት የማይነጋገሩ ከሆነ አያውቁም የሚል ግምትን ልጆች ይወስዳሉ:: ይህ ደግሞ በወላጅ የመተማመናቸውን ነገር ይቀንሰዋል:: አባዬ አያውቀውም፣ እማዬ አታውቀውም ማለት ከጀመሩ ደግሞ ከወላጆቻቸው ጋር የሚኖራቸውን ውይይት ያዳክመዋል::

በውጭው ዓለም የሚኖሩ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውን ወላጆች፣ በተለይም ከሀገር ቤት ልጆቻቸውን ይዘው የሚሄዱ ወላጆች፣ ትልቁ ፈተና ከልጆቻቸው ጋር የዕውቀት እና የቋንቋ መለያየት ነው:: ብዙ ጊዜ ልጆቹ ትምህርት ቤት እንደገቡ ወዲያ ውኑ የሀገሩን ባሕል እና ቋንቋ ይለምዱታል:: የሚውሉትም ከሀገሬው ሰዎች ጋር ስለሆነ የተሻለ ተጋላጭነት አላቸው:: ወላ ጆች ግን አብዛኛውን ጊዜ ከሀገራቸው ሰው ጋር ያሳልፋሉ:: ሥራ ቢገቡም የተወሰኑ ነገሮችን በሀገሬው ቋንቋ ሊናገሩ ይች ላሉ እንጂ የልጆቻቸውን ያህል ሊያግባቡ የሚችል አካባቢ አይገጥማቸውም::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ የተነሣ አንዳንድ ወላጆች ቋንቋን ከልጆቻቸው ለመማር ሲሉ ቤታቸው ውስጥ በእናት ቋንቋቸው ሳይሆን በሄዱበት ሀገር ቋንቋ ልጆቻቸውን ማነጋገር ይጀምራሉ። እንኳንስ የልጆቻቸውን ትምህርት ሊከታተሉ ይቅርና እነርሱ ራሳቸው ከልጆቻቸው እንደሚማሩ ልጆቹ ሲያውቁ ኢትዮጵያዊነቱን እና ኢትዮጵያዊውን ባሕል እየተው ቅልጥ ብለው ወደዚያኛው ሀገር ይገባሉ። በመካከል በልጆች እና በወላጆች መካከል ችግር ሲፈጠር መግባባት አይቻልም።

መጀመርያ ነገር ልጆቹን እና ወላጆቹን የሚያግባባ ቋንቋ አይገኝም። የወላጆችን ቋንቋ ልጆች ረስተውታል፣ የልጆቹን ቋንቋ ደግሞ ወላጆች ገና በሚገባ አልለመዱትም። «አላውቅበት እል ኩኝ ያንቺን አማርኛ» ያለው ነገር ይመጣል። በሌላ በኩል ደግሞ በሁለቱ መካከል የእሴት ልዩነት ተከስቷል። ልጆቹ የተማሩት «ጥሩ ነገር» ወላጆች ከሚያውቁት «ጥሩ ነገር» ተለይቷል።

አንድ ጊዜ እንዲያውም በልጆች እና በወላጆች መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት ለተቀመጡት ሽማግሌዎች አንድ አዳጊ ልጅ የተናገረው ነገር የችግሩን ስፋት ቁልጭ አድርጎ ያሳየዋል ብዬ አስባለሁ። «እባቴ የኢትዮጵያን ባሕል እና ተረት ነግሮኝ አያውቅም፣ የዚህን አገር ተረትም አያው ቃቸውም፣ የኢትዮጵያን ቢነግረኝ ኖሮ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደኔ እንግሊ እንዴትሆን እያለ ለመምከር ይችል ነበረ፡ የዚህን ሀገር ቢያውቅም በዚያ ይመክረኝ ነበረ። እርሱ እና እኔ በምን እንግባባ?» አለ እሱ።

አንዳንድ ወላጆች ይህንን ችግር ለመፍታት የሚሞክሩት አስጠኚ በመቅጠር ነው። በርግጥም የሚያስጠናው ሰው የትምህርት ችግሮችን በተወሰነ መልኩ ይፈታ ይሆናል። ወላጅን ግን ሊተካ አይችልም። ወላጆች ጠዋት ወደ ሥራ ሲገቡ ልጆችም በዚያው ሰዓት ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ። ማታ ወላጆች ከሥራ ሲመለሱ ልጆች የቤት ሥራ መሥራት ወይንም ማጥ ናት አለባቸው፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ይመሽና ልጆች በጊዜ ይተ ኛሉ። ታድያ ልጆች እና ወላጆች ጥናት ላይ ወይም የቤት ሥራው ላይ ካልተገናኙ መቼ ሊገናኙ ነው? ወላጆች ልጆቻ ቸውን ለአስጠኚዎች ብቻ ከተዋቸው የሚኖራቸውን የማንኙ ነት ገመድ በራሳቸው ጊዜ እየበጠሱት ነው ማለት ነው።

ስደተኞችን በብዛት በሚቀበሉ እንደ አሜሪካ፣ ካናዳ እና አውስትራሊያ ባሉ ሀገሮች እንደተለመደው ሁሉ ወላጆች የልጆቻ ቸውን የትምህርት ሂደት እንዴት ማገዝ እንደሚችሉ የሚያሠለጥኑ እና የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ያስፈል ጋናል። እነዚህ ተቋማት ለብቻቸው ወይም ከትምህርት ቤቶች ጋር ሊቋቋሙ ይችላሉ። ተቋማቱ በአንድ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በኩል መምህራን ስለ ወላጆች ሁኔታ ተገንዝበው፣ በትምህርቱ ሂደት ወላ ጆችን ጭምር መርዳት እንዳለባቸው ምክር እና ሥልጠና ሲሰጡ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወላጆች ከልጆቻቸው ትምህርት ጋር እንዴት መጓዝ እንደሚችሉ ያሠለጥናሉ፤ ይመክራሉ።

ያለበለዚያማ ፈረንጆቹ እስኪተኙ እየጠበቅን እስከ መቼ አምሽተን ቤታችን እንገባለን?



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

# ካልሞትክ አይገሉህም

**ልጆ ተሰነፉ** ቆርጦ ነው የመጣው:: «ምን ዋጋ አለው ብለው ነው፤ ከንግዲህማ ምንም ተስፋ የለኝምኮ» አላቸው ሽማግሌውን:: «ምን ሆንሃል፣ ጤና የለህም እንዴ?» አሉት ሽማግሌው:: «ጤና ብቻ ሳይሆን ከንግዲህ ምንም ነገር አይኖረኝም» አለ ወጣቱ:: «እንዴት?» አሉት ሽማግሌው እየገረማ ቸው:: «ብቻ ገድለው ቀበሩኝኮ፤ ከንግዲህ ምን ቀራቸው:: የፈ ለጉትን ሁሉ አድርገዋል፤ እንዳልነግ አድርገው ጥለውኛል፣ እን ዳልጠገን አድርገው ሰብረውኛል» አለና የወጣቱ ዕንባ ዱብ ዱብ አለ::

«ካልሞትክ በቀር ሊገድሉህ አይችሉም» አሉት ሽማግሌው ኮስተር ብለው:: ቀና አለና ትኩር ብሎ አያቸው:: «ካልገደሉህ በቀር ልትሞት አትችልም ማለትዎ ነው?» አለና ጠየቃቸው:: «ወዴት ወዴት፤ ካልሞትክ አይገድሉህም:: የሞተን እንጂ ያልሞተን መግደል አይቻልም:: የጠፋን እንጂ ያልጠፋን ማጥፋት አይቻልም፤ የተሰበረን እንጂ ያልተሰበረን መስበር አይቻልም»

«አልገባኝም አባቴ» ዕንባው ቆመ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

«እየህ የሰው እድሜ ሁለት ዓይነት ነው፤ አንዱ የተፈጥሮ ዕድሜ ነው። ይሄ ሊያጥርም ሊረዝምም ይችላል። በሰው እጅ፣ በበሽታ፣ በርጅና፣ በአደጋ፣ በመሳሰለው ሁሉ ያልፋል። ይሄኛው እድሜ ብዙ ጊዜ ካንተ ቁጥጥር ውጭ ነው። በተባለም ለሌላ አደጋ የተጋለጠ ነው። ዋናው ዕድሜ ግን ይሄ አይደለም። ዋናው ታሪካዊ እድሜ ነው። ይሄኛው እድሜ እንደየ ሰው ፍላጎት እና ተግባር ብቻ ይለያያል። ይህኛውን ማስረዘምም ማሳጠረም የምትችለው አንተ ብቻ ነህ። ይህኛው እድሜ በተፈጥሯዊ ዘመንህ ኀሊናህ የሚያምንበትን፣ ትክክል ነው ብለህ የምታስበውን፣ ለሰው ልጆች የሚጠቅመውን፣ እና ወደ ትውልድ የሚተላለፈውን ነገር እስከሠራህ ድረስ ማንም ሊያሳጥረው አይችልም። »

«ሰውን ሰው አያጠፋውም፤ ሰው መጀመርያ ራሱን ያጠፋል፤ ራሱ መጥፋቱን ሲያረጋግጡ ደግሞ ሌሎች ያጠፉታል። ማን ኛውም ነገር እንዳጠቃቀምህ ነው። አንዳንዶች ሲሞቱ ይወለዳሉ፤ ሌሎች ደግሞ ሲወለዱ ይሞታሉ። እስኪ ስማዕታት ናቸው ብለን የምናከብራቸውን ሰዎች ተመልከት፤ ለምን የሞቱበትን ቀን በክብር እናስበዋለን። እነዚህ ሰዎች ከመኖር ለሚ በልጥ ዓላማ የሞቱ ናቸውና፣ በሞቱበት ቀን ለማይጠፋ ልደት ተወልደዋል። ስለዚህ ያ ቀን የተወለዱበት ቀን በመሆኑ በደስታ ይከበራል። ምናልባት ጠላቶቻቸው



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የጠፉቸው መስሏቸው ነው፤ ግን ሳያስቡት ለማይጠፉ ልደት ወለዷቸው።

«አየህ እነዚህ ሰዎች ቀድመው ራሳቸው ስላልሞቱ ሰዎች ሊገድሏቸው አልቻሉም፤ ህያውን መግደል አይቻልምና። አንተም ቀድመህ ካልተሸነፍክ የሚያሸንፍህ፣ ቀድመህ ካልወደቅክ የሚ ጥልህ፣ ቀድመህ ካልከሰርክ የሚያከስርህ፣ ቀድመህ ድል ካልሆ ንክ የሚረታህ አይኖርም። ማንኛውም ውድቀት በሌሎች ሰዎች ምክንያት ብቻ አይመጣም፤ በአንተ አጠቃቀም እንጂ። አንዳንዶች ሞትን ለልደት፣ ሌሎችም ልደትን ለሞት ተጠቅ መውበታል። አንዳንድ ሳይንቲስቶች ከትምህርት ቤት ባይባ ረሩ ኖሮ ሳይንቲስት ባልሆኑ ነበር። አንዳንዶች ባይቸገሩ ኖሮ አይፈጥሩም ነበር። ሌሎቹም ባይሰቃዩ ኖሮ እንዳች አይሠ ሩም ነበር። ወሳኙ የደረሰብህ ነገር አይደለም፤ ወሳኙ አጠቃ ቀምህ ነው። ከውድቀትህ ስኬትን ማመንጨት፤ ወይንም ደግሞ ከስኬትህ ውድቀትን መውለድ ትችላለህ።»

«እስኪ ኢትዮጵያውያን በዒ ቴዎድሮስን ሲያስቧቸው፣ ከሕይወታቸው ውስጥ የትኛው ተግባራቸው ነው የሚታሰባቸው? ያች በመቅደላ አምባ እጄን ጠላት አይይዘውም ብለው ራሳቸ ውን የሠውባትን ክስተት አይደለም? ያች ቀን የሞቱባት ቀን አይደለችምኑ፤ ዐፄ ቴዎድሮስ ለሌላ ዓይነት ልደት፣ ለማይጠፉ ልደት



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

የተወለዱባት ቀን ናት፡፡ ምናልባትም ያንን የመሰለ አስደናቂ መሥዋዕትነትን ባያሳዩን ኖሮ ዛሬ እርሳ ቸውን የምናስባቸው በሌላ ነገር በሆነ ነበር፡፡

**የመቅደላው ላይ ሬሳ**

**የዚያ አንበሳ**

**የካሣ**

**በመቶ ዓመቱ ቢያገሣ**

**ስንቱን ስንቱን ቀሰቀሰውሳ፤**

የተባለው ለዚህ አይደለም፡፡ የሚያገሣ ሬሳ አይተህ ታውቃለህ፡፡
ዝም ብሎ አያቸው፡፡ ከንቱ ዲስኩር የሚደሰኩሩም መሰለለው፡፡

«እና እንደዚህ ከሆንኩ በኋላ፣ እንዲህ አረንቋ ውስጥ ከወደቅኩ በኋላ፣ ካለቀልኝ በኋላ፣ ተስፋ አለህ ነው የሚሉኝ» ንዴቱ ሊመጣበት ነው፡፡

«እስኪ መጀመርያ ይህንን ታሪክ ስማኝ፣» አሉና መተረክ ጀመሩ፡፡

«አንድ ገሥማሥ የሚባል ፈረስ የነበረው ሰው ነበረ፡፡ ሰውዬው ይህንን ፈረስ ለብዙ ዓመታት ሲገለገልበት ኖሯል፡፡ በብዙ ቦታዎች ብዙ አስደናቂ ነገሮችን አብረው አይተዋል፣ ሠርተዋልም፡፡ በብዙ ዐውደ ውጊያዎች ውለዋል፡፡ እያሌ ውድድሮ ችን አሸንፈዋል፡፡ ከልጆቹ እኩል ይወደው ነበር፡፡ እንደ ራሱ አድርጎም ይጠነቀቅለት ነበር፡፡



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ ቀን የገሥግሥ ጌታ ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር መንገድ ሲሄዱ ዋሉና ደክሟቸው ሜዳ ላይ አረፍ አሉ:: ሁሉም ፈረሶቻቸውን ሣር እንዲግጡ ለቀቋቸው:: ገሥግሥ ሣር እየጋጠ እያለ የቆመበት ቦታ ከዳውና መሬቱ ተንሸራትቶ ወደ ገደል ውስጥ ገባ:: ገደሉ በጣም ሩቅ እና መግቢያም የሌለው ነበር:: እዚያ ቦታ ሆኖ የሚያሰማውን ጩኸት ሰምተው ጌታውና ጓደ ኞቹ መጡ:: ሲያዩት ገሥግሥ እጅግ በጣም ጥልቅ ከሆነ ጉድ ጓድ ውስጥ ወድቋል:: እርሱን ለማውጣት የሚያስችል ነገር እንዳለ ብለው ጥቂት አሰቡ፣ ግን ለጊዜው አልመጣላቸውም:: ባለቤቱ አዘነ::

ጓደኞቹም ከኀዘኑ አጽናኑትና «ምንም ማድረግ አይቻልም:: ከዚህ በኋላ ገሥግሥም አርጅቷል፤ አሁን ደግሞ እዚህ ገደል ውስጥ በመውደቁ ምክንያት እጅግ ይጎዳል፤ ከዚህ በኋላ ምንም ያህል አይጠቅምህም:: እናም ካሉን ትርፍ ፈረሶች አንዱን ይዘህ መንገዳችንን እንቀጥል» አሉት:: ባለቤቱ እጅግ አዘነ:: የእነርሱን ንግግር የሚሰማው ገሥግሥም በጣም አዘነ:: የነበረውን አገልግሎት፣ የዋለበትን ቦታ፣ ያሳለፈውን ጊዜ እና ሁኔታ፣ ዛሬ የደረሰበትን ጉዳት እና ድካም እያሰበ በጣም ተሰማው:: ይበልጥ ደግሞ የጌታውን እና የጓደኞቹን ተስፋ የመቁረጥ ንግግር ሲሰማ እርሱም ተስፋ ቆረጠ::

ባለቤቱ አንድ ሃሳብ ለጓደኞቹ አቀረበ:: «ከዚህ በኋላ ገሥግሥን ለማውጣት መሞከር ከንቱ ድካም ነው:: ነገር ግን



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ሁኔታ ጥሎ መሄድም ኅሊናን እረፍት የሚነሣ ነው:: ባይሆን ባለበት ጉድጓድ በሰላም እንዲሞት አፈር እናልብሰው አሉ ቸው:: ሁሉም በሃሳቡ ተስማሙ:: ገሥግሥ ግን ደብልቀ አዘነ፣ ደብልቀም ተሰፋ ቆረጠ:: ከዚህ በኋላ ምንም ዋጋ እንደ ሌለው፣ የመኖር ተስፋውም እንደ መነመነ፣ ልጡ የተራበ፣ ጉድጓዱ የተማሰ እንደ ሆነ ተሰማው:: ሞቱን እያየው ሊሞት ነው::

ከዚያ ጉድጓድ በተአምራት መውጣትን ተመኘ:: ግን ምንም መንገድ ሊታየው አልቻለም:: ቀድሞ ራሱ ስለ ሞተ ሞትን የሚያመልጥበት እንዳች ብልሃት አጣ:: ቀድመህ ስትሞት እንደዚህ ነው:: የማምለጫው መንገድ አይታይህም:: የማይታይህ ስለሌለ አይደለም፣ ከያንዳንዱ ችግር የመውጫ መንገድ አለ:: ያንን የምታየው ግን ቀድመህ ካልሞትክ ብቻ ነው::

የመጀመርያዎቹ ከረቶች እና አፈር ገሥግሥ ላይ ወደቁ:: ከወደቁበት ድንጋዮች እና አፈር ይልቅ ሞትን ማሰቡ ገሥግሥን ጎዳው:: «እየሞትኩ ነው ማለት ነው» ብሎ ማሰቡ ደብልቀ አመመው:: መጀመርያ የወደቁበትን ድንጋዩን እና አፈሩን ጀርባውን በማንቃነቅ ከላዩ ላይ አራገፈ:: እነዚያ ከላዩ ላይ የነበሩ ድንጋዮች እና አፈር እርሱ ከጀርባው ሲያራግፋቸው ከእግሩ ሥር ወረቁ::



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ይኼኔ ገሥግሥ እንዳች ሃሳብ ብልጭ አለለት፡፡ «ለምን ቀድሞ እሞታለሁ፡ ያለችኝን ጥቂት እድልም ብትሆን ለምን አልጠቀምባትም፡፡» አለና ከላዩ ላይ የሚወርደውን ድንጋይ እና አፈር ማራገፉን ቀጠለ፡፡ ድንጋዩ እና አፈሩ ያመዋል፡ ነገር ግን ለመኖር እየታገለ፡ ለማሸነፍም እየጣረ ስለነበር ሕመሙን የሚያስችል ብርታት አገኘ፡፡

ድንጋዩን እና አፈሩን ባራገፈው መጠን እግሩ ሥር ይወርድና መሬቱን ይደለድለዋል፡፡ ያን ጊዜ ጉድጓዱ እየሞላ ይሄዳል፡፡ ጉድጓዱ በሞላ ቁጥር ደግሞ ገሥግሥ ወደ ላይ ከፍ ይላል፡፡ ሰዎቹ ከላይ የመቃብር ድንጋይ እና አፈር ይጨምራሉ፡ ከሥር ደግሞ ገሥግሥ የመቃብሩን ድንጋይ እና አፈር እየደለደለ ከመቃብር ለመውጫ ይጠቀምበታል፡፡ እነርሱ አፈር እና ድንጋይ በጨመሩ ቁጥር ገሥግሥ አፈሩን እና ድንጋዩን እያራገፈ ጉድጓዱ ውስጥ በመደልደል ጉድጓዱን ይሞላ ነበር፡፡ ሕይወትን የሚያጣፍጠው ተጋድሎ ነውና ገሥግሥ ከመከራው ውስጥ ደስታ ማመንጨት ጀመረ፡፡ ቀድመህ ካልሞትክ የመቃብርህን ድንጋይ እና አፈር ለሌላ ሕይወት መወለጃ ታደርገዋለህ፡፡

ሰዎቹ ጉድጓዱን ሊሞላ የሚችል አፈር ጨምረው ሲፈጽሙ ገሥግሥ ከገደሉ ውስጥ ብቅ አለ፡፡ የጨመሩት አፈር ከገሥግሥ እግር ሥር እየተደለደለ ገሥግሥን ወደ ላይ ከፍ አደረገው እንጂ አልቀበረውም ነበር፡፡ «እኔን ለመቅበር



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

በማሰብ ችሁ አመሰግናችኋለሁ፤ ምክንያቱም አዲስ ትምህርት አስተ ምራችሁኛልና። ከዚህ በኋላ ግን ከእናንተ ጋር አልሄድም፤ ሌላ ፈረስ ሆኛለሁና» ብሏቸው በሌላ መንገድ ሄደ።»

ታሪኩን ጨረሱና ዝም ብለው አዩት። ተደንቆ እርሱም ዝም ብሎ ያያቸው ነበር።

«የሚያልቅልህ አለቀኝ ያልክ ቀን ነው፤ የምትሞተው ሞትኩ ብለህ የተቀበልከው ዕለት ነው፤ የምትሸነፈው፤ ልብህ የተረታ ዕለት ነው። አፈር ስለጨመሩብህ ብቻ ልትቀበር አትችልምከ፤ አፈሩን ማራገፍ ካልቻልክ እንጂ፤ ተስፋ ከቆረጥክ ወለል ብሎ የተከፈተው ሰፊውም በር ቢሆን አይታይህም፤ ብርታቱ ካለህ ግን ማንም የማያየውን በስላች የተከፈተውን የሥርጥ መንገድም ቢሆን ታየዋለህ፤ ቀድመህ ካልተሸነፍክ እሳት ወስ ጥም ሆነህ ቢሆን ትዘመራለህ፤ ከተሸነፍክ ግን አልጋ ላይም ሆነህ ታለቅሳለህ።

«አሁን ያደረጉህን ተውና የሆንከውን አስብ፤ ያጋጠመህን ተውና የወሰንከውን አስብ፤ ያውልህ የመውጫ መንገዱ፤ ግን ለህያዋን እንጂ ለሙታን አይታይምና፤ ቀድመህ አለመሞትህን ርግጠኛ ሁን»

ውስጡን አዳመጠው።

ካምፓላ፣ ዑጋንዳ



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF



እነሆ ሁለተኛው የወንች መጽሐፍ -የሁለቱ ሐሙልቶች ወግ እና ሌሎች- የሚለውን ተከትሎ መጣ። የመጀመሪያው መጽሐፍ ጉዞ ከተሳካ ሌላም ይከተላል ብለን ነበር። በአንባብያን ብርታት፣ በአከፋፋዮች ትጋት፣ በመጻሕፍት አዟሪዎች ትእግሥት የተነሣ የመጀመሪያው መጽሐፍ ተሳክቷል። በኢትዮጵያ እና በ24 የዓለም ሀገሮች ተሠራጭቶ ለመነበብም ችሏል። እስከ ዛሬም ለአራት ጊዜያት ታትሟል።

ቀጣዩ የተሳካ ይሆን ዘንድም ተመሳሳዩን ጸሎት እና ጥረት ይጠይቃል። እግዚአብሔር ይርዳን። በተረቶቻችን፣ በአባባሎቻችን፣ በጠባዮቻችን፣ በአመለካከቶቻችን፣ በርእዮተ ዓለሞቻችን፣ በእምነቶቻችን እና በባህሎቻችን ላይ የተመሠረቱት እነዚህ ወጎች የጉዞ ማስታዎሻዎቹን አዳብለው መጥተዋል። ትዝናኑባቸዋላችሁ፣ ትማሩባቸዋላችሁ፣ ትወያዩባቸዋላችሁ፣ ትታዘቡባቸዋላችሁ፣ አብራችሁም ትጓዙባቸዋላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ይህንን እያነበባችሁ ሦስተኛው መጽሐፍ እስኪመጣ ድረስ በአዲስ ጉዳይ መጽሔት እና በwww.danielkibret.com ብሎግ /ጦማሩ/ ላይ የሚወጡትን እየከታተላችሁ ጠብቁ።

መልካም ንባብ።

ዋጋ ብር 75.00

Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF